# ኦሪት ዘዳግም

## ምዕራፍ ፩ ።

፩ ዝንቱ ውእቱ ነገር ዘነገሮሙ ሙሴ ለኵሉ ፳ኤል በማዕ
ዶተ ዮርዳኖስ በመንገለ በረቢሃ በኀበ ባሕረ ኤርትራ በማ
እከለ ፋራን ወጦፌል ወሉባን ወአውሎን ወዘኬሬቦን ።
፪ በዐሠሩ መዋዕል እምኮሬብ በፍኖተ ደብረ ሴይር እስ
ከ ቃዴስ በርኔ ።

፫ ወኮነ አመ አርብዓ ዓም አመ ዓሡር ወአሚሩ ወርኀ
አመ ሠርቀ ወርኅ ነገሮሙ ሙሴ ለኵሉ ደቂቀ እስራኤል
ኵሎ ዘአዘዞ እግዚአብሔር ይንግሮሙ ።

፬ እምድኅረ ቀተሎ ለሴዎን ንጉሠ አሞሬዎን ዘይነብር
ውስተ ሐሴቦን ወለዖግ ንጉሠ ባሳን ዘይነብር ውስተ አስ
ጣሮት ወኤንድራይን ።

፭ በማዕዶተ ዮርዳኖስ ውስተ ምድረ ሞአብ ወአኀዘ ሙሴ
ይንግር ዘንተ ሕገ ወይቤ እግዚአብሔር አምላክነ ነገረነ
በኮሬብ ወይቤለነ አክለክሙ ኀዲሮቱ ውስተ ዝንቱ ደብር።
፯ ተንሥኡ እንክ ወሑሩ ወባኡ ውስተ ደብረ አሞሬዎን
ወውስተ ኵሉ ማኅደረ ዓረብ ውስተ ደብሩ ወውስተ ገዳ
ሙ ወውስተ ሊብ ወውስተ ጲራልያ ዘምድረ ከነአን ወአን
ጢሊባኖን እስከ ፈለግ ዐቢይ ፈለገ ኤፍራጥስ ።

፰ ናሁ ወሀብኩክሙ ይእተ ምድረ እንተ መሐልኩ ለአ
በዊክሙ ቅድሜክሙ ለአብርሃም ወለይስሐቅ ወለያዕቆብ
ከመ አሀቦሙ ሎሙ ወለዘርኦሙ እምድኅሬሆሙ ምድረ
እንተ ትውኅዝ ሐሊበ ወመዓረ ።
፱ ወእቤለክሙ በውእቱ መዋዕል እንዘ እብል ኢይክል
ባሕቲትየ ጸዊሎተክሙ ፣ እስመ አብዝኀነ እግዚአብሔር
አምላክነ ።
ወናሁ ብዙኃን አንትሙ ዮም ከመ ከዋክብተ ሰማይ።
፲ ወያብዝኀክሙ እግዚአብሔር አምላክሙ ለአበዊነ
ምእልፊተ ወይባርክሙ በከመ ይቤለክሙ ።
፲፩ ወእፎ እክል ባሕቲትየ ፆማክሙ ወሥራሐክሙ ወተ
ባህሎተክሙ ።
፲፪ አምጽኡ ለክሙ እደወ ጠቢባነ ወለባውያነ ወም ...
ራነ እምነገድክሙ ወእሠይሞሙ ለክሙ መሳፍንተ ... ።

ምዕራፍ ፩ ።

በዘኬፈበያና በአውሎን በሉባንና በጦፌል ፣ በፋራን
መካከል በኤርትራ ባሕር ዙንድ በግራዋ በኩል በዮርዳኖስ
ማዶ ለእስራኤል ሁሉ ሙሴ የነገራቸው ይህ ነው ።
ከኮሬብ ጀምሮ እስከ ቃዴስ በርኔ ድረስ በሴይር ተራ
ራ መንገድ በዓሥር ቀን ተጉዘው በአሥረኛው ቀን ያስተ
ማረው ትምህርት ይህ ነው ። ዘዳ፣ ፪ ፲፬ ፣ ፱ ፳፫ ።
ከግብጽ በወጡ በአርባው ዘመን በአሥራ አንደኛው
ወር (በየካቲት መባቻ) ለእስራኤል ልጆች ሁሉ እንዲነግራ
ቸው እግዚአብሔር ያዘዘውን ሁሉ ለእስራኤል ልጆች
ሁሉ ነገራቸው ። ዘኁ፣ ፲፭ ፴፰ ፣ ፩ ሳሙ፣ ፳፰ ፩ ።
በኤንድራይንና በአስጣሮት የሚኖር የባሳን ንጉሥ
ዓግን በሐሴቦን የሚኖር የአሞሬዎንን ንጉሥ ሴዎንን በሞ
ዓብ አውራጃ በዮርዳኖስ ማዶ ከገደሉት በኋላ የነገራቸው
ነገር ይህ ነው ። ዘኁ፣ ፳፩ ፴፫ ፣ ኢያ፣ ፲፪ ፬ ።
ሙሴ ይህን ሕግ ያስተምር ጀመረ ፣ ፈጣሪያችን እግዚ
አብሔር በዚህ ተራራ መስፈር በቃችሁ ብሎ ሙሴ በኮ
ሬብ ነገረን አለ ። ዘኁ፣ ፲ ፲፩ ፣ ዘዳ፣ ፪ ፫ ።
እንግዲህ ከዚህ ተነሥታችሁ ወደ አሞሬዎን ተራራ
ወደ ዓረብም አገር ሁሉ ወደ ደጋውም ወደ ቈላውም
ወደ ቀኙም ወደ ግራውም እስከ ታላቁ ኤፍራጥስ ወንዝ
ድረስ በከነዓን አገር ወደ ደሴቱም ወደ ደጋውም ተነ
ሥታችሁ ግቡ ። ዘፍ፣ ፲፪ ፯ ፣ ፲፫ - ፲፰ ።
ለነሳቸው ከነሳቸውም በኋላ ለልጆቻቸው እሰጣቸው
ዘንድ ለአባቶቻቸው ለአብርሃም ለይስሐቅና ለያዕቆብ የማ
ልሁላቸውን በፊታችሁ የምታዩዋትን ማርና ወተት የም
ታፈስውን ያችን አገር እነሆ ሰጥቻችኋለሁ ።
ፈጣሪያችን እግዚአብሔር አብዝቶናልና ብቻዬን መሥ
ራት (መፍረድ) አልችልም ብዬ በዚያ ወራት ነገርኋችሁ።

እነሆ እናንተ እንደ ሰማይ ከዋክብ ዛሬ ብዙዎች ናችሁ።
ያባቶቻችን ፈጣሪ እግዚአብሔር አበዛችኋለሁ ብሎ
እንደ ተናገረ የብዙ ብዙ አድርጎ ያብዛችሁ ይባርካችሁ።
ድካማችሁን ክርክራችሁንና ሸክማችሁን ብቻዬን
እንዴምን እችላለሁ ፣ ፩ ነገ፣ ፫ ፰ ፣ ፪ ቆሮ፣ ፲፩ ፳፰ ።
ለናንተ ሹማምንት አድርጌ እሾምላችሁ ዘንድ ከየነገ
ዶቻችሁ አዋቆችን አስተዋዮችን ጥበበኞችን ሰዎች መርጣ
ችሁ አምጡ ። ዘፀ፣ ፲፰ ፳፩ ፣ ዘኁ፣ ፲፩ ፲፯ ።

፲፫ ወአውሥእክሙኒ ወትቤሉኒ ሠናይ ዝንቱ ቃል ወትቤሉኒ ግበር ከማሁ ።

፲፬ ወነሣእኩ እምውስቴትክሙ እደወ ጠቢባነ ወማእምራነ ወለባውያነ ወሤምክዎሙ ላዕሌክሙ ይኩኑክሙ መላእክተ ዓሠርቱ ምእት ወመላእክተ ምእት ፣ ወመላእክተ ሐምሳ ፣ ወመላእክተ ዐሠርቱ ፣ ወጸሐፍቶሙ ለመኳንንቲክሙ ።

፲፭ ወእቤሎሙ በውእቱ መዋዕል ስምዑ ማእከለ አኀዊክሙ ወማእከለ ግዩር ፣ ወማእከለ ብእሲ ወእኁሁ ፣ ወአግብኡ ፍትሐ በጽድቅ ።

፲፮ ወኢትንሥኡ ገጸ በፍትሕ ፣ ኢ ለንኡስ ወኢ ለዐቢይ ወኰንኑ በጽድቅ ወኢትንሥኡ ገጸ ሰብእ እስመ ፍትሕ ዘእግዚአብሔር ውእቱ ፣ ወለእመበ ዘዐዐበክሙ ነገር ታዐርጉ ኀቤየ ወእሰምዖ ።

፲፯ ወአዘዝኩክሙ በውእቱ መዋዕል ኵሎ ቃለ ዘትገብሩ ።

፲፰ ወግዕዝነ እምኮሬብ ወሖርነ ኵሎ ዝክተ ገዳመ ዐቢየ ወግሩመ ዘርኢክሙ በፍኖተ ደብረ አሞሬዎን በከመ አዘዘነ እግዚአብሔር አምላክነ ወበጻሕነ እስከ ቃዴስ በርኔ ።

፲፱ ወነገርኩክሙ በውእቱ መዋዕል ወእቤለክሙ ብጽሑ እስከ ደብረ አሞሬዎን ዘይሁበክሙ እግዚአብሔር አምላክክሙ ።

፳ ወናሁ ርእዩ ከመ ወሀበክሙ እግዚአብሔር አምላክክሙ ይእተ ምድረ ቅድመ ገጽክሙ ዕርጉ እንከ ወተዋረሱ በከመ ይቤለክሙ እግዚአብሔር አምላክሙ ለአበዊነ ኢትፍርሁ ወኢትደንግፁ ።

፳፩ ወእምዝ መጻእክሙ ኵልክሙ ኀቤየ ወትቤሉኒ ንፈኑ እደወ ቅድሜነ ይርአይዋ ለይእቲ ምድር ለነ ፣ ወይዜንዉነ ዜናሃ ለይእቲ ፍኖት እንተ ሀለወነ ንዕርግ ውስቴታ ፣ ወለአህጉርኒ እለ ሀለወነ ንባእ ውስቴቶን ።

፳፪ ወአደመኒ ውእቱ ነገር ወነሣእኩ እምውስቴትክሙ ዐሠርተ ወክልኤተ እደወ በበአሐዱ ብእሲ እምነገድ ።

፳፫ ወሖሩ ወዐርጉ ውስተ ደብር ወበጽሑ ውስተ ቈላተ ዐጽቅ ወርእይዋ ።

፳፬ ወነሥኡ ምስሌሆሙ እምፍሬሃ ለይእቲ ምድር ወአምጽኡ ኀቤነ ወንቤ ሠናይት ምድር ዘይሁበነ እግዚአብሔር አምላክነ ።

፳፭ ወአበይክሙ ዐሪገ ወክሕድክሙ ቃለ እግዚአብሔር አምላክክሙ ።

፳፮ ወአንጐርጐርክሙ በውስተ ተዓይኒክሙ ፣ ወትቤሉ እስመ ይጸልአነ እግዚአብሔር አውጽአነ እምድረ ግብጽ ከመ ያግብአነ ውስተ እዴሆሙ ለአሞሬዎን ወከመ ይሠ

፳፯ ርወነ ፣ አይቴ እንከ ነዐርግ ንሕነ ።

ወብሕቱ አኀዊክሙ አክሐድዎ ለልብክሙ ወይቤሉ

፳፰ ክሙ ዐቢይ ሕዝብ ወብዙኅ ወይጸንዑ እምኔክሙ ፣ ወአህጉሪሆሙኒ ዐበይት ወበቶን ጥቅም ዘይበጽሕ እስከ ሰማይ ወርኢነ በህየ ደቂቆሙ ለእለ ያርብኅ ።

ወእቤለክሙ ኢትፍርሁ ወኢትደንግፁ እምኔሆሙ ።

፳፱ እግዚአብሔር አምላክክሙ ውእቱ ይፀብእ ለክሙ ምስሌክሙ ወውእቱ የሐውር ቅድመ ገጽክሙ በከመ ኵሉ ዘገብረ ለክሙ በምድረ ግብጽ ።

ይህ ቃል ያማረ የተወደደ ነው ፣ አሁን እንደ ተናገር ከው አድርግ ብላችሁ መለሳችሁልኝ ፤ ።

እኔም ከናንተ ውስጥ አዋቆችን ብልሆችን አስተዋዮችን መርጬ የሺ አለቆች ፣ የመቶ አለቆች ፣ የአምሳ አለቆች ፣ የዓሥር አለቆች አድርጌ ሾምሁላችሁ ለመኳንንቶቻችሁም ጸሐፍቶች አደርግኋቸው ።

ወንድም ከወንድሙ ጋር በተጣላ ጊዜ ነገሩን ሰምታችሁ በመጻተኛውና በወንድሞቻችሁ መካከል እውነት ፍረዱ ብዬ በዚያ ወራት ነገርኋቸው ። ዮሐ፣ ፯ ፳፬ ።

በፍርድ ጊዜ ለትንሹም ለትልቁም ፊት አይታችሁ አታድሉ ፣ እውነተኛው ፍርድ የእግዚአብሔር ገንዘብ ነውና የሰው ፊት አይታችሁ አታድሉ ፣ የረቀቃችሁም ፍርድ ቢኖር ወደኔ አድርሱት ፣ እኔ እሰማዋለሁ ።

የምትሠሩትን ሥራ ሁሉ በዚያ ወራት አዘዝኋችሁ ።

ፈጣሪያችን እግዚአብሔር እንዳዘዘን ከኮሬብ ተጕዘን በአሞሬዎን ተራራ መንገድ ያያችሁት ይህን የሚያስፈራ ታላቅ ተራራ ምድረ በዳ ተጕዘን እስከ ቃዴስ በርኔ ደረስን።

ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር እስከ ሚሰጣችሁ እስከ አሞሬዎን ተራራ ድረስ ሂዱ ብዬ በዚያ ወራት ነገርኋችሁ ። ፩ ሳሙ፣ ፲፯ ፯፣ ፳፬ - ፳፫፣ ዘዳ፣ ፰ ፲፬ ።

እነሆም ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር ያችን ምድር በፊታችሁ እንደ ሰጣችሁ እዩ (አስተውሉ) ያባቶቻችን ፈጣሪ እግዚአብሔር ትወርሷታላችሁ እንዳላቸው እንግዲህ ውረሷት አትፍሩ አትደንግጡ ። ዘዳ፣ ፴፩ ፰፣ ኢያ፣ ፩ ፱ ።

ከዚህ በኋላ ሁላችሁ ወደኔ መጥታችሁ ከኛ አስቀድሞ ሰዎችን ልከን ያችን አገር ይዩልን ፣ ወደነሳቸው እንገባ ዘንድ ያለን እነዚያን አገሮችና ወደዚ እንወጣ ዘንድ ያለን የዚያች አገር ጕዳናንና ወሬዋን ይንገሩን አላችሁኝ ።

ያም ነገር ደስ አሰኘኝ ከየነገዱ አንዳንድ ሰው መርጬ ከናንተ ዓሥራ ሁለት ሰዎች ተቀበልኩ ። ዘኍ፣ ፲፫ ፫ ።

ሂደውም ወደ ተራራው አገር ወጥተው የወይን ዘለላ ወዳለበት ቈላ ደርሰው ያችን አገር አዩዋት ።

ከዚያች አገር ምድር ፍሬ ይዘው ወደኛ አመጡልን እኛም ፈጣሪያችን እግዚአብሔር የሚሰጠን ያችን አገር መልካም ናት አልን ። ዘኍ፣ ፲፫ ፳፱፣ ዘዳ፣ ፱ ፲፫ ።

ወደዚ መውጣትን እምቢ አላችሁ ፣ የፈጣሪያችሁ የእግዚአብሔርን ቃል ክዳችሁ ። ዘዳ፣ ፩ ፵፫፣ ኢያ፣ ፩ ፲፰ ።

በሰፈራችሁም እንጕራጕራችሁ እግዚአብሔር ጠልቶናልና በአሞሬዎን እጅ ሊጥለን ከግብጽ ምድር አወጣን ፣ እንግዲህ እኛ ወዴት እንወጣለን ፤ አላችሁ ።

ነገር ግን ወንድሞቻችሁ (ሕዝቡ) ወገኑ ፈጽሞ ብዙ ነው ፣ ከናንተ ይበረታሉ ፣ አምባዎቻቸውም የፀኑ ናቸው እስከ ሰማይ የሚደርስ ቅጽር አላቸው በዚያ የአርበኞችን ልጆች አየን ብለው ልቡናችሁን አስከዱት ።

እኔም ከነሱ የተነሳ ያጠፉናል ብላችሁ አትፍሩ ።

ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር ከናንተ ጋር ሆኖ ይዋጋላችኋል ፣ በግብጽ አገር እንዳደረገላችሁ ሁሉ በፊታችሁ የሚሄድ እርሱ ነው ። ዘፀ፣ ፲፬ ፲፬ ፣ ነህ፣ ፬ ፳ ።

| | | |
|---|---|---|
| ወበውስተ ገዳም ዘርኢክሙ በከመ ሴሰየክሙ እግዚአብሔር አምላክክሙ በከመ ይሴሲ ብእሲ ውሉዶ በኵሉ ፍኖት እንተ ሖርክሙ እስከ በጻሕክሙ ውስተ ዝንቱ መካን ። | ፴ | አባት ልጁን እንዲመግብ በዚህ ባያችሁት ምድረ በዳም ወደዚህ ቦታ እስክትደርሱ ድረስ በሄዳችሁበት ጎዳናም ሁሉ ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር እንደ መገባችሁ መጠን። |
| ወኢአመንክምዎ በዝንቱ ቃል ለእግዚአብሔር አምላክክሙ ዘየሐውር ቅድሜክሙ ውስተ ፍኖት ከመ ይኅረይ ለክሙ መካነ ወይምራሕክሙ ሌሊተ በእሳት ከመ ያርኢክሙ ፍኖተ ዘተሐውሩ በቲ መዓልተኒ በደመና ። | ፴፩ | ቦታን ይመርጥላችሁ ዘንድ ሌሊት በዓምደ እሳት ፥ ቀንም በደመና የምትሄዱበትን ጎዳና ያሳያችሁ ዘንድ በጎዳናው ፊታውራሪ ሆኖ የሚሄድ ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔርን በዚህ ቃል አላመናችሁትም ። ዘፀ፡ ፲፫ ፳፩ ። |
| ወሰምዐ እግዚአብሔር ቃለ ነገርክሙ ወተምዐ ወመሐለ ወይቤ ከመ ኢይሬእይዋ እሉ እደው ለይእቲ ምድር ቡርክት ዘመሐልኩ ለአበዊሆሙ ዘእንበለ ካሌብ ወልደ ዮፎኒ ። | ፴፪ | እግዚአብሔርም የነገራችሁን ቃል ሰምቶ ተቈጣ ለአባቶቻቸው የማልኩላቸው የተባረከች ያችን ምድር ከዮፎኒ ልጅ ከካሌብ በቀር እነዚህ ሰዎች እንዳያዩዋት ብሎ ማለ ። ዘኍ፡ ፲፬ ፳፪ ፥ መዝ፡ ፺፭ ፲፩ ። |
| ወውእቱ ይሬእያ ወሎቱ እሁብ ለይእቲ ምድር እንተ ውስቴታ ዐርገ ወለደቂቁ እስመ አምኅበ እግዚአብሔር ውእቱ ልቡ ። | ፴፫ | እሱ ያያታል (ይወርሳታል) የወጣበት ያችን አገር ለርሱ ለልጆቹም እሰጣታለሁ ፥ ልቡናው ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ሁኗልና ። ዘኍ፡ ፲፫ ፲፬ ፥ ኢያ፡ ፲፬ ፲፬ ። |
| ወኪያየኒ ተምዕዐኒ እግዚአብሔር በእንቲአክሙ ወይቤለኒ አንተኒ ኢትበውእ ህየ ። | ፴፬ | እኔንም እግዚአብሔር በናንተ ምክንያት ተቈጣኝ ፥ አንተም ወደዚያ አትገባም አለኝ ። ዘኍ፡ ፳፯ ፲፬ ። |
| እስመ ኢያሱ ወልደ ነዌ ዘይቀውም ቅድሜከ ውእቱ ዘይበውእ ህየ ኪያሁ አጽንዖ ወውእቱ ያወርሶሙ ይእተ ምድረ ለእስራኤል ። | ፴፭ | በፊትህ የሚቆም የነዌ ልጅ ኢያሱ እርሱ ወደዚያ የሚገባ ነውና እሱን አጽናው ያችንም አገር እርሱ ለእስራኤል ያወርሳታል ። |
| ወደቂቅክሙ እለ ትቤሉ ይፄወዉ ወኵሉ ሕፃን ንኡስ ዘኢየአምር ዮም ሠናይተ ወእኪተ እሙንቱ ይበውኡ ህየ ፥ ወሎሙ እሁብ ወእሙንቱ ይወርስዋ ። | ፴፮ | ይማረካሉ የምትሏቸው ልጆቻችሁ ክፉና በጎ ዛሬ የማያውቅ ሕፃን ሁሉ ትንሹም ሁሉ ወደዚያ ይገባሉ ፥ ለነሱ እሰጣታለሁ ፥ እነሱም ይወርሷታል ። |
| ወአንትሙሰ ተመየጡ ወገዐዙ ውስተ ገዳም ውስተ ፍኖተ ባሕረ ኤርትራ ። | ፴፯ | እናንተ ግን የኤርትራን ባሕር መንገድ ይዛችሁ ወደ ምድረ በዳ ተጓዙ ። ዘኍ፡ ፲፬ ፳፭ ፥ ዘዳ፡ ፪ ፩ ። |
| ወአውሣእክሙኒ ወትቤሉኒ አበስነ ቅድመ እግዚአብሔር አምላክነ ነዐርግ ንሕነ ወንትቃተል ወንገብር ኵሎ በከመ አዘዘነ እግዚአብሔር አምላክነ ፥ ወነሣእክሙ ብእሲ ብእሲ ንዋየ ሐቅልክሙ ወዐረግሙ ውስተ ደብር ። | ፴፰ | ፈጣሪያችን እግዚአብሔርን በድለናልና ፥ ፈጣሪያችን እግዚአብሔር እንዳዘዘን እኛም መጥተን እንዋጋለን ሁሉንም እናደርጋለን ብላችሁ መለሳችሁልኝ ፥ አንዱም አንዱም ሰው ጋሻ ጦራችሁን ይዛችሁ ወደ ተራራው ወጣችሁ። |
| ወይቤለኒ እግዚአብሔር በሎሙ ኢትዕርጉ ወኢትትቃተሉ እስመ ኢሀለውኩ ምስሌክሙ ከመ ኢትትቀጥቀጡ ቅድመ ፀርክሙ ። | ፴፱ | እግዚአብሔርም በረድኤት ከናንተ ጋር የለሁምና በጠላቶቻችሁ ፊት እንዳትጠፉ ወጥታችሁ አትዋጉ በላቸው አለኝ ። ዘኍ፡ ፲፬ ፵፭ ፥ ፲፬ ፵ ። |
| ወነገርኩክሙ ወኢሰማዕክሙኒ ወተዐወርክሙ ቃለ እግዚአብሔር ፥ ወተኀየልክሙ ወዐረግሙ ውስተ ደብር ። | ፵ | እኔም ነገርኋችሁ አልሰማችሁኝም የእግዚአብሔርን ቃል ቸል አላችሁ ፥ ተበራትታችሁ ወደ ተራራ ወጣችሁ ። |
| ወወፅኡ አሞሬዎን እለ ይነብሩ ውስተ ውእቱ ደብር ወተቀበሉክሙ ወአንተውክሙ ወሰደዱክሙ ወነደፉክሙ ከመ ንህብ ወወግኡክሙ እምሴይር እስከ ሔርማ ። | ፵፩ | በዚያው ተራራ የሚኖሩ የአሞሬዎን ሰዎች ወጥተው ተጋጠሙዋችሁ ፥ ድል ነሥተውም አባረሩዋችሁ ፥ እንደ ንብም እየነደፉ አሸበሯችሁ ፥ ከሴይር እስከ ሔርማ ድረስ ወጓችሁ ። መዝ፡ ፻፲፰ ፱ ፥ ፻፲፰ ፲፪ ። |
| ወነበርክሙ ወበከይክሙ ቅድመ እግዚአብሔር ወኢሰምዐክሙ ቃለክሙ ወኢነጸረክሙ ። | ፵፪ | ተቀምጣችሁ በእግዚአብሔር ፊት አለቀሳችሁ ፥ ነገር ግን ቃላችሁን አልሰማችሁም በምሕረትም አላያችሁም ። |
| ወነበርክሙ ውስተ ቃዴስ ብዙኀ መዋዕለ አምጣነ ነበርክሙ ቀዲሙ ። | ፵፫ | ቀድሞ የኖራችሁትን ያህል ብዙ ዘመን በቃዴስ ተቀመጣችሁ ። ዘኍ፡ ፳፩ ፳፬ ፥ መሳ፡ ፲፬ ፯ ። |

## ምዕራፍ ፪ ።

| | | |
|---|---|---|
| ወተመየጥነ ወሖርነ ውስተ ገዳም ፍኖተ ባሕረ ኤርትራ በከመ ይቤለኒ እግዚአብሔር ወዖድናሁ ለደብረ ሴይር ብዙኀ መዋዕለ ። | ፩ | እግዚአብሔር እንደ ነገረን ተመልሰን የኤርትራን ባሕር መንገድ ይዘን ወደ ምድረ በዳ ሄድን የሴይርንም ተራራ ብዙ ቀን (ዘመን) ዞርነው ። ዘኍ፡ ፲፬ ፳፭ ። |
| ወይቤለኒ እግዚአብሔር ከነክሙ ዐውዶቱ ለዝንቱ ደብር ግብኡ እንከሰ ለመንገለ መስዕ ። | ፪ | እግዚአብሔር ይህን ተራራ መዞር በቃችሁ እንግዲህ ወዲህ ወደ ሰሜን ተመለሱ አለኝ ። ዘዳ፡ ፩ ፯ ። |

፫ ወአዝዞሙ ለሕዝብ ወበሎሙ ፤ ናሁ ተሐውሩ አንትሙ እንተ አድዋሊሆሙ ለአኀዊክሙ ደቂቀ ኤሳው እለ ይነብሩ ውስተ ምድረ ሴይር ወይፈርሁክሙ ጥቀ ።

ሕዝቡን እንዲህ ብለህ እዘዛቸው ፤ በሴይር ወዳሉ ወደ ዔሳው ልጆች ወደ ወንድሞቻችሁ አውራጃ ሂዱ ፤ እነሳቸውም እጅግ ይፈሩዋቿኋል ፡ ዘኍ ፳ ፲፬ ፡ ፳፩ ፡ ፳፩።

፬ ዑቁ ኢትትቃተሉ ምስሌሆሙ እስመ ኢይሁበክሙ እምድሮሙ ርስተ ወኢምሥጋረ እግር ፤ እስመ መክፈልቶ ወሀብክዎ ለኤሳው ደብረ ሴይር ።

የሴይርን ተራራ ለዔሳው ዕጣ አድርጌ ስለ ሰጠሁት ፤ ከምድራቸው አንድ ጫማ ስንኳ አይሰጣችሁምና ከነርሱ ጋር እንዳትዋጉ ዕወቁ ። ዘፍ፡ ፴፰ ፬ ፡ ኢያ፡ ፳፬ ፬ ።

፭ ወተሣየጡ እክለ እምኀቤሆሙ በወርቅክሙ ወተሴሰዩ ወማየኒ በመስፈርት ንሥኡ እምኀቤሆሙ በወርቅክሙ ወስትዩ ፤ እስመ ባረከክሙ እግዚአብሔር አምላክክሙ በኵሉ ግብረ እደዊክሙ ።

ከነሳቸው በወርቃችሁ እህል ሸምታችሁ ተመገቡ ፤ ውኃንም በመለኪያ ከነሳቸው በወርቃችሁ ገዝታችሁ ጠጡ ፤ ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር በእጃችሁ ሥራ ሁሉ ባርኳችኋልና (አከብሯችኋልና) ።

፮ አእምር እፎ ዐደውክሁ ለዝንቱ ገዳም ዐቢይ ዘግሩም ውእቱ ፤ ናሁ አርባዓ ዓመ ሀለወ ምስሌከ እግዚአብሔር አምላክከ እንዘ አልቦ ዘያኀጥእከ እምኵሉ ዘነበብከ ።

ጽኑ የሆነ የሚያስፈራ ይህን ምድረ በዳ እንዴት እንደዞርከው ከተናገርከው ሁሉ ፈጣሪህ እግዚአብሔር ያሳጣህ ሳይኖር ፵ ዘመን ካንተ ጋር በረድኤት እንደነበረ ዕወቅ ።

፯ ወተዐደውናሆሙ ለአኀዊነ ደቂቀ ኤሳው እለ ይነብሩ ውስተ ሴይር ኀበ ፍኖተ ዓረባ እምኤሎም ወእምጋስዮን ጋቤር ወእምዝ ተመየጥነ ወዐደውነ ፍኖተ ገዳም ዘሞአብ ።

ከጋስዮን ጋቤርና ከኤሉም ተነሥተን በሴይር የሚኖሩ የዔሳው ልጆች ወንድሞቻችንን አልፈናቸው ወደ ዓረባ ጐዳና ሄድን ከዚህ በኋላ ተመልሰን በሞዓብ ምድረ በዳ ጐዳና አልፈን ሄድን ። ዘፍ፡ ፲፱ ፴፮ ።

፰ ወይቤለኒ እግዚአብሔር ኢትፃረርዎሙ ለሞዓባውያን ወኢትትቃተሉ ምስሌሆሙ እስመ ኢይሁበክሙ ርስተ እምድሮሙ እስመ ለደቂቀ ሎጥ ወሀብክዎሙ ርስቶሙ ።

እግዚአብሔር ለሎጥ ልጆች ርስት አድርጌ ስለ ሰጠኋቸው ከምድራቸው ምንም ርስት አይሰጣችሁምና ፤ የሞዓብን ልጆች አትጣሏቸው ከነሱ ጋር አትዋጉ አለኝ ።

፱ ወዘሚን ቀዲሙ ነበሩ ውስቴታ ሕዝብ ዐበይት ጥቀ ወጽኑዓን ከመ እለ ውስተ አቂም ።

በአቂም እንደነበሩ ሰዎች በጉልበት የጸኑ ፡ በቁመት የረዘሙ እጅግ ታላላቅና ብዙ ወገን የሚሆኑ ዘሚናውያን አስቀድሞ በውስጧ ነበሩ ። ዘኍ፡ ፲፫ ፪ ፡ ዘዳ፡ ፱ ፪ ።

፲ ወራፋይን ከዐበ የኀድሩ እሙንቱኒ ከመ እለ ውስተ አቂም ፤ ወሞዓባውያን ዘሚን ይብልዎሙ ።

በአቂም ኃይለኞች እንደ ነበሩ እነዚያ ኃይለኞችም ዳግመኛ ይኖሩበት ነበር ፤ የሞዓብም ሰዎች ዘሚን (ኃያላን) ይሏቸው ነበር ፤ (ራፋይን ረጃጅሞች) ። ዘፍ፡ ፬ ፭ ።

፲፩ ወኮሬዎስ ውስተ ሴይር ይነብሩ ቀዲሙ ወደቂቀ ኤሳው አጥፍእዎሙ ወቀጥቀጥዎሙ እምቅድመ ገጾሙ ወነበሩ በመካኖሙ ፤ ከማሁ ይገብርዋ እስራኤል ለምድረ ርስቶሙ ዘወሀቦሙ እግዚአብሔር ።

(ኮሬዎስ) ኃይለኞችም ቀድሞ በሴይር ይኖሩበት ነበር ፤ የዔሳው ልጆች ከፊታቸው ፈጽመው አጥፍተዋቸው በበታቸው ኖሩ ፤ እግዚአብሔር ርስት አድርጎ የሰጣቸው አገራቸውን የእስራኤል ልጆች እንደሱ ያድርጓት ።

፲፪ ወይእዜኒ ተንሥኡ ወገዐዙ አንትሙ ወሖሩ ውስተ ቈላተ ዛሬድ ፤ ወተዐደውናሁ ለቈላተ ዛሬድ ።

አሁንም እናንተ ተነሥታችሁ ተጕዛችሁ ወደ ዛሬድ አውራጃ ሂዱ ፤ የዛሬድንም አውራጃ አልፈነው ሄድን ።

፲፫ ወመዋዕሊሁ በዘቦቱ ግዕዝነ እምቃዴስ በርኔ እስከ ተዐደውናሁ ለቈላተ ዛሬድ ሠላሳ ወሰመንቱ ዓመት እስከ ሞቱ ኵሎሙ እደው ዘይእቲ ትውልድ እለ መስተቃትላን እሙንቱ ፤ ወጠፍኡ እማእከለ ትዕይንት በከመ መሐለ ላዕሌሆሙ እግዚአብሔር እግዚእ ።

የዛሬድን ሸለቆ እስከ ተሻገርንበት ድረስ ጌታ እግዚአብሔር እንደ ማለባቸው እነዚያ ሰልፈኞች የዚያች ትውልድ ወገን የሆኑ ሰዎች ሁሉ እስኪ ጠፉ ድረስ ከቃዴስ በርኔ የተጓዝንበት ዘመን ሠላሳ ስምንት ዓመት ሆነ ።

፲፬ እስመ እደ እግዚአብሔር ሀለወት ላዕሌሆሙ ከመ ታጥፍአሙ እማእከላ ትእይንት እስከ ወድቁ ።

ጨርሰው እስከ ጠፉ ድረስ ከሰፈር ለይታ ታጠፋቸው ዘንድ የእግዚአብሔር እደ መዓቱ በላያቸው ላይ ነበረችና።

፲፭ ወኮነ እምዘወድቁ ኵሎሙ ውእቶሙ እደው መስተቃትላን ወሞቱ እማእከለ ሕዝብ ።

አርበኞች የሆኑ እነዚያ ሰልፈኞች ሁሉ ከሕዝቡ መካከል ተለይተው ሞተው ከጠፉ በኋላ እንዲህ ሆነ ።

፲፮ ወነበበኒ እግዚአብሔር ወይቤለኒ ናሁ ተሐውሩ ወተዓድዉ ውስተ አድዋሊሆሙ ለሞዓብ ፤ ወትበጽሑ ቅሩበሙ ለደቂቀ አሞን ።

እግዚአብሔርም እንዲህ ብሎ ተናገረኝ ፤ እነሆ የሞዓብን አውራጃ ተሻግራችሁ ትሄዳላችሁ ከአሞን ልጆችም አቅራቢያ ትደርሳላችሁ ። ዘፍ፡ ፲፱ ፴፰ ።

፲፯ ኢትፃረርዎሙ ወኢትትአኀዙ ቀትለ ምስሌሆሙ እስመ ኢይሁበክሙ ርስተ እምድሮሙ ለደቂቀ አሞን እስመ ለደቂቀ ሎጥ ወሀብክዎሙ መክፈልቶሙ ።

ለሎጥ ልጆች ዕጣ አድርጌ ስለ ሰጠኋቸው ከአሞን ልጆች ምድር ርስት አልሰጣችሁምና አትጣሏቸው ከነሱም ጋር ሰልፍ አትግጠሙ (አትዋጉ) ብሎ ነገረኝ ።

፲፰ ወይእቲ ምድረ ራፋይን ትሰመይ ፤ እስመ ራፋይን ይነብሩ ውስቴታ ቀዲሙ ፤ ወአሞናውያንኒ ዘሚን ይብልዎሙ።

ቀድሞ (ራፋይን) ኃይለኞች ነበሩባትና ያችም አገር የኃይለኞች አገር ትባላለች ፤ አሞናውያን ግን ዘሚን (ኃያ

፲፱ ሕዝብ ዐበይት ወብዙኃን ወጽኑዓን ወኀያላን ፡ ከመ እለ አቂም ዘአጥፍአሙ እግዚአብሔር እምቅድመ ገጾሙ ።

፳ ወወረስዎሙ ወነበሩ ህየንቴሆሙ ፡ ከመ ገብሩ ደቂቀ ኤሳው እለ ይነብሩ ውስተ ሴይር በከመ አስዐሮሙ እግዚአብሔር እምቅድመ ገጾሙ ለኮራውያን ወወረስዎሙ ወነበሩ ህየንቴሆሙ እስከ ዛቲ ዕለት ።

፳፩ ወለሔዋውያንኒ እለ ይነብሩ ውስተ አሴሮት እስከ ጋዜስ ወቀጳዶቅያ አጥፍእዎሙ ወነበሩ ህየንቴሆሙ ።

፳፪ ወይእዜኒ ተንሥኡ ወገዐዙ አንትሙ ወዕድውዎ ለቈላተ አርኖን ፡ ናሁ አግባእክዎ ውስተ እዴከ ለሴዎን ንጉሠ ሐሴቦን አሞርያዊ ወለምድሩ ወምልክ ወተዋረሶ ወአኀዞሙ ወተቃተሎሙ ።

፳፫ ወበዛቲ ዕለት አቀድም አምጽአ ላዕለ ኵሉ አሕዛብ እለ ሀለዉ መትሕተ ሰማይ ከመ ይፍርሁከ ወይርዐዱ እምኔከ ወይደንግፁ እምከመ ሰምዑ ስመከ ፡ ወትእኅዞሙ ፍርሃት እምቅድመ ገጽከ ።

፳፬ ወፈነውኩ ተናብልተ እምነ ገዳም ዘቄድሞት ኀበ ሴዎን ንጉሠ ሐሴቦን በቃለ ሰላም እንዘ እብል ፡ እኅልፍ እንተ ምድርከ ወፍኖተ አሐውር ወኢይትገኃሥ ኢ ለየማን ወኢ ለፀጋም ።

፳፭ እክለኒ በወርቅየ ትሁበኒ ወእሴሰይ ፡ ወማየኒ በወርቅየ ትሁበኒ ወእሰቲ ፡ ወዳእሙ እኅልፍ በእግርየ ።

፳፮ በከመ ገብሩ ሊተ ደቂቀ ኤሳው እለ ይነብሩ ውስተ ሴይር ፡ ወሞዓባውያንኒ እለ ይነብሩ ውስተ አሮኤር እስከ አዐድዎ ለዮርዳኖስ ውስተ ምድር እንተ ወሀበነ እግዚአብሔር አምላክነ ።

፳፯ ወአበየ ሴዎን ንጉሠ ሐሴቦን አኅልፎተነ እንተ ኀቤሁ እስመ አጽንዐ እግዚአብሔር አምላክነ መንፈሶ ወአእከየ ልቦ ከመ ይግባእ ውስተ እዴነ በይእቲ ዕለት ።

፳፰ ወይቤለኒ እግዚአብሔር ናሁ አኀዝኩ አግብኦ ውስተ እዴከ በቅድመ ገጽከ ለሴዎን ንጉሠ ሐሴቦን አሞርያዊ ወምድሮኒ ፡ ወአኀዝ ወተዋረስ ምድሮ ርስተ ።

፳፱ ወወፅአ ሴዎን ወተቀበለነ ውእቱ ወኵሉ ሕዝቡ ከመ ይትቃተለነ በኢያሳ ።

፴ ወአግብኦ እግዚአብሔር አምላክነ ውስተ እዴነ ወቀተልናሁ ሎቱ ወለኵሉ ደቂቁ ወለኵሉ ሕዝቡ ።

፴፩ ወነሣእነ ኵሎ አህጉሪሁ በውእቱ መዋዕል ወአጥፋእናሆን ለኵሎን አህጉሪሁ ፡ ወአንስትያሆሙኒ ወደቂቆሙኒ ወአልቦ ዘአትረፍነ ነፋጺተ እምኔሆሙ ዘእንበለ እንስሳሆሙ ዘማሕረክነ ወበርበርነ አህጉሪሆሙ ።

፴፪ ወነሣእነ ምድሮሙ እምአሮኤር እንተ ማዕዶተ ፈለገ ፡ አርኖን ወሀገረኒ እንተ ሀለወት ውስተ ቈላት እስከ ደብረ ገለአድ ።

፴፫ ወአልቦ ሀገር እንተ አምሰጠተነ እስመ ኵሎ አህጉረ አግብአ እግዚአብሔር አምላክነ ውስተ እዴነ ዘእንበለ ም

ላን) ይሏቸው ነበር ። ዘፍ፡ ፲፬ ፭፡ ዘዳ፡ ፪ ፲፩ ።

እግዚአብሔር ከፊታቸው እንዳጠፋቸው ኃይለኞች ታላላቅ የበዙ የጸኑ ወገኖች ናቸው ። ዘዳ፡ ፪ ፲ ።

እግዚአብሔር ኃይለኞችን አጥፍቶላቸው በሴይር የሚኖሩ የዔሳው ልጆች ወርሰዋቸው በስነሱ ፈንታ እስከዚያች ቀን ድረስ እንደ ኖሩ የሎጥም ልጆች ወርሰዋቸው በስነሱ ፈንታ ኖሩ ። ዘፍ፡ ፲ ፲፱፡ ኢያ፡ ፲፫ ፫ ።

እስከ ቀጳዶቅያና እስከ ጋዜስ ድረስ በአሴሮት ይኖሩ የነበሩት ኃይለኞችን አጥፍተው በስነሳቸው ኖሩ ።

አሁንም እናንተ ተነሥታችሁ ተጕዛችሁ የአርኖንን ሸለቆ ተሻግራችሁት ሂዱ ፡ እነሆ አሞራዊውን የሐሴቦን ንጉሥ ሴዎንንና ምድሩን በእጅህ አሳልፌ ጣልኩት ፡ ግዛት ፡ ውረሳት ፡ ተዋግተህ ያዛቸው ። ዘዐ፡ ፲፩ ፲፫ ።

በዚችም ቀን ከሰማይ በታች ባሉ አሕዛብ ሁሉ ላይ ካንተ የተነሣ ይፈሩ ይርዱ ይንቀጠቀጡ ዘንድ መፍራትን መራድ መንቀጥቀጥን ስምህንም ሲጠሩ በሰሙ ጊዜ ይደነግጡ ዘንድ መደንገጥን ማምጣት እጀምራለሁ ፡ ከፊትህም የተነሣ ፍርሃት ድንጋጤ ትይዛቸዋለች ። ዘዐ፡ ፲፭ ፲፱ ።

የሰላምን ቃል ይነግሩት ዘንድ ከቄድሞት ምድረ በዳ ወደ ሐሴቦን ንጉሥ ወደ ሴዎን መልእክተኞችን ላክሁ እንዲህ ብዬ ፡ በአገርህ ላይ ልለፍ በአውራው ጐዳና እሄዳለሁ ወደ ቀኝም ወደ ግራም አልተላለፍም ።

እኽልንም በገንዘቤ ትሸጥልኝ አለህ እመገባለሁ ፡ ውኃንም በገንዘቤ ትሸጥልኛለህ እጠጣለሁ ፡ በእግሬ ብቻ ልለፍ እንጂ ። ዘኍ፡ ፳ ፲፱ ።

ፈጣሪያችን እግዚአብሔር ወደ ሰጠን ምድር ወደ ዮርዳኖስ እስክንሻገር ድረስ በአሮኤር የሚኖሩ ሞዓባውያንና በሴይር የሚኖሩ የዔሳው ልጆች እንዳደረጉልኝ በአገርህ እሄዳለሁ እንጂ ውኃም በገንዘቤ ሰጥተኸኝ እጠጣለሁ ፡ እኽልም በገንዘቤ ሸምቼ እበላለሁ ።

በዚያች ቀን በእጃችን ይወድቅ ዘንድ ፈጣሪያችን እግዚአብሔር ልቡናውን አጽንቶታልና የሐሴቦን ንጉሥ ሴዎን በአገሩ ማሳለፍን እም ቢ አለ ። ዘኍ፡ ፳፩ ፳፫ ።

እግዚአብሔርም እነሆ አገሩን ርስት አድርገህ ወርሰህ ትገዛ ዘንድ የአሞሬዎን ንጉሥ ሴዎንን አገሩንም እያየህ በእጅህ እጥለው ዘንድ ጀመርኩ አለኝ ። ዘዳ፡ ፪ ፱ ።

ሴዎንም ሕዝቡን ሠራዊቱን ሁሉ ይዞ በኢያሳ ይሰለፈን ዘንድ ወጥቶ ገጠመን ። ዘኍ፡ ፳፬ ፳፫ ።

ፈጣሪያችን እግዚአብሔርም በእጃችን ጣለው ፡ እሱን ገደልነው ፡ ልጆቹንም ወገኖቹንም ገደልናቸው ።

በዚያም ወራት አገሮቹን ሁሉ እጅ አደረግን ፡ አገሮቹንም ሁሉ አጠፋናቸው ፡ ልጆቻቸውንና ሚስቶቻቸውን አጠፋናቸው ፡ ከዘረፍናቸው ከከብቶቻቸው በቀር ያስቀረነው ሸሽተኛ የለም አገራቸውንም ዘረፍን ። ዘዐ፡ ፫ ፮ ።

በአርኖን ወንዝ ማዶ ካለው ከአሮኤር ጀምሮ በቈላ ያሉ አገሮቻቸውንም እስከ ገለአድ ተራራ ድረስ አገራቸውን እጅ አደረግን ።

ካልደረስንበት ከአሞን ልጆች አገር በቀር ፈጣሪያችን እግዚአብሔር አገሮቹን ሁሉ በእጃችን ጥሎልናልና ያመ

ድረ ደቂቀ አሞን ዘኢበጻሕነ ።

፴፯ ወኵሉ ዘውስተ ፈለገ ያቦቅ ወአህጉረኒ ዘውስተ ቴርኔ በከመ አዘዘነ፡እግዚአብሔር አምላክነ ።

ምዕራፍ ፫ ።

፩ ወተመየጥነ ወዐረግነ ውስተ ፍኖተ ባሳን ወወፅአ ዓግ ንጉሠ ባሳን ወተቀበለነ ውእቱ ወኵሉ ሕዝቡ ውስተ ኤን ድራይን ከመ ይትቃተለነ ።

፪ ወይቤለኒ እግዚአብሔር ኢትፍርሆ እስመ ውስተ እ ዴከ አገብአ ወለኵሉ ሕዝቡ ፥ ወለኵሉ ምድሩ ፥ ወትገብሮ ከመ ገበርከሙ ለሴዎን ንጉሠ አሞሬዎን ዘይነብር ውስተ ሐሴቦን ።

፫ ወአግብአ እግዚአብሔር አምላክነ ውስተ እዴነ ለዓግ ንጉሠ ባሳን ወለኵሉ ሕዝቡ ወቀተልናሁ እስከ ኢያትረፍነ እምኔሁ ዘርአ ።

፬ ወአስተጋባእነ ኵሎ አህጉሪሁ በውእቱ መዋዕል ወአ ልቦ ሀገር ዘኢነሣእነ እምኔሆሙ ፥ ስሳ አህጉረ ወኵሎ ዘአ ድያማ ለአርጎብ ዘመንግሥቱ ለዓግ በባሳን ።

፭ ወኵሎን አህጉረ እለ ቦን ጥቅም ወነዋኃት አረፋቲሆን እለ ቦን መዓፁት ወመናሥግት ዘእንበለ አህጉረ ፌርዜዎን እለ ብዙኃት እማንቱ ጥቀ ።

፮ ወሠረውናሆሙ በከመ ገበርነ በሴዎን ንጉሠ ሐሴቦን ፥ ወአጥፋእነ ኵሎ አህጉረ ኅቡረ ፥ ወአንስቲያሆሙኒ ወደቂቆሙኒ እስከ ኢያትረፍነ ነፍሲተ ።

፯ ወኵሎ እንስሳሆሙ ወምኅርከ ዘበርበርነ እምአህጉ ሪሆሙ ።

፰ ወነሣእነ ምድሮሙ በውእቱ መዋዕል እምእደዊሆሙ ለክልኤቱ ነገሥተ አሞሬዎን እለ ሀለዉ ማዕዶተ ዮርዳኖስ እምፈለገ አርኖን እስከ ፈለገ ኤርሞን ዘይብልዎ ሰብአ ፊንቂስ አኤርሞን ፥ ወሰኒዮርስ ወአሞሬዎን ይብልዎ ሳኔር ።

፱ ወኵሎ አህጉረ እለ ኔሶር ፥ ወኵሎ ዘገለአድ ፥ ወኵሎ ዘባሳን እስከ ኤልክድ ፥ ወኤንድራይን ሀገረ መንግሥቱ ለዓግ በባሳን ።

፲ በሕቱ እስመ ዓግ ንጉሠ ባሳን ውእቱ ዘተርፈ እምራ ፋይን ፥ ወናሁ ዐራቱ ዐራተ ሐጺን ሀለወት ውስተ ጽን ፎሙ ለደቂቀ አሞን ትስዕ በእመት ኑኃ፡ ወርብዕ በእመት ግድማ ።

፲፩ ወበርበርናሃ ለይእቲ ምድር በውእቱ መዋዕል እምአ ሮኤር እስከ ማዕዶተ ፈለግ ዘአርኖን ወመንፈቃ ለደብረ ገለአድ ፥ ወአህጉሪሁኒ ወሀብክዎሙ ለሮቤል ወለጋድ ።

፲፪ ወዘተርፈ እምገለአድ ወኵሎ ባሳን እመንግሥቱ ለዓግ ወሀብክዎሙ ለመንፈቀ ነገደ ምናሴ ወኵሎ ዘአድያሚሃ ለአርጎብ ዝንቱ ኵሉ ባሳን ዘይትኌለቍ ውስተ ምድረ ራፋይን ።

፲፫ ወኢያእር ወልደ ምናሴ ነሥአ ኵሎ አድያሚሃ ለአ ርጎብ እስከ ደወለ ጌርጋሴ ወመከጢ ፥ ወሰመዮ በስሙ ለባሳን አውታይ ኢያእር እስከ ዛቲ ዕለት ፥ ወለማኪር ወሀ ብክዎ ገለአድሃ ።

ለጠችን አገር የለም ። ዘዳ፡ ፪ ፲፱ ።

ፈጣሪያችን እግዚአብሔር እንዳዘዘን ቴርኔ በሚባል አገር ውስጥና በያቦቅ ወንዝ ያሉትን አገሮች ሁሉ እጅ አደረግን ። ዘፍ፡ ፴፪ ፳፪፡ ዘዳ፡ ፪ ፭ ።

ምዕራፍ ፫ ።

ተመልሰን ወደ ባሳን ጐዳና ወጣን የባሳን ንጉሥ ዓግ ም ይዋጋን ዘንድ እሱ ከሕዝቡ ሁሉ ጋር ሁኖ በኤንድራ ይን ተቀበለን ። ዘኍ፡ ፳፩ ፴፫ ፥ ዘዳ፡ ፳፱ ፯ ።

እግዚአብሔርም ሠራዊቱንም አገሩንም በእጅህ እጥ ለዋለሁና አትፍራው ፥ በሐሴቦን የሚኖር የአሞሬዎን ንጉሥ ሴዎንን እንዳደረግኸው ታደርገዋለህ አለኝ ።

ፈጣሪያችን እግዚአብሔር የባሳን ንጉሥ ዓግን ከሠራዊቱ ጋር በእጃችን ጣለው ፥ ከሱም ዘር ሳናስቀር አጠፋነው ።

በዚያ ወራት አገሮቹን ሁሉ እጅ አደረግናቸው ፥ ከነ ሳቸው እጅ ያላደረግነው አገር የለም ስሳውን አገር በባሳን ያለ የዓግ ግዛት የአርጎብን አውራጃ ሁሉ እጅ አደረግን ።

እጅግ ብዙ የሆኑ የፌርዜዎን አገሮች ሳይቀሩ ምሽጎ ቻቸውም ረጃጅሞች የሆኑ መዝጊያ ቍልፍ ያላቸው አገ ሮቹን ሁሉ እጅ አደረግን ።

የሐሴቦን ንጉሥ ሴዎንን እንዳጠፋነው እነሳቸውንም አጠፋናቸው አገሮቻቸውንም ሁሉ በአንድነት አጠፋን ፥ የሚሸሸ ሳይቀር ልጆቻቸውንና ሚስቶቻቸውንም አጠፋን።

ከአገሮቻቸው የዘረፍነው ገንዘባቸውንና ከብቶቻቸው ንም ሁሉ አጠፋን። መዝ፡ ፻፴፭ ፲፱ ።

በዮርዳኖስ ማዶ ካሉ ከሁለቱ ከአሞሬዎን ነገሥታት እጅ ከአርኖን ወንዝ ጀምሮ የፊንቂስ ሰዎች አኤርሞን ፥ የአሞሬዎንና የሰኒዮርስ ሰዎች ሳኔር የሚሉት ምድራቸ ውን እጅ አደረግን ። ዘዳ፡ ፪ ፴፰፡ ኢያ፡ ፲፩ ፫ ።

በባሳን ያለ እስከ ዓግ ግዛት አገር ኤንድራይንና እስከ ኤልክድ ድረስ የገለዓድንና የኔሶርን አገሮች ሁሉ እጅ አደረግን ። ኢያ፡ ፲፪ ፭ ፥ ፲፫ ፲፩ ።

ነገር ግን ከአርበኞች የባሳን ንጉሥ ዓግ ነበርና እነሆ የብረት አልጋ የምትሆን አልጋ በአሞን ልጆች አገር ዳርቻ ነበረች፡ አቈልቋይዋ ዘጠኝ ክንድ፡ ወርዷ አራት ክንድ ነበር። ፪ ሳሙ፡ ፲፪ ፳፯ ።

ከአሮኤር ጀምሮ እስከ አርኖን ወንዝ ማዶ ድረስ በዚያ ወራት ያችን አገር ዘረፍናት ፥ የገለዓድ ዶጋ እኩሌታ ሸለ ቆዎችንና አገሮቻቸውንም ለሮቤልና ለጋድ ሰጠኋቸው ።

ከዓግ ግዛትና ከገለዓድ የቀረውን ባሳንንም ሁሉ የአር ጎብንም አውራጃ ሁሉ ለምናሴ ነገድ እኩሌታ ሰጠኋቸው ይህ ባሳን ሁሉ ከአርበኞች አገር ጋራ የሚቈጠር ነው ።

የምናሴ ልጅ ኢያእርም እስከ ጌርጋሴና እስከ መከጢ አውራጃ ድረስ የአርጎብን አውራጃ ሁሉ እጅ አደረገ ፥ እስከዚችም ቀን ድረስ ባሳንን በስሙ የኢያእር (አውታይ) መንደር ብሎ ጠራው ፥ ለማኪርም ገለዓድን ሰጠሁት ።

፲፬ ወለሮቤል ወለጋድ ወሀብክዎሙ እምድረ ገለአድ እስ ከ ፈለገ አርኖን ዘማእከለ ፈለገ አድባር ወእስከ ኢያቦቅ ፈለገ አድባር ዘደቂቀ አሞን ።

የአሞን ልጆች እስከ ያዙት የደጋ ወንዝ እስከሌቡት እስከ ኢያቦቅ ድረስና በደጋ ወንዝ መከከል እስከ አርኖን ወንዝ ከገለዓድ አገር ለጋድና ለሮቤል ሰጠኋቸው ።

፲፭ ወዓረብ ወዮርዳኖስ ወሰኖሙ ለመከናሬ ወእስከ ባሕረ ዓረብ ባሕረ ኤሌቂ እምአሲዶን ዘፋስጋ ጽባሒሁ ።

የምሥራቁ ፋስጋ ከሚሆን ከአሲዶን ጀምሮ ይኸውም ባሕረ ጨው ነው ፤ በስተ ግራ እስከለ ባሕር ድረስ ዮርዳኖስና ዓረብ ለመከናሬ ወሰናቸው ነው ። ዘኍ፣ ፴፱ ፲፰ ።

፲፮ ወአዘዝኩክሙ በውእቱ መዋዕል ወእቤለክሙ እግዚ አብሔር አምላክክሙ ወሀበክሙ ዘተ ምድረ መክፈልተ ክሙ ከመ ትሑሩ ምስለ ንዋየ ሐቅልክሙ ቅድሜሆሙ ለደቂቀ እስራኤል ኣኃዊክሙ ኵሎ ደቂቀ ኃይል ።

ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር ይህችን ምድር ርስት አድ ርጎ ሰጣችሁ እናንተ ግን ኃይል ያላችሁ ልጆች ሁሉ የጦር መሣሪያዎቻችሁን ይዛችሁ በወንድሞቻችሁ በእስራኤል ልጆች ፊት ትሄዳላችሁ ብዬ በዚያ ወራት አዘዝኋችሁ ።

፲፯ ዘእንበለ አንስትያክሙ ወደቂቅክሙ ወአእምር ከመሂ ብዙኅ እንስሳ ብክሙ

ከልጆቻችሁና ከሚስቶቻችሁ በቀር ብዙ ከብት እንዳ ላችሁም አውቃለሁ ።

፲፰ ወይንበር ባሕቲቱ ውስተ አህጉሪክሙ ዘወሀብኩክሙ እስከ አመ ያዐርፎሙ እግዚአብሔር አምላክነ ለአኀዊክሙ ከማክሙ ።

ነገር ግን ፈጣሪያችን እግዚአብሔር ወንድሞቻችሁን እናንተን ርስት ሰጥቶ እንዳሳረፈ ፤ ርስት ሰጥቶ እስኪያሳ ርፋቸው ድረስ በሰጠኋችሁ ከተሞች ይኑሩ (ይቀመጡ) ።

፲፱ ወይወርሱ እሙንቱሂ ምድረ እንተ ይሁቦሙ እግዚአ ብሔር አምላክነ በማዕዶተ ዮርዳኖስ ፤ ወእምዝ ትገብኡ ኵልክሙ ውስተ ርስትክሙ ዘወሀብኩክሙ ።

እነሳቸውም ፈጣሪያችን እግዚአብሔር በዮርዳኖስ ወድያ ማዶ የሚሰጣቸውን አገር እስኪወርሱ ድረስ በዚያ ይኑሩ ፤ ከዚህ በኋላ ሁላችሁም ወደ ሰጠኋችሁ ርስታችሁ ትመለሳላችሁ ። ኢያ፣ ፳፪ ፬ ።

፳ ወአዘዝክዎ ለኢያሱኒ በውእቱ መዋዕል ወእቤሎ ርእ ያ አዕይንቲከ ኵሎ ዘገብረ እግዚአብሔር በእሉ ክልኤቱ ነገሥት ከማሁ ይገብር እግዚአብሔር በኵሉ መንግሥት ኀበ ተሐውር አንተ ህየ ፤ ወኢትፍራህ እምኔሆሙ እስመ እግዚአብሔር ይፀብአሙ ለክሙ ።

በዚያ ወራት ኢያሱን አዘዝኩት በሊህ በሁለቱ ነገሥ ታት እግዚአብሔር ያደረገውን ነገር ዓይኖችህ አይተዋል እንደዚሁም አንተ በዚያ በምታልፍበት ግዛት ሁሉ ላይ ያደርጋል እግዚአብሔር ያጠፋላችኋልና ከነሡ የተነሣ አትፍራ ።

፳፩ ወሰአልክዎ ለእግዚአብሔር በውእቱ መዋዕል ወእ ቤሎ እግዚኦ እግዚእየ አንተ አኀዝከ ታርእዮ ለገብርከ ዕበየከ ወኀይለከ ወጽንዐ እዴከ ወልዕልና መዝራዕትከ ፤ ወመኑ ውእቱ አምላክ በሰማይ ወበምድር ዘይገብር በከ መ ገበርከ አንተ ።

በዚያ ወራት እግዚአብሔርን ለመንኩት አቤቱ ጌታዬ ከሃሊነትህንና ገናናነትህን ጽኑ ሥልጣንህን ለኔ ለባርያህ ትገልጥ ዘንድ ጀመርክ ፤ አንተ እንደምታደርገው በሰማ ይና በምድር የሚያደርግ ማነው ፤ ።

፳፪ አብሕኒ እዕዱ ወእርአያ ለይእቲ ምድር ቡርክት እንተ ሀለወት ማዕዶተ ዮርዳኖስ ወለውእቱ ደብር ቡሩክ ወለአ ንጢሊባኖን ።

ተሻግሬ በዮርዳኖስ ወድያ ማዶ ያለችውን የከበረች ውን አገር አያት ዘንድ አንጢሊባኖንንና ያን የከበረውን ተራራ አየው ዘንድ አሰናብተኝ አልሁት ። ዘዳ፣ ፩ ፳፪ ።

፳፫ ወተጸመመኒ እግዚአብሔር ወኢሰምዐኒ ፤ ወይቤለኒ እግዚአብሔር በዝኑ አከለከ ወኢትድግም እንከ ተናግሮ ዘንተ ቃለ አላ ዕርግ ውስተ ርእስ ዘውቅር ።

እግዚአብሔርም ቸል አለኝ አልሰማኝም ፤ በቃህ በዛ (ይበቃሃል) የኖራ ግንብ ወዳለበት ተራራ ወጥተህ ፤ በዓ ይኖችህ ወደ ምዕራብ ፤ ወደ ሰሜን ፤ ወደ ደቡብ ፤ ወደ ምሥራቅ ፤ ተመልከት እንጂ ፤ እንግዲህ ወዲህ ይህንን ቃል አትድገመው አለኝ ።

፳፬ ወነጽር በአዕይንቲከ መንገለ ባሕር ወመስዕ ወአዜብ ወሠርቅ ወርኢ በአዕይንቲከ እስመ ኢተዐድዎ ለዝንቱ ዮርዳኖስ ።

ይህን ዮርዳኖስን አትሻገረውምና በዓይኖችህ ምድሪ ቱን እይ ፤ (እይ እንጂ ይህን ቃል አትናገር አለኝ) ።

፳፭ ወአዝዞ ለኢያሱ ወአጽንዖ ሎቱ እስመ ውእቱ የዐዱ ቅድሜሁ ለዝንቱ ሕዝብ ወውእቱ ያወርሶ ምድረ እንተ ርኢከ ።

ነገር ግን ኢያሱን እዘዘው ፤ እሱን አጽናው አደፋፍ ረው በዚህ ወገኔ ፊት ዮርዳኖስን ይሻገራልና ፤ አንተ ያየ ሃትን ምድር እሱን ያወርሳቸዋልና ። ዘኍ፣ ፳፯ ፲፰ ።

፳፮ ወነበርነ ውስተ ወግር ኀበ ቤተ ፌጎር ።

የፌጎር ቤት ባለበት ከረብታም ሰፍረን ተቀመጥን ።

ምዕራፍ ፬ ።

ምዕራፍ ፬ ።

፩ ወይእዜኒ እስራኤል ስምዐ ኵነኔሁ ወፍትሖ ለእግዚ አብሔር ዘእሜህረክሙ አነ ዮም ከመ ትግበሩ ወትሕየዉ ወትብዝኁ ወትምልኡ ወትበኡ ወትረስዋ ለምድር ዘይሁ

አሁንም እስራኤል ሆይ ታደርጉት ዘንድ በሕይወትም ትኖሩ ዘንድ እንድትበዙም በዚህም ዓለም ትመሉ ዘንድ የአባቶቻችሁ ፈጣሪ እግዚአብሔር የሚሰጣችሁንም አገር

በከሙ እግዚአብሔር አምላክሙ ለአበዊክሙ ።

ትወርሷት ዘንድ እኔ አሁን የማስተምራችሁን የእግዚአብሔር ፍርዱን ሥርዓቱን ስሙ ። ዘሌዋ፡ ፲፰ ፬ ።

፪ ወኢትወስኩ ላዕለ ዝ ቃል ዘአኤዝዘክሙ አነ ዮም ወኢታንትጉ እምኔሁ ከመ ትዕቀቡ ኵሎ ትእዛዘ ለእግዚአብሔር አምላክክሙ ።

እኔ አሁን በማዝዛችሁ ቃል ላይ አትጨምሩ ፤ የፈጣሪያችሁ የእግዚአብሔርን ሕጉን ትጠብቁ ዘንድ ከሱም አታጕድሉ ። ዘዳ፡ ፲፪ ፴፪ ፡ ራእ፡ ፳፪ ፲፱ ።

፫ አዕይንቲክሙ ርእያ ኵሎ ዘገብረ እግዚአብሔር አምላክነ በብዔል ፌጎር እስመ ኵሎ ብእሴ ዘሖረ ድኅረ ብዔል ፌጎር ቀጥቀጠ እግዚአብሔር አምላክክሙ እምኔክሙ ።

ብዔል ፌጎርን ያመለከ ሰው ሁሉ ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር ከናንተ አጥፍቶታልና ፈጣሪያችን እግዚአብሔር ያደረገውን ሁሉ ዓይኖቻችሁ አይተዋል ።

፬ ወአንትሙሰ እለ ገባእክሙ ኀበ እግዚአብሔር አምላክክሙ ሕያዋን ኵልክሙ ዮም ።

ወደ ፈጣሪያችሁ ወደ እግዚአብሔር የተመለሳችሁ እናንተ ግን ፤ ዛሬ ሁላችሁም ደኅና ናችሁ ።

፭ ናሁ ርእዩ ዘአርአይኩክሙ ኵነኔ ወፍትሐ በከመ አዘዘኒ እግዚአብሔር እግበር ከማሁ ትግበሩ በምድር ዘትበውኡ ህየ አንትሙ ከመ ትትዋረስዋ ።

እነሆ ገብታችሁ በምትወርሷት ምድር በዚያ እንደ ዚሁ ታደርጉ ዘንድ እግዚአብሔር እንዳዘዘኝ ያስተማርኳችሁን አምልኮቱንና ዘጠኙን ሕገጋት እነሆ አስተውሉ ።

፮ ወዕቀብዎ ወግበርዎ እስመ ውእቱ ጥበብክሙ ወአእምሮትክሙ በቅድመ ኵሉ አሕዛብ እለ ይሰምዕዎ ለዝንቱ ኵሉ ኵነኔ ወይብሉ ናሁ ዝንቱ ሕዝብ ጠቢብ ወማእምር ወሕዝብ ዐቢይ ውእቱ ዝንቱ ።

ይህንን ሥርዓቱን ፍርዱን ጠብቁት አድርጉትም ይህን ሁሉ በሚሰሙት አሕዛብ ፊት እሱ ጥበባችሁ ዕውቀታችሁ ነውና እነሆ ይህ ወገን ብልህ አዋቂ ገናና ወገን ነው ይላሉ ። ምሳ፡ ፩ ፯ ፤ ኢዮ፡ ፳፰ ፳፰ ።

፯ ወመኑ ውእቱ ሕዝብ ዐቢይ ዘቦቱ አምላክ ዘይቀርቦ ከመ አምላክነ እግዚአብሔር በኵሉ ዘጸዋዕናሁ ።

በለመነው ሁሉ እንደ ፈጣሪያችን እግዚአብሔር የሚቀርበው ፈጣሪ ያለው ታላቅ ወገን ማን ነው ! ።

፰ ወመኑ ውእቱ ሕዝብ ዐቢይ ዘቦቱ ኵነኔ ወፍትሕ ዘጽድቅ በከመ ዝንቱ ኵሉ ሕግ ዘአነ እሁበክሙ ዮም ቅድሜክሙ ።

እነሆ አሁን እኔ በፊታችሁ በማስተምራችሁ ሕግ ሁሉ እውነት ፤ ሕግና ሥርዓት ያለው ታላቅ ወገን ማነው ! ።

፱ ዑቅ ርእሰከ ወዕቀብ ነፍሰከ ጥቀ ከመ ኢትርሳዕ ኵሎ ዘንተ ነገረ ዘርእያ አዕይንቲከ ወኢይደኅእ እምልብከ በኵሉ መዋዕለ ሕይወትከ ወመሀሮሙ ለደቂቅከ ወለደቂቀ ደቂቅከ ።

ለራስህ ዕወቅ ዓይኖችህ ያዩት ይህን ሁሉ ነገር እን ዳትዘነጋ ፈጽመህ ሰውነትህን ጠብቅ በኖርህበት ዘመን ሁሉ ከልቡናህ አይውጣ ፤ ለልጆችህና ለልጅ ልጆችህም አስተምራቸው ። ዘፍ፡ ፲፰ ፲፱ ፤ ዘዳ፡ ፲፩ ፲፱ ።

፲ ወአይድዖሙ ዘከመ ቆምክሙ ቅድመ እግዚአብሔር አምላክክሙ በኮሬብ አመ ዕለተ ተጋባእክሙ እስመ ይቤለኒ እግዚአብሔር አስተጋብኦሙ ለሕዝብ ኀቤየ ወይስምዑ ቃልየ ከመ ይትመሀሩ ፈሪሀትየ በኵሉ መዋዕል ዘቦቱ የሐይዉ እሙንቱ ላዕለ ምድር ወይምሀሩ ለደቂቆሙ ።

እግዚአብሔር ሕዝቡን ወደኔ ሰብስባቸው እነሳቸው በዚህ ዓለም በሕይወት በሚኖሩበት ዘመን ሁሉ አምልኮቴን ይማሩ ዘንድ ለልጆቻቸውም ያስተምሩ ዘንድ ቃሌን ይስሙ ብሎኛልና በኮሬብ በተሰበሰባችሁ ጊዜ በፈጣሪያችሁ በእግዚአብሔር ፊት እንደቆማችሁ ንገራቸው ።

፲፩ ወመጻእክሙ ወቆምክሙ ታሕተ ደብር ፤ ወይነድድ ደብሩ በእሳት እስከ ሰማይ ፤ ወጽልመት ወዓውሎ ወጣቃ ።

መጥታችሁም ከተራራው በታች ቆማችሁ ፤ ተራራውም እስከ ሰማይ ድረስ እንደ እሳት ይነድ ነበር ጨለማ ጥቅል ነፋስም ነበር ። ዘፀ፡ ፲፱ ፲፰ ፡ ዕ ፲፰ ።

፲፪ ወነበበኒ እግዚአብሔር በማእከለ እሳት ወሰማዕክሙ አንትሙ ቃሎ እንዘ ይትናገር ወርእየቶሰ ኢርኢክሙ ዘእንበለ ቃሎ ዘሰማዕክሙ ።

በእሳት መካከል እግዚአብሔር ተናገረኝ ሲናገርም እናንተ ቃሉን ሰምታችኋል ከሰማችሁት ቃል በቀር መልኩን ግን አላያችሁትም ። ዘዳ፡ ፭ ፳፬ ፡ ፱ ፴፫ ።

፲፫ ወአይድዐክሙ ኪዳኖ ዘአዘዘክሙ ከመ ትግበሩ ዐሠሩ ቃላተ ዘጸሐፎን ውስተ ክልኤ ጽላተ ዘእብን ።

በሁለቱ የዕንቍ ጽላት የጻፋቸውን ዓሥሩን ቃላት ትጠብቁ ዘንድ ያዘዛችሁን ቃል ኪዳኑን ነገራችሁ ።

፲፬ ወሊተኒ ዘአዘዘኒ እግዚአብሔር ከመ እምሀርክሙ በውእቱ መዋዕል ኵነኔ ወፍትሐ ዘትገብሩ በምድር እንተ ውስቴታ ትበውኡ አንትሙ ትረስዋ ።

ትወርሷት ዘንድ እናንተ በምትገቡበት አገር የምታደርጉትን አምልኮትና ዘጠኙን ሕገጋት በዚያ ወራት አስተምራችሁ ዘንድ እግዚአብሔር አዘዘኝ ። ዘፀ፡ ፳፩ ፩ ።

፲፭ ወዕቀቡ ጥቀ ነፍሰክሙ እስመ ኢርኢክሙ ርእየቶ በይእቲ ዕለት እንተ ባቲ ተናገረክሙ እግዚአብሔር በኮሬብ ላዕለ ደብር እማእከለ እሳት ከመ ኢትጌግዩ ።

እንዳትበድሉ በተራራው ላይ በእሳት መካከል ሁኖ በኮሬብ እግዚአብሔር በተናገረበት በዚያ ቀን ፊቱን አላያችሁትምና ፈጽማችሁ ሰውነታችሁን ጠብቁ ።

፲፮ ወኢትግበሩ ለክሙ ግልፎ በአምሳለ ኵሉ ምስል ፤ በአምሳለ ተባዕት አው በአምሳለ አንስት ።

ምስሉን ሁሉ በማስመሰል በምስሉ ሁሉ አምሳል በወንድ አምሳል ወይም በሴት አምሳል ።

፲፯ ወበአምሳለ ኵሉ እንስሳ ዘሀለወ ላዕለ ምድር ወበአምሳለ ኵሉ ዖፍ ወኵሉ ሠረረ ዘይሠርር በታሕተ ሰማይ ።

በዚህ ዓለም ባለ ከብት ሁሉ አምሳል በወፍም ሁሉ አምሳል ከሰማይ በታች በሚበረው ሁሉ አምሳል ።

፲፰ ወበአምሳለ ኵሉ ሐያው ዘይትሐወስ ላዕለ ምድር ወበ አምሳለ ኵሉ ዐሣ ዘሀለወ ውስተ ማይ መትሕተ ምድር ።

በምድር ላይ በሚንቀሳቀሰው በደመ ነፍስ ሕያው በሆነው ሁሉ አምሳል ፣ ከምድር በታች በውኃው ውስጥ ባለ ዓሣ ሁሉ አምሳል ጣዖትን አትሥሩ ። ዘዳ፡ ፭ ፳፫ ።

፲፱ ወለእመ ነጸርከ ሰማየ ወርኢከ ፀሐየ ወወርኀ ወከዋክብተ ወኵሎ ሠርጓቲሃ ለሰማይ ዮጊ ትጌጊ ወትሰግድ ሎሙ ወታመልኮሙ ለእለ ገብረ እግዚአብሔር አምላክከ ለኵሉ አሕዛብ ዘታሕተ ሰማይ ።

ዓይናችሁን ወደ ሰማይ አቅንተህ ጨረቃና ፀሐይን ጌጠ ጃን ከዋክብትንም ሁሉ አይተህ እነሆ ትበድላለህ ፤ ከሰማይ በታች ላሉ አሕዛብ ሁሉ ፈጣሪህ እግዚአብሔር የፈጠራቸውንም ሁሉ ትሰግድላቸው ታመልካቸውም አለህ ።

፳ ወኪያክሙሰ ነሥአክሙ እግዚአብሔር ወአውፅአክሙ እምእቶነ ሐፂን እምግብጽ ከመ ትኩንዎ መክፈልተ ሕዝቡ እስከ ዛቲ ዕለት ።

እናንተን ግን እስከዚች ቀን ድረስ የወገናቹን ዕድል ፈንታ ትሆኑ ዘንድ ጽኑ አገዛዝ ካለበት ከግብጽ አገር አውጥቶ እግዚአብሔር ገንዘብ አደረጋችሁ ።

፳፩ ወተምዕዐ እግዚአብሔር በእንተ ዘተቤሉ አንትሙ ፣ ወመሐለ ከመ ኢየዐድዎ ለዝንቱ ዮርዳኖስ ወከመ ኢይበውእ ውስተ ምድር ዘይሁበከ እግዚአብሔር አምላክከ ርስተ ።

እናንተ በተናገራችሁት ነገር ምክንያት እግዚአብሔር አኔን ተቈጣኝ ይህን ዮርዳኖስንም እንዳልሻገር ፈጣሪህ እግዚአብሔር ርስት አድርጎ ወደሚሰጥህም አገር እንዳልገባ ማለ ። ዘዳ፡ ፩ ፴፯ ።

፳፪ ናሁ አንሰ እመውት በዛቲ ምድር ወኢየዐድዎ ለዮርዳኖስ ወአንትሙሰ ተዐድውዎ ለዮርዳኖስ ወትትዌረስዋ ለይእቲ ምድር ቡርክት ።

እነሆ እኔ በዚች ምድር እሞታለሁ ፤ ዮርዳኖስን አልሻገረውም እናንተ ግን ዮርዳኖስን ተሻግራችሁ ይህችን የተመሰገነችውን አገር ትወርሷታላችሁ ። ፪ ጴጥ፡ ፩ ፲፫ ።

፳፫ ወዑቁ እንከ አንትሙ ኢትርስዕዎ ኪዳኖ ለእግዚአብሔር አምላክክሙ ዘተካየደ ምስሌክሙ ወእመ አበስክሙ ወገበርክሙ ለክሙ ግልፈ በአምሳለ ኵሉ ምስል ዘበእንቲአሁ ቀሠፈከ እግዚአብሔር አምላክከ ።

እንግዲህ እናንተም ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋራ የተማማለውን ቃል ኪዳኑን እንዳትረሱ ዕወቁ ፤ ብትበድሉና ፈጣሪህ እግዚአብሔር በቀሠፈህ ምስል ሁሉ ጣዖትን ብትሠሩ ።

፳፬ እስመ እግዚአብሔር አምላክከ እሳት እንተ ታኀልቅ ውእቱ ፣ ወአምላክ ቀናኢ ውእቱ ።

ፈጣሪህ እግዚአብሔር የምታጠፋ እሳት ነውና ፣ ለአምላክነቱም የሚቀና አምላክ ነውና ። ዘፀ፡ ፳ ፭ ።

፳፭ ወለእመ ወለድከ ደቂቀ ወአዋልደ ወደቂቀ ደቂቅከ ወኑንደይክሙ ላዕለ ምድር ወአበስክሙ ወገበርክሙ እኪተ ቅድመ እግዚአብሔር አምላክክሙ ከመ ታምዕዖ ።

ሴቶች ልጆችና ወንዶች ልጆችንም ብትወልድ የልጅ ልጅም ብታይ በዚህም ዓለም ብዙ ዘመን ብትኖሩ ብትበድሉ በሁሉም አምሳል ለናንተ ጣኦት ብትሠሩ ታስቆጡትም ዘንድ በፈጣሪያችሁ በእግዚአብሔር ዘንድ ክፉ ነገር ብታደርጉ ። ፪ ነገ፡ ፲፯ ፲፯ ።

፳፮ ናሁ አስምዕ ለክሙ ሰማየ ወምድረ ከመ ትጠፍኡ ወትደመሰሱ እምድር እንተ ላቲ አንትሙ ተዐድውዎ ለዮርዳኖስ ህየ ከመ ትትዌረስዋ ወኢታኑንድዩ መዋዕለ ውስቴታ አላ ተቀጥቅጦ ትትቀጠቀጡ ።

ትወርሷት ዘንድ እናንተ ወደዚያ ዮርዳኖስን ከምትሻገሩላት አገር ፈጽማችሁ እንደምትጠፉ እነሆ ሰማይንና ምድርን አዳኝባችኋለሁ ፤ ፈጽማችሁ ትጠፋላችሁ እንጂ በዚ ብዙ ዘመን አትኖሩም ። ዘዳ፡ ፴ ፲፱ ።

፳፯ ወይዘርወክሙ እግዚአብሔር ውስተ ኵሉ አሕዛብ ወትተርፉ ውኁዳነ በኍልቍ ውስተ ኵሉ አሕዛብ እለ ውስቴቶሙ ያበውአክሙ እግዚአብሔር ህየ ።

እግዚአብሔር በአሕዛብ አገር ሁሉ ይበትናችኋል ፤ እግዚአብሔር አስማርኮ ወስዶ በዚያ በሚያኖራችሁ በአሕዛብ አገር በቍጥር ጥቂቶች ሁናችሁ ትቀራላችሁ ።

፳፰ ወታመልኩ በህየ አማልክተ ግብረ እደ እጓለ እመሕያው ዕፀወ ፣ ወእእብነ ፣ እለ ኢይሬእዩ ፣ ወኢይሰምዑ ወኢይበልዑ ፣ ወኢያጼንዉ ።

በዚያም የማያዩ የማይሰሙ የማይበሉ የማያሸቱ ሰው ሠራሽ የሚሆኑ የአሕዛብ ጣኦታት ዕንጨትንና ድንጊያዎችን ታመልካላችሁ ። ዘዳ፡ ፳፰ ፴፯ ፣ ኤር፡ ፲፮ ፲፫ ።

፳፱ ወአምዝ ተኀሥሥዎ ለእግዚአብሔር አምላክክሙ በህየ ወትረክብዎ ሶበ ኀሠሥክምዎ በኵሉ ልብክሙ ወበ ኵሉ ነፍስክሙ በሕማምክሙ ።

ከዚህ በኋላ ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔርን (በንስሐ) ትፈልጉታላችሁ በመከራችሁም ጊዜ በፍጹም ሰውነታችሁና በፍጹም ልቡናችሁ በዚያ በፈለጋችሁት ጊዜ (በረድኤት) ታገኙታላችሁ ። ዘሌ፡ ፳፮ ፴፱ ፣ ዘዳ፡ ፴፩ ፫ ።

፴ ወይረክበክሙ ኵሉ ዝንቱ ነገር በደኃሪ መዋዕል ወትትመየጡ ኀበ እግዚአብሔር አምላክክሙ ወይሰምዐክሙ ።

በኋላ ዘመን ይህ ሁሉ ነገር አግኝቶአችሁ (በንስሐ) ወደ ፈጣሪያችሁ ወደ እግዚአብሔር ትመለሳችሁ ፣ እሱም ይሰማችኋል ። ዘኍ፡ ፵፱ ፴፱ ፣ ሆሴ፡ ፫ ፭ ።

፴፩ እስመ አምላክ መሐሪ ውእቱ እግዚአብሔር አምላክከ ኢየኀድገከ ወኢያጠፍአከ ወኢይረስዕ ኪዳኖሙ ለአበዊከ ዘመሐለ ሎሙ ።

ፈጣሪህ እግዚአብሔርም ይቅር ባይ አምላክ ነውና በረድኤት ተለይቶ አያጠፋህም ፣ ለአባቶችህ የማለላቸውንም መሐላ አይዘነጋም ። ዘፀ፡ ፴፬ ፮ ፣ ነህ፡ ፱ ፴፩ ።

፴፪ ተሰአሉ ዘቀዲሙ መዋዕለ ዘኮነ እምቅድሜክሙ እም አመ ፈጠሮ እግዚአብሔር ለእጓለ እመሕያው ዲበ ምድር እምአጽናፈ ሰማይ እስከ አጽናፈ ሰማይ ለእመ ኮነ ከመ ዝንቱ ነገር ።

እግዚአብሔር ሰውን ከፈጠረው ጀምሮ ከሰማይ ዳር ቻ እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ እንደዚህ ያለ ነገር ተደርጎ እንደሆነ ከናንተ አስቀድሞ የነበረውን ዘመን ጠይቁ ።

፴፫ ወለእመ ሰምዑ ሕዝብ ቃለ እግዚአብሔር አምላክ ዘሕያው እንዘ ይትናገር እማእከለ እሳት በከመ ሰማዕከ አንተ ወሐየውከ ።

አንተ ሰምተህ እንደ ዳንክ በእሳት መካከል ሲናገር ሕዝቡ ሕያው የሚሆን የእግዚአብሔር አምላክ ቃልን ሰምተው ድነው እንደሆነ ። ዘፀ ፳፬ ፲፩ ፡ ፴፫ ፳ ።

፴፬ ለእመ አመከረ እግዚአብሔር ወቦአ ወነሥአ ሎቱ ሕ ዝበ እማእከሉ ሕዝብ በአመክሮ ወበተአምር ወበመድምም ወበቀትል ወበእድ ጽንዕት ወበመዝራዕት ልዑል ወመደ ንግፅ ዐቢይ በከመ ኵሉ ዘገብረ እግዚአብሔር በምድረ ግብጽ በቅድሜከ እንዘ ትሬኢ ።

እግዚአብሔር በፊትህ እያየህ በግብጽ ምድር ላንተ እንዳደረገው ሁሉ በመፈታተን በድንቅ ተአምራት በጽ ናች እጅና በተዘረጋች ክንድ በታላቅ ማስደንገጥም እግዚ አብሔር ከሌላ ወገን ገብቶ የፈተነው ወገን አለ እንደሆነ ጠይቅ ።

፴፭ ከመ ታእምር ከመ ውእቱ እግዚአብሔር አምላክ ወአ ልቦ ባዕድ አምላክ ዘእንበሌሁ ።

እግዚአብሔርም ፈጣሪ እንደሆነ ታውቅ ዘንድ ያለሱም ሌላ አምላክ እንደ ሌለ ታውቅ ዘንድ ጠይቅ ። ዘፀ ፮ ፫ ።

፴፮ እምሰማይ ተሰምዐ ቃሉ ከመ ይምሀርከ ወበምድር አርአየ እሳቶ ዐቢየ ወሰማዕከ ቃሎ እማእከለ እሳት ።

ያስተምርህም ዘንድ ከሰማይ ወርዶ ቃሉ ተሰማ በም ድርም የሚያስፈራ እሳቱን አሳየ ፡ በእሳቱም መካከል ቃሉን ሰምተሃል ። ዘፀ ፲፱ ፲፬ ።

፴፯ እስመ ያፈቅሮሙ ለአበዊከ ወኀረዮሙ ወለዘርኦሙ እምድኅሬሆሙ ኪያከ እምኵሉ አሕዛብ ወአውፅአከ ውእ ቱ በኀይሉ ዐቢይ እምግብጽ ።

አባቶችህን ይወዳቸዋልና ፡ ስለዚህ ከነርሱ በኋላ ከአ ሕዛብ ሁሉ ለይቶ እናንተን ልጆቻቸውን ዘራቸውን መረ ጠ ፡ የመረጠህ እርሱም በጽኑ ከሃሊነቱ ከግብጽ አወጣህ ።

፴፰ ከመ ያጥፍኦሙ ለአሕዛብ ዐበይት ወጽኑዓን እምቅ ድመ ገጽከ ወከመ ያብእከ ወየሀብከ ምድሮሙ ትረስ በከ መ ሀለውከ ዮም ።

ታላላቆች ጽኑዓን የሚሆኑ አሕዛብን ከፊትህ ያጠፋ ቸው ዘንድ ትወርስም ዘንድ እንዳለህ አገራቸውንም ይሰ ጥህ ዘንድ በፍጹም ኃይሉ ከግብጽ አወጣህ ። ዘዳ ፲ ፲፭ ።

፴፱ ወትእምር ዮም ከመ ውእቱ እግዚአብሔር አምላክከ ውእቱ እግዚአብሔር በሰማይ በላዕሉ ወበምድር በታሕቱ ወአልቦ ባዕድ ዘእንበሌሁ ።

ከምድር በላይ ባለ በሰማይ ፡ ከሰማይ በታች ባለ በም ድርም ፈጣሪህ እግዚአብሔር እንደሆነ ያለሱም ሌላ ፈጣ ሪ እንደሌለ አሁን ታውቃለህ ። ዘዳ ፬ ፴፭ ።

፵ ወዕቀቡ ኵነኔሁ ወትእዛዞ ዘአኤዝዘክሙ አነ ዮም ከመ ሠናየ ይኩንክሙ ፡ ወለውሉድክሙሂ እምድኅሬክሙ ፡ ወከመ ይኑኅ መዋዕሊክሙ ውስተ ምድር ዘይሁበክሙ እግዚአብሔር አምላክክሙ በኵሉ መዋዕል ።

በዘመኑ ሁሉ ለናንተ ከናንተም በኋላ ለልጆቻችሁ በጎ ነገር ይሆንላችሁ ዘንድ ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር በሚሰጣችሁ ምድር ዕድሜያችሁ ይረዝም ዘንድ እኔ ዛሬ የማዝዛችሁ ሥርዓቱን ትእዛዙን ጠብቁ ። ዘሌ ፳፪ ፴፩ ።

፵፩ ወይእተ አሚረ ፈለጠ ሙሴ ሠላሰ አህጉረ በማዕዶተ ዮርዳኖስ መንገለ ሠርቀ ፀሐይ ከመ ይስኪ ህየ ቀታሊ ዘቀ ተለ ካልአ እንዘ ኢያአምር ወኢኮነ ጸላኢሁ ትካት ወይስኪ ውስተ አሐቲ እምእላንቱ አህጉር ወየሐዩ ።

ሙሴም ያን ጊዜ በዮርዳኖስ ማዶ በስተምሥራቅ በኩል ሦስት መማፀኛዎችን አህጉር ለየ ፡ ሳያውቅ ጥንተ ጠላቱ ሳይሆን ባልንጀራውን የገደለ ሰው በዚያ ይማጠን ዘንድ ከነዚያ መማጠኛዎች በአንዲቱ ተማጥኖ ይድናል ።

፵፪ ቤሶር በገዳም ውስተ ምድረ ሐቅል ዘሮቤል ፡ ወአራ ሞት በገለአድ ዘጋድ ፡ ወአውሎን ዘባሳን ዘምናሴ ።

እነዚህም የጋድ ዕፃ በምትሆን በገለዓድ ያለች አራ ሞትና የሮቤል ዕፃ በምትሆን ምድረ በዳ ያለች ባሶር ፡ የምናሴ ዕጻ በምትሆን በባሳን ያለች አውሎን ናቸው ።

፵፫ ዝንቱ ውእቱ ሕግ ዘአዘዞሙ ሙሴ በቅድሜሆሙ ለደ ቂቀ እስራኤል ።

ሙሴ በእስራኤል ልጆች ፊት ያዘዛቸው ሥርዓት ይህ ነው ።

፵፬ ወዝንቱ ውእቱ ትእዛዝ ወኵነኔ ወፍትሕ ኵሉ ዘነገሮሙ ሙሴ ለኵሉ ደቂቀ እስራኤል በገዳም ወፂአሙ እምድረ ግብጽ ።

ከግብጽ ከወጡ በኋላ ለእስራኤል ልጆች በምድረ በዳ ሙሴ የነገራቸው ትእዛዝ ሥርዓትና ፍርድ ይህ ነው ።

፵፭ በማዕዶተ ዮርዳኖስ በቈላት ዘቅሩበ ቤተ ፌጎር በም ድረ ሴዎን ንጉሠ አሞሬዎን ዘይነብር ውስተ ሐሴቦን ዘቀተ ሎ ሙሴ ወደቂቀ እስራኤል ወፂአሙ እምድረ ግብጽ ።

ከግብጽ ከወጡ በኋላ ሙሴና የእስራኤል ልጆች የገ ደሉት በሐሴቦን በሚኖር በአሞሬዎን ንጉሥ በሴዎን ምድር በፌጎር ቤት አቅራቢያ በሚሆን ሸለቆ በዮርዳኖስ ማዶ የነገራቸው ይህ ነው ። ዘኊ ፫ ፳፱ ።

፵፮ ወተዋረሱ ምድሮ ወምድረ ዓግ ንጉሠ ባሳን ክል ኤቱ ነገሥተ አሞሬዎን እለ ይነብሩ ማዕዶተ ዮርዳኖስ መንገለ ሠርቀ ፀሐይ ።

ምድሩንም ወረሱ የባሳን ንጉሥ የዓግን አገርንም ወረ ሱ ፡ እነዚህም በፀሐይ መውጫ አንጻር ባለ በዮርዳኖስ ማዶ የሚኖሩ ሁለቱ ነገሥታት ናቸው ። ዘኍ ፳፩ ፴፭ ።

፵፰ እምአሮኤር እንተ ማዕዶተ ፈለገ አርኖን እስከ ደብረ
ሴዎን ዘኤርሞን ።
፵፱ ወኵሉ ዓረብ ለማዕዶተ ዮርዳኖስ ዘመንገለ ሠርቀ
ፀሐይ ዘመትሕተ አሴዶን ዘበ መንደቅ ።

## ምዕራፍ ፭ ።

፩ ወጸውዖሙ ሙሴ ለኵሎሙ ማኅበረ እስራኤል ወይ
ቤሎሙ ስምዑ እስራኤል ኵሉ ኵነኔ ወፍትሐ ዘአነ እነግ
ረክሙ ዮም ውስተ ዕዘኒክሙ በዛቲ ዕለት ወተመሀሩ ግበ
ሮቶ ወዐቂቦቶ ።
፪ እግዚእብሔር አምላክክሙ አቀመ ኪዳኖ ምስሌክሙ
በኮሬብ አኮ ለአበዊክሙ ዘአቀመ ዘንተ ኪዳነ አላ ለክሙ
እስመ አንትሙ ሀለውክሙ ዝየ ዮም ኵልክሙ ሕያዋን ።

፫ ገጸ በገጽ ተናገረክሙ እግዚአብሔር በደብር ማእከለ
እሳት ።
፬ ወአንሰ እቀውም ማእከለ እግዚአብሔር ወማእከሌ
ክሙ በይእቲ ዕለት ከመ እንግርክሙ ቃሎ ለእግዚአብ
ሔር እስመ ፈራህክሙ እምቅድመ ገጸ እሳት ወኢዐረግሙ
ውስተ ደብር ።
፭ ወይቤ አነ ውእቱ እግዚአብሔር አምላክከ ዘአውፃእ
ኩከ እምድረ ግብጽ እምቤተ ቅንየት ወኢይኩንከ ባዕድ
አምላክ ዘእንበሌየ ።
፮ ወኢትግበር ለከ አምላከ ዘግልፎ ወኢ በኵሉ አም
ሳል ዘውስተ ሰማይ በላዕሉ ፤ ወኢ ዘውስተ ምድር በታ
ሕቱ ፤ ወኢ በኵሉ ዘውስተ ማይ ዘመትሕተ ምድር ፤
ወኢትስግድ ሎሙ ወኢታምልኮሙ ።

፯ እስመ አነ እግዚአብሔር አምላክከ አምላክ ቀናኢ
ዘእኅልቁ ኃጣውአ ወላዲ ላዕለ ውሉድ እስከ ሣልስ ወራ
ብዕ ትውልድ ለእለ ይጸልኡኒ ።
፰ ወእገብር ምሕረተ እስከ ዐሠርቱ ምእት ትውልድ ፤
ለእለ ያፈቅሩኒ ወለእለ የዐቅቡ ትእዛዝየ ።

፱ ወኢትምሐል በስመ እግዚአብሔር አምላክከ በሐ
ሰት ፤ እስመ ኢያነጽሖ እግዚአብሔር ለዘይምሕል በስሙ
በሐሰት ።
፲ ወዕቀብ ዕለተ ሰንበት ወቀድሳ በከመ አዘዘከ እግዚአ
ብሔር አምላክከ ።
፲፩ ስዱሰ መዋዕለ ትገብር ኵሎ ግብረከ ወሳብዕት ዕለት
ሰንበቱ ለእግዚአብሔር አምላክከ ።
፲፪ ወኢትግበር ባቲ ኵሎ ግብረከ ኢ ወልድከ ፤ ወኢ
ወለትከ ፤ ወኢ ገብርከ ፤ ወኢ አመትከ ፤ ወኢ ላሕምከ ፤
ወኢ አድግከ ፤ ወኢ ኵሉ እንስሳከ ፤ ወኢ ግዩር ዘውስተ
ደደከ ከመ ያዕርፍ ገብርከ ወአመትከ ከማከ ።

፲፫ ወትዘከር ከመ ገብር አንተ በምድረ ግብጽ ወአውፅ
አከ እግዚአብሔር አምላክከ እምህየ በእድ ጽንዕት ፤ ወበ

በአርኖን ወንዝ ዳር ካለች ከአሮኤር ጀምሮ የኤር
ሞን ክፍል እስከምትሆን እስከ ሴዎን ተራራ ድረስ ።
ቅጽር ካለበት ከአሴዶን በታች በፀሐይ መውጫ እን
ጻር ያለ የዮርዳኖስን ማዶ ግራ ሁሉ ወረሱ ።

## ምዕራፍ ፭ ።

ሙሴ የእስራኤልን ወገኖች ሁሉ ጠርቶ እስራኤል
ሆይ በዚች ቀን በጆሮቻችሁ ስትሰሙ ዛሬ እኔ የምነግራች
ሁን ሥርዓትና ፍርድ ሁሉ ስሙ ፤ መሥራቱን መፈጸ
ሙን መጠበቁንም ተማሩ ።
ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር በኮሬብ ከናንተ ጋር መሐ
ላውን አጸና ፤ እናንተ ሁላችሁ አሁን በዚህ በሕይወት
አላችሁና ፤ ይህን መሐላውን ያጸና ለናንተ ነው እንጂ
ለአባቶቻችሁ አይደለም ። ዕብ፥ ፰ ፱ ።
እግዚአብሔር በደብረ ሲና በእሳት መካከል ሁኖ ፊት
ለፊት ተነጋገራችሁ ።
እሳትን ከማየት የተነሣ ፈርታችሁ ወደ ደብረ ሲና
አልወጣችሁም ነበርና ፤ እኔ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እነግ
ግራችሁ ዘንድ በዚች ቀን በናንተና በእግዚአብሔር መካ
ከል ቁሜ ነበር ። ዘፀ፥ ፳ ፳፩ ፤ ፳፱ ፤ ፪ ነገ፥ ፫ ፲፱ ።
ጽኑ አገዛዝ ካለበት ከምድረ ግብጽ ያወጣሁህ ፈጣ
ሪህ እኔ እግዚአብሔር ነኝና ያለኔ ሌላ አምላክ አይኑርህ ።

ከምድር በላይ ባለው በሰማይ የፀሐይና የጨረቃን
ምስል ሁሉ ፤ ከሰማይ በታች ከምድር በላይ ያሉ የእንስ
ሳትንም ምስል ሁሉ ከምድርም በታች ባለ በውኃው
ውስጥ ባሉ በአዞ በጉማሬውም አምሳል ሁሉ የተቀረጹ
ጣኦትን አትሥራ ፤ አትስገድላቸው አታምልካቸውም ።
ለአምልኮቴ የምቀና የአባትንም ኃጢአት ቂም የሚ
በሚጠሉኝ ልጆች እስከ ሦስት ፤ እስከ አራት ትውልድ
ድረስ የማመጣ ።
ለሚወዱኝ ትእዛዜንም ለሚጠብቁ ልጆች ግን እስከ
ሺሕ ትውልድ ድረስ ቸርነቴን የማደርግ ፈጣሪ እኔ እግዚ
አብሔር ነኝና አትስገድላቸው አትገዛላቸውም ።
በሐሰት ስሙን ጠርቶ የሚምለውን ሰው እግዚአብ
ሔር አያነጻውምና የፈጣሪህ የእግዚአብሔርን ስም በሐ
ሰት ጠርተህ አትማል ። ዘዳ፥ ፱ ፬ ፤ ኤር፥ ፴፪ ፲፰ ።
ፈጣሪህ እግዚአብሔር እንዳዘዘህ ዕለተ ሰንበትን (ቅዳ
ሜን) ጠብቀህ አክብራት ። ዘፀ፥ ፳ ፰ ፤ ነህ፥ ፲፫ ፴፯ ።
ስድስት ቀን ሥራህን ሁሉ ሥራ ፤ ሰባተኛይቱ ቀን
ግን የፈጣሪህ የእግዚአብሔር በዓል ናት ።
ሥራህን ሁሉ አትሥራባት ወንድ ልጅህ ሴት ልጅህ
ወንድ ባርያህ ፤ ሴት ባርያህም ሎሌህም ፤ ገረድህም ፤ በሬ
ህም ፤ ከብትህም ፤ ከደጅህም ያለ መጻተኛ እንግዳም ወን
ድ ባርያህና ሴት ባርያህ አንተ እንደምታርፍበት ያርፍ
ዘንድ ሥራህን ሁሉ አትሥራባት ።
በግብጽ አገር አንተ ተገዢ እንደ ነበርህ ፈጣሪህ እግዚአ
ብሔርም በጸናች ሥልጣን ከፍ ባለ ኃይል ከዚያ እንዳወ

| | | |
|---|---|---|
| መዝሬዕት ፈውፈ ፣ መበበይንዝ አዘዘከ እግዚአብሔር አምላክከ ከመ ትዕቀብ ዕለተ ሰንበት ወትቀድሶ ። | | ጣሀ አስብ፤ ስለዚህም ዕለተ ሰንበትን ትጠብቃት ታከብራት ዘንድ ፈጣሪህ እግዚአብሔር አዘዘህ ። |
| አክብር አባከ ወእመከ በከመ አዘዘከ እግዚአብሔር አምላክከ ከመ ይኩን ሠናየ ላዕሌከ፤ ወይኑኅ መዋዕሊከ በዲበ ምድር ዘይሁበከ እግዚአብሔር አምላክከ ። | ፲፬ | ፈጣሪህ እግዚአብሔር በሚሰጥህ ምድር ላይ መልካም ነገር እንዲሆንልህ ዕድሜህም እንዲረዝምልህ እግዚአብሔር አምላክህ እንዳዘዘህ፤ አባትህንና እናትህን አክብር (ርዳ) ። ዘፀ፡ ፳ ፲፪፤ ዘሌ፡ ፲፱ ፫ ። |
| ወኢትሐር ኀበ ብእሲተ ብእሲ ። | ፲፭ | ወደ ጉልማሳ ሚስት አትሂድ (አትድረስ)። |
| ወኢትቅትል ነፍሰ ። | ፲፮ | ነፍስ አትግደል ። ማቴ፡ ፭ ፳፩ ። |
| ወኢትሰርቅ ። | ፲፯ | አትስረቅ ። ዘፀ፡ ፳ ፲፭ ። |
| ወኢትኩን ስምዐ በሐሰት ላዕለ ቢጽከ፤ ወኢተሐሱ ስምዐ ። | ፲፰ | በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር፤ ምስክርነትን አታሳብል ። |
| ወኢትፍቱ ብእሲተ ካልእከ ወኢትፍቱ ቤቶ ለካልእከ ኢገራህቶ ወኢገብሮ፤ ኢአመቶ ወኢላሕሞ፤ ኢአድጎ ወኢእምዙሉ እንስሳሁ፤ ወኢእምዙሉ ዘቦቱ ለካልእከ ። | ፲፱ | የባልንጀራህን ሚስት አትመኝ፤ ቤቱንም እርሻውንም ሴት ባርያውንና ወንድ ባርያውንም፤ በሬውንና አህያውን ከከብቶቹም ሁሉ በባልንጀራህ ካለው ገንዘብ ሁሉ አትመኝ። |
| ዝንቱ ነገር ዘተናገረ እግዚአብሔር ለኩሉ ተዓይኒክሙ በውስተ ደብር በማእከለ እሳት፤ ወጽልመት፤ ወዐውሎ፤ ወቆባር፤ ወቃል ዐቢይ ወኢደገመ እንከ፤ ወጸሐፎ ውስተ ክልኤ ጽላት ዘእብን፤ ወወሀበኒ እግዚአብሔር ። | ፳ | በጨለማና በእሳት፤ በጽጋግና በጥቅል ነፋስ መካከል ሁሉ በሲና ተራራ ላይ በታላቅ ድምፅ እግዚአብሔር ለሠራዊቶቻችሁ ሁሉ የተናገረው ነገር ይህ ነው፤ ከዚያ በኋላ ግን አልጨመረም (አልተሰማም) እግዚአብሔር በሁለቱ የድንጋይ ጽላቶች ጽፎ ሰጠኝ ። ዘፀ፡ ፲፱ ፲፮ ፳ ። |
| ወኮነ ሶበ ሰማዕክሙ ውእቱ ቃለ እማእከለ እሳት ወደ ብሩሂ ይነድድ በእሳት ወመጻእክሙ ኀቤየ ኵልክሙ መላእክተ ነገድክሙ ወአእሩጊክሙ ። | ፳፩ | በእሳቱ መካከል ይህን ቃል በሰማችሁ ጊዜ እንዲህ ሆነ፤ ተራራው በእሳት ይቃጠል ነበር፤ ሽማግሌዎቻችሁና የነገዶቻችሁ አለቆች ወደኔ መጣችሁ ። ዘፀ፡ ፳፬ ፲፪ ። |
| ወትቤሉኒ ናሁ አርአየነ እግዚአብሔር አምላክነ ስብሐቲሁ ወቃሎኒ ሰማዕነ እማእከለ እሳት ወዮም አእመርነ በዛቲ ዕለት ከመ ይትናገር እግዚአብሔር ምስለ ሰብእ ወየሐዩ ። | ፳፪ | እነሆ ፈጣሪያችን እግዚአብሔር ክብሩን ጌትነቱን አሳየን በእሳቱም መካከል ቃሉን ሰማን እግዚአብሔር ከሰው ጋር ተነጋግሮ ሰው እንዲድን ዛሬ ዐወቅን ። |
| ወይእዜኒ ኢንሙት ወኢታጥፍአነ ዛቲ እሳት ዐባይ ለእመ ደገምነ ንሕነ ሰሚዖተ ቃሉ ለእግዚአብሔር አምላክነ ዓዲ ንመውት እንከ ። | ፳፫ | አሁንም እንሙት ይህችም ታላቅ እሳት አታጥፋን፤ ዳግመኛ የፈጣሪያችን የእግዚአብሔርን ቃል መስማትን ብንደግም እንሞታለን ። ዘፀ፡ ፲፱ ፲፬፤ ዘዳ፡ ፲፩ ፮ ። |
| ወመኑ ውእቱ ዘሥጋ ዘይሰምዖ ቃሎ ለእግዚአብሔር ዘሕያው እንዘ ይትናገር እማእከለ እሳት ከማነ ወየሐዩ ። | ፳፬ | ሕያው የሚሆን እግዚአብሔር በእሳት መካከል ሆኖ ሲናገር ቃሉን እንደኛ ሰምቶ የሚድን ሥጋዊ ደማዊ ማነው፤ ። ዘዳ፡ ፲፰ ፲፯ ። |
| ሑር አንተ ወስማዕ ኵሎ ዘይብል እግዚአብሔር አምላክነ ወንግረነ አንተ ኵሎ ዘይቤለከ እግዚአብሔር አምላክነ፤ ወንሰምዕ ወንገብር ። | ፳፭ | አንተ ሂደህ (ቀርበህ) ፈጣሪያችን እግዚአብሔር የሚለውን ሁሉ ሰምተህ ፈጣሪያችን እግዚአብሔር ያለህን አንተ ንገረን ሰምተንም እናደርጋለን አላችሁኝ ። |
| ወሰምዐ እግዚአብሔር ቃለ ነገርክሙ ዘነበብክሙ ወዘትቤሉኒ፤ ወይቤለኒ እግዚአብሔር ሰማዕኩ ቃሎሙ ዘይቤሉ ዝንቱ ሕዝብ ኵሎ ዘይቤሉከ ወርቱዕ ኵሉ ዘይቤሉ ። | ፳፮ | እግዚአብሔርም ያላችሁኝን የነገራችሁኝን ቃል ሰምቶ እነሆ እነዚህ ወገኖች የሚሉህን ቃል ሰማሁ፤ የተናገሩት ነገር ሁሉ የተገባ ነው አለኝ ። ዘፀ፡ ፳ ፲፱ ። |
| መኑ እምወሀቦሙ ከመዝ ይኩን ላዕሌሆሙ ከመ ይፍርሁኒ ወይዕቀቡ ትእዛዝየ በኵሉ መዋዕሊሆሙ ከመ ሠናይተ ትኩኖሙ ወለውሉዶሙ እስከ ለዓለም ። | ፳፯ | ለነሳቸውም ለልጆቻቸውም በጎ ይሆንላቸው ዘንድ በለ ዘመናቸው ሁሉ እስከ ዘለዓለም ድረስ ይፈሩኝና ሕጌን ይጠብቁ ዘንድ እንደዚህ ያለ ዕውቀት ማን በሰጣቸው፤ ። |
| ሑር ወበሎሙ እትዉ ውስተ አብያቲክሙ ። | ፳፰ | ሂደህ ወደየ ቤታችሁ (ድንኳናችሁ) ግቡ በላቸው ። |
| ወአንተሰ ቁም ኀቤየ እንግርከ ትእዛዝየ ወኵነኔየ ወፍትሕየ ወኵሎ ዘትሜህሮሙ ወይግበሩ ከማሁ ውስተ ምድር እንተ አነ እሁቦሙ ርስቶሙ ። | ፳፱ | አንተ ግን የምታስተምራቸው ትእዛዜን ሥርዓቴንና ፍርዴን ሁሉ እነግርህ ዘንድ በዚህ አጠገቤ ቁም እነሳቸው ርስት አድርጌ በምሰጣቸው ምድር እንደዚሁ ያድርጉ አለኝ ። |
| ወዕቀቡ ከመ ትግበሩ በከመ አዘዝኩክሙ፤ በከመ አዘዘኒ እግዚአብሔር አምላክክሙ ። | ፴ | እናንተም ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር እንዳዘዘኝ ታደርጉ ዘንድ፤ ያዘዝኋችሁን ሁሉ ጠብቁ ። ገላ፡ ፫ ፲፱ ። |

፴፩ ወኢትትገኀሡ ኢለየማን ወኢለፀጋም እምኵሉ ፍኖት ዘአዘዘክሙ እግዚአብሔር አምላክክሙ ከመ ትሑሩ በቲ ከመ ሠናይተ ትኩንክሙ፤ ወከመ ታዕርፉ ወይኑኅ መዋዕሊክሙ ውስተ ምድር እንተ ትትዋረሱ።

በጎ ነገር ይደረግላችሁ ዘንድ ከመከራም ታርፉ ዘንድ በምትወርሷትም ምድር ዕድሜያችሁ እንዲረዝምላችሁ ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር ካዘዛችሁ ሥርዓት ወደ ቀኝም ወደ ግራም አትበሉ። ዘዳ፣ ፲፯ ፳፤ ኢያ፣ ፩ ፯።

## ምዕራፍ ፮።

፩ ወዝንቱ ውእቱ ትእዛዝ ወኵነኔ ወፍትሕ ዘአዘዘ እግዚአብሔር አምላክነ ከመ እምህርክሙ ትግበሩ በውስተ ምድር እንተ ውስቴታ ትበውኡ ትትዋረስዋ።

ትወርሷት ዘንድ በምትገቡባት አገር ልታደርጉት ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር እንዳስተምራችሁ ያዘዘው ትእዛዝ ሥርዓትና ፍርድ ይህ ነው። ዘዳ፣ ፬ ፩።

፪ ከመ ትፍርህዎ ለእግዚአብሔር አምላክክሙ ወከመ ትዕቀቡ ኵሎ ኵነኔሁ ወትእዛዞ ዘአነ እኤዝዘክሙ ዮም፤ አንትሙ ወደቂቅክሙ ወደቂቀ ደቂቅክሙ በኵሉ መዋዕለ ሕይወትክሙ ከመ ይኑኅ መዋዕሊክሙ።

እናንተም ልጆቻችሁና የልጅ ልጆቻችሁ ዘመናችሁ ይበዛ ዘንድ ዛሬ እኔ የማዝዛችሁን ትእዛዝ በለ ዘመናችሁ ሁሉ ትጠብቁ ዘንድ ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔርን ትፈሩት ዘንድ እግዚአብሔር ያዘዘው ትእዛዝ ይህ ነው።

፫ ስምዑ እስራኤል ከመ ትግበሩ ወከመ ትዕቀቡ ከመ ሠናይተ ትኩንክሙ፤ ወከመ ይኑኅ መዋዕሊክሙ ወከመ ትትባዝኁ ጥቀ በከመ ይቤ እግዚአብሔር አምላክሙ ለአበዊክሙ ከመ የሀብክሙ ምድረ እንተ ትውኅዝ ሐሊበ ወመዓረ።

ማርና ወተት የምታስገኘውን ምድር ይሰጣችሁ ዘንድ የአባቶቻችሁ አምላክ እግዚአብሔርም እንደተናገረ እጅግ እንድትበዙ ዕድሜያችሁም እንዲረዝም በጎ ነገርም እንዲደረግላችሁ ትጠብቁና ታደርጉ ዘንድ እስራኤል ሆይ ስሙ። ዘፍ፣ ፲፩ ፫።

፬ ወዝንቱ ውእቱ ትእዛዝ ወኵነኔ ኵሉ ዘአዘዞሙ ሙሴ ለደቂቀ እስራኤል በገዳም ወፂኦሙ እምድረ ግብጽ።

ከግብጽ ምድር ከወጡ በኋላ ሙሴ ለእስራኤል ልጆች በምድረ በዳ ያዘዛቸው ትእዛዝ (ዘጠኙ ሕገጋት "ሰባ,, (ወንበበሙ) ሁሉ ይህ ነው። ኢሳ፣ ፱ ፯።

፭ ስማዕ እስራኤል እግዚአብሔር አምላክከ አሐዱ ውእቱ።

እስራኤል ሆይ ስማ ፈጣሪህ እግዚአብሔር አንድ ነው።

፮ ወአፍቅሮ ለእግዚአብሔር አምላክከ በኵሉ ልብከ፤ ወበኵሉ ነፍስከ፤ ወበኵሉ ሕሊናከ ወበኵሉ ኀይልከ።

ፈጣሪህ እግዚአብሔርን በፍጹም ልቡናህ፤ በፍጹም ሰውነትህ፤ በፍጹም አእምሮህ በፍጹም አሳብህ ውደደው።

፯ ወየሀሉ ውስተ ልብከ ወውስተ ነፍስከ ዝንቱ ኵሉ ነገር ዘአነ እነግረከ ዮም።

እኔ አሁን የምነግርህ ይህ ነገር ሁሉ በልቡናህም በሰውነትህም ይኑር። ዘዳ፣ ፬ ፱፤ ኢሳ፣ ፶፩ ፯።

፰ ወመሀሮ ለውሉድከ ወንግር ኪያሁ እንዘ ትነብር ውስተ ቤት፤ ወእንዘ ተሐውር ውስተ ፍኖት፤ ወለእመ ሰከብከ፤ ወለእመ ተንሣእከ።

ልጆችህንም አስተምረው፤ በቤትህም ተቀምጠህ በጐዳናም ስትሄድ፤ ስትተኛም፤ ስትነሣም ይህን ንገረው።

፱ ወግበሮ ከመ ትእምርት ውስተ እዴከ ወይኩንከ ዘኢይትሐወስ እምቅድመ አዕይንቲከ።

በእጅህ እንደ ምልክት (ቀለበት) አድርገው በዓይኖችህም እንደማይንቀሳቀስ (እንደ መስተዋት) ይሁንልህ።

፲ ወጸሐፎ ውስተ ምርፋቃት ኆኅተ አብያቲከ ወውስተ ደደያቲከ።

በቤቶችህ በር መቃኖችና በደጃፎችህም መድረክ ላይ ጻፈው። ኢያ፣ ፲፩ ፳፤ መዝ፣ ፻፳ ፵፬።

፲፩ ወአመ አብአከ እግዚአብሔር አምላክከ ውስተ ምድር እንተ መሐለ ለአበዊከ ለአብርሃም ወለይስሐቅ ወለያዕቆብ ከመ የሀብከ አህጉረ ዐበይተ ወሠናያተ ዘኢነደቀ።

የጸኑና ያማሩ ያልሠራኻቸውን ታላላቅ ከተሞች ይሰጥህ ዘንድ ፈጣሪህ እግዚአብሔር ላባቶችህ ለአብርሃም ለይስሐቅና ለያዕቆብ ወደ ማለለት አገር በገባህ ጊዜ።

፲፪ ወአብያተ ዘምሉእ እምኵሉ በረከት ዘኢዘገብከ፤ ወዐዘቅተ ዘውቅሮ ዘኢወቀርከ፤ ወአዕፃዳተ ወይን ወአዕፃዳተ ዘይት ዘኢተከልከ።

ያልደለብከውን ድልቡን ሁሉ የተመሉ ቤቶችን ያልቈፈርከው በዓለ የተሠራ የውኃ ጕድጓድንም ያልተከልከው የዘይትና የወይን ቦታዎችንም ይሰጥህ ዘንድ ወደ ማለበት አገር በገባህ ጊዜ።

፲፫ ወእምድኅረ በላዕከ ወጸገብከ፤ ዑቅ እንከ ኢትርስዖ ለእግዚአብሔር አምላክከ ዘአውፅአከ እምድረ ግብጽ እም ቤተ ቅኔት።

በልተህ ከጠገብክ በኋላ ጽኑ አገዛዝ ካለበት ከግብጽ አገር ያወጣህ ፈጣሪህ እግዚአብሔርን እንግዲህ እንዳትረሳው ዕወቅ። ዘፀ፣ ፲፫ ፫።

፲፬ ወፍርሆ ለእግዚአብሔር አምላክከ፤ ወሎቱ ለባሕቲቱ አምልክ፤ ወሎቱ ትልዎ፤ ወበስመ ዚአሁ መሐል።

ፈጣሪህ እግዚአብሔርን ፍራው፤ እሱንም ብቻ አምልከው፤ በአምልኮትም ተከተለው፤ በሱም ስም ማል።

፲፭ ወኢትሖሩ ድኅረ አማልክት ነኪር ኅበ አማልክተ አሕዛብ እለ ዐውድከ፤ እስመ አምላክ ቀናኢ ውእቱ እግዚአብሔር አምላክከ።

ሌላ የሚያመልካቸውን አማልክት አትከተል በዙርያ ያሉ የአሕዛብ ጣአታትንም አታምልክ ፈጣሪህ እግዚአብሔር ለአምላክነቱ ቀናተኛ ነውና። መዝ፣ ፲፰ ፩።

፲፮ ወዐቀ ኢይትመዓዕከ እግዚአብሔር አምላክከ በመዐቱ ፡ ወኢይሠርወከ እምገጸ ምድር ።

ፈጣሪህ እግዚአብሔር ተቈጥቶ ከዚህ ዓለም እንዳያጠፋህ ዕወቅ ። ማቴ፡ ፬ ፯ ፡ ሉቃ፡ ፬ ፲፪ ።

፲፯ ወኢታመክሮ ለእግዚአብሔር አምላክከ በከመ አመከርክሙ አመ ዕለተ መንሱት ።

ጥፋት በታዘዘበት ቀን እንደተፈታተንከው ፈጣሪህ እግዚአብሔርን አትፈታተነው ። ዘጸ፡ ፲፯ ፳፱ ።

፲፰ ተዐቀብ ወዕቀብ ትእዛዞ ለእግዚአብሔር አምላክከ ፡ ወስምዖ ኵሎ ዘአዘዘከ ።

እሱን ከመፈታተን ተጠበቅ ፡ ፈጣሪህ እግዚአብሔር ያዘዘህንም ትእዛዝ ሁሉ ሰምተህ ጠብቅ ።

፲፱ ከመ ትግበር ዘሠናይ ወዘአደም በቅድሜሁ ለእግዚአብሔር አምላክከ ከመ ሠናይት ትኩንከ ወትበእ ወትትዋረስ ምድረ ሡርክቶ ዘመሐለ እግዚአብሔር ለአበዊከ ።

በጎ ነገር እንድትደረግልህ በፈጣሪህ በእግዚአብሔር ፊት ያማረውንና የሚወደደውን ታደርግ ዘንድ እግዚአብሔር ላባቶችህ ወደ ማለላቸው ወደ ክበረች ምድር ገብተህ ትወርስ ዘንድ ። ዘኍ፡ ፴፫ ፶፪ ።

፳ ከመ ይስድድ ለከ ኵሎ ፀረከ እምቅድመ ገጽከ በከመ ይቤ እግዚአብሔር ።

አጠፋልኻለሁ ብሎ እንደተናገረ እግዚአብሔር ጠላቶችህን ከፊትህ ያጠፋልህ ዘንድ ያዘዘህን ፍርዱን ስማ ።

፳፩ ወሶበ ተስእለከ ወልድከ ጌሠመ ወይብለከ ፡ ምንት ውእቱ ዝንቱ ትእዛዝ ወኵነኔ ወፍትሕ ኵሉ ዘአዘዘነ እግዚአብሔር አምላክነ ።

ፈጣሪያችን እግዚአብሔር ያዘዘን ይህ ትእዛዝ ሥርዓትና ፍርድ ምንድርነው ፡ ብሎ ልጅህ ነገ በጠየቀህ ጊዜ ።

፳፪ ትብሎ ለወልድከ አግብርቲሁ ንሕነ ለፈርዖን በብሔረ ግብጽ ወአውፅአነ እግዚአብሔር አምላክነ እምህየ ፡ በእድ ጽንዕት ወበመዝራዕት ልዑል ።

በግብጽ አገር እኛ ለፈርዖን ተገዦዎች ሁነን ሳለ ፈጣሪያችን እግዚአብሔር በዘጠኝ መቅሠፍት በዐሥረኛው ሞተ በኵር ከዚያ ከግብጽ አወጣን በለው ። ዘጸ፡ ፬ ፴፱ ።

፳፫ ወፈነወ እግዚአብሔር ተአምረ ወመድምመ ዐቢየ ፡ ወእኩየ ላዕለ ግብጽ ወላዕለ ፈርዖን ወመገብቱ ወአግብርቲሁ ወላዕለ ቤቱ በቅድሜነ ።

እግዚአብሔር በፈርዖንና በሹማምንቱ በባሮቹና በቤቱ ላይ እኛ እያየን ድንቅ ድንቅ ተአምራቱን አደረገ ።

፳፬ ወኪያነ አውፅአነ እምህየ ከመ ያብአነ ውስተ ዛቲ ምድር ፡ ወየሀበነ ዘመሐለ ከመ የሀበሙ ለአበዊነ ።

እኛን ግን ወደዚች አገር ያገባን ዘንድ ላባቶቻችን ይሰጣቸው ዘንድ የማለላቸውንም ይሰጠን ዘንድ ከዚያ አወጣን ።

፳፭ ወአዘዘነ እግዚአብሔር ዘንተ ኵሎ ኵነኔ ወፍትሐ ከመ ንግበር ወከመ ንፍርሆ ለእግዚአብሔር አምላክነ ከመ ሠናይት ትኩን በኵሉ መዋዕሊነ ላዕሌነ ወከመ ንሕየው በከመ ዮም ።

እንደ ዛሬ በሕይወት እንዳለን በሕይወት እንዲያኖረን ባለ ዘመናችንም በጎ ነገር እንድትሆንልን ፈጣሪያችን እግዚአብሔርንም እንፈራው ዘንድ እናደርገውም ዘንድ ይህን ሁሉ ሥርዓትና ትእዛዝ አዘዘን ትለዋለህ ።

፳፮ ወከመ ንርከብ ምሕረተ ለእመ ዐቀብነ ከመ ንግበር ዘንተ ኵሎ ትእዛዘ በቅድመ እግዚአብሔር አምላክነ በከመ አዘዘነ እግዚአብሔር ።

ሕጉን ብንጠብቅ ይቅርታውን እናገኝ ዘንድ እግዚአብሔር እንዳዘዘን በፈጣሪያችን በእግዚአብሔር ፊት ይህን ሁሉ ትእዛዝ እንፈጽም ዘንድ አዘዘን ። ዘዳ፡ ፳፬ ፲፫ ።

## ምዕራፍ ፯ ።

፩ ወለእመ አብአከ እግዚአብሔር አምላክከ ውስተ ምድር እንተ ባቲ ተሐውር ህየ ከመ ትረሳ ፡ ወአሰሰለ አሕዛበ ዐበይተ ወብዙኃነ እምቅድመ ገጽከ ኬጤዎን ፡ ወጌርጌሴዎን ፡ ወአሞሬዎን ፡ ወከናኔዎን ፡ ወፌርዜዎን ፡ ወኤዌዎን ፡ ወኢያቡሴዎን ሰብዐቱ አሕዛበ ዐበይተ እለ ይጸንዑከ ።

ትወርሳት ዘንድ ወደዚያ ወደ ምትሄድበት አገር ፈጣሪህ እግዚአብሔር በገባህ ጊዜ የሚበረታቱብህ ታላላቅ የሆኑ ሰባቱ አሕዛብን ከፊትህ ባሰወገዳቸው ጊዜ እነዚህም ኬጤዎን ፡ ጌርጌሴዎን ፡ አሞሬዎን ፡ ከናኔዎን ፡ ፌርዜዎን ፡ ኤዌዎን ፡ ኢያቡሴዎን ናቸው ፡ እነዚህን ሁሉ ከፊትህ ባራቃቸው ጊዜ ።

፪ ወአግብኦሙ ውስተ እዴከ ወቀተልኮሙ ወአጥፍኦ አጥፍኦሙ ወኢትትከየድ ምስሌሆሙ ኪዳነ ፡ ወኢትምሐሮሙ ።

ፈጣሪህ እግዚአብሔር እነዚህን በእጅህ በማለልህና በገደልኻቸው (ድል በነሣኻቸው) ጊዜ ማጥፋትን አጥፋቸው ከነሱም ጋር ቃል ኪዳን አትግባ (አትማማል) አትራራላቸው ። ዘሌ፡ ፳፯ ፳፰ ፡ ዘዳ፡ ፯ ፳፫ ።

፫ ወኢትትሐመዎሙ ወለትከ ወኢተሀብ ለወልዶሙ ፡ ወወለቶ ኢትንሣእ ለወልድከ ።

ከነሱም ጋር አትጋቡ (አትጋቧቸው) ሴት ልጅህን ለወንድ ልጁ አታጋባ ፡ ሴት ልጁንም ለወንድ ልጅህ አትውሰድ ። ኢያ፡ ፳፫ ፲፪ ።

፬ እስመ ያስሕቶ ለወልድከ እምኔየ ወያመልክ ባዕዳነ አማልክተ ወይትመዐዕ እግዚአብሔር መዐተ ላዕሌክሙ ወይሤርወክሙ ፍጡነ ።

ልጅህን በአምልኮት ከኔ ያርቀዋልና ፡ ሌሎች አማልክትን እንዲያመልክ ያደርገዋልና እግዚአብሔር በናንተ ላይ ፈጽሞ ይቈጣልና ፡ ፈጥኖም ያጠፋችኋልና ።

፭ እላ ከመዝ ግበርዎሙ ምሥዋዓቲሆሙ ንሥቱ ፡ ወምስላቲሆሙ ቀጥቅጡ ፡ ወአእዋማቲሆሙ ግዝሙ ፡ ወአማልክቲሆሙ ዘግልፎ አውዕዩ በእሳት ።

፮ እስመ ሕዝብ ቅዱስ አንተ ለእግዚአብሔር አምላክከ ወኪያከ ኀብደረ ወኀረየ እግዚአብሔር አምላክከ ከመ ትኩኖ ሕዝበ ሉቱ እምኵሉ አሕዛብ ፡ እለ ሀለዉ ዲበ ገጸ ምድር።

፯ ወአኮ እስመ ትበዝኁ አንትሙ እምኵሉ አሕዛብ ዘአብደረ ኀርዮትክሙ እግዚአብሔር ፡ አንትሙሰ ትውኀዱ እምኵሉ አሕዛብ ።

፰ እላ እስመ ያፈቅረክሙ እግዚአብሔር ወእስመ የዐቅብ መሐላሁ ዘመሐለ ለአበዊክሙ ወበበይነ ዝንቱ አውፅአክሙ በእድ ጽንዕት ወበመዝራዕት ልዕልት ወቤዘወክሙ እምቅኔት ወእምእዴሁ ለፈርዖን ንጉሠ ግብጽ ።

፱ ወተአምር ከመ እግዚአብሔር ውእቱ አምላክከ ፡ ውእቱ እግዚእ ፡ ወውእቱ አምላክ ማእምን ዘየዐቅብ ኪዳኖ ወምሕረቶ ለእለ ያፈቅርዎ ወየዐቅቡ ትእዛዞ እስከ ዐሠርቱ ምእት ትውልድ ።

፲ ወይትቤቀሎሙ ለእለ ይጸልእዎ በቅድመ ገጾሙ ወይሤርዎሙ ወኢያጐነዲ ሠርዎቶሙ ለእለ ይጸልእዎ በቅድመ ገጾሙ ።

፲፩ ወዕቀቡ ትእዛዞ ወኵነኔሁ ወፍትሖ ኵሎ ዘአነ እኤዝዘክሙ ዮም ከመ ትግበርዎ ።

፲፪ ወእምከመ ሰማዕክሙ ዘንተ ኵነኔሁ ወዐቀብክምዎ ወገበርክምዎ ፡ እግዚአብሔርኒ የዐቅብ ለክሙ ኪዳኖ ወምሕረቶ ዘመሐለ ለአበዊክሙ ።

፲፫ ወያፈቅረከ ወይባርከከ ወያስተበዝኀከ ወይባርክ ለከ ፍሬ ከርሥከ ወፍሬ ምድርከ ወሥርናየከ ወወይነከ ወቅብዐከ ወአዕባዳተ ላሕምከ ወመራዕየ አባግዒከ ላዕለ ምድር ዘመሐለ ለአበዊከ ከመ የሀብከ ።

፲፬ ወትከውን ቡሩከ እምኵሉ አሕዛብ ፡ ወአልበ መካን እምአንስትያከ ፡ ወአመት እንተ አልባቲ ውሉድ ፡ ወኢመካን እምእንስሳከ ።

፲፭ ወያሴስል እግዚአብሔር እምኔከ ኵሎ ደዌ ወኵሎ ሕማመ እኩየ ዘርኢከ ዘመጽአ ላዕለ ግብጽ ፡ ወኢያመጽአ ላዕሌከ ለውእቱ ኵሉ ዘርኢከ ወይመይጦ እምኔከ ወይወስዶ ላዕለ ፀርከ ወላዕለ ኵሎሙ እለ ይጸልኡከ ።

፲፮ ወትበልዕ ምኅርከሆሙ ለአሕዛብ ዘይሁበከ እግዚአብሔር አምላክከ ፡ ወኢትምሐከሙ ዐይንከ ፡ ወኢታምልክ አምልክቲሆሙ እስመ እኩይ ውእቱ ለከ ዝንቱ ።

፲፯ ወለእመሰ ትብል በልብከ ይበዝኁ እምኔየ ዝንቱ ሕዝብ ወእፎ እክል አጥፍኦቶ ኢትፍርሆ ።

፲፰ ተዘከር ተዘከር ኵሎ ዘገብረ እግዚአብሔር አምላክከ ላዕለ ፈርዖን ወላዕለ ኵሉ ግብጽ ዐቢየ መንሱተ ዘርእያ አዕይንቲከ ወውእተ ተአምረ ።

ነገር ግን እንዲህ አድርጓቸው ፡ መሠውያዎቻቸውን አፍርሱ ፡ ምስሎቻቸውን ስበሩ ፡ የሚያመልኩዋቸው ዕን ጨቶቻቸውንም ቍረጡ ፡ ተመትተው የተቀረጹ አማልክቶቻቸውንም በእሳት አቃጥሉ ። ዘፀ፡ ፳፫ ፳፬፡ ፴፬ ፲፫ ።

አንተ ለፈጣሪህ ለእግዚአብሔር በዚህ ዓለም ከሉት አሕዛብ ሁሉ ተለይተህ ወገን ትሆነው ዘንድ ፈጣሪህ እግዚአብሔር አንተን ፈጽሞ መርጦሃልና ። ዘፀ፡ ፲፱ ፭ ።

ከአሕዛብ ሁሉ መመረጣችሁን የወደደ እግዚአብሔር እናንተ ትበዛላችሁ ብሎ አይደለም ይልቁንም ከአሕዛብ ሁሉ እናንተ ታንሳላችሁ ። ዘዳ፡ ፲፰ ፱ ።

ላባቶቻችሁ የማለውን መሐላ ስለ ጠበቀ ፡ እግዚአብሔር ይወዳችኋልና ነው እንጂ ፡ ስለዚህ ነገር እግዚአብሔር በዘጠኝ መቅሠፍት ፡ በዐሥረኛው ሞተ በኵር ነፃ አወጣችሁ ፡ ከግብጽ ንጉሥ ከፈርዖን እጅ ከባርነት ቤት ተበዦችሁ (ዋጃችሁ)። ዘዳ፡ ፱ ፴፱ ፡ ፲ ፲፭ ።

እስከ ዓሥር ትውልድ ድረስ ትእዛዙን ለሚጠብቁ ሰዎች ቸርነቱን መሐላውን የሚጠብቅ የታመነ አምላክ ገዢ እሱ መሆኑን ታውቃለህ ። ኢሳ፡ ፵፱ ፯ ።

የሚጠሉትን ሰዎች በፊታቸው ይበቀላቸዋል ያጠፋቸዋልም በሕግ በአምልኮት የሚጠሉትንም ማጥፋታቸውን አይዘገይም ። ዘዳ፡ ፴፪ ፴፭ ፡ ኢሳ፡ ፶፱ ፲፰ ።

ታደርጉት ዘንድ ዛሬ እኔ የማዛችሁን ትእዛዙን ሥርዓቱንና ፍርዱን ሁሉ ጠብቁ ።

ይህን ሥርዓት ሰምታችሁ ብትጠብቁት ግን እግዚአብሔርም ለአባቶቻችሁ የማለውን ቃል ኪዳን ቸርነቱን ይጠብቅላችኋል ። ዘሌ፡ ፳፯ ፱ ፡ ሮሜ ፱ ፲፫ ።

ይወድሃል ፡ ያከብርሃል ፡ ያበዛሃል የወለድከው ልጅህን ይባርክልሃል ፡ የምድርህንም ፍሬ ሥንዴህን ወይንህን ዘይትህን ያበዛልሃል ፡ የላምህን የበጎችህን መንጋ መሠማሪያ ይሰጥህ ዘንድ ለአባቶችህ የማለላቸውን ምድር ያሰፋልሃል ። ዘፍ፡ ፳፱ ፲፯ ፡ ዘዳ፡ ፳፰ ፬ ።

ከአሕዛብ ሁሉ ተለይተህ የተባረክህ (የተመሰገንህ) ትሆናለህ ከሚስቶችህም የማትወልድ የለም ፡ ልጅ የሌላትም ባርያ የለችም ከላምህ ከበሬህም የማይወልድ የለም።

በግብጻውያን ላይ ሲመጣ (ሲደረግ) ያየኸውን ክፉውን ሕማምና ደዌ ሁሉ እግዚአብሔር ከንተ ያርቅልሃል ያየኸውን መከራ ሁሉ ወዳንተ አያመጣውም ፡ ከንተ መልሶ በሚጠሉህ ጠላቶችህ ሁሉ ላይ ይመልሰዋል ።

ፈጣሪህ እግዚአብሔር የሚሰጥህ የአሕዛብን ምርኮ ትበላለህ ፡ ዓይንህም አትራራላቸው ይህ ሁሉ ላንተ ክፉ ነውና ጣኦቶቻቸውንም አታምልክ ። ዘዳ፡ ፯ ፲፮ ፡ ፲፫ ፰ ።

በልብህ ይህ ወገን ከኔ ይልቅ ይበዛል ፡ እንዴት እችላቸዋለሁ ብለህ አትፍራው ። ዘፀ፡ ፲፰ ፱ ፡ ዘኍ፡ ፴፫ ፶፫ ።

ፈጣሪህ እግዚአብሔር በግብጽና በፈርዖን ላይ ያደረገውን ሁሉ አስብ ፡ ዓይኖችህ ያዩት የሚያስደንቀውን ይህን ተአምራት አስብ ። ዘዳ፡ ፩ ፳፱ ፡ ዘኍ፡ ፴፫ ፶፫ ።

፲፱ ወመድምመ በበይት ወበእድ ጽንዕት ወበመዝራዕት ልዑል ዘከመ አውፅአከ እምህየ ከማሁ ይገብሮሙ እግዚአብሔር አምላክከሙ ለኵሎሙ አሕዛብ እለ ትፈርሁ አንትሙ እምቅድመ ገጸሙ ።

፳ ወይፌኑ እግዚአብሔር አምላክከ ቅድሜከ መቅሠፍተ ላዕሌሆሙ እስከ ያጠፍኦሙ ለእለ ተርፉ ወለእለ ተኀብኡ እምኔከ ።

፳፩ ወኢትደንግፅ እምቅድመ ገጸሙ እስመ እግዚአብሔር አምላክከ ሀለወ ምስሌከ ወውእቱ እግዚአብሔር አምላክ ዐቢይ ወጽኑዕ ።

፳፪ ወያጠፍኦሙ ለእሉ አሕዛብ እምቅድመ ገጽከ በበንስቲት ንስቲት ወኢትበል አጠፍኦሙ ፍጡነ ከመ ኢትኩን ምድር ሐቅለ ፡ ወኢይብዝኁ ላዕሌከ አራዊተ ገዳም ።

፳፫ ወያገብኦሙ እግዚአብሔር አምላክከ ውስተ እዴከ ወይደመስሶሙ በዐቢይ ሕርትምና እስከ ያጠፍኦሙ ።

፳፬ ወያገብኦሙ ለነገሥቶሙ ውስተ እዴከ ወይደመስስ ስሞሙ እምውእቱ መካን ወአልቦ ዘይትቃወም ቅድመ ገጽከ እስከ ያጠፍኦሙ እግዚአብሔር ።

፳፭ ወኵሎ ግልፎ አማልክቲሆሙ አውዕዮ በእሳት ፡ ወኢትፍቱ ኢ ወርቀ ፡ ወኢ ብሩረ ፡ ወኢ ብርተ እምኔሆሙ ፡ ወኢትንሣእ ለከ ከመ ኢትጌጊ በሙ እስመ ርኩሳን እሙንቱ በኀበ እግዚአብሔር አምላክከ ።

፳፮ ወኢታብእ ርኩሰ ውስተ ቤትከ ወኢትኩን ርጉመ ከማሁ አርኵሶ ታረኵሶ ፡ ወአስቆርሮ ታስቆርሮ እስመ ርጉም ውእቱ ።

ምዕራፍ ፰ ፡

፩ ወዕቀቡ ከመ ትግበሩ ኵሎ ትእዛዘ ዘአኤዝዘክሙ ዮም ከመ ትሕየዉ ወትትበዝኁ ወትባኡ ትትዋረስዋ ለምድር ዘመሐለ እግዚአብሔር ለአበዊክሙ ።

፪ ወትዘክር ኵሎ ፍኖተ ዘወሰደከ እግዚአብሔር አምላክከ ውስተ ገዳም ከመ ያሕምምከ ወከመ ያመክርከ ወከመ ያእምር ልበከ ለእመ ትዐቅብ ትእዛዞ ወለእመ አልቦ ።

፫ ወአሕመመከ ወአርኀበከ ወአምዝ መና ሲሴየከ ዘኢየአምሩ አበዊከ ከመ ያርኢከ ከመ ኢኮነ በእክል ባሕቲቱ ዘየሐዩ ሰብእ አላ በኵሉ ቃል እንተ ትወፅእ እምአፉሁ ለእግዚአብሔር የሐዩ ሰብእ ።

፬ ወአልባሲከኒ ኢበልየ በላዕሌከ ወእገሪከኒ ኢረስሐ ናሁ አርብዓ ዓም ።

፭ ወአእምር በልብከ እስመ በከመ ይጌሥፅ ብእሲ ወልዶ ከማሁ ይጌሥፀከ እግዚአብሔር አምላክከ ።

፮ ወዕቀብ ኵሎ ትእዛዘ ለእግዚአብሔር አምላክከ ከመ ትሖር በፍኖቱ ወትፍርሆ ።

፯ እስመ እግዚአብሔር አምላክከ ያበውእከ ውስተ ምድር ቡርክት ወብዝኀት ዘአፍላገ ማይ ፡ ወዐዘቃቲሃ ከመ ቈላይ ወይትከዐው ውስተ ገዳም ወውስተ አድባር ።

ክፍ ብለ ሥልጣኑ ፡ በጸናች እጁ ፈጣሪህ እግዚአብሔር ከግብጽ እንዳወጣህ ከፊታቸው የተነሳ አናንተ የምትፈሩዋቸው አሕዛብን ሁሉ ያጠፋላችኋል ። ዘዳ፡ ፪ ፴፱ ።

ከንተ የተሠወሩትን ፡ ከጦር የተረፉትን እስኪያጠፋቸው ድረስ ድርስ ፡ ፈጣሪህ እግዚአብሔር በላያቸው ላይ መቅሠፍትን ይሰድባቸዋል ። ዘፀ፡ ፳፫ ፳፫ ።

ፈጣሪህ እግዚአብሔር በረድኤት ካንተ ጋር አለና ፡ ከፊታቸው የተነሣ አትደንግጥ ፡ እሱ ፈጣሪህ እግዚአብሔር ታላቅና ጽኑ ነውና ። ዘኍ፡ ፲፩ ፳ ፡ ዘዳ፡ ፲ ፲፯ ።

ጥቂት ጥቂት እያለ እሊህን አሕዛብ ያጠፋቸዋል ፡ ነገር ግን ምድሪቱ ምድረ በዳ እንዳትሆን በምድረ በዳ ያሉ አራዊትም በንተ ላይ እንዳይበዙብህ ፈጥኜ አጠፋቸዋለሁ አትበል ። ዘፀ፡ ፳፫ ፳፱ ፡ ዘዳ፡ ፯ ፩ ።

ፈጣሪህ እግዚአብሔር በእጅህ ይጥላቸዋል ፡ እስኪያጠፋቸውም ድረስ ድርስ በታላቅ ኍሰቍልና ያጠፋቸዋል ።

ንጉሦቻቸውን በእጅህ ይጥላቸዋል ፡ ከዚያ ቦታ ስማቸውን ያጠፋል እግዚአብሔርም እስኪያጠፋቸው ድረስ በፊትህ የሚቃወምህ የለም ። ዘዳ፡ ፱ ፲፱ ፡ ኢያ፡ ፲ ፳፱ ።

ዓይን ፡ ጆሮ ፡ እጅ ፡ እግር ፡ የተቀረጸላቸው ጣኦቶቻቸውን በእሳት አቃጥሉ ፡ ከነሱም ወርቁን ፡ ብሩን ፡ ናሱን አትመኝ ፡ እነሱ በፈጣሪህ በእግዚአብሔር ዘንድ ርኩሳን ናቸውና በነሱ እንዳትስት ላንተ አትውሰድ ።

ርኩሱን ጣኦት ወደ ቤት አታግባ እንደሱም የተረገምኽ አትሁን የተረገመ ነውና ማርከስን አርክሰው መጸየፍን ተጸየፈው ። ዘሌ፡ ፳፮ ፳፰ ፡ ዘዳ፡ ፲፫ ፲፯ ።

ምዕራፍ ፰ ።

እግዚአብሔር ላባቶቻችሁ የማለላቸውን ምድር ትወርሱ ዘንድ በሕይወት እንድትኖሩ እንድትበዙም እኔ ዛሬ የማዛችሁን ትእዛዝ ሁሉ ታደርጉ ዘንድ ጠብቁ ።

ሊያሳዝንህና ሊፈትንህ ትእዛዙን ትጠብቅም እንደሆነ አትጠብቅም እንደሆነ ልቡናህን መርምሮ ያውቅ ዘንድ ፈጣሪህ እግዚአብሔር ወደ ምድረ በዳ የወሰደህን ጐዳና ሁሉ አስብ ። ዘፀ፡ ፲፭ ፳፭ ፡ ዘዳ፡ ፩ ፫ ።

መከራ አጸናብህ አስራበህ ሰው የሚድን ከእግዚአብሔር አፍ በምትወጣው ቃል ሁሉ ነው እንጂ ሰው የሚድነው በእኽል ብቻ እንዳይደለ ይገልጥልህ ዘንድ ከዚህ በኋላ አባቶችህ የሚያውቁትን መና መገበህ ።

በላይህ ላይ ያለ ልብስህ አላረጀም ፡ እግርህም አልነቃም (አልጐረበም) እነሆ እንዲህ ሲሆን አርባ ዘመን ነው ።

አባት ልጁን እንዲገሥፅ ፈጣሪህ እግዚአብሔርም ይገሥፅኻልና በልብህ አስተውል ።

በሕጉ ጸንተህ ትኖር ዘንድ የፈጠረህ እግዚአብሔርንም ትፈራው ዘንድ ትእዛዙን ሁሉ ጠብቅ ።

ፈጣሪህ እግዚአብሔር ወደ ተባረከች ፡ ወደ ሰፋች የሚፈሰው ውኃዋም ጕድጓዷም እንደ ወንዝ በደጋውም በቈላውም ወደ ሚፈሰው ወደዚያች አገር ያገባኻል ።

፰ ምድረ ሥርናይ ወሰገም ወዐፀደ ወይን ወበለስ ወሮማን ፡ ምድረ ቅብዕ ወዘይት ወመዓር ።

፱ ምድር እንተ ኢክነት በአስተእክሎ ዘትበልዖ ለእክላ ወአልቦ ዘተኀጥአ ምንተኒ ውስቴታ ፡ ምድር እንተ እበኒሃ ሐጺን ወእምውስተ አድባሪሃ ይኤልድዎ ለብርት ።

፲ ወብላዕ ወጽገብ ወባርክ ለእግዚአብሔር አምላክከ በውስተ ምድር ቡርክት ዘወሀበከ ።

፲፩ ዑቅ ርእሰከ ወኢትርስዖ ለእግዚአብሔር አምላክከ ከመ ትዕቀብ ትእዛዞ ወፍትሖ ወኵነኔሁ ወኵሎ ዘአነ እኤዝዘከ ዮም ።

፲፪ ዮጊ ሶበ በላዕከ ወጸገብከ ወነደቀ አብያተ ሠናያነ ወነበርከ ውስቴቶሙ ፡ ወበዝኃ ለከ አበግዒከ ወአልሕምቲከ ወሶበ በዝኀ ለከ ወርቅ ወብሩር ወበዝኀ ለከ ኵሉ ንዋይከ ዮጊ ታዐቢ ልበከ ።

፲፫ ወትረስዖ ለእግዚአብሔር አምላክከ ዘአውፅአከ እምድረ ግብጽ እምቤተ ቅኔት ።

፲፬ ወወሰደከ ውስተ ገዳም ዐቢይ ወግሩም ዘውስቴቱ አራዊተ ምድር ዘይነስኩ ወዐቃርብት ወጽምእ ዘአልቦ ማይ ለሰትይ ዘአውፅአ ለከ እምውስተ እብነ ኰኵሕ ነቅዐ ማይ ጥዑም ።

፲፭ ወሴሰየከ መና በገዳም ዘኢየአምሩ አበዊከ ከመ ያሕምምከ ወያመክርከ ወያሠኒ ላዕሌከ በደኃሪትከ ።

፲፮ ወኢትበል በልብከ በኃይልየ ወበጽንዐ እዴየ ገበርኩ ዘንተ ኵሎ ኀይለ ዓቢየ ።

፲፯ ወተዘከሮ ለእግዚአብሔር አምላክከ እስመ ውእቱ ይሁበከ ኀይለ ከመ ያቅም ኪዳኖ ዘመሐለ ለአበዊከ በከመ ዮም ።

፲፰ ወለእመ ረሲዐ ረሳዕከሁ ለእግዚአብሔር አምላክከ ወሖርከ ድኅረ ባዕዳን አማልክት ወአምለክሆሙ ወሰገድከ ሎሙ ፡ አሰምዕ ላዕሌከ ዮም ሰማየ ወምድረ ከመ ጠፊአ ትጠፍእ ።

፲፱ በከመ አሕዛብ ኵሎሙ እለ ደምሰሶሙ እግዚአብሔር እምቅድመ ገጽከ ከማሁ ትደመሰስ ለእመ ኢሰማዕከ ቃለ እግዚአብሔር አምላክከ ።

የገብስና የሥንዴ ፡ የበለስና የወይን የሮማንም አገር የዘይት የቅቤና የማርም አገር ወደ ምትሆን አገር ።

እኽሏን በማብቃቃት የምትበላው ወዳልሆነች በውስጧም ምንምን የሚታጣ ወደ ሌለበት ደንጊያዋም ብረት ወደ ሆነ ከተራራዋም ነሐስን ወደ ሚፈነቅሉበት ያገባኻል።

በልተህ ጠግበህ በሰጠህ በተባረከች አገር ፈጣሪህ እግዚአብሔርን አመስግነው ። ዘዳ፡ ፴፫ ፳፩ ።

ለራስህ ዕወቅ ፡ ትእዛዙን ፍርዱን ቀጣቱን እኔ ዛሬ የማዝህን ሁሉ ትጠብቅ ዘንድ ፈጣሪህ እግዚአብሔርን አትዘንጋው ።

ወይም እኮ በልተህ በጠገብክ ጊዜ ያማሩ ቤቶችንም ሠርተህ በውስጣቸው በተቀመጥክ ጊዜ ፡ ላሞችህም በጎችህም በበዙልህ ጊዜ ወርቁም ብሩም በበዛልህ ጊዜ ገንዘብህ ሁሉ በበዛልህ ጊዜ ልብህን ታኰራው ይሆናል ።

ወይም እኮ ከግብጽ ከባርነት ቤት ያወጣህ ፈጣሪህ እግዚአብሔርን ትረሳው ይሆናል ፡፡ መዝ፡ ፻፮ ፳፩ ።

በውስጡ የሚናከሱ አውሬዎች ጊንጦች ወዳሉበት ሊጠጡት ውኃ ወደ ሌለበት የውኃ ጥማት ወደ ጸናበት ታላቅና ግሩም ወደሆነ ወደሚያስፈራ ምድረ በዳ የወሰደህ የጠራ የውኃ ምንጭ ከደንጊያው ላንተ ያወጣልህ ።

ወይም እኮ በመጨረሻ ዘመንህ በጎ ነገር ሊያደርግልህ ሊያሳዝንህ ሊፈትንህ ፡ በምድረ በዳ አባቶችህ ያላወቁትን መና የመገበህ ፈጣሪህ እግዚአብሔርን ትረሳው ይሆናል።

በልቡናህም በኀልበቴ ፡ በእጄም ብርታት ይህን ሁሉ ታላቅ ኃይል አደረግሁ አትበል ። ፩ ቆሮ፡ ፬ ፯ ።

እንደ ዛሬ ለአባቶችህ የማለውን መሐላውን ያጸናልህ ዘንድ እሱ ኃይልን ይሰጥኻልና ፈጣሪህ እግዚአብሔርን አስበው ። ምሳ፡ ፲ ፳፪ ፡ ሆሴ፡ ፪ ፰ ።

ፈጣሪህ እግዚአብሔርን መርሳትን ብትረሳው ፡ ልዩ የሆኑ ጣኦታትን ተከትለህ ብትሄድ ብታመልካቸውና ብትሰግድላቸው ፈጽመህ እንድትጠፋ ሰማይንና ምድርን አዳኝብኻለሁ ። መሳ፡ ፲ ፳፪ ።

የፈጣሪህ የእግዚአብሔርን ቃል ካልሰማህ ከፊትህ እንዳጠፋቸው አሕዛብ ሁሉ ፡ እንደዚሁ ትደመሰሳለህ (ትጠፋለህ) ። ዘዳ፡ ፯ ፲፬ ፡ ፬ ፳፯ ።

## ምዕራፍ ፱ ።

፩ ስማዕ እስራኤል ናሁ ተዐድዎ አንተ ዮም ለዮርዳኖስ ከመ ትሑር ትትዋረሶሙ ለአሕዛብ ዐበይት እለ ይጸንዑከ ወአህጉረ ዐበይተ ዘአረፍተ ቅጽሮን ይበጽሕ እስከ ሰማይ ።

፪ ሕዝብ ዐቢይ ወብዙኅ ወነዋኃት ደቂቀ ኤናቅ እለ ትብሎሙ አንተ ።

፫ ወተአምር ዮም ከመ እግዚአብሔር አምላክከ የሐውር ቅድመ ገጽከ እሳት ዘይዌድእ ውእቱ ፡ ወውእቱ ይሜርዎሙ ወያነትዮሙ እምቅድመ ገጽከ ፡ ወያጠፍኦሙ ወይደመስሶሙ ፍጡነ በከመ ይቤለከ ።

፬ ወኢትበል በልብከ ሶበ አጥፍኦሙ እግዚአብሔር ለውእቶሙ አሕዛብ እምቅድመ ገጽከ በበይነ ጽድቅየ አብአኒ

እስራኤል ሆይ ስማ ! የሚጸኑብህ አሕዛብን ልትወርሳቸው ትሄድ ዘንድ እነሆ አሁን አንተ ዮርዳኖስን ትሻገረዋለህ ፡ የቅጽራቸው ግምብ (ኖራ) እስከ ሰማይ የሚደርስ ታላላቅ አምባዎችንም ታፈርሳለህ ። ዘኍ፡ ፩ ፳፰ ።

ይኸውም ታላቅ ብዙ ወገን አንተ የአርበኞች ልጆች (የኤናቅ ልጆች) የምትላቸው ረጃጅሞች ናቸው ።

አሁንም በፊትህ የሚሄድ ፈጣሪህ እግዚአብሔር እንደሆነ ታውቃለህ ፤ የሚያጠፋም እሳት ነው ፡ እሱም ከፊትህ ያሸሻቸዋል ያጠፋቸዋል ፡ አጠፋቸዋለሁ እንዳለህም ፈጥኖ ያጠፋቸዋል ። ዘፀ፡ ፲፰ ፱ ፡ ዘዳ፡ ፴፩ ፫ ።

እግዚአብሔር እነዚያን አሕዛብ ከፊትህ በጠፋቸው ጊዜ ፡ ያችን የከበረች አገር አወርሳት ዘንድ በልብህ ስለ

እግዚአብሔር እትዋረሳ ለዛቲ ምድር ቡርክት ፣ አኮ በበ
ይነ ጽድቅከ ወአኮ በበይነ ንጽሐ ልብከ ዘትበውእ አንተ
ትትዋረሳ ለምድሮሙ ።
፭ አላ በበይነ ኀጢአቶሙ ለውእቶሙ አሕዛብ ያጠፍ
አሙ እግዚአብሔር እምቅድመ ገጽከ ወከመ ያቅም ኪዳኖ
ዘመሐለ ለአበዊከ ለአብርሃም ወለይስሐቅ ወለያዕቆብ ።
፮ ወተአምር ዮም ከመ አኮ በበይነ ጽድቅከ ዘይሁ
በከሃ ለይእቲ ምድር ቡርክት ፣ እስኩ ሕዝብ ዘያገዝፍ
ክሳዶ አንተ ።
፯ ወተዘከር ወኢትርሳዕ ሚ መጠነ አምዐዕከሁ ለእግዚ
ብሔር አምላክከ በገዳም እምአመ አውዓእከ እምድረ ግብ
ጽ እስከ በጻሕክሙ ውስተ ዝንቱ መካን እንዘ ትከሕድዎ
ለእግዚአብሔር አምላክክሙ ።
፰ ወበኮሬብኒ አምዐዕክምዎ ለእግዚአብሔር ወተምዐ
እግዚአብሔር ላዕሌክሙ ከመ ያጥፍእክሙ ።
፱ አመ ዐረጉ አነ ውስተ ደብር ከመ እንሣእ ክልኤ
ጽላተ ዘእብን ጽላተ ዘኪዳን ዘተከየደ እግዚአብሔር
ምስሌክሙ ።
፲ ወነበርኩ ውስተ ደብር አርብዓ መዓልተ ወአርብዓ
ሌሊተ እክለ ኢበላዕኩ ወማየ ኢሰተይኩ ።
፲፩ ወወሀበኒ እግዚአብሔር ክልኤ ጽላተ ዘእብን ዘተ
ጽሕፉ በአጽባዕቱ ለእግዚአብሔር ወጽሑፍ ውስቴቶን
ኵሉ ቃል ዘነገረነ እግዚአሔር በውስተ ደብር አመ
ተጋባእክሙ ።
፲፪ በአርብዓ መዓልት ወበአርብዓ ሌሊት ወሀበኒ እግዚአ
ብሔር ክልኤ ጽላተ ዘእብን ወጽላተ ዘኪዳን ።

፲፫ ወይቤለኒ እግዚአብሔር ተንሥእ ወሑር ፍጡነ እም
ዝየ እስመ አበሱ ሕዝብከ ዘአውፃእከ እምድረ ግብጽ
ወፍጡነ ክሕዱ እምፍኖት ዘአዘዝክሙ ወገብሩ ሎሙ
ስብከ ።
፲፬ ወይቤለኒ እግዚአብሔር እቤለከ ምዕረ ወክዕበ እንዘ
እብል ርኢክዎ ለዝንቱ ሕዝብ ከመ ሕዝብ ግዙፈ ክሳድ
ውእቱ ።
፲፭ ኅድገኒ እጥፍኦ ወእደምስስ ስሞ እምታሕተ ሰማይ
ወእገብረከ ውስተ ሕዝብ ዐቢይ ወጽኑዕ ወዘይበዝኅ እም
ዝንቱ ፈድፋደ ።
፲፮ ወተመየጥኩ ወወረድኩ እምደብር ወደብሩሂ ይነ
ድድ በእሳት ወእልክቱሂ ክልኤ ጽላት ውስተ ክልኤሆን
እደውየ ።
፲፯ ወሶበ ርኢኩ ከመ አበስክሙ ቅድመ እግዚአብሔር
አምላክክሙ ወገበርክሙ ለክሙ ስብከ ወኅደግሙ ፍኖተ
ዘአዘዘክሙ እግዚአብሔር ፣ ነሣእክዎን ለእልክቱ ክልኤ
ጽላት ወገደፍክዎን እምውስተ ክልኤሆን እደውየ ወቀጥ
ቀጥክዎን በቅድሜክሙ ።
፲፰ ወሰአልኩ ዳግመ ቅድመ እግዚአብሔር በከመ ቀዲ
ሙ አርብዓ መዓልተ ወአርብዓ ሌሊተ ፣ እክለ ኢበላዕኩ
ወማየ ኢሰተይኩ ፣ በእንተ ኵሉ ኀጣውኢክሙ ዘአበ
ስክሙ ወገበርክሙ እኩየ ቅድመ እግዚአብሔር አም

እውነተኛነቴ አገባኝ አትበል ፣ አገራቸውን ትወርሳት ዘን
ድ አንተ የምትገባ ስለ ልቡናህ ንጽሕና ፣ ስለ እውነተኛ
ነትህ አይደለም ። ዘፍ፣ ፲፭ ፲፯ ፣ ዘዳ፣ ፰ ፲፯ ፣ ፲፰ - ፲፱ ።
ሳቦችህ ለአብርሃም ለይስሐቅ ለያዕቆብ የማለውን
ቃል ኪዳን ያጸና ዘንድ እግዚአብሔር እነዚያን አሕዛብ
በኃጢአታቸው ምክንያት ከፊትህ አጠፋቸው እንጂ ።
አንተ ክፋደ ልቡናውን የሚያጸና ወገን ነህና ያችን
የተባረከች አገር ስለ እውነተኛነትህ እንደማይሰጥህ
አሁን ታውቃለህ ። ዘፀ፣ ፴፪ ፱ ፣ ዘዳ፣ ፱ ፲፫ ፣ ፲ ፲፮ ።
ከግብጽ ምድር ከወጣህ ጀምሮ ፈጣሪያችሁ እግዚአ
ብሔርን ክዳችሁት ወደዚህ ቦታ እስክትደርሱ ድረስ በም
ድረ በዳ ፈጣሪህ እግዚአብሔርን ምን ያህል እንዳሳ
ዘንከው አስብ ፣ አትዘንጋ ። ዘፀ፣ ፲፬ ፲፩ ፣ ፲፮ ፪ ።
በኮሬብም እግዚአብሔርን አሳዘናችሁት (አስቈጣች
ሁት) እግዚአብሔርም ያጠፋችሁ ዘንድ በናንተ ላይ ተቈጣ።
እግዚአብሔር ከናንተ ጋር የተማማለበቸውን የቃል
ኪዳን ጽላቶችን ዓሥሩ ቃላት የተጻፈበቸውን የዕንቍ
ጽላቶች እቀበል ዘንድ እኔ ወደ ተራራ በወጣሁ ጊዜ ።
እኽል ሳልበላ ፣ ውኃም ሳልጠጣ አርባ ቀን ፣ አርባ
ሌሊት በተራራው ላይ ተቀመጥኩ ። ዘፀ፣ ፳፬ ፲፰ ።
እግዚአብሔርም ፣ በእግዚአብሔር ጣቶች የተጻፉ
ሁለት የድንጋይ ጽላቶችን ሰጠኝ ፣ በተሰበሰባችሁም ጊዜ
እግዚአብሔር በተራራ ላይ የነገረን ነገር ሁሉ በነሳቸው
ተጽፏል ።
በአርባ ቀንና በአርባ ሌሊት ፣ (እግዚአብሔር ዓሠርቱ
ቃላት የተጻፈበቸው) ሁለቱን የዕንቍ ጽላት የቃል ኪዳ
ኑን ጽላቶች ሰጠኝ ።
ከግብጽ ምድር ያወጣኻቸው ወገኖችህ በድለዋልና ፣
ከዘዝኻቸው ሥርዓት ወጥተው ፈጥነው ከደዋልና ጣኦ
ትም ሠርተዋልና ፣ እግዚአብሔር ከዚህ ቦታ ተነሥተህ
ሂድ አለኝ ። ዘፀ፣ ፴፪ ፰ ፣ መሳ፣ ፪ ፲፯ ።
እግዚአብሔር ይህ ወገን ልቡናው የጸና (አንገተ ደን
ዳና) እንደሆነ አየሁት ብዬ አንድ ጊዜ ሁለት ጊዜ ነገር
ኩህ አለኝ ። ዘፀ፣ ፴፪ ፱ ፣ ዘዳ፣ ፱ ፮ ።
አጠፋው ዘንድ ስሙንም ከሰማይ በታች አጠፋው
ዘንድ ተወኝ ፣ ገናና ጽኑ በሆነ ከዚህም ፈጽሞ በሚበዛ
ወገን መካከል እሾምኻለሁ አለኝ ። መዝ፣ ፻፱ ፲፫ ።
እኔም ተመልሼ ከተራራው ወረድኩ ፣ ተራራውም
በእሳት ተከብቦ ይነድ ነበር ፣ እነዚህም ሁለት ጽላቶች
በሁለቱ እጆቼ ተይዘው ነበር ። ዘፀ፣ ፴፪ ፲፭ ፣ ዘዳ፣ ፬ ፴ ።
በእግዚአብሔር ፊት እንደበደላችሁ ለናንተም ጣኦ
ትን እንደሠራችሁ ፣ እግዚአብሔር ያዘዛችሁንም ሥርዓት
እንደ ተዋችሁ በየሁ ጊዜ ሁለቱን ጽላቶች ይገር ከሁለቱ
እጆቼ ጥዬ በፊታችሁ ሰበርኳቸው ። ዘፀ፣ ፴፪ ፲፱ ።

ስለ በደላችሁበት ኃጢአታችሁ ታሳዝኑት ዘንድ
በፈጣሪያችሁ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ነገር ስላደረ
ጋችሁ እኽል ሳልበላ ውኃም ሳልጠጣ ፣ እንደ ቀደመው
ዳግመኛ በእግዚአብሔር ፊት አርባ ቀን ፣ አርባ ሌሊት

ላክክሙ ከመ ታምዕዕዎ ።
፲፱ ወፈራህኩ በእንተ መዓቱ ዘተምዐ እግዚአብሔር ላዕ ሌክሙ ከመ ያጥፍእክሙ ወሰምዐኒ እግዚአብሔር በው እቱ መዋዕል ።
፳ ወላዕለ አሮንሂ ተምዐ እግዚአብሔር ጥቀ ከመ ይሥ ርዎ ፤ ወጸለይኩ በእንተ አሮንሂ በውእቱ መዋዕል ወበእ ንተ ጌጋይክሙሂ ዘገበርክሙ ላሕመ ።
፳፩ ወነሣእክዎ ወቀጥቀጥክዎ ወሐረጽክዎ እስከ አድቀቅ ክዎ በሕቁ ወኮነ ጥቀ ከመ ጸበል ወወደይክዎ ለውእቱ ሐሪጽ ውስተ ነቅዕ ዘይወርድ እምደብር ።
፳፪ ወበኀበ ውዕየትኒ ወእመ መንሱትኒ ወበኀበ መቃብረ ፍትወትኒ አምዐዕክምዎ ለእግዚአብሔር አምላክክሙ ።
፳፫ ወአመሂ ፈነወክሙ እግዚአብሔር እምቃዴስ በርኔ ወይቤለክሙ ዕርጉ ወተዋረስዋ ለይእቲ ምድር ዘእሁበ ክሙ ፤ ክሕድክሙ ቃለ እግዚአብሔር አምላክክሙ ወኢ አመንክምዎ ወኢሰማዕክሙ ቃሎ ።
፳፬ ወኮንክሙ ከሐድያነ እግዚአብሔር እምይእቲ ዕለት እንተ ተአምረ ለክሙ ።
፳፭ ወሰአልኩ ለክሙ ቅድመ እግዚአብሔር አርብዐ መዓ ልተ ወአርብዓ ሌሊተ በከመ ሰአልኩ ቀዲሙ እስመ ይቤ እግዚአብሔር ከመ ያጥፍእክሙ ።
፳፮ ወጸለይኩ ኀበ እግዚአብሔር ወእቤ እግዚኦ ንጉሠሙ ለአማልክት ኢትሥርዎሙ ለሕዝብከ ወለመክፈልትከ ዘቤ ዘውከ በኀይልከ ዐቢይ ዘአውፃእከ እምግብጽ በዐቢይ ኀይልከ ወበእዴከ ጽንዕት ወበመዝራዕትከ ልዑል ።
፳፯ ተዘከር አብርሃምሃ ወይስሐቅሃ ወያዕቆብሃ አግብርቲከ እለ መሐልከ ሎሙ በርእስከ ወኢትነጽር እከዮሙ ለእሉ ሕዝብ ወአበሳሆሙ ወጌጋዮሙ ።
፳፰ ከመ ኢይበሉ እለ ይነብሩ ውስተ ምድር እለ እምነ ቤሆሙ አውፃእከነ እስመ ስእነ እግዚአብሔር አብእቶሙ ውስተ ምድር እንተ ይቤሎሙ ወእስመ ይጸልኦሙ አው ፅኦሙ ከመ ይቅትሎሙ በገዳም ።
፳፱ ወእሉሰ ሕዝብከ እሙንቱ ወርስትከ እለ አውፃእከ እምግብጽ በዐቢይ ኀይልከ ወበጽኑዕ ወልዑል መዝራ ዕትከ ።

ምዕራፍ ፲ ።

፩ ወይቤለኒ እግዚአብሔር በውእቱ መዋዕል ቅር ለከ ክልኤ ጽላተ ዘእብን ከመ እለ ቀዲሙ ፤ ወዕርግ ኀቤየ ውስተ ደብር ወግበር ታቦተ እምዕፅ ።
፪ ወእጽሕፍ ውስተ ውእቶን ጽላት ኵሎ ቃለ ዘሀለወ ውስተ እልክቱ ጽላት እለ ቀዲሙ ቀጥቀጥከ ወደዮን ው ስተ ታቦት ።
፫ ወገበርኩ ታቦተ እምዕፅ ዘኢይነቅዝ ወወቀርኩ ክልኤ ጽላተ ዘእብን ከመ እለ ቀዲሙ ፤ ወዐረጉ ውስተ ደብር ፤ ወውስተ እዴየ ውእቶን ክልኤሆን ጽላት ።

ለመንኩ ።
እግዚአብሔር ያጠፋችሁ ዘንድ ስለ ተቈጣው ቍጣ፤ ፈራሁ ፤ በዚያም ወራት እግዚአብሔር ልመናዬን ሰማኝ።

ያጠፋው ዘንድ እግዚአብሔር በአሮን ላይ አጥብቆ ተቈጣ ፤ እኔም በዚያ ወራት ስለ አሮን ለመንኩ ፤ ለምንም ስለ ሠራችሁበት ኃጢአታችሁ ጸለይሁ ።
እንምቼም ሰበበርኩት ፈጽሞ አድቅ እስኪደቅ (እስኪ ለዝብ) ድረስ ፈጨሁት አለዘብኩት እንደ ትቢያም ሆነ ፤ ከተራራው በሚወርድ ውኃም ውስጥ ጨመርሁት ።
እሳት በተነሣበት በታ በጥፋትም ጊዜ በምኞት መቃ ብርም ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔርን አሳዘናችሁት ።
እግዚአብሔርም ከቃዴስ በርኔ በላካችሁ ጊዜ ያችን የምሰጣችሁ አገር ወጥታችሁ ውረሷት ባላችሁም ጊዜ ፤ የፈጣሪያችሁ የእግዚአብሔርን ቃል ካዳችሁ ፤ አላመናች ሁትም ቃሉን አልሰማችሁም ። ዘኍ፡ ፲፫ ፳፯፤ ፲፬ ፩ ።
ለናንተ ከታወቀበት (ከተገለጠበት) ቀን ጀምሮ በእግ ዚአብሔር ዐመፀኞች ነበራችሁ ።
አስቀድሞም እንደ ለመንኩ አርባ ቀን አርባ ሌሊት በእግዚአብሔር ፊት ለመንኩ ፤ እግዚአብሔር ያጠፋችሁ ዘንድ አጠፋቸዋለሁ ብሏልና ። ዘዳ፡ ፱ ፲፱ ።
አቤቱ የአማልክት ንጉሣቸው በጌትነትህ በገናናነትህ በታላቅነትህ የተበገሠኻቸውን በታላቅ ኃይልህ በክሃሊነ ትህ በጸናች እጅህ በተዘረጋች ክንድህ ከግብጽ ያወ ጣኻቸው ወገንህን ርስትህን አታጥፋቸው ብዬ ወደ እግዚ አብሔር ለመንኩ ። ዘፀ፡ ፴፪ ፲፩ ።
ሕያው አነ ብለህ የማልክላቸው ባሮችህ አብርሃምን ይስሐቅንና ያዕቆብን አስብ ፤ የነዚህን ወገኖች ክፋታቸ ውን በደላቸውንና ስሕተታቸውን አትመልከት ።
ከነሳቸው ዘንድ ያወጣኸንን በግብጽ የሚኖሩ ሰዎች በምድረ በዳ ያጠፋቸው ዘንድ አወጣቸው አወርሳችኋ ለሁ ብሎ ወደ ተናገራቸው ምድር ማግባት ተስኖታልና ስለ ጠላቸውም በምድረ በዳ ይገድላቸው ዘንድ ከግብጽ ምድር አወጣቸው እንዳይሉህ በደላቸውን አትመልከት።
እሊህስ ቢብዙ ተአምራት በታላቅ ኃይልህ በጽኑ ሥል ጣንህ በተዘረጋም ክንድህ ከግብጽ ያወጣኻቸው ወገኖ ችህ ናቸው ። ፩ ነገ፡ ፰ ፶፫፤ ነህ፡ ፩ ፲ ።

ምዕራፍ ፲ ።

እግዚአብሔር በዚያ ወራት እንዲህ አለኝ ፤ የፊተኞ ችን ጽላቶች አስመስለህ ሁለት የዕንቍ ጽላቶችን ቀረጽ ከኔ ዘንድም ወደ ተራራው ወጥተህ ከማይነቅዝ ዕንጨት ማጥን ሥራ ። ዘፀ፡ ፴፬ ፲ ።
ቀድሞ በሰበርካቸው በነዚያ ጽላቶች ያለውን ቃል ሁሉ በነዚያ ጽላቶች ላይ እጽፋለሁ ፤ በታቦቱም ውስጥ አኑራቸው አለኝ ። ዘፀ፡ ፴፬ ፪ ።
ከማይነቅዝም ዕንጨት ማጥን ሠራሁ ፤ ወደ ተራራ ውም ወጥቼ እንደ ቀደሙቱ ሁለት የዕንቍ ጽላቶች ቀረ ጽኩ ፤ እነዚያም ሁለት ጽላቶች በእጄ ተይዘው ነበር ።

፬ ወጸሐፈ ውስተ ውእቶን ጽላት በከመ ውእቶን ጽላት ዘቀዲሙ ዓሥሩ ቃላተ ዘነገረነ እግዚአብሔር በደብረ ሲና በማእከለ እሳት ።

በደብረ ሲና በእሳት መካከል ሆኖ እግዚአብሔር የነገረንን ዓሥሩን ቃላት በነዚያ ጽላቶች ላይ ቀድሞ እንደ ተጻፉቱ ጻፍኩ። ዘፀ፡ ፴፬ ፳፰፣ ዘዳ፡ ፬ ፲፫ ።

፭ ወወደይክዎን ውስተ ታቦት ለውእቶን ጽላት ዘገበርኩ ወነበሩ ህየ በከመ አዘዘኒ እግዚአብሔር ።

እነዚያ የቀረጽኳቸውንም ጽላቶች በማኅደር (ታቦት) ውስጥ አኖርኳቸው እግዚአብሔርም እንዳዘዘኝ በዚያ ኖሩ።

፮ ወግዕዙ ደቂቀ እስራኤል እምኒ በሮት ዘደቂቀ ኢያቅም ዘሚሰቢ ወበህየ ሞተ አሮን ወተቀብረ፥ ወተሠይመ በህየ አልአዛር ወልዱ ክህነ ህየንቴሁ ።

እስራኤልም የሚሰቢ ወገን የሚሆኑ የአርበኞች ልጆች ከሉቦት ከቤሮት ተጓዙ፤ በዚያም አሮን ሙቶ በዚያ ተቀበረ ልጁ አልአዛርም በዚያ ስለሱ ፈንታ ካህን ሆነ።

፯ ወእምህየ ግዕዙ ውስተ ጉድጎድ፥ ወእምጉድጎድ ውስተ ኤጤቤታ ምድር ዘአንቅዕተ ማይ ።

ከዚያም ወደ ጉድጎድ ተጓዙ፤ ከጉድጎድም የውኃ ምንጭ ወዳለበት አገር ወደ ኤጤቤታ ተጓዙ። ዘኍ፡ ፴፫ ፴፪።

፰ ወበውእቱ መዋዕል ፈለጦሙ እግዚአብሔር ለነገደ ሌዊ ከመ ይፁሩ ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር፥ ወከመ ይቁሙ ቅድመ እግዚአብሔር ወይግበሩ ወይጸልዩ በስመ ዚአሁ እስከ ዛቲ ዕለት ።

እግዚአብሔርም በዚያ ወራት የእግዚአብሔር የሕጉ ማደሪያ ታቦትን ይሸከሙ ዘንድ በእግዚአብሔርም ፊት ይቆሙ ዘንድ ሥራውንም ሊሠሩ ስሙንም ጠርተው ይጸልዩ ዘንድ የሌዊን ወገኖች ለያቸው። ዘሌ፡ ፱ ፳፪።

፱ ወበበይነ ዝንቱ አልቦሙ ለሌዋውያን ክፍል ወርስት ምስለ አኀዊሆሙ እስመ እግዚአብሔር ውእቱ ክፍሎሙ በከመ ይቤሎሙ ።

ስለዚህም ነገር ለሌዋውያን ከወንድሞቻቸው ጋር ዕድል ፈንታ ርስት አልነበራቸውም እንደ ነገራቸው ዕድላቸው ፈንታቸው እግዚአብሔር ነውና። ዘኍ፡ ፲፰ ፳፱።

፲ ወአንሰ ቆምኩ ውስተ ደብር አርብዐ መዓልተ ወአርብዐ ሌሊተ ወሰምዐኒ እግዚአብሔር በውእቱ መዋዕል ወኢ ደገከሙ እግዚአብሔር ወኢያጥፍአክሙ ።

እኔም እንደ ፊተኛው አርባ ቀንና አርባ ሌሊት በተራራው ቆየሁ (ተቀመጥኩ) እግዚአብሔርም በዚያ ወራት ልመናዬን ሰማኝ እግዚአብሔርም ተዋችሁ አላጠፋችሁም ።

፲፩ ወይቤለኒ እግዚአብሔር ሑር ወንግር ቅድሜሆሙ ለእሉ ሕዝብ ይበኡ ወይትዋረስዋ ለምድር ዘመሐልኩ ለአበዊሆሙ ከመ እሁቦሙ ።

እግዚአብሔር እሰጣቸው ዘንድ ለአባቶቻቸው የማልኩላቸውን ምድር ገብተው ይወርሷት ዘንድ ሂደህ በሊህ ወገኖች ፊት ንገር አለኝ። ዘፀ፡ ፴፫ ፩።

፲፪ ወይእዜኒ እስራኤል፣ ምንተ ይፈቅድ እግዚአብሔር እምኀቤከ እንበለ ከመ ትፍርሆ ወትሑር በኵሉ ፍናዊሁ ወከመ ታፍቅሮ ወታምልክ በኵሉ ልብከ ወበኵሉ ነፍስከ ወትዕቀብ ትእዛዞ ወኵነኔሁ ኵሎ ዘአነ እኤዝዘከ ዮም ከመ ሠናየ ይኩንከ ።

አሁንም እስራኤል ሆይ፤ እግዚአብሔር ከንተ ምን ይሻል (ምን ይሻል ይመስልሃል) ትፈራው፥ በሕጉም ሁሉ ጸንተህ ትኖር ዘንድ፥ ትወደውም ዘንድ፥ በፍጹም ልቡናህ፥ በፍጹም ሰውነትህ ታመልከው ዘንድ ነው እንጂ፥ በጎ ነገር ሊደረግልህ እኔ አሁን የማዝዝህን ትእዛዙን ሥርዓቱን ትጠብቅ ዘንድ ነው እንጂ አሁንስ እስራኤል ከንተ ምን ይሻል፤

፲፫ ወናሁ ለእግዚአብሔር አምላክከ ሰማይ ወሰማየ ሰማያት ወምድር ወኵሉ ዘውስቴታ ።

ይህ ሰማይ፥ ከሰማይም በላይ ያለ ሰማይ ምድርም በውስጧም ያለ ሁሉ እነሆ የፈጣሪህ የእግዚአብሔር ገንዘብ ነው። ዘፍ፡ ፲፬ ፲፱፥ ፩ ነገ፡ ፰፯።

፲፬ ወዳእሙ አበዊክሙ አብደረ ያፍቅሮሙ ወኀረየ ዘርአሙ እምድኅሬሆሙ ኪያክሙ እምኵሉ አሕዛብ እስከ ዛቲ ዕለት ።

ቢወዳቸው አባቶቻችሁን ብቻ መረጠ፥ እስከዚች ቀን ድረስ ከአሕዛብ ሁሉ ከነሱቸውም በኋላ እናንተ ልጆቻቸውን መረጠ። ዘዳ፡ ፬ ፴፯ ፯ - ፯።

፲፭ ወግዝሩ እከዮ ለልብክሙ ወኢታግዝፉ ክሳደክሙ እንከ፣ እስመ እግዚአብሔር አምላክክሙ ውእቱ ።

የልባችሁን ሸለፈት ግረዙ (ክፋትን አርቁ) እንግዲህ ወዲህ አንገተ ደንዳና አትሁኑ፥ ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር ነውና።

፲፮ አምላከ አማልክት ወእግዚአ አጋእዝት ውእቱ እግዚአብሔር ዐቢይ ወጽኑዕ ወግሩም ዘኢያደሉ ለገጽ ወኢይነሥእ ሕልያነ ።

የአማልክት (የካህናት) አምላክ የጌቶችም ጌታ ነው፥ እግዚአብሔር ገናና ጽኑ ኃያል የሚያስፈራ (ግሩም) ነው የሰው ፊት አይቶም የማያደላ ነው፥ ማማለጃም የማይቀበል ነው። ፪ ዜና ፲፱ ፯፥ ግብ፡ ሐዋ፡ ፲ ፴፬።

፲፯ ወይገብር ፍትሐ ለግዩር ወለእጓለ ማውታ፥ ወለዕቤር ወያፈቅሮ ለግዩር ወይሁብ ሲሳዮ ወልብሶ ።

እናት አባት ለሞተበት ለስደተኛና ለባልቴት እውነት ይፈርዳል ስደተኛን ይወዳል፥ ልብሱንና ምግቡንም ይሰጣል። ኢሳ፡ ፶፪ ፳፪፥ መዝ፡ ፻፲፮ ፱።

፲፰ ወአፍቅርዎ ለግዩር እስመ አንትሙኒ ግዩራነ ኮንክሙ በምድረ ግብጽ ።

እናንተ በግብጽ አገር ስደተኞች ነበራችሁና ስደተኛውን ውደዱት። ዘፀ፡ ፳፪ ፳፪፥ መዝ፡ ፰ ፰።

፳ ለእግዚአብሔር አምላክከ ፍርሆ ወሎቱ ለባሕቲቱ አምልክ ፡ ወሎቱ ትልም ወበስሙ ዚአሁ መሐል ።

ፈጣሪህ እግዚአብሔርን ፍራው ፡ እሱን ብቻ አምልከው በአምልኮትም እሱን ተከተለው በስሙም ማል ።

፳፩ እስመ ውእቱ ትምክሕትከ ወውእቱ አምላክከ ዘገብረ ለከ ዐቢያተ ወእላንተ ክቡራተ ዘርእያ አዕይንቲከ ።

መመኪያህ ነውና ደጋግ ተአምራት ያደረገልህ ዐይኖችህ ያዩዋቸው እነዚያን የከበሩ ታላላቅ ተአምራት ያደረገልህ ፈጣሪህ ነውና ፡ (በስሙ ማል) ። ዘዳ፡ ፲ር ፴ ፴ ፳ ።

፳፪ በሰብዓ ነፍስ ወረዱ አበዊከ ውስተ ምድረ ግብጽ ወይእዜሰ ገብረከ እግዚአብሔር አምላክከ ከመ ከዋክብተ ሰማይ ብዙኀ ።

አባቶችህ ሰባ ነፍስ ሁነው ወደ ግብጽ ምድር ወረዱ አሁን ግን ፈጣሪህ እግዚአብሔር እንደ ሰማይ ከዋክብቶች አበዛህ ። መዝ፡ ፳፱ ፫ ፡ ፶፯ ፳፩ ፡ ኤር፡ ፲፯ ፲፱ ።

## ምዕራፍ ፲፩ ።

፩ ወአፍቅሮ ለእግዚአብሔር አምላክከ ወዕቀብ ሕጎ ወኵነኔሁ ወትእዛዞ ወፍትሖ በኵሉ መዋዕለ ሕይወትከ ።

ፈጣሪህ እግዚአብሔርን ውደደው ፡ በሕይወት በኖርክበት ዘመን ሁሉ ሕጉን ትእዛዙን ፍርዱን ጠብቅ ።

፪ ወተአምሩ ዮም ከመ አኮ ደቂቅክሙ ዘርእዩ ወአእመሩ ተግሣጾ ለእግዚአብሔር አምላክክሙ ወዕበያቲሁ ወእደ ጽንዐተ ወመዝራዕተ ልዑለ ።

አሁን ተአምራቱን ያዩ ልጆቻችሁ እንዳይደሉ ዕወቁ የፈጣሪያችሁ የእግዚአብሔርን ተግሣፅ ገናናነቱን የጸናች ሥልጣኑን የተዘረጋ ክንዱን ። ዘዳ፡ ፰ ፭ ፡ ፫ ፳፬ ።

፫ ወተአምሪሁ ወመድምሞ ወኵሎ ዘገብረ በማእከለ ግብጽ ፡ ወበፈርዖን ንጉሠ ግብጽ ወበኵሉ ምድሩ ።

በፈርዖንና በግብጻውያን መካከል በሀገሩም ሁሉ ያደረገውን ድንቅ ተአምራቱን ዕወቁ ። ዘዳ፡ ፯ ፳፱ ።

፬ ወኵሎ ዘገብረ በኀይሎሙ ለግብጽ ወበሠረገላቲሆሙ ወበአፍራሲሆሙ ዘከመ ከደኖሙ ማየ ባሕረ ኤርትራ ላዕለ ገጾሙ እንዘ ይዴግኑክሙ እሙንቱ እምድኅሬክሙ ወአጥፍኦሙ እግዚአብሔር አምላክክሙ እስከ ዛቲ ዕለት ።

በግብጽ ሠራዊት በፈረሶቻቸውና በሠረገሎቻቸው እነሱ በኋላችሁ ሲከተሉዋችሁ የኤርትራ ባሕር ውኃ ፊታቸውን እንደ ሸፈናቸው ያደረገውን ሁሉ እስከዚችም ቀን ድረስ ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር እንዳጠፋቸው ዕወቁ።

፭ ወኵሎ ዘገብረ ለክሙ በገዳም እስከ በጻሕክሙ ውስተ ዛቲ መካን ።

ወደዚች ቦታ እስክትደርሱ ድረስ በምድረ በዳ ያደረገላችሁን ሁሉ ። መዝ፡ ፸፯ ፲፯ ።

፮ ወኵሎ ዘገብረ ለክሙ በዳታን ወበአቤሮን ደቂቀ ኤልያብ ወልደ ሮቤል እንተ ፈትሐት ምድር አፉሃ ወውኅጠቶሙ ወለአብያቲሆሙ ፡ ወለደብትሪሆሙ ፡ ወለኵሉ ንዋያቲሆሙ ዘምስሌሆሙ እማእከሎሙ ለደቂቀ እስራኤል ።

በእስራኤል ልጆች መካከል ምድር አፍዋን ከፍታ ቤተ ሰቦቻቸውን ድንኳኖቻቸውን ለነርሱ የነበራቸውንም ገንዘብ ሁሉ በዋጠቻቸው በሮቤል ልጅ በኤልያብ ልጆች በዳታንና በአቤሮን ያደረገውን ያወቁ እንዳይደሉ ዛሬ ታውቃላችሁ ።

፯ እስመ አዕይንቲክሙ ርእያ ኵሎ ግብረ ዐቢያተ ዘገብረ እግዚአብሔር ።

እግዚአብሔር ያደረገላችሁን ታላላቅ ተአምራቶች ሁሉ ዓይኖቻችሁ አይተዋልና ።

፰ ወዕቀቡ ኵሎ ትእዛዞ ዘአነ እኤዝዘክሙ ዮም ከመ ትሕየዉ ወትትባዝኁ ወትባኡ ትትዋረስዋ ለምድር እንተ ላቲ ተዐድዉ ዮርዳኖስ ከመ ትትዋረስዋ በህየ ።

ከመከራው ትድኑ ዘንድ የብዙ ብዙም ትሆኑ ዘንድ በዚያም ትወርሷት ዘንድ ዮርዳኖስን የምትሻገሩላት ምድር ገብታችሁ እንድትወርሷት ዛሬ እኔ የማዝዛችሁን ትእዛዙን ሁሉ ጠብቁ ። ኢያ፡ ፩ ፯ ።

፱ ወከመ ይኑኅ መዋዕሊክሙ በዲበ ምድር ዘመሐለ እግዚአብሔር ለአበዊክሙ ከመ የሀቦሙ ወለዘርኦሙ እምድኅሬሆሙ ምድረ እንተ ታውኅዝ ሐሊበ ወመዓረ ።

ለነሳቸው ይሰጣቸው ዘንድ ከነሳቸውም በኋላ ለልጆቻቸው ይሰጣቸው ዘንድ እግዚአብሔር ላባቶቻቸው በማለላቸው ማርና ወተት (ተድላ ደስታ) በምታስገኝ አገር ዘመናችሁ ይበዛ ዘንድ ትእዛዙን ሁሉ ጠብቁ ።

፲ ወከመዝ ይእቲ ምድር እንተ ትበውእ ህየ ትትዋረሳ ፡ አኮ ከመ ምድረ ግብጽ ይእቲ እንተ እም ኀሃ ወፃእከ ሶበ ይዘርኡ ዘርአ ይሰቅዩ በእገሪሆሙ ከመ ዐፀደ ሐምል ።

ትወርሳት ዘንድ ወደዚያ የምትገባባት ምድር እንደ ዚህ ናት ከሷ እንደ ወጣህባት እንደ ግብጽ ምድር አይደለችም ፡ ዘር በዘሩ ጊዜ እንደ ተክል ቦታ በእግራቸው እየጫጫሩ ያጠጣሉ ። ዘኁ፡ ፲፬ ፲፰ ።

፲፩ ወምድርሰ እንተ ህየ ትበውእ ከመ ትትዋረሳ ምድር ይእቲ እንተ ባቲ አድባር ወአምዳር ወእምዝናመ ሰማይ ትሰቲ ማየ ።

ትወርሳት ዘንድ ወደዚያ የምትገባበት ምድር ግን ተራራዎችና ሜዳዎች ያሉባት አገር ናት ከሰማይ ዝናም የምትጠጣ አገር ናት ። ዘዳ ፰ ፯ ።

፲፪ ምድር እንተ ዘልፈ ይሔውጻ እግዚአብሔር አምላክከ ወአዕይንቲሁ ለእግዚአብሔር አምላክከ ላዕሌሃ እምርእሰ ዓመት እስከ ማኅለቅተ ዓመት ።

ፈጣሪህ እግዚአብሔር ዘወትር (በረድኤት) የሚጐበኛት አገር ናት ፡ የፈጣሪህ እግዚአብሔር ዓይኖችም ከዘመን መብቻ ጀምሮ እስከ ዘመን መጨረሻ ድረስ እሷን ይመለከታሉ ። ፩ ነገ፡ ፱ ፫ ።

፲፫ ወለእመሰ ሰሚዐ ሰማዕከ ኵሎ ትእዛዘ ዘአነ እኤዝዘከ ዮም ከመ ታፍቅሮ ለእግዚአብሔር አምላክከ ወታምልከ በኵሉ ልብከ ወበኵሉ ነፍስከ ፡ ይሁብ ዝናመ በበመዋዕሊሁ ላዕለ ምድርከሙ ዘነግህኒ ወዘሠርክኒ ።

፲፬ ወእስተጋቢአከ እክለከ ወወይነከ ወቅብዐከ ይሁብ ማዕረ ውስተ ገዳምከ ለእንስሳከ ወትበልዕ ወትጸግብ ።

፲፭ ወዑቁ ባሕቱ ኢታስብሑ ልበክሙ ወኢትክሐዱ ወኢትሑሩ ወኢታምልኩ ባዕዳነ አማልክተ ወኢትስግዱ ሎሙ ።

፲፮ ወይትመዓዕ እግዚአብሔር መዐተ ላዕሌክሙ ፡ ወየዐፅዋ ለሰማይ ወኢያመጽእ ዝናመ ወምድርኒ ኢትሁብ ፍሬሃ ወትጠፍኡ ፍጡነ እምድር ቡርክት ዘወሀበክሙ እግዚአብሔር ።

፲፯ ወዕቀብዎ ለዝንቱ ነገር ውስተ ልብክሙ ወውስተ ነፍስክሙ ወረስይዎ ተአምረ ውስተ እዴክሙ ወይኩን ዘኢይትሐወስ እምቅድመ አዕይንቲክሙ ።

፲፰ ወመሀርዎሙ ለደቂቅክሙ ከመ ይትናገሩ ቦቱ ለእመ ነበሩ ውስተ ቤት ፡ ወለእመኒ ሖሩ ውስተ ፍኖት ወሰበኒ ትሰክብ ወሰበኒ ትትነሣእ ።

፲፱ ወጸሐፍዎ ውስተ መርፈቀ ኆኀተ ቤትክሙ ከመ ይብዛኃ መዋዕሊክሙ ፡ ወመዋዕለ ውሉድክሙ ውስተ ምድር ዘመሐለ እግዚአብሔር ለአበዊክሙ ከመ የሀቦሙ በአምጣነ መዋዕለ ሰማይ ውስተ ምድር ።

፳ ወለእመ ሰሚዐ ሰማዕክሙ ኵሎ ትእዛዘ ዘአነ እኤዝዘክሙ ዮም ከመ ትግበሩ ወታፍቅርዎ ለእግዚአብሔር አምላክክሙ ወከመ ትሑሩ በኵሉ ፍናዊሁ ወከመ ትትልውዎ ያወፅኦሙ እግዚአብሔር ለኵሉ አሕዛብ እምቅድመ ገጽክሙ ።

፳፩ ወትትዋረስዎሙ ለአሕዛብ ዐበይት እለ ይጸንዑ ፈድፋደ እምኔክሙ ።

፳፪ ወኵሉ መካን ኀበ ኬደ መከየደ እገሪክሙ ለክሙ ውእቱ እምገዳም ወእምአንጢሊባኖን ወእምፈለግ ዐቢይ ፈለገ ኤፍራጥስ እስከ ባሕር እንተ መንገለ ዐረብ ይከውን ደወልክሙ ።

፳፫ ወአልቦ መኑሂ ዘይትቃወም ቅድመ ገጽክሙ ወይወዲ እግዚአብሔር ፍርሀተክሙ ወርዕደተክሙ ላዕለ ኵሉ ገጸ ምድር እንተ ዐረግሙ ላዕሌሃ በከመ ይቤለክሙ እግዚአብሔር ።

፳፬ ወናሁ አነ ዮም አቀውም ቅድሜክሙ በረከተ ወመርገመ ።

፳፭ በረከትሰ ለእመ ሰማዕክሙ ኵሎ ትእዛዘ ለእግዚአብሔር አምላክክሙ ዘአነ እኤዝዘክሙ ዮም ።

፳፮ ወመርገምሰ ለእመ ኢሰማዕክሙ ኵሎ ትእዛዘ ለእግዚአብሔር አምላክክሙ ዘአነ እኤዝዘክሙ ዮም ወኀደግምዋ ለፍኖት ዘአነ እኤዝዘክሙ ዮም ወሖርክሙ ወአምለክሙ ባዕዳነ አማልክተ ዘኢተአምሩ ።

፳፯ ወሶበ አብአከ እግዚአብሔር አምላክከ ውስተ ምድር እንተ ላቲ ተዐዱ ዮርዳኖስ ከመ ትትዋረሳ በህየ ታገብእ በረከተ ላዕለ ደብረ ገሪዛን ወመርገመ ላዕለ ደብረ ጌባል ።

ፈጣሪህ እግዚአብሔርን ትወደው ዘንድ በፍጹም ልቡናህ በፍጹም ሰውነትህም ታመልከው ዘንድ እኔ አሁን የማዝህን ትእዛዝ ሁሉ ፈጽመህ ብትሰማ የማታውንና የጧቱን ዝናም በሀገራችሁ በየወራቱ ይሰጣል ።

እኽልህን ወይንህን ዘይትህን ከሰበሰብክ በኋላ ለከብቶችህ በምድረ በዳ ሣርን ይሰጣል በልተህም ትጠግባለህ።

ነገር ግን ልባችሁን እንዳታጽኑ እንዳትክዱ ሂዳችሁም ልዩ የሆኑ ጣኦታትን እንዳታመልኩ ለነሱቸውም እንዳትሰግዱ ዕወቁ ፡ (ተጠንቀቁ) ። ዘዳ፡ ፲፱ ፲፯ ፡ ኢዮ፡ ፴፩ ፳፯ ።

እግዚአብሔርም በናንተ ተቈጥቶ ሰማይን ይዘጋታል ፡ ዝናምንም አያዘንምም ምድርም ፍሬዋን አትሰጥም ፡ እግዚአብሔር ከሰጣችሁ ከተባረከችም ምድር ፈጥናችሁ ትጠፋላችሁ ።

ይህን ነገር በልቡናችሁና በሰውነታችሁ አስተውሉት (ጠብቁት) በጣታችሁም ምልክት (እንደቀለበት) አድርጉት በፊታችሁም እንደ መስተዋት የማይንቀሳቀስ ይሁን ።

በቤትም ቢቀመጡ ፡ መንገድንም ቢሄዱ ፡ እንዲነጋገሩበት ለልጆቻችሁ አስተምሩዋቸው በተኛህም ጊዜ በተነሣህም ጊዜ አስተምሯቸው ። ዘዳ፡ ፬ ፱ ።

በምድር ላይ በሰማይ ዘመን መጠን ይሰጣቸው ዘንድ ለአበቶቻችሁ በማለላቸው ምድር ላይ ዘመናችሁና የልጆቻችሁ ዘመን ይበዛ (ይረዝም) ዘንድ ።

ፈቃዱን ታደርጉ ዘንድ ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔርን ትወዱት ዘንድ በሕጉም ሁሉ ጸንታችሁ ትኖሩ ዘንድ በአምልኮትም ትከተሉት ዘንድ እኔ አሁን የማዛችሁ ትእዛዙን ሁሉ ብትሰሙ ፡ እግዚአብሔር እነዚህን አሕዛብ ከፊታችሁ ያወጣቸዋል ። ዘዳ፡ ፮ ፲፯ ፡ ፲ ፳ ።

ከናንተ እጅግ የሚበረቱ አሕዛብን ሁሉ ትወርሷቸው አላችሁ ። ዘዳ፡ ፬ ፴፰ ።

ከምድረ በዳ ከአንጢሊባኖን ጀምሮ የእግራችሁ ኮቴ የረገጠው ቦታ ሁሉ ለናንተ ይሆናል ፡ ከታላቁ ወንዝ ከኤፍራጥስ ጀምሮ በስተምዕራብ እስካለው ባሕር ድረስ ድንብራችሁ ይሆናል ። ዘፍ፡ ፲፭ ፲፰ ፡ ዘፀ፡ ፳፫ ፴፩ ።

በፊታችሁም ማንም ማን የሚቃወም የለም ፡ እግዚአብሔር እንዳላችሁ ማንቀጥቀጣችሁን መፈራታችሁን ወደ ቧ ወደ ወጣችሁበት አገር ይመልሰዋል ። ዘፀ፡ ፳፫ ፳፯ ።

እነሆ እኔ አሁን ርግማንንና ምርቃትን በፊታችሁ አጸናለሁ ። ዘዳ፡ ፴፩ ፲፱ ።

ምርቃቱ እኔ አሁን የማዛችሁ የፈጣሪያችሁ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ሁሉ ብትሰሙ ነው ። ዘዳ፡ ፳፰ ፱ - ፴ ።

ርግማኑም አሁን እኔ የማዛችሁ የፈጣሪያችሁ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ሁሉ ባትሰሙ ፡ እኔ አሁን የማዛችሁ ሥርዓቱንም ብትተዉ ሂዳችሁም የማታውቋቸው ልዩ ልዩ አማልክትን ብታመልኩ ነው ። ዘዳ፡ ፳፰ ፲፭ ፡ ፮ ፲፬ ።

ፈጣሪህ እግዚአብሔር በዚያ ትወርሳት ዘንድ ዮርዳኖስን ወደ ምትሻገርላት አገር በገባህ ጊዜ ገሪዛን በሚባል ተራራ ምርቃትን ትመርቃለህ ፡ ጌባል በሚባል ተራራም

፴ ዘሀለዉ በማዕዶተ ዮርዳኖስ ድኅረ ፍኖተ ዘመንገለ
ዐረበ ፀሐይ በምድረ ከነአን እለ ሀለዉ ውስተ ዐረበ
መአኃዝ ጎልጎል ቅሩበ ዕፀት ነዋኅ ።
፴፩ ወናሁ ተዐድውዎ ለዮርዳኖስ አንትሙ ከመ ትበኡ
ትረስዋ ለምድር ዘይሁበክሙ እግዚአብሔር አምላክክሙ
መክፈልተክሙ በኵሉ መዋዕል ዘትነብሩ ውስቴታ ።

፴፪ ወዕቀቡ ከመ ትግበሩ ኵሎ ትእዛዘ ወፍትሐ ዘአነ እሁ
በክሙ ቅድሜክሙ ዮም ።

ምዕራፍ ፲፪ ።

፩ ወዝንቱ ውእቱ ትእዛዝ ወፍትሕ ዘተዐቅቡ ከመ ትግ
በሩ በምድር ዘይሁበክሙ እግዚአብር አምላክክሙ መክፈ
ልተክሙ በኵሉ መዋዕል ዘተሐይዉ አንትሙ ላዕለ
ምድር ።
፪ ወደምስሶ ደምስስዎ ለኵሉ መካን ዘውስቴቱ አምለኩ
አማልክቲሆሙ አሕዛብ ዘአንትሙ ትወርስዎሙ በዲበ አድ
ባር ነዋኃት ወአውግር ወበታሕተ አእዋም ዘዐቀ ቈጽል ።

፫ ወንሥቱ ምሥዋዓቲሆሙ ፡ ወቀጥቅጡ ምስላቲሆሙ
ወግዝሙ አእዋማቲሆሙ ፡ ወአውዕዩ በእሳት ግልፎ አማ
ልክቲሆሙ ፡ ወደምስሱ አስማቲሆሙ እምውእቱ መካን ።
፬ ወኢትግበሩ ከመዝ ለእግዚአብሔር አምላክክሙ በሕ
ሐቲ እምአህጉሪክሙ ዘአንበለ ውስተ መካን ዘኀረየ እግ
ዚአብሔር ከመ ይሰመይ ስሙ በህየ ።
፭ ወትወስዱ መሥዋዕተክሙ ወቍርባነክሙ ወቀዳሚያ
ቲክሙ ወብፅዓቲክሙ ወዘበፈቃድክሙ ወዘዐሥራቲክሙ
ወበኵረ አልሕምቲክሙ ወዘአባግዒክሙ ።

፮ ወብልዑ በህየ በቅድመ እግዚአብሔር አምላክክሙ
ወተፈሥሑ በኵሉ ዘውስቴቱ ወደይክሙ እዴክሙ አን
ትሙ ፡ ወቤትክሙኒ እስመ ባረከክሙ እግዚአብሔር አም
ላክክሙ ።
፯ ወኢትግበሩ ኵሎ ዘንሕነ ንገብር ዮም በዝየ አሐዱ
አሐዱ እምኔክሙ ዘአደሞ በቅድሜሁ ።
፰ እስመ ኢበጻሕክሙ እስከ ይእዜ ውስተ ምዕራፍክሙ
ወውስተ ርስትክሙ ዘይሁበክሙ እግዚአብሔር አምላ
ክክሙ ።
፱ ወዕድዉ ዮርዳኖስ ወንበሩ ውስተ ምድር ዘያወርሰ
ክሙ እግዚአብሔር አምላክክሙ ወያዐርፈክሙ እምኵሉ
ፀርክሙ እለ ዐደውክሙ ወትነብሩ ተአሚነክሙ ።

፲ ወይኩን ዝክቱ መካን ዘኀረየ እግዚአብሔር አምላክ
ክሙ ከመ ይሰመይ ስሙ በህየ ወትወስዱ ኵሎ ዘአነ እኤ
ዝዘክሙ ዮም መሥዋዕተክሙ ወቍርባነክሙ ወዐሥራተ
ክሙ ወቀዳምያተ እደዊክሙ ወሀብተክሙ ኅሩየ ወኵሎ
መባእክሙ ወኵሎ ዘበፃዕክሙ ለአምላክክሙ ።

ርግማንን ትረግማለህ ። ዘዳ፡ ፳፯ ፲፪ - ፲፫ ።
፴ እነዚህም ለረጅም ዘፍ አቅራቢያ በሆነ ሜዳ መያያዣ
በሆነ በፀሐይ መግቢያ በከነዓን ምድር ከመንገዱ አንጻር
በዮርዳኖስ ማዶ ያሉ ናቸው ። ዘፍ፡ ፲፫ ፲፰፡ ፲፪ ፮።
፴፩ በዚ በምትኖሩበት ዘመን ሁሉ ፈጣሪያችሁ እግዚአ
ብሔር ዕድል ፈንታ አድርጎ የሚሰጣችሁ ምድርን ልትወ
ርሷት ትገቡ ዘንድ እነሆ እናንተ ዮርዳኖስን ትሻገሩት
አላችሁ ። ዘዳ፡ ፱ ፩ ።
፴፪ እነሆ አሁን እኔ በፊታችሁ የማስተምራችሁ ትእዛ
ዙንና ፍርዱን ታደርጉ ዘንድ ጠብቁ ።

ምዕራፍ ፲፪ ።

፩ በአገር በምትኖሩበት ዘመን ሁሉ ፈጣሪያችሁ እግዚ
አብሔር ርስት አድርጎ በሚሰጣችሁ አገር ታደርጉት ዘን
ድ የምትጠብቁት ትእዛዝና ፍርድ ይህ ነው ።

፪ እናንተ የምትወርሱዋቸው አሕዛብ በከረብቶችና ረጃ
ጅም በሆኑ ተራሮች ላይ ቅጠል ባላቸው ዛፎችም ሥር
ጣኦቶቻቸውን ያመለኩበትን በታ ሁሉ ፈጽማችሁ
አጥፉት ። ፩ ነገ፡ ፲፬ ፳፫፡ ፪ ነገ፡ ፲፯ ፬ ።
፫ መሠውያዎቻቸውን አፍርሱ ምስሎቻቸውንም ስበሩ
የማምለኪያ ዛፎቻቸውንም ቍረጡ ፡ ጣኦቶቻቸውን በእ
ሳት አቃጥሉ ፡ ስማቸውንም ከዚያ በታ አጥፉ ።
፬ በዚያ ስሙ ይጠራ ዘንድ እግዚአብሔር በመረጠው
በታ ነው እንጂ ከአገሮቻችሁ በአንዲቱ አገር ለፈጣሪያ
ያችሁ እግዚአብሔር እንደዚህ አታድርጉ ።
፭ ቍርባናችሁንና መሥዋዕታችሁን ስለታችሁንና ያዝ
መራችሁን መጀመሪያ ዓሥራታችሁንና በፈቃዳችሁ የም
ታደርጉትን ከላሞቻችሁና ከበጎቻችሁ መጀመሪያ የተወ
ለደውን ውሰዱ ። ዘዳ፡ ፲፭ ፲፬፡ ፲፰ ፮ ።
፮ (ወስዳችሁ) በፈጣሪያችሁ በእግዚአብሔር ፊት በዚያ
ብሉት ፡ ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር ባርኳችኋልና እናን
ተና ወገናችሁ እጃችሁን ባገባችሁበት ሁሉ ደስ ይበላችሁ።

፯ አንዱም አንዱም በፊቱ መልካም መስሎ የታየውን
ዛሬ እኛ የምናደርገውን ሁሉ አታድርጉ ።
፰ ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር ወደሚሰጣችሁ ርስታች
ሁና ወደ ማረፊያችሁ ገና አልደረሳችሁምና ።

፱ ዮርዳኖስን ተሻግራችሁ ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር
በሚያወርሳችሁ አገር ኑሩ ፡ በዙርያችሁ ካሉ ጠላቶቻችሁ
ሁሉ ያሳርፋችኋል ፡ ከመከራውም ተዘልላችሁ ትኖራ
ላችሁ ። ዘዳ፡ ፲፩ ፴፩ ። መሳ፡ ፲፯ ፮ ።
፲ ስሙ በዚያ ይጠራበት ዘንድ ፈጣሪያችሁ እግዚአብ
ሔር የመረጠውን ያ በታ የከበረ ይሁን ፡ እኔ አሁን የማዘ
ችሁን ሁሉ መሥዋዕታችሁን ቍርባናችሁን የእዝመራ
ችሁ መጀመሪያና ዓሥራታችሁን የተመረጠ መባችሁን
ሁሉ ወዳችሁ የምትሰጡትን ገንዘባችሁን ለፈጣሪያችሁ
የተሳላችሁትን ሁሉ ወደዚያ ውሰዱ ። ዘዳ፡ ፲፪ ፭ ።

፲፪ ወተፈሥሑ ቅድመ እግዚአብሔር አምላክክሙ አንትሙ ወደቂቅክሙ ወአዋልዲክሙ ወአግብርቲክሙ ወአእማቲክሙ ወሌዋውያን እለ ውስተ አንቀጽክሙ እስመ አልቦሙ ክፍል ወርስት ምስሌክሙ ።

እናንተ በፈጣሪያችሁ በእግዚአብሔር ፊት ደስ ይበላችሁ ሴቶች ልጆቻችሁና ወንዶች ልጆቻችሁ ሴቶች ባሮቻችሁና ወንዶች ባሮቻችሁ ከናንተ ጋር ርስት ዕድል ፈንታ የላቸውምና በሀገሮቻችሁ ያሉ ሌዋውያንም ደስ ይበላቸው ። ዘዳ፣ ፲ ፱ ፣ ፲፬ ፳፱ ።

፲፫ ወዑቅ ርእሰከ ወኢትግበር መሥዋዕተከ በኵሉ መካን በኀበ ዘርኢከ ዘእንበለ በውስተ መካን ዘኀረየ እግዚአብሔር አምላክከ በውስተ አሐዱ መካን እምሕዝብከ ህየ ትገብር ኵሉ መሥዋዕተከ ወኵሉ ዘአነ እኤዝዘከ ዮም ።

ፈጣሪህ እግዚአብሔር በመረጠው ቦታ እንጂ በያኸው ቦታ ሁሉ መሥዋዕት እንዳትሠዋ ለራስህ ዕወቅ ፣ ከወገኖችህ ቦታ በአንዱ ቦታ መሥዋዕትህን ሠዋ ፣ እኔ አሁን የማዝህንም ሁሉ አድርግ ። ፩ ነገ፣ ፲፪ ፳፯ - ፳፰ ።

፲፭ ወባሕቱ በኵሉ መካን ዘወፀከ ትጠብሕ በህየ ወትበልዕ ሥጋ በከመ በረከቱ ለእግዚአብሔር እግዚእ ዘወሀበከ በኵሉ አህጉር ዘርኩሳኒ ወዘንጹሓኒ ኅቡረ ብልዕዎ ከመ ወይጠል አው ከመ ኀየል ።

ነገር ግን በሰጠህ ቦታ ሁሉ በዚያ ሥጋን አርደህ ብላ ፣ ገዢ የሚሆን እግዚአብሔር በሰጠህ አገር ሁሉ እንደ ሰጠህ በረከት መጠን ንጹሕ የሆነ ንጹሕም ያልሆነ ሰው እንደ ሚዳቋ (ፈቆ) እንደ ዋልያ አንድነት ብሉት ።

፲፮ ወባሕቱ ደሞ ኢትብልዑ ውስተ ምድር ክዐውዎ ከመ ማይ ።

ነገር ግን እንደ ውኃ ከምድር አፍስሱት እንጂ ደሙን አትብሉት ። ዘሌዋ፣ ፫ ፲፯ ።

፲፯ ወኢትክል በሊዖቶ በኵሉ አህጉሪከ ወዐሥራተ ወይንከ ወእክልከ ወቅብዕከ ወበኵረ አልሕምቲከ ወዘአባግዒከ ወኵሉ ብፅዓቲከ ዘበፃዕከ ወዘበፈቃድከ ወቀዳምያተ እደዊከ ።

የእኽልህን የወይንህንና የዘይትህን ዓሥራት ከበጎችህና ከላሞችህ መጀመሪያ የተወለደውን በፈቃድህ የምታደርገውንና የተሳልከውን ስለትህን ሁሉ በእጅህ ያለ ያዝ መራህንም መጀመሪያ በአገርህ ሁሉ መብላት አትችልም ።

፲፰ በቅድመ እግዚአብሔር አምላክከ ብላዕ በውስተ መካን ዘኀረየ እግዚአብሔር አምላክከ አንተ ወደቂቅከ ወወለትከ ወገብርከ ወአመትከ ወግዩር ዘውስተ ሀገርከ ወትትፌሣሕ በቅድመ እግዚአብሔር አምላክከ በኵሉ ዘወደይከ ውስቴቱ እዴከ ።

ፈጣሪህ እግዚአብሔር በመረጠው በዚያ ቦታ በፈጣሪህ በእግዚአብሔር ፊት አንተ ብላ ፣ ሴት ልጅህና ወንድ ልጅህ ፣ ሴት ባርያህና ወንድ ባርያህ ፣ በአገርህ ያለ ስደተኛም ይብሉት ፣ እጅህን ባኖርክበት ገንዘብ ሁሉ በፈጣሪህ በእግዚአብሔር ፊት ደስ ይበልህ ። ዘዳ፣ ፲፩ ፲፪ ።

፲፱ ወዑቅ ርእሰከ ኢትኅድጎ ለሌዋዊ በኵሉ መዋዕል ዘሕያው አንተ ላዕለ ምድር ።

አንተ በአገር በሕይወት በኖርክበት ዘመን ሁሉ ከህኑን እንዳትተወው ለራስህ ዕወቅ ። ዘዳ፣ ፲፬ ፳፯ ።

፳ ወለእመኒ አርኀበ ለከ እግዚአብሔር ደወለከ በከመ ይቤለከ ወትቤ እበልዕ ሥጋ እምኵሉ ዘፈተወት ነፍስከ ብላዕ ።

አስፋፋሃለሁ እንዳለህ እግዚአብሔር አውራጃህን ከሰፋልህ ሥጋ እበላለሁ ብትል ሰውነትህ የወደደችውን ብላ።

፳፩ ወለእመሰ ርኁቅ ውእቱ መካን ኀበ ኀረየ እግዚአብሔር አምላክከ ከመ ይሰመይ ስሙ በህየ ትጠብሕ እምኵሉ እልሕምቲከ ወአባግዒከ እምዘወሀበከ እግዚአብሔር አምላክከ በከመ አዘዝኩከ ወብላዕ በሀገርከ ዘፈተወት ነፍስከ ።

ነገር ግን በዚያ ስሙ ይጠራበት (ይመሰገንበት) ዘንድ የመረጠው ቦታ የራቀ ቢሆን ፈጣሪህ እግዚአብሔር ከሰጠህ ከላሞችህና ከበጎችህ መንጋ አርደህ እንዳዘዝኩህ በአገርህ ሰውነትህ የወደደችውን ብላ ።

፳፪ በከመ ትበልዑ ወይጠለ አው ኀየለ ከማሁ ብልዑ ዘርኩስኒ ወዘንጹሕኒ ።

ፈቆን ወይም ዋልያን እንድትበሉ እንደዚሁ ንጹሕ ያልሆነ ሰውና ንጹሕ የሆነውም ሰው (ሳትከለክሉ) ብሉት ።

፳፫ ወተዐቀብ ጥቀ ከመ ኢትብላዕ ደመ እስመ ደሙ ነፍሱ ውእቱ ወኢትብልዑ ነፍሰ ምስለ ሥጋ አላ ውስተ ምድር ክዐውዎ ከመ ማይ ።

ደሙ ነፍሱ ነውና ብርንዶ እንዳትበላ ፈጽመህ ተጠንቀቅ እንደ ውኃ በምድር ላይ አፍሱት እንጂ ነፍስን ከሥጋ ጋር አትብሉ ። ዘፍ፣ ፱ ፬ ፣ ዘዳ፣ ፲፪ ፲፮ ።

፳፭ ወኢትብልዖ ከመ ሠናየ ይኩንከ ወለውሉድከኒ እምድኅሬከ ፣ ለእመ ገበርከ ዘሠናይ ወዘአዳም ቅድመ እግዚአብሔር አምላክከ ።

በፈጣሪህ በእግዚአብሔር ፊት ያማረውንና የተወደደውን ብታደርግ በጎ ነገር ሊደረግልህ ከንተም በኋላ ለልጆችህ በጎ ነገር ሊደረግላቸው አትብላው ። ዘዳ፣ ፬ ፵ ።

፳፮ ወባሕቱ ዘረሰይከ ቅዱሰ ወዘበፃዕከ ንሣእ ወሑር ውስተ መካን ኀበ ኀረየ እግዚአብሔር አምላክከ ከመ ይሰመይ ስሙ በህየ ።

ነገር ግን የተሳልከውንና የለየኸውን ይዘህ በዚያ ስሙ ይጠራበት ዘንድ ፈጣሪህ እግዚአብሔር ወደ መረጠው ቦታ ሂድ ። ዘኍ፣ ፲፰ ፲፱ ፣ ፩ ሳሙ፣ ፩ ፲፬ ።

፳፯ ወትገብር ሥጋሁ መሥዋዕተ ወትወዲ ላዕለ ምሥዋዕ ወደሞሰ ትክዑ ኀበ መንበረ ምሥዋዕ ዘእግዚአብሔር አምላክከ ወብላዕ እምነ ሥጋሁ ።

ሥጋውንም መሥዋዕት አድርገህ በመሠውያው ላይ አኑር ፣ ደሙን ግን በፈጣሪህ በእግዚአብሔር መሠውያ መቀመጫ ላይ አፍሰው ሥጋውንም ብላ ። ዘሌ፣ ፲፯ ፲፩ ።

፳፰ ወዕቀብ ወስማዕ ኵሎ ቃለ ዘአነ እኤዝዘከ ዮም ከመ

በፈጣሪህ በእግዚአብሔር ፊት መልካምና ቀና ነገር

ሠናየ ይኩንከ ወላውሉድከ ለዓለም ፡ ለእመ ገበርከ ዘሠ
ናይ ወዘአዳም ቅድመ እግዚአብሔር አምላክከ ።

፳፱ ወለእመሂ አጥፍኦሙ እግዚአብሔር አምላክከ ለአሕ
ዛብ ዘአንተ ትበውእ ህየ ከመ ትትዋረሶሙ እምቅድመ
ገጽከ ወትነብር ውስተ ምድሮሙ ዑቅ ርእሰከ ።
፴ ወኢትፍቅድ ተሊዎቶሙ እምድኅረ ተሠረዉ እምቅ
ድመ ገጽከ ወኢትፍቅድ አማልክቲሆሙ ወኢትበል ከመ
ዘይገብሩ አሕዛብ ለአማልክቲሆሙ እገብር አነኒ ።

፴፩ ወኢትግበር ከማሁ ለእግዚአብሔር አምላክከ እስመ
ኵሎ እግዚአብሔር ርኩሰ ዘይገብሩ አሕዛብ ለአማልክቲ
ሆሙ እስመ ደቂቆሙ ወአዋልዲሆሙ ያውዕዩ በእሳት
ለአማልክቲሆሙ ።
፴፪ ወኵሎ ቃለ ዘአነ እኤዝዘከ ዮም ከያሁ ዕቀብ ለገቢር
ወኢትወስክ ላዕሌሁ ወኢታንኪ እምኔሁ ።

ምዕራፍ ፲፫ ።

፩ ወለእመኒ ተንሥአ እምኔከ ነቢይ አው ሐላሚ ሕልም
ወወሀበከ ተአምረ አው መድምመ ወበጽሐ ተአምሪሁ
አው መድምሙ ዘይቤለከ እንዘ ይብል ነዐ ንሑር ወናም
ልክ አማልክተ ባዕደ ዘኢተአምሩ ኢትስምዖ ቃሎ ለው
እቱ ነቢይ አው ለውእቱ ሐላሚ ሕልም ።
፪ እስመ ያሜክረክሙ እግዚአብሔር አምላክክሙ ከመ
ይርአይ ለእመ ታፈቅርዎ እምኵሉ ልብክሙ ወእምኵሉ
ነፍስክሙ ።
፫ ወትልውዎ ለእግዚአብሔር አምላክክሙ ወኪያሁ
ፍርሁ ወትእዛዞ ዕቀቡ ወቃሎ ስምዑ ወኀቤሁ ተማኅፀኑ ።

፬ ወዝኩቱሰ ነቢይ አው ሐላሚ ሕልም ለይሙት እስመ
ነገረከ በዘያስሕተከ እምእግዚአብሔር አምላክከ ዘአውፅ
አከ እምድረ ግብጽ ወቤዘወከ እምቅኔት ።
፭ እስመ ፈቀደ ያኅድግ ፍኖተ ዘአዘዘከ እግዚአብሔር
አምላክከ ከመ ትሑር ባቲ ወታሰስል ወታማስን እኩየ
እምኔከ ።
፮ ወለእመኒ አስተብቍዐከ እኁከ ዘእምአቡከ ፡ አው ዘእ
ምእምከ ፡ አው ወልድከ ፡ አው ወለትከ ፡ አው ብእሲትከ
እንተ ውስተ ሕፅንከ ፡ አው ዓርክከ ዘከመ ነፍስከ ወይቤ
ለከ በጽሚት ነዐ ንሑር ወናምልክ ካዕዳነ አማልክተ ዘኢ
ተአምር አንተ ወአበዊከ ።

፯ እምአማልክተ አሕዛብ እለ ዐውድክሙ ወእለ ቅሩብ
ክሙ ፡ አው እለ ርኁቃን እምኔክሙ እምአጽናፈ ምድር
እስከ አጽናፈ ምድር ኢትኅበር ምስሌሁ ወኢትስምዖ
ወኢትምሐኮ ዐይንከ ወኢትምሐሮ ወኢትኅብእ ።
፰ አይድዕ ወነግር በእንቲአሁ ወእደዊከ ይቅድማ ቀቲ
ሎቶ ፡ ወእምዝ እደወ ኵሉ ሕዝብ ይውግሩሁ በአእባን
ወይቅትልዎ ።

ብታደርግ ላንተም ከንተም በኋላ ለልጆችህ ለዘለዓለሙ
በጎ ነገር ሊደረግልህ ዛሬ እኔ የማዝህን ቃሉን ሁሉ ሰም
ተህ ጠብቅ ። መዝ፡ ፻፳ ፲፫ ፡ ምሳ፡ ፫ ፲፬ ።
ትወርሳቸው ዘንድ አንተ ወደዚያ የምትገባባቸው
አሕዛብን ፈጣሪህ እግዚአብሔር ከፊትህ ባጠፋቸው ጊዜ
በአገሬቸውም በተቀመጥህ ጊዜ ፡ ለራስህ ለጠቅ ።
ከፊትህ ከጠፉ በኋላ እነሳቸውን መከተልን አትው
ደድ ፡ ጣኦቶቻቸውንም አትውደድ ፡ አሕዛብ ለጣኦቶቻ
ቸው ልጆቻቸውን እንዲሠዉ እኔም ልጄን እሠዋለሁ
አትበል ። ዘዳ፡ ፯ ፲፯ ፡ ፯ ፲፬ ።
ሴቶች ልጆቻቸውንና ወንዶች ልጆቻቸውን ለጣኦቶ
ቻቸው በእሳት የሚሠዉ ስለሆነ እግዚአብሔር አሕዛብ
ለጣኦቶቻቸው የሚሠዉትን ኃጢአት ጠልቷልና ለፈጣ
ሪህ ለእግዚአብሔር እንደዚህ አታድርግ ።
እኔ ዛሬ የማዝህን ቃል ሁሉ ያነኑ ለመሥራት ጠብቅ
በሱ ላይ አትጨምር ፡ ከሱም አታጉድል ።

ምዕራፍ ፲፫ ።

ከንተ ነቢየ ሐሰት ሕልም አላሚ ቢነሣ ምልክት ቢነ
ግርህ ወይም ተአምር ቢያደርግ ምልክቱም ቢደርስ የነገ
ረህ ተአምራቱም ቢደረግና እንሂድ የማታውቋቸውን
ጣኦታቱን እናምልክ ብሎ ቢነግርህ ይህንን ነቢይ ወይም
ሕልም ሐላሚውን ቃሉን አትስሙት (አትቀበሉት) ።
ፈጣ ሪያችሁ እግዚአብሔርን በፍጹም ልቡናችሁ ፡
በፍጹም ሰውነታችሁ ትወዱት እንደሆነ ያይ ዘንድ ፈጣሪ
ያችሁ እግዚአብሔር ይፈትናችኋልና ። ማቴ፡ ፳፬ ፳፬ ።
ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔርን በሕግ በአምልኮት ተከ
ተሉት እሱንም ፍሩት ፡ ሕጉን ጠብቁ ፡ ቃሉንም ስሙ ፡
በሱም ተማጠኑ ። ዘዳ፡ ፫ ፳ ፡ ፪ ነገ፡ ፳፫ ፫ ።
ይህ ነቢየ ሐሰት ወይም ሕልም ሐላሚው ግን ይሙ
ት ፡ ከግብጽ አገርና ከአገዛዝም ከወጣህ ፈጣሪህ እግዚአ
ብሔር በሚያስትህ ገንዘብ የሚያስትህን ነገር ነግሮሃልና ።
ጸንተህ ትኖርበት ዘንድ ፈጣሪህ እግዚአብሔር ያዘዘ
ህን ሕግ ያስተውህ ዘንድ ወድዷልና ክፉን ሰው ከንተ
ለይተህ አርቅ (አጥፋ) ። ዘዳ፡ ፲፰ ፳ ፡ ኤር፡ ፲፬ ፲፭ ።
ከባትህ የተወለደው ወይም ከናትህ የተወለደ ወንድ
ምህ ቢለምንህ ወይም ወንድ ልጅህ ፡ ወይም ሴት ልጅህ ፡
ወይም ባጠገብህ የምትተኛ ሚስትህ ብትለምንህ ወይም
እንደ ሰውነትህ የምትወደው ወዳጅህ በሥውር ና እንሂድ
አንተ የምታውቃቸውን አባቶችህም የማያውቋቸውን አማ
ልክት እናምልክ ቢልህ ።
በዙሪያችሁና ባጠገባችሁ ከምድር ዳርቻ እስከ ምድር
ዳርቻ ድረስ ከናንተ ከራቁ ከአሕዛብ ጣኦታት ከሱ ጋራ
አንድ አትሁን ፡ አትስማው ዓይንህም አትራራለት አትማ
ረው ኃጢአቱን አትሠውርለት ። ዘዳ፡ ፯ ፬ ።
የሱን ነገር ፈጽመህ ተናገር እጆችህም እሱን ለመግ
ደል ይቀደሙ ፡ ከዚህ በኋላ የሕዝቡ ሁሉ እጆች በደ
ንጊያ ወግረው ይግደሉት ። ዘዳ፡ ፲፯ ፫ ፡ ፯ ፲፯ ።

| | | |
|---|---|---|
| እስመ ፈቀደ ያርኅቀ እምእግዚአብሔር አምላክከ ዘአውፅአከ እምድረ ግብጽ ወእምቤተ ቅኔት ። | ፱ | ከግብጽ አገርና ከአገዛዝም ቤት ከወጣህ ፈጣሪህ ከእግዚአብሔር ሊያርቅህ ወዷልና ። |
| ወኵሉ እስራኤል ሰሚዖ ይፍራህ ወኢይድግም እንከ ገቢረ እኩይ ውስቴትክሙ ። | ፲ | እስራኤል ሁሉ ይህን ሰምቶ በፍንት ዘንድ ዳግመኛ ክፉ ነገር መሥራት አያድርግ ። ዘዳ፡ ፲፯ ፲፫ ፡ ፲፱ ፳ ። |
| ወለእመኒ ሰማዕከ በውስተ አሐቲ እምአህጉሪከ ዘወሀበከ እግዚአብሔር አምላክከ ከመ ትንበር ህየ እንዘ ይብሉ ወፅኡ አደው ኃጥአን እምኔነ ። | ፲፩ | በዚያች ትኖር ዘንድ ፈጣሪህ እግዚአብሔር ከሰጠህ በአንዲቱ አገር ከኛ ወገን ኃጥአን ሰዎች ተነው ሲሉ ብትሰማ ። |
| ወአክሐድዎሙ ለኵሎሙ እለ ይነብሩ ውስተ አህጉሪሆሙ ወይቤልዎሙ ንዑ ንሑር ወናምልክ ባዕዳነ አማልክተ ዘኢተአምሩ ትሴአል ወተሐትት ጥቀ ። | ፲፪ | በከተማው ያሉትን ሰዎች ተነሥተው ኑ ሂደን የማታውቋቸው አማልክትን እናምልክ ብለው አሳቱዋቸው ሲሉ ብትሰማ ፈጽመህ መርምረህ ተረዳ ። |
| ወእምከመ እሙነ ወጥዩቀ ኮነ ነገሩ ከመ ኮነ ርኩሰ ውስቴትክሙ ቀቲለ ትቀትል በሐፂን ኵሎሙ እለ ይነብሩ ውስተ ይእቲ ሀገር ። | ፲፫ | በፍንት ዘንድ ኃጢአት እንደሆነ ነገሩ የታመነ የተረዳ ከሆነ በዚያች አገር የሚኖሩትን ሰዎች ሁሉ በጦር ግደል ። |
| ወረጊመ ትረግም ኵሎ ዘሀለወ ውስቴታ ፡ ወኵሎ ንዋያ ታስተጋብእ ማእከለ መርኅባ ወታውዒ በእሳት ። | ፲፬ | በዚም ያለውን ሁሉ ርገም ፡ ገንዘቧንም ሁሉ ሰብስበህ በአደባባይ መካከል በእሳት አቃጥል ። |
| ወሀገራኒ ምስለ ኵሉ ንዋያ ወለኵላ ሀገር ከማሁ ትገብራ በቅድመ እግዚአብሔር አምላክከ ፡ ወአልቦ ዘይነብር ውስቴታ ለዓለም ወኢትነድቅ ። | ፲፭ | አገሯንም ከዕቃዋ ሁሉ ጋር ሌላውንም አገር ሁሉ በፈጣሪህ በእግዚአብሔር ፊት እንደሱ አድርግ ፡ ለዘለዓለም የሚኖርበት አይኑር እንደገና አትሥራት ። |
| ወኢትግሥሥ በእዴከ ምንተኒ ዘርጉም እምዘውስቴታ ከመ ይሚጥ እግዚአብሔር መዐቶ ወየሀብከ ምሕረቶ ወይምሐርከ ወያስተብዝኅከ በከመ መሐለ ለአበዊከ ። | ፲፮ | እግዚአብሔር ቍጣውን መልሶ ይቅርታውን ይሰጥህ ዘንድ ይራራልህም ዘንድ እግዚአብሔር ለአባቶችህ እንደ ማለ ፡ ያበዛህም ዘንድ በዚ ካለው የተረገመውን ምንም ምን በእጅህ አትንካ ። ዘፍ፡ ፳፪ ፲፯ ። |
| ወለእመ ሰሚዐ ሰማዕከ ቃሎ ወዐቀብከ ኵሎ ትእዛዞ ዘአነ እኤዝዘከ ዮም ወገበርከ ዘሠናይ ወዘአዳም ቅድመ እግዚአብሔር አምላክከ ወልደ ትከውን ሎቱ ። | ፲፯ | ቃሉን መስማትን ከሰማህ እኔ ዛሬ የማዝህን ትእዛዙን ሁሉ ብትጠብቅ በፈጣሪህ በእግዚአብሔር ፊት በጎ ነገርንና ያማረውን ብታደርግ ፡ የሱ ልጅ ትሆናለህ ። |
| ምዕራፍ ፲፬ ። | | ምዕራፍ ፲፬ ። |
| ወኢትትላጸይ ርእሰከ ለዘሞተ እስመ ሕዝብ ቅዱስ አንተ ለእግዚአብሔር አምላክከ ወኪያከ ኅረየ ከመ ትኩኖ ሕዝበ ለርእሱ እምኵሉ አሕዛብ ዘውስተ ገጸ ምድር ። | ፩ | አንተ ለፈጣሪህ ለእግዚአብሔር የተለየህ ወገን ነህና ለሱም ወገን ትሆነው ዘንድ በምድር ካሉ ከአሕዛብ ሁሉ መርጦሃልና ለሞተ ሰው ራስህን አትላጭ ። |
| ወኢትብልዑ ዘንተ ኵሎ ርኩሰ ፡ ወዝንቱ ውእቱ ዘትበልዑ እምእንስሳ ላሕም ፡ ወበግዕ ፡ ወጠሊ ፡ ወኃየል ፡ ወወይጠል ወቶራ ፡ ወደስክን ፡ ወውዕላ ፡ ወአረጋ ፡ ወዘራት ። | ፪ | ርኩስ የሆነውን ሁሉ አትብሉ ፡ ከእንስሳት ወገን የምትበሉት ይህ ነው ፡ ላም ፡ ፍየልና ፡ በግ ፡ (ኃየል) ዋልያ ፡ ሚዳቋ ፡ (ቶራ) አጋዘን ፡ (ዳስክን) ድኩርስ ፡ (ውዕላ) ቡሐር ፡ (አረጋ) ሰሳ ፡ (ዘራት ጅራተ ቀጭን) ወይም በራይሌ ናቸው ። ዘሌዋ፡ ፲፩ ፪ - ፳፫ ። |
| ወኵሉ እንስሳ ዘንፉቅ ሰኰናሁ ወዘንፉቅ ጽፈሪሁ ወክልኤቱ ጽፈሪሁ ወያመሰኵዕ ዝንቱ ዘትበልዑ እምእንስሳ ። | ፫ | ሰኰናው የተለየ ጥፍሩ የተሰነጠቀ ጥፍሩ ሁለት የሆነውና የሚያመሰኳው እንስሳ ሁሉ ከእንስሳት የምትበሉት ይህ ነው ። ኢሳ፡ ፶፩ ፳ ፡ ፩ ነገ፡ ፬ ፳፫ ። |
| ወዝንቱ ዘኢትበልዑ እምዘያመሰኵዕ ወዘንፉቅ ሰኰናሁ ወዘክፉል ጽፈሪሁ ገመል ፡ ወዳስዴዳ እስመ ያመሰኵዑ ፡ ወኢኮነ ንፉቀ ሰኰናሆሙ ፡ ወርኩሳን እሙንቱ ለክሙ ። | ፬ | ከሚያመሰኳው ሰኰናው ከተለየው ጥፍሩም ከተሰነጠቀው የማትበሉት ይህ ነው ፡ ግመል ፡ (ዳስዴዳ) ጥንቸል ነው ፡ ያመሰኳሉና ሰኰናቸውም አልተለየምና ለናንተ የረከሱ ናቸው ። |
| ወኪሮግልዮስኒ ፡ ወሐራውያ ፡ እስመ ንፉቅ ሰኰናሆሙ ወኢያመሰኵዑ ርኩሳን እሙንቱ ለክሙ ። | ፭ | (ኪሮግልዮስ) አሽክክ ፡ (ሐራውያ) እሪያ እሱማ ሰኰናቸው የተለየ ነውና ፡ አያመሰኩምምና ፡ እነሱቸው ለናንተ የረከሱ ናቸው ። |
| ወዝእብኒ እስመ ንፉቅ ሰኰናሁ ወክፉል ጽፈሪሁ ወኢያመሰኵዕ ርኩሳን እሙንቱ ለክሙ እምነ ሥጋሆሙ ኢትብልዑ ወበድኖሙ ኢትግሥሡ ። | ፮ | ጅብም ሰኰናው የተለየ ጥፍሩም የተሰነጠቀ ነው ፡ ነገር ግን አያመሰኳምና እነሱቸው ለናንተ የረከሱ ናቸው ፡ ሥጋቸውን አትብሉ ፡ ውዳቂያቸውንም አትዳሥሡ ። |

፱ ወዝንቱ ውእቱ ዘትበልዑ እምእንስሳ ወዘኢትበልዑ እምእንስሳ ወዝ ዘትበልዑ ዘእም ውስተ ማይ ዘኵሉ ዘቦቱ ክንፍ ወቅማር ብልዑ ።

ከእንስሳት የምትበሉትና የማትበሉት ይህ ነው ፤ በውኃው ውስጥ ከሚኖሩት የምትበሉት ይህ ነው ፤ (ክንፍ) ገለፈት (ቅማር) ማንርጥ ያለውን ሁሉ ብሉ ።

፲ ወዘኵሉ ዘአልቦቱ ክንፍ ወቅማር ኢትብልዑ ፤ ርኩስ ውእቱ ዝንቱ ለክሙ ።

ቅርፍት ማንርጥ የሌለውን ሁሉ አትብሉ ፤ ይህ ለናንተ የረከሰ ነው ።

፲፩ ወኵሉ ዖፈ ንጹሕ ብልዑ ።

ንጹሕ የሆነውን ወፍ ሁሉ ብሉ ።

፲፪ ወዝንቱ ዘኢትበልዑ እምኔሆሙ ንስር ፣ ወጊጳ ፣ ወኤልያጦን ፣ ወግሪጳ ፣ ወሆባይ ፣ ወዘአምሳሊሁ ።

ከነሱቸው የማትበሉት ይህ ነው ፤ (ንስር) አሞራ ፤ (ጊጳ) አገዳሰበር አሞራ ፤ (ኤልያጦን) አቢቁ ዋጭ አሞራ (ግሪጳ) ጭላት (ጭልፊት) አሞራ ፤ ሆባይ ፤ አንጭት አሞራና የመሰለውንም ።

፲፫ ወቋዕ ወዘአምሳሊሁ ።

(ቋዕ) ቍራ ፤ የመሰለውም ሁሉ ነው ።

፲፬ ወሰገኖ ፣ ወገላውቃ ፣ ወለሮን ፣ ወአሮድዮን ፣ ወቀቀኖ ፣ ወኢብን ፣ ወቅጥራቅጥሬን ፣ ወጉዛ ፣ ወዘአምሳሊሁ ።

ሰጐን ፤ (ገላውቃ) አራት ራስ አሞራ ፤ (ለሮን) ይብራ (ዝዪ) ፤ (አሮድዮን) ዖፈ ያሬድ ፤ (ቀቀኖ) ጋጋኖ ፤ (ኢብን) የመስቀል ወፍ ፤ ጉጉት ፤ (ቅጥራ ቅጥሬን) የውኃ ዶሮ ፤ ድምቢጥ ፤ (ጉዛ) ጭላትና የመሰለውም ነው ።

፲፭ ወሄጳጳ ፣ ወጉጓ ፣ ወአባጉንባሕ ወከዶራዮን ፣ ወዘአምሳሊሁ ።

(ሄጳጳ) ቃላቅ አሞራ ፤ (ጉጋ) ጃንጁላቴ አሞራ ፤ (አባ ጉንበሕ) እርኩም ፤ (ከራድዮን) ነጭ ወፍ ሳቢሳ ፤ የመሰለውም ነው ።

፲፮ ወጽርፍርዮን ፣ ወጽግንት ።

ጽርፍርዮና (ጽርፍርዮን) ጥንብ አንሣ አሞራ (ጽግንት) የሌት ወፍ ናቸው ።

፲፯ ወእሉ ኵሎሙ አዕዋፍ ርኩሳን እሙንቱ ለክሙ ወኢትብልዑ እምኔሆሙ ።

እነዚህ ወፎች ሁሉ ለናንተ የረከሱ ናቸው ፤ ከነሱ ቸው አትብሉ ። ዘሌ ፲፩ ፳፩ ።

፲፰ ወእምኵሉ አዕዋፍ ዘንጹሕ ብልዑ ።

ሊበሉዋቸው ከሚገቡ ወፎች ወገን ብሉ ።

፲፱ ወኵሉ ማውታ ኢትብልዑ ለፈላሲ ዘውስተ ሀገርክሙ አው ለባዕድ ሀብዎሙ ይብልዑ ፤ እስመ ሕዝብ ቅዱስ አንተ ለእግዚአብሔር አምላክከ ።

አንተ ለፈጣሪህ እግዚአብሔር የተለየህ ወገን ነህና የበተከውን ሁሉ አትብሉ ፤ በሀገራችሁ ላለ ስደተኛና ወይም ለሌላ ይበሉ ዘንድ ስጡቸው ።

፳ ወኢታብስል ማሕስአ በሐሊበ እሙ ።

ጠቦቱን በናቱ ወተት አትቀቅለው ።

፳፩ ዐሥራተ ትዔሥር እምኵሉ እክልከ ዘዘራእከ ዘታአቱ እምውስተ ገራውሂከ በበዓመቱ ።

ዘርተህ ከመረትከው እኽል ሁሉ በዓመት በዓመት አሥራት አውጣ ። ዘሌ ፳፯ ፲፯ ፤ ዘዳ ፲፬ ፯ ።

፳፪ ወብልዖ በበዓመት በቅድመ እግዚአብሔር አምላክከ በመከን ዘኅረየ እግዚአብሔር አምላክከ ከመ ይሰመይ ስሙ በህየ ።

ስሙ በዚያ ይጠራ ዘንድ ፈጣሪህ እግዚአብሔር በመረጠው ቦታ በፈጣሪህ እግዚአብሔር ፊት በዓመት በዓመቱ ብላው ።

፳፫ ወታበውእ ዓሥራቲሁ ለእክልከ ወለወይንከ ወለቅብዕከ ወለበኵረ አልሕምቲከ ወአባግዒከ ከመ ትትመሀር ፈሪሆቶ ለእግዚአብሔር አምላክከ በኵሉ መዋዕል ።

በዘመኑ ሁሉ ፈጣሪህ እግዚአብሔር መፍራትን ትማር ዘንድ የእኽልን የወይንህንና የዘይትህን ዓሥራት አቅርብ ፤ ከበጎችህና ከላሞችህም መጀመሪያ የተወለደውን አግባ ። ዘዳ ፲፬ ፳፯ ፤ ፲፱ ፯ ።

፳፬ ወለእመሰ ርኁቅ ውእቱ እምኔከ ፍኖቱ ወኢትክል ወሲዶ እስመ ውእቱ መከን ዘኅረየ እግዚአብሔር አምላክከ ከመ ይሰመይ ስሙ በህየ እስመ ባረከከ እግዚአብሔር አምላክከ ፤ ወትሬስዮ ለብሩር ።

ነገር ግን ጐዳናው ከንተ የራቀ ቢሆን በዚያ ስሙ ይጠራ ዘንድ ፈጣሪህ እግዚአብሔር የመረጠው ቦታ ሩቅ ነውና ለመውሰድ ባትችል ፈጣሪህ እግዚአብሔር ስላከበረህ እኽሉን ለብር ለውጠው ።

፳፭ ወትነሥእ ብሩር በእዴከ ወተሐውር ኀበ መከን ዘኅረየ እግዚአብሔር አምላክከ ወትሁብ ብሩረ ለኵሉ ዘፈተወት ነፍስከ ።

ብሩንም በእጅህ ይዘህ ፈጣሪህ ወደ መረጠው ቦታ ሂድ ፤ ብሩን (ዋጋውን) ሰውነትህ ለወደደችው ሁሉ ስጥ ።

፳፮ አው ለላሕም ፣ አው ለበግዕ ፣ አው ለወይን ፣ አው ለሜስ ፣ አው ለኵሉ ዘፈተወት ነፍስከ ፤ ወብላዕ በህየ በቅድመ እግዚአብሔር አምላክከ ወትትፌሣሕ አንተ ወቤትከ ።

ወይም ላሕም ፤ ወይም በግ ፤ ወይም ወይን ወይም ጠጅ ወይም ሰውነትህ የወደደችውን ሁሉ ገዝተህ በፈጣሪህ በእግዚአብሔር ፊት በዚያው በልተህ አንተና ወገንህ ደስ ይበልህ ።

፳፯ ወለሌዋዊ ዘውስተ ሀገርከ ኢትግድፎ እስመ አልቦ

ከንተ ጋር ርስትና ፈንታ የሌለውንና በአገርህ ያለ ከህ

ክፍለ ወርስት ምስሌከ ።

፳፰ ወበማልዕ ዓም ታበውእ ኵሎ ዓሥራተ እክልከ ወዘ ዓመታቲሁሰ ታነብር ውስተ ቤትከ፤ ወእምዝ ይመጽእ ምስሌከ ሌዋዊ እስመ አልቦ ክፍለ ወርስት ምስሌከ ።

፳፱ ወግዩር ወእጓለ ማውታ ወዕቤር ዘውስተ ሀገርከ ይብልዑ ከመ ይባርከ እግዚአብሔር አምላክከ በኵሉ ግብርከ ዘገበርከ ።

ምዕራፍ ፲፭ ።

፩ ወበሳብዕ ዓም ትገብር ኅድገተ፤ ወከመዝ ውእቱ ትእዛዙ ለኅድገት ዘይትኀደግ ።

፪ ኵሎ ንዋየከ ዘይፈድየከ ካልእከ ወእኁከ ኢትትፈደይ እስመ ኅድገተ ተሰምየት ለእግዚአብሔር አምላክከ ።

፫ ወዘኀበ ነኪርሰ ትትፈደይ ኵሎ ዘብከ ኀቤሁ፤ ወዘ ኀበ እኁከሰ ኅድገተ ትገብር ኵሎ ዘይፈድየከ ።

፬ እስመ አልቦ ነዳይ እምኔከ እስመ ባርኮ ይባርከከ እግዚአብሔር አምላክከ በውስተ ምድር ዘይሁበከ እግዚአብሔር አምላክከ ርስተ ዘትወርስ ።

፭ ወለእመ ሰሚዐ ሰማዕከ ቃለ እግዚአብሔር አምላክከ ወዐቀብከ ወገበርከ ኵሎ ትእዛዞ ዘአነ እኤዝዘከ ዮም እስመ ባረከከ እግዚአብሔር አምላክከ በከመ ይቤለከ ።

፮ ወትሌቅሕ ለባዕዳን አሕዛብ ብዙኃን ወአንተሰ ኢትት ሌቃሕ ወትኴንኖሙ ለአሕዛብ ብዙኃን አንተ ወለከሰ ኢይኴንኑከ ።

፯ ወለእመሰቦ ዘተጽነሰ እምአኀዊከ በእሐቲ እምአህጉሪከ ዘወሀበከ እግዚአብሔር አምላክከ ኢታጽንዕ ልበከ ወኢ ትሚጥ እዴከ እምውሂቦቱ ለእኁከ ።

፰ ወፍታሕ ወአርኁ እዴከ ወሀቦ ለእኁከ እምዘሰአለከ ።

፱ ወዑቅ ርእሰከ ኢይኩን ቃለ ኀጢአት ውስተ ልብከ እንዘ ትብል ቀሩብ ውእቱ ዓመተ ኅድገት ዘሳብዕ ዓም ወኢይሁብ ወያስኪ ዐይኖ እኁከ ወይጸርሕ ላዕሌከ ኀበ እግዚአብሔር ወይከውን ኀጢአተ ላዕሌከ ።

፲ አሳ ውሂበኒ ሀቦ፤ ወለቅሐኒ ለቅሖ መጠነ ሰአለከ፤ ወኢይተክዝ ልብከ እንዘ ትሁቦ እስመ በበይነ ዝንቱ ይባርከከ እግዚአብሔር አምላክከ በኵሉ ምግባሪከ በውስተ ኵሉ ዘወደይከ እዴከ ።

፲፩ እስመ ኢይትኀጣእ ነዳይ ውስተ ምድርከ፤ ወበበይነ ዝንቱ እኤዝዘከ አነ ዮም ትግበር ዘንተ ነገረ፤ ወእቤለከ ከመ ትፍታሕ ወከመ ታርኁ እዴከ ለእኁከ ነዳይ ወለዘይስእለከኒ ዘቅሩብከ ዘውስተ ምድርከ ሀቦ ።

፲፪ ወለእመኒ ተሠይጠ ኀቤከ እኁከ ዕብራዊ፤ አው ዕብ

ኑን አትተወው ። ዘኁ፡ ፲፰ ፳፡ ዘዳ፡ ፲፬ ፲፱ ።

በሦስተኛው ዓመት የእኽልህን ሁሉ ዓሥራት አምጥተህ የሁለቱን ዓመት እኽል ግን በቤትህ አኑረው፤ ከንተ ጋር ርስትና ፈንታ የለውምና ከዚህ በኋላ ከሀኑ ከንተ ጋራ ይምጣ ።

ፈጣሪህ እግዚአብሔር በደረግኸው ሥራ ሁሉ ያከብርህ ዘንድ እናት አባቱ የሞቱበት ልጅና ስደተኛ በአገርህም ያሉት በልተው ይብሉ ። ዘዳ፡ ፲፭ ፲ ።

ምዕራፍ ፲፭ ።

በሰባተኛው (በየሰባቱ) ዓመት፤ ዓመተ ኅድገትን አድርግ (አክብር) ኅድገት የሚደረግበት የዓመት ኅድገትም ሥራቱ እንዲህ ነው ። ዘፀ፡ ፳፫ ፲፫፡ ዘዳ፡ ፲፭ ፲፱ ።

ለፈጣሪህ ለእግዚአብሔር ዓመተ ኅድገት ታብላለችና ወንድምህ ባልንጀራህ የሚከፍልህን ገንዘብ ሁሉ አትክፈል (አትቀበል) ። ዘፍ፡ ፴፮ ፲፬ ።

ከሌላ (አሕዛብ) ግን በሉ ዘንድ ያለ ገንዘብህን ሁሉ ተቀበል፤ ወንድምህ የሚከፍልህን ገንዘብ ግን ተውለት ።

ፈጣሪህ እግዚአብሔር ርስት አድርጎ በሚሰጥህ ምድር ፈጣሪህ እግዚአብሔር መባረኩን ስለሚባርክህ በመካከልህ ድኻ የለምና ። ዘዳ፡ ፳፫ ፳ ።

የፈጣሪህ የእግዚአብሔርን ቃል ብትሰማ ሕጉንም ብትጠብቅ እኔ አሁን የማዝዝህን ይህን ትእዛዙንም ብታደርግ አከብርሃለሁ እንዳለህ ፈጣሪህ እግዚአብሔር አክብሮኻልና ።

ብዙዎች ለሆኑ ለሌሎች አሕዛብ ታበድራለህ፤ አንተ ግን አትበደርም፤ አንተ ብዙዎች አሕዛብን ትገዛቸዋለህ፤ አንተን ግን አይገዙህም ።

ፈጣሪህ እግዚአብሔር ከሰጠህ አገሮች በአንዲቱ አገር ከወንድሞችህ የተቸገረ ቢኖር ልብህን አታጽና (አትጨክን) ለወንድምህ ከመስጠትም እጅህን አትጠፍ ።

(ጕተራህን ከፍተህ) እጅህን ዘርግተህ ለወንድምህ የለመነህን ስጠው ። ዘሌ፡ ፳፭ ፴፭ ።

ዕረፍት የሚደረግበት ሰባተኛው ዘመን ቅርብ ነው፤ አልሰጠውም እያልክ በልብህ የኃጢአትን ነገር እንዳታስብ ለራስህ ዕወቅ፤ ወንድምህ በዓይኑ ለማየት ይጠላኻል ወደ እግዚአብሔርም ይጮህብሃል፤ በንተም ኃጢአት ይሆንብኻል ። ዘዳ፡ ፲፫ ፲፫፡ ፩ ሳሙ፡ ፩ ፲፯ ።

መስጠትን ስጠው፤ የለመነህንም ያህል ማበደርን አበድረው እንጂ ስትሰጠውም ልብህ አይዘን ስለዚህም ፈጣሪህ እግዚአብሔር በሥራህ ሁሉ በእጅህም በያዝከው ሁሉ ያከብርኻል ። ፪ ቆሮ፡ ፱ ፯፡ ሉቃ፡ ፯ ፴፭ ።

በአገርህ ድኻ አይታጣምና፤ ስለዚህ ይህን ነገር ታደርግ ዘንድ ጕተራህን ከፍተህ፤ እጅህን ዘርግተህ ለድኻው ወንድምህና በአቅራቢያህ ላለው ለለመነህ ትሰጠው ዘንድ እኔ አሁን አዝኻለሁ ። ማቴ፡ ፳፮ ፲፩፡ ማር፡ ፲፬ ፯ ።

እስራኤላዊ ወንድምህ ላንተ ቢሸጥልህ ወይም ዕብራ

| | | |
|---|---|---|
| ራዊት ስድስተ ዓመተ ይትቀነይ ለከ ወበሳብዕ ዓም ትፌንዎ አግዓዘከ እምኀቤከ ። | | ዊቱ ሴት ብትሸጥልህ ስድስት ዓመት ይገዛልህ፤ በሰባተኛው ዓመት ከንተ ዘንድ ነፃ አውጥተህ ስደደው ። |
| ወአመ ትፌንዎ አግዓዘከ እምኀቤከ ኢትፌንዎ ዕራቆ ። | ፲፫ | ከንተም ነፃ አውጥተህ በሰናበትከው ጊዜ ባዶ እጁን አትስደደው ። |
| አላ ስንቀ ታሰንቆ እምአባግዒከ ወእምእክልከ ወእምክያዱ ወይንከ በአምጣነ ባረከከ እግዚአብሔር አምላክከ ትሁቦ ። | ፲፬ | ከበጎችህ ከእኽልህና ከወይንህ ዓውድማ ስጠው ፈጣሪህ እግዚአብሔር ያከበረህን ያህል ስጠው እንጂ ባዶ እጁን አታሰናብተው ። ዘጸ፡ ፫ ፲፰ ። |
| ወተዘከር ከመ ገብር አንተ በምድረ ግብጽ፥ ወቤዘወከ እግዚአብሔር አምላክከ እምህየ፥ ወበበይነ ዝንቱ አኤዝዘከ አነ ዮም ከመ ትግበር ዘንተ ነገረ ። | ፲፭ | አንተ በግብጽ አገር ሳለህ ባርያ (ተገዥ) እንደነበርህ ፈጣሪህ እግዚአብሔርም ከዚያ እንዳዳነህ አስብ፥ ስለዚህም ይህን ነገር ታደርግ ዘንድ እኔ አሁን አዝዝሃለሁ ። |
| ወለእመሰ ይቤለከ ለሊሁ ኢይወፅእ እምኀቤከ፤ እስመ አፍቀረከ ወለቤትከኒ እስመ ኀየሰ ነቢር ኀቤከ፥ ትነሥእ መስፌ ወትሰቍሮ እንግዘ ኀበ ኆኀት በኀበ መድረክ ። | ፲፮ | ባንተ ዘንድ መኖር ስለተሻለው አንተን ወድጃለሁ ቤትህንም ወድጃለሁና ከንተ ዘንድ አልወጣም ቢልህ ግን፥ ወስፌ አምጥተህ በደጃፉ መድረክ አፍንጫውን ትበሳዋለህ ። ዘፀ፡ ፳፩ ፭ ። |
| ወይኩንከ ገብረ ለዓለም፥ ወለእመኒ አመትከ ከማሁ ከመ ትገብር ። | ፲፯ | ለዘለዓለሙ ተገዥ ይሁንህ፥ ሴት ባርያህም ብትሆን እንዲሁ አድርግ ። |
| ወኢይዕዕብከ ፈንዎቱ አግዓዘ እምኀቤከ እስመ እምነ ዓመተ ቅንየት ተቀንየ ለከ ስድስተ ዓመተ ወይባርከከ እግዚአብሔር አምላክከ በኵሉ ዘገበርከ ። | ፲፰ | መግዛት ከጀመረበት ዓመት ጀምሮ ስድስት ዓመት ተገዝቶልሃልና ከንተ አርነት ማውጣቱ አያስጨንቅህ በደረግኸውም ሥራህ ሁሉ አምላክህ እግዚአብሔር ያከብርሃል ። ኢሳ ፲፮ ፲፬፥ ፳፩ ፲፮ ። |
| ወኵሎ በኵረ ዘተወልደ እምአልሕምቲከ ወእምአባግዒከ ተባዕቶ ትቄድስ ለእግዚአብሔር አምላክከ ወኢትቅኒ በኵረ አልሕምቲከ ወኢትቀርፅ በኵረ አባግዒከ ። | ፲፱ | ከበጎችህና ከላሞችህ በኵር ሁኖ የተወለደውን ሁሉ ተባቱን ለፈጣሪህ ለእግዚአብሔር ለይ ከላሞችህም መጀመሪያ የተወለደውን አትረስ፥ ከበጎችህም መጀመሪያ የተወለደውን አትሸልት ። ዘፀ፡ ፲፫ ፫፥ ዘሌ፡ ፳ ፫ ። |
| በቅድመ እግዚአብሔር አምላክከ ብልዖ በበዓመት በውስተ መካን ዘኀረየ እግዚአብሔር አምላክከ አንተ ወኵሉ ቤትከ ። | ፳ | ፈጣሪህ እግዚአብሔር በመረጠው ቦታ ሁነህ አንተም ቤተ ሰብህም በየዓመቱ በእግዚአብሔር ፊት ብላው ። |
| ወለእመሰ ቦቱ ነውር እመኒ ዕውር ውእቱ፥ አው ሐንካስ፥ አው እምዘከነ ነውረ እኩይ ላዕሌሁ ኢትሡዖ ለእግዚአብሔር አምላክከ ። | ፳፩ | ነቀፋ ቢኖርበት ግን ዕውር፥ ወይም አንካሳ ቢሆን፥ ወይም በሱ ክፉ ነውር ከሆነው ወገን አንዳች ነውር ቢገኝበት ለፈጣሪህ እግዚአብሔር አትሠዋው ። |
| በሀገርከ ብልዖ፥ ርኩስኒ ወንጹሕኒ ኅቡረ ይብልዕዎ ከመ ወይጠል አው ከመ ኀየል ። | ፳፪ | በአገርህ ብላው ንጹሕ የሆነው ንጹሕም ያልሆነው ሰው እንደ ዋልያ፥ እንደ ፌቆ (ሚዳቋ) አንድነት ይብሉት። |
| ወዳእሙ ደሞ ኢትብልዑ፥ ከዐውዎ ውስተ ምድር ከመ ማይ ። | ፳፫ | በምድር ላይ እንደ ውኃ አፍስሱት እንጂ ደሙን አትብሉት ። ዘፍ፡ ፱ ፬፥ ዘሌ፡ ፯ ፳፯፥ ፲፯ ፲ ። |
| ምዕራፍ ፲፮ ። | | ምዕራፍ ፲፮ ። |
| ወዕቀብ ወርኀ ሚያን ወግበር ፋሲካሁ ለእግዚአብሔር አምላክከ፥ እስመ በወርኀ ሚያን ወፃእከ እምብሔረ ግብጽ ሌሊተ ። | ፩ | በሚያዝያ ወር ከግብጽ አገር በሌሊት ወጥተሃልና የሚያዝያን ወር ጠብቀህ የፈጣሪህ የእግዚአብሔርን በዓል (ፋሲካን) አክብር (አድርግ) ። ዘጸ፡ ፲፪ ፰ ። |
| ወትጠብሕ ፋሲካሁ ለእግዚአብሔር አምላክከ አባግዐ ወአልሕምተ በውስተ መካን ዘኀረየ እግዚአብሔር ከመ ይሰመይ ስሙ በህየ ። | ፪ | በዚያ ስሙ ይጠራ ዘንድ እግዚአብሔር በመረጠው ቦታ ላሞችንና በጎችን የፈጣሪህ እግዚአብሔርን በዓል በማክበር ሠዋ ። ዘኍ፡ ፳፰ ፲፱፥ ዘዳ፡ ፲፪ ፩ ። |
| ወኢትብላዕ ምስሌሁ ብሑአ ሰቡዐ መዋዕለ ናእተ ብላዕ ምስሌሁ ኅብስተ ሕማም እስመ በጕጕአ ወፃእከ እምግብጽ ከመ ትዘከር ዕለተ ፀአትከ እምድረ ግብጽ በኵሉ መዋዕለ ሕይወትከ ። | ፫ | ከሱ ጋራ የቦካውን (መጻጻ) አትብላ፥ በኖርክበት ዘመን ሁሉ ከግብጽ ምድር የወጣህበትን ቀን ታስብ ዘንድ ከግብጽ በችኰላ ወጥተሃልና ሰባት ቀን የመከራ እንጀራን ብላ ። ዘፀ፡ ፲፪ ፲፭፥ ኢሳ ፶፪ ፲፪ ። |
| ወኢያስተርኢ ብሑእ በኵሉ ደወልከ ሰቡዐ ዕለተ ወኢይቢት እምውዕቱ ሥጋ ዘጠባሕከ ሠርከ በቀዳሚት ዕለት ለነግህ ። | ፬ | በአገርህ ሁሉ ሰባት ቀን የቦካ (መጻጻ) አይታይ፥ በመጀመሪያይቱ ቀን ማታ ከረድኸው በግ ሥጋ ለማለዳ አይደር። |

| | | |
|---|---|---|
| ወኢትክል ጠቢሖቶ ለፋሲካ በውስተ አሐቲ እምአ ህጉሪከ ዘወሀበከ እግዚአብሔር አምላክከ እንበለ ውስተ መከን ዘኀረየ እግዚአብሔር አምላክከ ከመ ይሰመይ ስሙ በህየ ። | ፭ | ፈጣሪህ እግዚአብሔር ከሰጠህ አገሮች በአንዲቱ በዚያ ስሙ ይጠራበት ዘንድ ፈጣሪህ እግዚአብሔር በመረጠው ቦታ ነው እንጂ ፋሲካን ለማክበር መሥዋዕት መሠዋት አትችልም ። |
| ወበህየ ትጠብሖ ፋሲካ ሠርከ ጊዜ ተዐርብ ፀሐይ እስመ በውእቱ ጊዜ ወፃእከ እምድረ ግብጽ ። | ፮ | በዚያች አገር ከግብጽ ምድር ወጥተህልና ማታ ፀሐይ በምትገባበት ጊዜ በዚያ የፋሲካን መሥዋዕት ሠዋ ። |
| ወታበስል ወትጠብሕ ወትበልዕ በውእቱ መከን ዘኀረየ እግዚአብሔር አምላክከ ወትገብእ በነግህ ወተአቱ ውስተ ቤትከ ። | ፯ | ፈጣሪህ እግዚአብሔር በመረጠው በዚያ ቦታ ሠውተህ አብስለህ (ጠብሰህ) ብላ ፤ በጧት ተመልሰህም ወደ ቤትህ ትገባለህ ። ዘፀ ፲ ፰ ፤ ዮሐ ፪ ፲፫ ። |
| ሰዱስ መዋዕለ ብላዕ ናዕተ ወሳብዕትሰ ዕለት እንተ አስተዋፅኦ ይእቲ ዘበዓሉ ለእግዚአብሔር አምላክከ ወኢ ትግበር በቲ ኵሎ ግብረ እንበለ ዘይትገበር ለነፍስ ። | ፰ | ስድስት ቀን ቂጣን ብላ ፤ ሰባተኛይቱ ቀን ግን የፈጣሪህ የእግዚአብሔርን በዓል የሚያከብሩበትን የሚያወጣጡበት ናትና ለነፍስ ከሚሠሩት ሥራ በቀር ሥራውን ሁሉ አትሥራበት ። ዘፀ ፲፪ ፲፮ ፤ ዘሌ ፲፮ ፬ ። |
| ወትኌልቍ ለከ ሰቡዐ ሰናብተ እምዘአኀዝከ ትዕፅድ ማእረረከ ወትእኅዝ ትኈልቍ ሰቡዐ ሰናብተ ። | ፱ | አዝመራህን ታጭድ ዘንድ ከጀመርክበት ጀምሮ ሰባቱን እንድ ሰባቱን እንድ እያልክ እስከ ሰባት ድረስ ቍጠር ፤ ሰባቱንም ሱባዔ ልትቈጥር ትጀምራለህ ። |
| ወትገብር በዓለ ሰንበት ለእግዚአብሔር አምላክከ ብእ ምጣነ ትክል እዴከ ዘትሁብ ወበአምጣነ ባረከከ እግዚአ ብሔር አምላክከ ። | ፲ | ፈጣሪህ እግዚአብሔር በከበረህ መጠን እጅህም የም ትሰጠውን በምትችል መጠን ለፈጣሪህ እግዚአብሔር በዓለ ሰዊትን አክብር ። ፩ ቆሮ ፲፮ ፩ ። |
| ወትትፌሣሕ በቅድመ እግዚአብሔር አምላክከ አንተ ወደቂቅከ ወአዋልዲከ ወገብርከ ወአመትከ ወሌዋዊ ዘው ስተ ሀገርከ ፤ ወግዩር ወእጓለ ማውታ ወዕቤር እንተ ሀለ ወት ኀቤከ ውስተ ውእቱ መከን ዘኀረየ እግዚአብሔር አምላክከ ከመ ይሰመይ ስሙ በህየ ። | ፲፩ | አንተ በፈጣሪህ በእግዚአብሔር ፊት ደስ ይበልህ ፤ ሴቶች ልጆችህና ወንዶች ልጆችህ ፤ ሴት ባርያህና ወንድ ባርያህም ደስ ይበላቸው ፤ በአገርህ ውስጥ ያለ ካህንም ደስ ይበለው ፤ እናት አባቱ የሞቱበት ልጅና ፤ ስደተኛም ደስ ይበላቸው ፤ ስሙ ይጠራበት ዘንድ ፈጣሪህ እግዚአ ብሔር በመረጠው በዚያ ቦታ ያለች ባልቴትም ደስ ይበላት ። |
| ወተዘከር ከመ ገብር አንተ በምድረ ግብጽ ፤ ወዕቀብ ወግበር ኵሎ ዘንተ ትእዛዘ ። | ፲፪ | አንተ በግብጽ ምድር ባርያ (ተገዥ) እንደ ነበርክ አስብ ፤ ሕጉን ጠብቅ ፤ ይህን ትእዛዙንም ሁሉ ፈጽም ። |
| ወትገብር ለከ በዓለ መጸለት ሰቡዐ ዕለተ ሶበ አስተ ጋባእከ እክለከ እምውስተ ዐውድ ወእምውስተ ምክያደ ወይንከ ። | ፲፫ | ከወይን ዓውድማህና ከእኽል ዓውድማህ ወይንህ ንና እኽልህን በሰበሰብክ ጊዜ ሰባት ቀን የዳስ በዓል ላንተ አድርግ ። |
| ወትፈሣሕ በበዓልከ ወወልድከኒ ፤ ወወለትከኒ ፤ ወገብ ርከኒ ፤ ወአመትከኒ ፤ ወሌዋዊ ዘውስተ ሀገርከ ወግዩር ወእ ጓለ ማውታ ፤ ወዕቤር እንተ ሀለወት ውስተ ሀገርከ ። | ፲፬ | በበዓልህም ደስ ይበልህ ፤ ሴት ልጅህና ወንድ ልጅ ህም ሴት ባርያህና ወንድ ባርያህም ደስ ይበላቸው ፤ በአገ ርህ ያለ ካህንም ደስ ይበለው ፤ እናት አባቱ የሞቱበት ል ጅና ስደተኛም ደስ ይበላቸው ፤ በአገርህ ያለች ባልቴትም ደስ ይበላት ። ዮሐ ፯ ፴፯ ። |
| ሰቡዐ ዕለተ ትገብር በዓለ ለእግዚአብሔር አምላክከ በውስተ መከን ዘኀረየ እግዚአብሔር አምላክከ በኵሉ ወይንከ ወእክልከ ወበኵሉ ግብረ እደዊከ ። | ፲፭ | ፈጣሪህ እግዚአብሔር በመረጠው ቦታ በወይንህ በእ ኽልህ በእጅህ ሥራ ሁሉ ሰባት ቀን የፈጣሪህ የእግዚአ ብሔርን በዓል አድርግ ። ዘሌ ፳፫ ፴፱ ። |
| ወተፈሣሕ ሠለስተ ጊዜያተ በዓመት ወያስተርኢ ኵሉ ተባዕትከ ቅድመ እግዚአብሔር አምላክከ በውስተ መከን ዘኀረየ እግዚአብሔር በበዓለ ናእት ወበበዓለ ሰንበት ወበ በዓለ መጸለት ወኢያስተርኢ ቅድመ እግዚአብሔር አም ላክከ ዕራቀከ ። | ፲፮ | በዓመት ሦስት ጊዜ ደስ ይበልህ ፤ ወንድ ልጅህ ሁሉ እግዚአብሔር በመረጠው ቦታ በፈጣሪህ በእግዚአብሔር ፊት ይታይ ፤ በእሸትና ፤ በቂጣ ፤ በጥላም በሚደረግ በዓል በእግዚአብሔር ፊት ባዶህን አትታይ ። |
| አሐዱ አሐዱ በአምጣነ ኀይሉ እዴክሙ ወበአምጣነ በረ ከቱ ለእግዚአብሔር አምላክክሙ ዘወሀበክሙ ታመጽኡ ። | ፲፯ | በእጃችሁ ያለውን ያህልና እግዚአብሔር ፈጣሪያችሁ በሰጣችሁ በረከት መጠን አንዱም አንዱም መባችሁን አምጡ ። ዘኍ ፲፩ ፲፮ ፤ ዘዳ ፩ ፲፮ ። |
| መኳንንተ ለክሙ ፈታሕተ ወጸሐፍተ መበእ በኵሉ አህ ጉሪክሙ ዘወሀበክሙ እግዚአብሔር አምላክክሙ በበዘመ ድክሙ ወበበነገድክሙ ወይኰንንዎ ለሕዝብ ኵነኔ ጽድቀ ። | ፲፰ | ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር በሰጣችሁ አገሮች ሁሉ በየዘመዳችሁ በየነገዳችሁ ዳኞችን መባውን የሚጽፉ ሰዎ ችን ለናንተ ሹሙ ፤ ለሕዝቡም እውነተኛ ፍርድን ይፍ |

፲፱ ወኢያድልዉ ለገጽ ፡ ወኢይንሥኡ ሕልያነ ፡ እስመ ሕልያን ያዐውሮሙ ለጠቢባን ወያሴስሎ ለቃለ ጽድቅ ።

፳ ዘይጸድቅኒ በጽድቁ ለይትሉ ከመ ትሕየዉ ወትባኡ ትትዋረሱ ምድረ ዘይሁበክሙ እግዚአብሔር አምላክክሙ ፤

፳፩ ወኢትትክል ለከ አመ እምውስተ ኵሉ ዕፀ ዘያመልኩ ኵሉ አሕዛብ ኀበ ምሥዋዑ ለእግዚአብሔር አምላክከ ።

፳፪ ወኢትግበር ምስለ ዘይጸልኦ እግዚአብሔር አምላክከ በጥቃ ምሥዋዑ ለእግዚአብሔር ዘትገብር ለከ ፡ ወኢታቅም ለከ ሐውልተ ።

ምዕርፍ ፲፯ ።

፩ ወኢትሡዕ ለእግዚአብሔር አምላክከ ላሕመ ፡ አው በግዐ ዘቦቱ ነውር ላዕሌሁ ፤ ወኵሉ ነገር እኩይ ርኩስ ውእቱ በኀበ እግዚአብሔር አምላክከ ።

፪ ወለእመኒ ተረክቡ በውስተ አሐቲ እምአህጉሪከ ዘወሀበከ እግዚአብሔር አምላክከ ብእሲ ፡ አው ብእሲት ፡ ዘገብሩ እኩየ በቅድመ እግዚአብሔር አምላክከ እለ ተዐወሩ ሕጎ፥

፫ ወሖሩ ወአምለኩ በዕዳነ አማልክተ ወሰገዱ ሎሙ ለፀሐይ አው ለወርኅ ፡ አው እምውስተ ሠርጕቲሃ ለሰማይ ዘኢአዘዘከ እግዚአብሔር አምላክከ ፡ ወእምከመ ሰማዕከ ተሐትት ጥቀ ።

፬ ወለእመ እሙነ ከነ ዝ ነገር ርኩስ በውስተ እስራኤል ወታወፅአ ለውእቱ ብእሲ ወእመኒ ብእሲት ይእቲ ወይውግርዎሙ በእብን ወይቅትልዎሙ ።

፮ በክልኤቱ ወሠለስቱ ሰማዕት ይመውቱ እለ ይመውቱ ወኢይመውቱ በአሐዱ ስምዕ ።

፯ ወእደዊሆሙ ለውእቶሙ ሰማዕት ይቅድማ ቀቲሎቶሙ ወእምድኅሬሆሙ እደወ ኵሉ ሕዝብ ወታወፅእ እኩየ እምኔክሙ ።

፰ ወለእመቦ ዘተስእነከ ቃል በውስተ ፍትሕ ዘማእከለ ደም ወደም ፡ ወማእከለ ንጹሕ ለእንጽሕ ፡ ወማእከለ ላኳ ወላኳ ፡ ቃለ ፍትሕ በውስተ አህጉሪከ ትነሥእ ወተዐርግ ውስተ መካን ዘኀረየ እግዚአብሔር አምላክከ ከመ ይሰመይ ስሙ በህየ ።

፱ ወተሐውር ኀበ ካህናት ወሌዋውያን ወኀበ መኳንንት እለ ሀለዉ በውእቱ መዋዕል ወትሴአል ወያየድዑከ ፍትሐ።

፲ ወትገብር በከመ ቃል ዘነገሩከ በውእቱ መካን ዘኀረየ እግዚአብሔር አምላክከ ከመ ይሰመይ ስሙ በህየ ወዕቀብ ኵሎ ከመ ትግበር ዘመሀሩከ ሕጎ።

፲ ወበከመ ፍትሑ ዘነገሩከ ግበር ወኢትትገኃሥ እም ቃል ዘነገሩከ ኢ ለየማን ወኢ ለፀጋም ።

ረዱለት ። ዘፀ፡ ፳፫ ፪፡ ዘሌ፡ ፲፱ ፲፯ ።

ፊት አይተው አያድሉ (አያዳሉ) ማማለጃ (ጉቦ) አይቀበሉ ፡ ማማለጃ አዋቂዎችን አላዋቂዎች ያደርጋቸዋልና እውነተኛውንም ነገር ያስለውጠዋልና (ያጣምመዋልና)።

ልትወርሷት ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር በሚሰጣችሁ አገር ገብታችሁ በሕይወት ትኖሩ ዘንድ እውነተኛውም ሰው በእውነቱ ጸንቶ ይኑር ። ሕዝ፡ ፲፰ ፰ ።

አሕዛብ ሁሉ ከሚያመልኩት ዛፍ ቈርጠህ ዕንጨቱን በፈጣሪህ በእግዚአብሔር መሠውያ አጠገብ ዓፀድ አድርገህ አትትከል (አታቁም) ።

ፈጣሪህ እግዚአብሔር የሚጠላውን ምስል በእግዚአብሔር መሠውያ አጠገብ አትሥራ ፡ ትክል ደንጊያንም አታቁም ። ዘፀ፡ ፳፫ ፳፪ ፡ ፩ ነገ፡ ፲፱ ፲፭ ።

ምዕራፍ ፲፯ ።

ለፈጣሪህ ለእግዚአብሔር ነቀፋ ያለበትን በሬን ወይም በግን አትሠዋ ፡ ክፉም ነገር ሁሉ በፈጣሪህ በእግዚአብሔር ዘንድ የሚያስጸይፍ ነውና ። ዘፀ፡ ፲፪ ፫ ።

ፈጣሪህ እግዚአብሔር ከሰጠህ አገሮች በአንዲቱ አገር በፈጣሪህ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ሥራን የሠሩ ሕጉንም ቸል ያሉ ወንድ ወይም ሴት ቢገኙ ።

ሄደው ልዩ ጣኦታትን ቢያመልኩ ለፀሐይና ለጨረቃም ቢሰግዱላቸው ፡ ፈጣሪህ እግዚአብሔር ላላዘዝህ ለሰማይ ጌጦች (ለከዋክብት) ሁሉ የሰገዱ ቢገኙ፡ ከሰማህ አጥብቀህ መርምር ።

ይህም ነገር እውነት ከሆነ በእስራኤል ዘንድ የሚያስጸይፍ (ርኩስ) ነው ፡ ያነን ሰው ከአገር አውጣው ፡ ሴትም ብትሆን ከአገር አውጣት ፡ በድንጋይ መትተውም ይግደሉዋቸው ።

የሚሞቱም ሰዎች በሁለት በሦስት ምስክር ይሙቱ ፡ በአንድ ምስክር ግን አይሙቱ ። ማቴ፡ ፲፰ ፲፯ ።

የነዚያ ምስክሮች እጆች አስቀድመው ይፈልሟቸው (ድንጋይ ይጣሉባቸው) ከነሱም በኋላ የሕዝቡ ሁሉ እጆች ይግደሉዋቸው ፡ እንዲህ አድርጋችሁ ከናንተ ክፉውን አጥፉ ። ዘዳ፡ ፲፫ ፱ ፡ ፲፫ ፭ ።

ደምን ለማንጻት ፡ በደምና በደም መካከል ያልበደለውንም ለማንጻት በንጹሕ መካከል ፡ በክርክርና በክርክር መካከል በአገሮችህ ለፍርድ የተሰነህ የፍርድ ነገር ቢኖር በዚያ ስሙ ይጠራበት ዘንድ ፈጣሪህ እግዚአብሔር ወደ መረጠው ቦታ ተነሥተህ ሂድ ። ዘፀ፡ ፳፩ ፲፫ ።

ወደ ሌዋውያንና ወደ ካህናቱ በዚያ ወራት ወዳሉ ወደ መኳንንቱም ሄደህ ጠይቅ ፡ ፍርዱን ይነግሩሃል ፡ እንደ ነገሩህም ቃል አድርግ ። ዘዳ፡ ፲፱ ፲፯ ።

በዚያ ስሙ ይጠራ ዘንድ ፈጣሪህ እግዚአብሔር በመረጠው ቦታ የተሾሙት እንደ ነገሩህ አድርግ፡ ያስተማሩህ ሕጉንም ታደርግ ዘንድ ሕጉን ሁሉ ጠብቅ ።

የነገሩህን ፍርዱን አድርግ፡ ከነገሩህም ቃል ወደ ቀኝም ወደ ግራም አትበል ። ሕገ፡ ፵፬ ፳፬ ።

፲፩ ወዘከቱ ብእሲ ዘይገብር ትዕቢተ ከመ ኢይትአዘዝ ለካህን ዘይቀውም ወይገብር በስሙ ለእግዚአብሔር አምላክከ አው ለመኰንን ዘሀሎ በውእቱ መዋዕል ፡ ለይሙት ውእቱ ብእሲ ፡ ወአሰስሉ እኩየ እም እስራኤል ።

በፈጣሪህ በእግዚአብሔር ስም ጸንቶ መሥዋዕትን ለሚሠዋ ካህን ወይም በዚያ ወራት ላለ ዳኛ እንዳይታዘዝ ትዕቢትን የሚያደርግ ያ ሰው ግን ይሙት ፡ እንዲህ አድር ጋችሁ ከእስራኤል ክፉውን አርቁ (አጥፉ) ።

፲፪ ወኵሉ ሕዝብ ሰሚዖ ይፍራህ ወኢይድግም እንከ አብሶ ።

እንግዲህ ዳግመኛ እንዳይበድል ሕዝቡ ሁሉ ሰምቶ ይፍራ ። ዘዳ፡ ፲፫ ፩ ።

፲፫ ወለእመ ቦእከ ውስተ ምድር ዘይሁበከ እግዚአብሔር አምላክከ መክፈልተከ ወተዋረስካሃ ወነበርከ ውስቴታ ወትቤ እሠይም ሊተ መልአከ ከመ ኵሉ አሕዛብ እለ ዐውድየ ።

ፈጣሪህ እግዚአብሔር ርስት አድርጎ ወደ ሚሰጥህ አገር ብትገባ ፡ ብትወርሳትም በርሷም ብትኖር በዙርያዬ እንዳሉ አሕዛብ ሁሉ አለቃን እሾማለሁ ብትል ።

፲፬ ወትሠይም ለከ መልአከ ዘኀረየ እግዚአብሔር አምላ ክከ ዘእምአኀዊከ ።

ከወንድሞችህ መካከል ፈጣሪህ እግዚአብሔር የመረ ጠውን አለቃ (ንጉሥ) ከወንድሞችህ ሹም (አንግሥ) ።

፲፭ ወኢትክል ሠይመ ለከ ብእሴ ነኪረ ዘኢኮነ እኁከ ከመ ኢያብዝኃ ሎቱ አፍራስ ወከመ ኢያግብአ ለሕዝብ ውስተ ግብጽ ፡ እስመ እግዚአብሔር ይቤ ኢትድግም እን ከ ገቢአታ ለይእቲ ፍኖት ።

እግዚአብሔር እንግዲህ ወደዚያች ጐዳና አትመለስ ብሏልና ለራሱ ፈረሶችን እንዳያበዛ ሕዝቡንም ወደ ግብጽ እንዳይመልሰው ወንድምህ ያልሆነ ባዕድ ሰው አትሹም ።

፲፮ ወኢያብዝኃ ሎቱ አንስተ ወኢይሚጥ ልቦ ወኢያብ ዝኃ ሎቱ ወርቀ ወብሩረ ጥቀ ።

ሚስቶችንም ለራሱ እንዳያበዛ ልቡንም እንዳይመልስ ለርሱም ወርቅና ብር እንዳያበዛ (አትሹም አታንግሥ) ።

፲፯ ወእበ ነበረ ውስተ ምኵናኑ ለይጽሐፍ ሎቱ ዘንተ ዳግመ ኦሪተ ውስተ መጽሐፍ እምኀበ ካህናት ሌዋውያን ።

በግዛቱም (በዙፋኑ) በተቀመጠ ጊዜ ከሌዋውያን ካህ ናት አንዱ ይህን ዳግም ሕግን በመጽሐፍ ይጻፍለት ።

፲፰ ወያነብሮ ኀቤሁ ወያንብብ ቦቱ በኵሉ መዋዕለ ሕይ ወቱ ከመ ይትመሀር ፍኖቶ ለእግዚአብሔር አምላኩ ወይ ዕቀብ ኵሎ ትእዛዞ ወይግበር ኵነኔሁ ።

ከጠገቡም ያኑረው ፡ የፈጣሪው የእግዚአብሔርን ሕግ ይማር ዘንድ ትእዛዙንም ሁሉ ይጠብቅ ዘንድ ፍርዱንም ያደርግ ዘንድ ። ዘዳ፡ ፱ ፲፡ ኢሳ፡ ፩ ፳ ።

፲፱ ከመ ኢያዕቢ ልቦ እምአኀዊሁ ወከመ ኢይኅድግ እምትእዛዙ ለእግዚአብሔር አምላኩ ወኢይትገኃሥ ኢ ለየማን ወኢ ለፀጋም ወከመ ያኑኅ መዋዕለ በውስተ ምኵ ናኑ ውእቱ ወውሉዱ ወአኃዊሁ በውስተ ደቂቀ እስራኤል።

ልቡናውን ከወንድሞቹ እንዳያኰራ የፈጣሪው የእግዚ አብሔርንም ትእዛዝ እንዳያፈርስ ወደ ቀኝም ወደ ግራም እንዳይል በግዛቱም ዘመኑን ያበዛ ዘንድ ልጆቹም ወንድ ሞቹም በእስራኤል መካከል ዘመናቸውን ያበዙ ዘንድ በሕይወት በኖሩበት ዘመን ሁሉ እሱን ያንብብ ።

## ምዕራፍ ፲፰ ።

፩ ወአልቦሙ መክፈልት ለካህናት ወሌዋውያን ወለኵሉ ሕዝበ ሌዊ ምስለ እስራኤል መብኣ ለእግዚአብሔር ክፍ ሎሙ ወኪያሁ ይሴሰዩ።

ለሌዋውያንና ለካህናት ለሌዊም ወገኖች ሁሉ ከእስራ ኤል ጋራ ፈንታ የላቸውም ፡ የእግዚአብሔር መባ ፈንታ ቸው ነውና እሱን ይመገቡ ። ዘኍ፡ ፲፰ ፳ - ፳፬ ።

፪ ወብሕቱ ክፍል አልቦሙ በውስተ አኀዊሆሙ እስመ እግዚአብሔር ውእቱ ክፍሎሙ በከመ ይቤሎሙ ።

ነገር ግን ፈንታቸው እኔ ነኝ እንዳላቸው እግዚአብ ሔር ፈንታቸው ነውና ፡ ከወንድሞቻቸው መካከል ፈንታ የላቸውም ።

፫ ወዝንቱ ውእቱ ሕጎሙ ለካህናት ዘእምኀበ ሕዝብ እለ ይጠብሑ ጥብሐ እመኒ ላሕመ ፡ ወእመኒ በግዐ ፡ ዘይሁብዎ ለካህን መዝራዕተ ፡ ወሕልቀ ፡ ወቈ/ ጤ ።

ፍርዱን በሚፈርዱ በሕዝቡ ዘንድ የካህናቱ ሥርዓት ይህ ነው ፡ በሬንም በግንም ቢያርዱ ለካህኑ ጕድኑንና ወርቹን ፡ ቈሽቱን ይስጡት ። ዘሌ፡ ፯ ፴ ፡ ፴፩ ፴፫ - ፴፬ ።

፬ ወቀዳሚ እክልከ ፡ ወቀዳሚ ወይንከ ፡ ወቀዳሚ ቅብ ዕከ ፡ አው እምዘቀረፅከ አባግዒከ ትሁቦ ።

ከእኽልህ የመጀመሪያውን ከወይንህ የመጀመሪያውን ከዘይትህም መጀመሪያ የሰቀምከውን ከሸለትካቸው ከበ ጎችህ ጠጕር የመጀመሪያውን ለካህኑ ስጠው ።

፭ እስመ ኀረዮ እግዚአብሔር አምላክ እም ኵሉ ሕዝብከ ከመ ይቁም ቅድሜሁ ወይትለአክ ወይባርክ በስሙ ዚአሁ ውእቱ ወደቂቁ በኵሉ መዋዕል ።

በፊቱ ይቆም ዘንድ ያገለግለውም ዘንድ እሱ ከልጆቹ ጋራ በዘመኑ ሁሉ ስሙን ያመሰግን ዘንድ ፈጣሪ እግዚ አብሔር መርጦታልና ። ዘፀ፡ ፳፱ ፳፱፡ ዘኍ፡ ፲፰ ፲፪ ።

፮ ወለእመ መጽአ ሌዋዊ እምውስተ አህጉሪከሙ ዘእም ኵሉ ደቂቀ እስራኤል ዘኀበ ይነብር ውእቱ እስመ ፈተወ በነፍሱ ከመ ይትለአክ በውእቱ መካን ኀበ ኀረየ እግዚአ ብሔር አምላክከ ።

ፈጣሪህ እግዚአብሔር በመረጠው ቦታ ያገለግል ዘንድ በልቡ ወዷልና አገልግሎቱን አበላልጦ እርሱ ከሚኖር ባቸው ከእስራኤል አገሮች ከንዱቱ ወጥቶ አንድ ሌዋዊ (ካህን) ቢመጣ ። ዘኍ፡ ፴፩ ፫ ።

፯ ወይትቀነይ ለስመ እግዚአብሔር አምላኩ ከመ ኵሉ አኀዊሁ ሌዋውያን እለ ይቀውሙ ህየ ቅድመ እግዚአብሔር ።

፰ ወይትከፈል መክፈልቶ ወይሴሰይ ዘእንበለ በሢመቱ ዘበሀገሩ ።

፱ ወለእመ በእከ ውስተ ምድር ዘይሁበከ እግዚአብሔር አምላክከ ፡ ኢትትመሀር ገቢረ ርኵሶሙ ለውእቶሙ አሕዛብ ።

፲ ወኢይትረከብ በውስቴትክሙ ዘይሠውዕ ወልዶ ፡ አው ወለቶ በእሳት ፡ ወዘያስተቃስም መቅስመ ፡ ወዘያስተሰግል ፡ ወዘይጤየር ፡ ወዘሥራይ ፡ ወዘሐረስ ፡ ወዘበጻውዕ ፡ ወዘያን ቅህ ምውተ ፡ ወዘያስተሰግል በዖፍ ።

፲፩ እስመ ርኩስ ውእቱ በኀበ እግዚአብሔር ኵሉ ዘይገብሮ ለዝንቱ ፡ እስመ በበይነ ዝንቱ ርኵሶሙ ያጠፍኦሙ እግዚአብሔር አምላክከ እምኔከ ።

፲፪ ወኩን ፍጹመ ቅድመ እግዚአብሔር አምላክከ ፡ እስመ እሉክቱ አሕዛብ ዘአንተ ትትዋረሶሙ እሙንቱ ያስተሰግሉ ወያጸምኡ መቅስመ ፡ ወለከሰ አኮ ከማሁ ።

፲፫ ነቢየ ወሀበከ እግዚአብሔር አምላክከ እምአኀዊከ ዘከማየ ፡ ወያነሥእ ለከ እግዚአብሔር አምላክከ ወሎቱ ስምዕዎ በኵሉ ።

፲፬ ወበኵሉ ዘሰአልክምዎ ለእግዚአብሔር አምላክክሙ በኮሬብ አመ ዕለተ ተጋባእክሙ ወትቤሉ ኢንደግም እንከ ሰሚዖተ ቃሉ ለእግዚአብሔር አምላክነ ፡ ወለዛቲኒ እሳት ዐባይ ኢንርአያ እንከ ከመ ኢንሙት ።

፲፭ ወይቤለኒ እግዚአብሔር አማን ኵሉ ዘይቤሉ ።

፲፮ ነቢየ አነሥእ ሎሙ እምአኀዊሆሙ ዘከማከ ወእነብር ቃልየ ውስተ አፉሁ ወይነግሮሙ ዘከመ አዘዝክዎ ።

፲፯ ወብእሲ ዘኢይሰምዖ ለውእቱ ነቢይ ኵሉ ዘ ነገረ በስመ ዚአየ አነ እትቤቀል እምኔሁ ።

፲፰ ወብሕቱ ነቢይ ዘይኤብስ ወይነብብ ቃለ በስምየ ዘኢአዘዝክዎ ይንብብ ፡ ወዘነበበሂ በስመ ባዕዳን አማልክት ለይሙት ውእቱ ነቢይ ።

፲፱ ወለእመሰ ትብል በልብከ እፎ አአምር ቃለ ዘኢይቤ እግዚአብሔር እምኵሉ ዘነበበ ነቢይ በስመ እግዚአብሔር እምከመ ኢበጽሐ ቃሉ ወኢኮነ በከመ ነበበ ፡ ኢነበቦ እግዚአብሔር ለውእቱ ቃል ወበሐሰት ነበበ ውእቱ ነቢይ ኢትስምዕዎ ።

ምዕራፍ ፲፱ ።

፩ ወለእመ አጥፍኦሙ እግዚአብሔር አምላክከ ለአሕዛብ ዘይሁበከ ምድሮሙ ወወረስኮሙ ወነበርከ ውስተ ምድሮሙ ወውስተ አህጉሪሆሙ ወውስተ አብያቲሆሙ ሠላሰ አህጉረ ትፈልጥ ለከ በማእከለ ምድርከ ዘወሀበከ እግዚአብሔር አምላክከ ።

፪ ወትአምር ለሊከ ፍኖቶን ወትከፍል ደወለ ምድርከ መሥልስተ ዘአስተከፈለከ እግዚአብሔር አምላክከ ፡ ወይኩን ህየ ምስካዩ ለኵሉ ቀታሊ ።

በእግዚአብሔር ፊት በዚያ እንደሚቆሙ እንደ ወንድሞቹ ሌዋውያን ሁሉ ለፈጣሪው ለእግዚአብሔር ስም ይገዛ ያገለግል ። ዘዳ፥ ፲፯ ፲፪ ፡ ፩ ዜና መ፥ ፳፫ ፯ ።

በአገሩ ካለ ከሹመቱ ገንዘብ በቀር ፈንታውን ተካፍሎ ይመገብ ፤ ፪ ዜና መ፥ ፴፩ ፬ ።

ፈጣሪህ እግዚአብሔር ወደሚሰጥህ አገር የገባህ እንደሆነ የነዚያን አሕዛብ ኃጢአት አትሥራ ፡ (ርኵሰታቸውን አትማር) ። ዘሌ፥ ፲፰ ፳፯ ፡ ዘዳ ፲፪ ፳፱ ።

ወንድ ልጁን ወይም ሴት ልጁን በእሳት የሚሠዋ ሟርትን የሚያሟርት የሚያስጠነቍል ጣኦትን የሚያስመልክ ሥርማሽ ቅጠል በጣሽ ምትሐተኛ ሙት አስነሣለሁ ባይ በወፍ የሚያሟርት በናንተ ዘንድ አይገኝ (አይኑር) ።

ይህን የሚያደርገው ሰው ሁሉ በእግዚአብሔር የተጠላ ነው ፡ ፈጣሪህ እግዚአብሔር ስለዚሁ ኃጢአታቸው ከንተ ለይቶ የሚያጠፋቸው ስለሆነ (ያጠፋቸዋል እኮ) ።

በፈጣሪህ በእግዚአብሔርም ዘንድ ፍጹም ኹን አንተ የምትወርሳቸው እነዚያ አሕዛብ ሟርትን ያሟርታሉና ያስጠነቍላሉና ላንተ ግን እንደዚህ ማድረግ አይገባህም ።

ፈጣሪህ እግዚአብሔር ከወንድሞችህ ለይቶ እንደኔ ያለ ነቢይ (አ ያሱን) ይሰጥኻል ፈጣሪህ እግዚአብሔር ያስነሣልኻል በሁሉም ዘንድ እሱን ስሙት ። ዘኍ፥ ፲፯ ፩ ።

በኮሬብ በተሰበሰባችሁ ጊዜ ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔርን በለመናችሁት ሁሉ የፈጣሪያችን የእግዚአብሔርን ቃል ዳግመኛ አንሰማ ፥ ያችንም የጠናች መቅሠፍት እንዳንሞት አንያት አላችሁ ። ዘፀ፥ ፳ ፲፱ ፡ ዘዳ፥ ፱ ፲ ።

እግዚአብሔርም የተናገሩት ሁሉ እውነት ነው አለኝ ።

ከወንድሞቻቸው እንዳንተ ያለ ነቢይ አስነሣላቸዋለሁ ፡ ቃሌንም በአንደበቱ እንዲያስተምር አደርገዋለሁ ፡ ያዘዝኩትንም ያስተምራቸዋል ። ዮሐ፥ ፩ ፵፭ ።

ይህን ሁሉ ነገር በስሜ የተናገረ ያነን ነቢይ (መምር) የማይሰማውን ሰው እኔ ተበቅዬ አጠፋዋለሁ ።

ነገር ግን ይናገር ዘንድ ያላዘዝኩትን ቃል በስሜ የሚናገር ፡ በጣኦታም ስም የሚናገር ያ ነቢይ ይሙት ። ግብ፥ ሐዋ፥ ፫ ፳፫ ።

በልብህ እግዚአብሔር ያልተናገረውን ቃል እንደምን አውቃለሁ ብትል ግን በእግዚአብሔር ስም ነቢዩ ከተናገረው ነገር ሁሉ ቃሉ ካልደረሰ ፡ እንደ ተናገረውም ካልሆነ ይህ ቃል እግዚአብሔር ያልተናገረው ነው ፡ ያ ነቢይ ሐሰተኛ ነው ፡ አትስሙት ። ዘዳ፥ ፲፰ ፳ ፡ ፲፫ ፫ ።

ምዕራፍ ፲፱ ።

አገራቸው የሚሰጥህ አሕዛብን ፈጣሪህ እግዚአብሔር በጠፋቸው በወረስኻቸውም ጊዜ ፡ በምድራቸው በቤቶቻቸውም በኖርክ ፈጣሪህ እግዚአብሔር በሰጠህ አገር መከከል ላንተ ሦስት ሀገረ ምስካዩን ለይ (መማጠኛዎች) ።

ነፍስ የገደሉ ይሸሹባቸው ዘንድ አንተ ጐዳናቸውን ታውቃለህ ፈጣሪህ እግዚአብሔር ያከፈለህ የአገርህን እውራጅ ሦስት አድርገህ ክፈል ፡ ነፍስ የገደለ መጠጊያው መሸሻው በዚያ ይሁን ።

፫ ወዝንቱ ውእቱ ሕጉ ለቀታሊ እምከመ ሰከየ ህየ ይሕየው ፤ ለእመ በኢያእምሮ ቀተሎ ለካልኡ ወለእመ ኢኮነ ጸላኢሁ ቀዲሙ ።

ነፍሰ ገዳይ ፍርዱ ይህ ነው ፤ በዚያ ከተማጠነ ይዳን በልንጀራውን በለማወቅ ከገደለው ተድሞ ጥንተ ጠላቱ ካልሆነ በዚያ ተማጥኖ ይዳን ። ዘዳ ፬ ፵፩ ፡ ፲፱ ፰ ።

፬ ወለእመቦ ዘሖረ ምስለ ካልኡ ሐቅለ ይሕጥብ ዕፀ ፡ ወወድቀ እምእዴሁ ጕድብ እንዘ ይገዝም ዕፀ ፡ ወወድቀ ሐጺን እምዕፁ ወወፈደ ላዕለ ካልኡ ወቀተሎ ይስከ ውእቱ ውስተ አሐቲ እምእላንቱ አህጉር ወየሐዩ ።

ዕንጨት ይለቅም ዘንድ ከባልንጀራው ጋራ ወደ ዱር ፫ ቢሄድ የሄደ ሰውም ቢኖር ዕንጨት ሊቈርጥ ገጀሞ ወድቆ ምሳሩም ከዛብያው ወልቆ በልንጀራውን መትቶ ቢገድለው እርሱ ከነዚያ አገሮች በአንዲቱ ተማጥኖ ይዳን ።

፭ ከመ ኢይዴግኖ አበ ደም ወኢይቅትሎ ለቀታሊ እስመ ተቀየሞ በልቡ ወይረክቦ ለእመ ርኍቀ ፍኖት ወይቀትሎ እንዘ ኢኮነ አበሳሁ ለሞት እስመ ኢኮነ ጸላኢሁ ለምዕት ቀዲሙ ።

ለሚቹ ጥንተ ጠላቱ ስላልሆነ፤ በቂም አልገደለውምና፤ መንገድ ቢርቀው ለሞት የሚያበቃ ኃጢአት ሳይኖርበት አግኝቶ ይገድለዋልና ተከትሎ ባለ ደመ ነፍሰ ገዳዩን እንዳይገድለው በአንዲቱ መማጠኛ ይማጠን ።

፮ ወበበይነ ዝንቱ አዘዝኩከ እንተ ትግበር ዘንተ ነገረ ፡ ወእቤለከ ሠላሰ አህጉረ ፍልጥ ለከ ።

ይህንን ነገር ታደርግ ዘንድ እኔ ስለዚህ ነገር አዘዝኩህ ሶስት ሦስት መማጠኛችን ለይ አልኩህ ።

፯ ወለእመ አርኀበ ለከ እግዚአብሔር ደወለከ በከመ መሐለ ለአበዊከ ወወሀበከ ኵሎ ምድረ ዘይቤ እሁበሙ ለአኀዊከ ።

እግዚአብሔር ላባቶችህ እንደማለ አውራጃህን ከሰፋልህ ለአባቶችህ እሰጣቸዋለሁ ያለውንም አገር ሁሉ ከሰጠህ ።

፰ ወለእመ ሰማዕከ ከመ ትግበር ዘንተ ኵሎ ትእዛዘ ዘአነ እኤዝዘከ ዮም ከመ ታፍቅሮ ለእግዚአብሔር አምላክከ ወከመ ትሖር በኵሉ ፍናዊሁ በኵሉ መዋዕል ፡ ወትዌስክ ለከ ዓዲ ሠላሰ አህጉረ ላዕለ እልክቱ ሠላስ ።

ፈጣሪህ እግዚአብሔርን ትወደው ዘንድ በዘመኑ ሁሉ በሕጉ ጸንተህ ትኖር ዘንድ እኔ አሁን የማዝህን ይህን ሁሉ ትእዛዝ ልታደርግ ከሰማህ በነዚያ በሦስት መማጠኛ ላይ ዳግመኛ ሦስት መማጠኛን ጨምር ። ዘዳ፣ ፲፱ ፪ ።

፱ ወኢይትክዐው ደም ንጹሕ ውስተ ምድር ዘወሀበከ እግዚአብሔር አምላክከ መክፈልተከ ወኢየሀሉ ውስቴትከ ቀታሌ ነፍስ ።

ፈጣሪህ እግዚአብሔር ርስት ፈንታ አድርጎ በሰጠህ አገር ላይ ንጹሕ ደም አይፍሰስ ነፍሰ ገዳይም በንተ ዘንድ አይኑር ። ዘኍ፣ ፴፭ ፲፯ - ፴፩ ።

፲ ወለእመቦ ብእሲ ዘይጸልእ ለካልኡ ወይጸንሖ ፡ ወእምዝ ተንሥአ ላዕሌሁ ወቀተሎ ወሰከየ ውስተ አሐቲ እምእላንቱ አህጉር ይፈንዉ ሊቃናተ ሀገሩ ወያመጽእዎ እምህየ ወይሜጥውዎ ኪያሁ ለአበ ደም ወይቀትሎ ።

በልንጀራውን የሚጠላው የሚሸምቅበትም ቢኖር ፤ ከዚህ በኋላ በጠላትነት ተነሥቶ ቢገድለው ከነዚያ መማጠኛ አገሮች በአንዲቱ ቢማጠን ፤ የአገሩ አለቆች ልከው ከዚያ አስወጥተው እሱን ለባለ ደም ይስጡት ይግደለው።

፲፩ ወበይንከ ኢትምሐኮ ወታንጽሕ ደመ ንጹሐ እምእስራኤል ወትከውን ሠናይት ላዕሌከ ።

ዓይንህም አትራራለት እንደዚህ አያደረግህ ከእስራኤል ንጹሕ ደምን አንጻ ላንተም በጎ ነገር ትደረግልሃለች።

፲፪ ወኢትትኀለፍ ደወለ ቢጽከ ዘሠርዑ አበዊከ በውስተ ርስትከ ዘተዋረስከ ዘወሀበከ እግዚአብሔር አምላክከ መክፈልተከ ።

ፈጣሪህ እግዚአብሔር ፈንታ አድርጎ ሰጥቶህ በወረስከት አገር አባቶችህ የሠሩትን የባልንጀራህን ድንበር አታፍርስ ። ዘዳ፣ ፳፯ ፲፯ ፣ ኢዮ፣ ፳፬ ፪ ።

፲፫ ወኢይክውን አሐዱ ሰማዕት ከመ ይኩን ስምዐ ላዕለ ሰብእ በኵሉ ጌጋይ ወበኵሉ አበሳ ዘአበሰ ፡ በአፈ ክልኤቱ ወሠለስቱ ሰማዕት የኀልቅ ኵሉ ነገር ።

በበደሉት በደል ሁሉ በሰዎች አንድ ምስክር አይሁን (አይቁም) ፤ ነገሩ ሁሉ በሁለት በሦስት ምስክር ይለቅ ። ማቴ፣ ፲፰ ፲፯ ፤ ፩ ጢሞ፣ ፭ ፲፱ ።

፲፬ ወለእመ አምጽኡ ሎቱ ለሰብእ ሰማዕተ በዓመፃ ወነበበ ላዕሌሁ ሐሰተ ፤ ይቀውሙ እልክቱ ክልኤቱ እደው እለ ይትኋሥሡ ቅድመ እግዚአብሔር ወቅድመ ካህናት ወቅመኳንንት እለ ሀ ወ. በውእቱ መዋዕል ወየሐትቱ መኳንንት ወይጤይቁ ።

በሰው ሐሰተኛ ምስክር በግፍ ሲያመጡበትና ሐሰት ቢመሰክሩበት በእግዚአብሔርና በካህናት ፊት በዚያ ወራት ባሉ በመኳንንትም ፊት የሚመራመሩ እነዚያ ሁለቱ ምስክሮች ይቆማሉ (ይቁሙ) ፤ ዳኞች እነዚያም ሁለት ምስክሮች መርምረው ነገሩን ይረዱ ።

፲፭ ወእልክቱ ክልኤቱ ሰማዕት ወለዝክቱኒ አሐዱ ዐማፂ ዘኮነ ስምዐ በሐሰት ወቆመ ላዕለ ካልኡ ይግበርዎ ዘከመ ፈቀደ ይግበር እኪተ ላዕለ ካልኡ ወታሴስሎ እኩየ እምኔክሙ ።

በባልንጀራው ላይ በሐሰት የመሰከረበትን ያንን አንዱን ሙጃ ሐሰተኛ ምስክርም ይመርምሩት ፤ በባልንጀራው ላይ ክፉ ነገር ሊያደርግበት እንደ ወደደ እንደሱ ያድርጉት ፤ እንዲህ እያደረጋችሁ ከናንተ ክፉውን አጥፉ ።

፲፮ ወባዕድኒ ሰሚዖ ይፍራህ ወኢይድግም እንከ ገቢረ ዘንተ ነገረ እኩየ በውስቴትክሙ ።

በናንተ ዘንድ ዳግመኛ ይህንን ክፉ ነገር እንዳያደርግ ሌላው ሰምቶ ይፍራ (ይቀጣ) ፤ ዓይንህም አትራራለት ።

፲፯ ወዐይንከ ኢትምሐኮ ፤ ነፍስ ህየንተ ነፍስ ፤ ወዐይን ህየንተ ዐይን ፤ ወስን ህየንተ ስን ፤ ወእድ ህየንተ እድ ፤ ወእግር ህየንተ እግር ።

ነፍስን ስለ ገደለ ነፍሱ ይሙት ፤ ዓይን ስላጠፋ ዓይኑ ይጥፉ ፤ ጥርስ ስለ ሰበረ ጥርሱ ይሰበር ፤ እጅ ስለ ቈረጠ እጁ ይቈረጥ ፤ እግር ስለ ሰበረ እግሩ ይሰበር ።

## ምዕራፍ ፳ ።

፩ ወለእመ ወፃእከ ፀብአ ላዕለ ፀርከ ወርኢከ አፍራሰ ወመስተጽዕናነ ወሕዝበ ዘይበዝኀከ ኢትፍራህ እምኔሆሙ እስመ እግዚአብሔር አምላክከ ዘአውፅአከ እምድረ ግብፅ ምስሌከ ውእቱ ።

ጠላትህን ለማጥፋት ወደ ሰልፍ ብትወጣ በፈረሶች ላይ የተቀመጡ ሰዎችንና ፈረሶችን አይተህ የሚበዛብህን ወገን ብታይ ከግብጽ ምድር ያወጣህ ፈጣሪህ እግዚአብሔር ከንተ ጋር አለና ከነሳቸው የተነሣ አትፍራ ።

፪ ወሶበ አኀዝከ ትትቃተል ይምጻእ ካህን ወይንግር ለሕዝብ ወይበሎሙ ፡ ስማዕ እስራኤል ናሁ ተሐውሩ አንትሙ ዮም ከመ ትቅትሉ ፀረክሙ ፡ ወኢይደንግፅክሙ ልብክሙ ወኢትፍርሁ ፡ ወኢትመምዑ ወኢትትገኀሡ እምቅድመ ገጾሙ ።

ልትዋጋ በጀመርክ ጊዜ ካህን መጥቶ ለሕዝቡ እስራኤል ሆይ ስማ! ጠላቶቻችሁን ታጠፉ ዘንድ እነሆ እናንተ አሁን ትሄዳላችሁ ፡ ነገር ግን ልቡናችሁ አይደንግጥባችሁ አትፍሩ አትሸበሩም ከፊታቸውም አትሸሽ ብሎ ይንገራቸው ።

፫ እስመ እግዚአብሔር አምላክክሙ የሐውር ፍጽመክሙ ከመ ይቅትል ፀረክሙ ወለክሙሰ ያድኅንክሙ ።

ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር ጠላቶቻችሁን ያጠፋላችሁ ዘንድ ፊታውራሪ ሁኖ ይሄድላችኋልና እናንተን ግን ያድናችኋል ። ዘዳ፥ ፳ ፰፥ ኢያ፥ ፵ ፳፫ ።

፬ ወይብልዎሙ ጸሐፍትኒ ለሕዝብ ለእመቦ ብእሲ ዘነደቀ ቤተ ሐዲሰ ወኢገብረ መድቅሐ ቤቱ ለይሑር ወይግባእ ውስተ ቤቱ ከመ ኢይሙት በውስተ ቀትል ፡ ወካልእ ብእሲ ኢይግበር መድቀሐ ቤቱ ።

ሹማምንቱም ሕዝቡን እንዲህ ይበሉዋቸው ፡ አዲስ ቤት ሠርቶ የቤቱን መመረቂያ ያላደረገ ሰው ቢኖር በሰልፍ እንዳይሞት ሌላም ሰው የቤቱን መመረቂያ እንዳያደርግበት ተመልሶ ወደ ቤቱ ይሂድ ይበሉዋቸው ።

፭ ወለእመቦ ብእሲ ዘተከለ ዐፀደ ወይን ወኢተፈሥሐ ቦቱ ለይሑር ወይግባእ ውስተ ቤቱ ከመ ኢይሙት በውስተ ቀትል ወካልእ ብእሲ ኢይትፈሣሕ ቦቱ ።

የወይንም ሐረግ ተክሎ በሱ ደስ ያላለው ሰው ቢኖር በሰልፍ ሙቶ ሌላ ሰው ደስ እንዳይልበት ተመልሶ ወደ ቤቱ ይግባ ። ዘዳ፥ ፳፰ ፴ ።

፮ ወለእመቦ ብእሲ ዘፈኀረ ብእሲተ ወኢነሥአ ለይሑር ወይግባእ ውስተ ቤቱ ከመ ኢይሙት በውስተ ቀትል ወካልእ ብእሲ ኢይንሥኣ ።

አጭቶ ሚስት ያላገባ ሰው ቢኖር በሰልፍ እንዳይሞት ሌላም ሰው እንዳያገባት ተመልሶ ወደ ቤቱ ይሂድ ።

፯ ወይድግሙ ብሂሎቶሙ ጸሐፍት ለሕዝብ ለእመቦ ብእሲ ፈራህ ለይግባእ ውስተ ቤቱ ከመ ኢያፍርህ ልበ ቢጹ ከማሁ ።

አለቆችም ደግመው ሕዝቡን እንዲህ ይበሉዋቸው ፡ ፈሪ ሰው ቢኖር የባልንጀራውን ልቡና እንደሱ እንዳያስፈራ ተመልሶ ወደ ቤቱ ይሂድ ። ዘዳ፥ ፩ ፳፰ ።

፰ ወሶበ አኅለቁ ነጊሮቶሙ ጸሐፍት ለሕዝብ ይሚሙ መላእክተ ሠራዊት እምዐበይተ ሕዝብ ።

ሹማምንቱ ለሕዝቡ ነግረው ከጨረሱ በኋላ ከሕዝቡ ታላላቆች የሠራዊት አለቃን ይሹሙ ።

፱ ወሶበ ትቀርብ ውስተ ሀገር ከመ ተትቃተል ፡ ትጼውዖሙ በቃለ ሰላም ።

ለመዋጋት ወደ አገር በቀረብክ ጊዜ አስቀድመህ በፍቅር ቃል ጥራቸው ። ፪ ሳሙ፥ ፳ ፲፰-፳ ።

፲ ወለእመ አውሥኡከ በቃለ ሰላም ወአርኀዉ ለከ ይኩኑከ ኵሉ ሕዝብ እለ ተረክቡ ውስቴታ እለ ያገብኡ ለከ ጸባሕተ ወምተናኒከኒ ይኩኑከ ።

የፍቅር ቃል ቢመልሱልህ በሩንም ቢከፍቱልህ በዚያ የተገኙ ወገኖች ሁሉ የሚገዙልህና ግብርም የሚያገቡልህ ይሁኑ ።

፲፩ ወለእመሰ ኢያውሥኡከ ሰላመ ወገብሩ ፀብአ ምስሌከ ትነብር ላዕሌሃ ወያገብኣ እግዚአብሔር አምላክከ ውስተ እዴከ ።

የፍቅር ቃል በይመልሱልህ ከንተም ጋር ፀብ ቢያደርጉ ግን በርሷ ላይ ተቀመጥ ፈጣሪህ እግዚአብሔርም ጠላትህን በእጅህ ይጥለዋል ።

፲፪ ወትቀትል ኵሎ ተባዕቶ በቀትለ ሐፂን ዘእንበለ አንስት ወንዋይ ።

ከንዝና ከሴቶችም በቀር ወንድ ወንዱን በጦር ግደል።

፲፫ ወኵሉ እንስሳ ወኵሉ ዘሀለወ ውስተ ሀገር ወኵሉ ጥሪቶሙ ትበረብር ለከ ፡ ወብላዕ ኵሉ በርበረ ፀርከ ዘወሀበከ እግዚአብሔር አምላክከ ።

ከብቱን ሁሉ በአገርም ያለውን ሁሉ ገንዘባቸውንም ሁሉ ላንተ ዝረፍ ፈጣሪህ እግዚአብሔር የሰጠህ የጠላትህን ገንዘብ ሁሉ ዘርፈህ ብላ ። ኢያ፥ ፰ ፪፥ ፳፪ ፰ ።

፲፬ ወከመዝ ትገብር ኵሎ አህጉረ እለ ጥቀ ርኁቃን እምኔከ ዘኢኮኑ እምአህጉሪሆሙ ለእሉ አሕዛብ ዘይሁበከ እግዚአብሔር አምላክከ ምድሮሙ ከመ ትትዋረስ ።

ትወርስ ዘንድ ፈጣሪህ እግዚአብሔር አገራቸውን ከሚሰጥህ ከነዚህ አሕዛብ አገሮች ያልሆኑ ከንተ ፈጽመው የራቁ አገሮችን ሁሉ እንዲህ አድርግ ። ዘዳ፥ ፯ ፩ ።

፲፭ ወኢታሕዩ ኵሎ ዘነፍስ አላ መርገመ ተረግሞሙ ለኬጤዎን ወለአሞሬዎን ወለከናኔዎን ወለፌርዜዎን ወለኤዌዎን ወለኢያቡሴዎን ወለጌርጌሴዎን በከመ አዘዘከ እግዚአብሔር አምላክከ ።

ፈጣሪህ እግዚአብሔር እንዳዘዘህ ፡ ኬጢዎንን አሞሬዎንን ፡ ፌርዜዎንን ፡ ከናኔዎንን ኢያቡሴዎንን ኤዌዎንንና ጌርጌሴዎንን ፡ መርገምን ረግመህ አጥፋቸው እንጂ ሰውን ሁሉ አታድን ።

፲፯ ከመ ኢይምሀሩከ ገቢረ ኵሉ ርኵሶሙ ወኵሉ ዘይገብሩ ለአማልክቲሆሙ ወትኤግዩ ቅድመ እግዚአብሔር አምላክክሙ ።

ኃጢአታቸውን ሁሉ መሥራትንና ለጣኦቶቻቸው እንደሚያደርጉት ሁሉ እንዳያስተምሩህ በፈጣሪያችሁ በእግዚአብሔርም ፊት እንዳትበድሉ ረግመህ አጥፋቸው ።

፲፰ ወለእመ ነበርከ ውስተ ሀገር ብዙኀ መዋዕለ ከመ ትትቃተላ ወከመ ትንሥኣ ኢትማስኖ ኣማ ወኢታውርድ ሐፂን ላዕሌሁ አላ እምኔሁ ብላዕ፣ በኑ ሰብእ ውእቱ አመ ገዳም ከመ ይምጻእ ቅድሜከ ወይበእ ውስተ ቅጽርከ ።

አጥፍተህ እጅ ታደርጋት ዘንድ በአገሬቱ ብዙ ቀን ብትኖርም ከፍሬዋ ብላ እንጂ በምሳር ዛፍዋን አትቍረጥ ወዳንተ ይመጣ ዘንድ ወደ ቅጽርህም ይገባ ዘንድ የምድረ በዳው ዕንጨት በውኑ ሰው ነውን ። ኢያ፣ ፳፱ ፲፱ ።

፲፱ ወበሕቱ ዕፀ ዘተአምር ከመ ኢይፈሪ ኪያሁ ትገዝም ወትመትር ወትነድቅ ሐፁረ ላዕለ ይእቲ ሀገር እንተ ትገብር ፀብአ ምስሌከ እስከ ታስተጋብአ ።

ነገር ግን እንዳያፈራ የምታውቀውን ዕንጨት ቍረጥ እጅ እስክታደርጋትም ድረስ ከንተ ጋር ፀብ በምታደርግ በዚያች አገር አጥር አጠር ። ኢሳ፣ ፳፱ ፫ ።

## ምዕራፍ ፳፩ ።

፩ ወለእመ ተረክበ ቅቱል ውዱቀ ውስተ ገዳም በውስተ ምድር ዘይሁበከ እግዚአብሔር አምላክከ ትትዋረሳ፣ ወኢያእመሩ ቀታሊሁ፣ ይወጽኡ ሊቃናቲክሙ ወመኳንንቲክሙ ወይሜጥኑ አህጉረ ዘዓውዱ ለውእቱ ቅቱል ።

ትወርሳት ዘንድ ፈጣሪህ እግዚአብሔር በሰጠህ አገር የሞተ ሰው በምድረ በዳ ወድቆ ቢገኝ ገዳዩንም ባያውቁት፣ ሹማምንቶቻችሁና አለቆቻችሁ ወጥተው ለተገደለው ሰው ቅርብ የምትሆን ያች አገርና በዚያ በሞተው ሰው አገር ዙርያ ያሉ አገሮችን ይለኩ ።

፪ ወሀገር እንተ ቅርብት ይእቲ መንገሌሁ ለውእቱ ቅቱል አእሩጊሃ ለይእቲ ሀገር ያመጽኡ እጐልተ እምአልሕምት እንተ ኢተቀንየት ወእንተ ኢሰሐበት አርዑተ ።

ለዚያ ለተገደለው አቅራቢያ የሆነች የዚያች አገር ሽማግሌዎች ያልቀናች ቀንበርንም ያልተሸከመች ጊደርን ከከብቶች ያምጡ ።

፫ ወያወርድዋ አእሩጊሃ ለይእቲ ሀገር ለይእቲ እጐልት ውስተ ቈላ መብአስ ዘኢተሐርሰ ወዘኢተዘርአ ውስቴቱ ወይመትሩ ሥረዊሃ ለይእቲ እጐልት በውስተ ቈላ ።

የዚያች አገር ሽማግሎች ያችን ጊደር ወዳልታረሰ ዘርም ወዳልተዘራ ጐጣጐጥ ወደ ሆነ በረኻ አውርደው የዚያች ጊደር ቋንጃዋን በበረኻ ይቍረጡት ።

፬ ወይመጽኡ ካህናት ወሌዋውያን እስመ ኪያሆሙ ኀረየ እግዚአብሔር ይቁሙ ቅድሜሁ ወይባርኩ በስመ ዚአሁ፣ ወበቃለ ዚአሆሙ ይቀውም ኵሉ ተስናን ወኵሉ ዘይትኃደግ ።

በፊቱ ይቆሙ ዘንድ ስሙንም ያመሰግኑ ዘንድ እግዚአብሔር እነሱቸውን መርጧልና ፍርዱ ሁሉ የሚቀረውም ሁሉ ነገር በነሱ ቃል ይፈረዳልና ሌዋውያንና ካህናት ይምጡ ። ዘዳ፣ ፲ ፰ ፣ ፩ ዜና መዋ፣ ፳፫ ፲፫ ።

፭ ወኵሉ አእሩጊሃ ለይእቲ ሀገር እንተ ቅርብት መንገሌሁ ለውእቱ ቅቱል ይትሐፀቡ እደዊሆሙ ላዕለ ርእሳ ለይእቲ እጐልት ዘመተሩ ሥረዊሃ በውስተ ቈላ ።

በዚያ በሞተው ሰው ዘንድ አቅራቢያ የምትሆን የዚያች አገር ሽማግሎች ሁሉ በበረኻ ቋንጃዋን በቈረጡት በዚያች ጊደር ራስ ላይ እጃቸውን ይታጠቡ ።

፮ ወይነብቡ ወይብሉ ኢከዐዋ እደዊነ ደሞ ለዝንቱ ወአዕይንቲነ ኢርእያ ።

የዚህን ሰው ደም እጆቻችን አላፈሰሱም ዓይኖቻችንም አላዩም ብለው ይናገሩ ። ማቴ፣ ፳፯ ፳፬ ።

፯ ወሥረይ ለሕዝብከ እስራኤል እግዚኦ ዘቤዘውክሆሙ እምድረ ግብጽ ከመ ኢይኩን ጌጋየ ነፍስ ላዕለ ሕዝብከ እስራኤል፣ ወይሠረ ሎሙ በእንተ ውእቱ ነፍስ ።

የዚህ ነፍስ ፍዳ በወገኖችህ እስራኤል ላይ እንዳይሆን አቤቱ ከግብጽ አገር ያወጣኻቸው ወገኖችህ እስራኤልን ይቅር በላቸው ይበሉ፣ ስለዚህም ነፍስ ይቅር ይላቸዋል ።

፰ ወአንተሰ አሰስል ጌጋየ ነፍስ እምላዕሌከ ወትከውን ሠናይተ ላዕሌከ ለእመ ገበርከ ዘሠናይ ወዘአዳም ቅድመ እግዚአብሔር አምላክከ ።

አንተ ግን የዚያን ሰው ፍዳ እንዲህ አድርገህ ከንተ አርቅ (አቃልል) በፈጣሪህ በእግዚአብሔር ፊት ያማረውንና የተወደደውን ብታደርግ ላንተም በን ነገር ትደረግልኻለች ። ዘዳ፣ ፲፬ ፲፫ ።

፱ ወለእመኒ ወፃእከ ፀብአ ላዕለ ፀርከ ወአግብኦሙ እግዚአብሔር አምላክከ ውስተ እዴከ ወፄወውከ ፄዋሆሙ ።

ጠላቶችህን ለመውጋት ወደ ሰልፍ ብትወጣ ፈጣሪህ እግዚአብሔርም ጠላቶችህን በእጅህ ቢጥላቸው ምርኮአቸውንም ብትማርክ ።

፲ ወርኢከ በውስተ ፄዋ ብእሲተ እንተ ሠናይ ርእየታ ወፈተውካሃ ወነሣእካሃ ለከ ትኩንከ ብእሲተ ።

በምርኮኞችም መካከል የተዋበች ሴት ብታይ ብትወዳትም (ብትመኛት) ላንተም ሚስት ልትሆን ብታገባት ።

፲፩ ወታበውኣ ውስተ ጽርሐ ቤትከ ወትላጽያ ርእሳ ወትፀፍራ ወታሴስል አልባሲሃ ዘበቱ ተፄወወት፣ ወታነብራ ውስተ ቤትከ ወትበኪ ለአቡሃ ወለእማ ሠላሰ መዋዕለ ።

ወደ እልፍኝህ አግብተህ ራሷን ላጭት ጽፍሯንም ቍረጣት የተማረከችበት ልብሷንም አውልቀህ በቤትህ አስቀምጣት፣ ለናቷና ለአባቷም ሠላሳ ቀን ታልቅስ ።

፲፪ ወእምድኅረ ዝንቱ ትበውእ ኀቤሃ ወትነብር ምስሌሃ ወትከውንከ ብእሲተ ።

ከዚህ በኋላ ድረስባት ከሷም ጋር ኑር፣ ሚስት ትሁንህ ። ዘዳ፣ ፳፫ ፱ ።

፲፫ ወእምዝ ለእመ ኢፈቀድካሃ ትፈንዋ እግእዚተ ወሠ ይጠሰ ኢትሠይጣ በወርቅ ወኢትክሕዳ ከመ አውሰብካሃ ።

ከዚህ በኋላ ባትወዳት ግን ነፃ አውጥተህ ስደዳት ፣ ነገር ግን በወርቅ አትሽጣት እንዳገባኻትም አትክዳት ።

፲፬ ወለእምኒ አውሰበ ብእሲ ክልኤ አንስተ ለአሐቲ ይጸልኣ ወለአሐቲ ያፈቅራ ወወለደት ሎቱ ወልደ በኵር እንተ ይጸልኣ ።

አንድ ሰው ሁለት ሚስቶች አግብቶ አንዷን ጠልቶ አንዷን ቢወድ የጠላትም የበኵር ልጅ ብትወልድለት ።

፲፭ እመ ያስተዋርሰሙ ንዋዮ ለደቂቁ ኢይክል አዕብዮቶ ለወልዳ ለእንተ ያፈቅራ ፣ ወተዐውሮቶ ለወልዳ ለእንተ ይጸልኣ ።

ለልጆቹ ገንዘቡን በሚያወርሳቸው ጊዜ የሚወዳት የሚስቱን ልጅ አለቃ ማድረግ አይችልም ፣ የሚጠላት የሚስቱን ልጅም ቸል ማለቱን (ማሳነሱን) አይችልም ።

፲፮ ወይሁብ ምክዕቢተ እምኵሉ ዘተረክበ ሎቱ እስመ ውእቱ ቀዳሚ ውሉዱ ወሎቱ ይሬሲ ዘበኵሩ ።

የልጆቹ አለቃ ነውና የተገኘ ገንዘቡን ሁሉ ዕጥፍ አድርጎ ለሱ ይስጠው ፣ ያለቅነቱንም ገንዘብ ለርሱ ያድርግለት ።

፲፯ ወለእመበ ዘቦቱ ወልድ ከሓዲ ወዝኁር ወኢይትኤዘዝ ለቃለ አቡሁ ወለቃለ እሙ ፣ ወይጌሥጽዎ ወኢይሰምዖሙ ይስድዎ ኀበ ሊቃናተ ሀገሩ ወውስተ አንቀጸ ብሔሩ ።

አሉተኛ ፣ ትዕቢተኛ ፣ ለናቱና ለአባቱ የማይታዘዝ ቢመክሩትም የማይሰማቸው ልጅ ቢኖር ፣ ወደ አገሩ አለቆች ወደ አገሩ አደባባይ ይውሰዱት ።

፲፰ ወይበልዎሙ ለሰብአ ሀገሮሙ ዝንቱ ወልድነ ይክሕደነ ወያዐቢ ርእሶ ወኢይሰምዕ ቃለነ ወይዜግር ወይሰክር ።

ወስደው ለአገራቸው ሰዎች ይህ ልጃችን አሉ ይሉናል ራሱንም ያኰራል ቃላችንን አይሰማም ፣ ይዘልላል ይሰክራልም ይበሉዋቸው ። ምሳ፣ ፳፫ ፳፩ ።

፲፱ ወይውግርዎ በእብን ሰብአ ሀገሩ ወይቅትልዎ ወታሴስሉ እኩየ እምኔክሙ ወኵሉ እስራኤል ሰሚዖ ይፍራህ ።

ያገሩም ሰዎች በደንጊያ መትተው ይግደሉት እንዲህ አድርጋችሁ ክፉንተ ክፉውን አርቁ (አጥፉ) ፣ እስራኤልም ሁሉ ይህን ሰምቶ ይፍራ ። ዘዳ፣ ፲፫ ፲፩ ።

፳ ወለእመበ ብእሲ ዘአበሰ ወበጽሐ ጌጋዩ ለኵነኔ ሞት ትሰቅልዎ ዲበ ዕፅ ወትቀትልዎ ።

የበደለ በደሉም ለሞት የሚያበቃ ሰው ቢኖር በዕንጨት ላይ ሰቅለው ይግደሉት ። ዘዳ፣ ፲፱ ፯ ።

፳፩ ወኢይቢት ሥጋሁ ዲበ ዕፅ አላ ቀቢረ ቅብርዎ በይእቲ ዕለት እስመ ርጉም ውእቱ በኀበ እግዚአብሔር ዘሰቀል ዲበ ዕፅ ወኢታርኵስዋ ለምድር ዘይሁበክሙ እግዚአብሔር አምላክክሙ ርስተ ።

በዕንጨት የተሰቀለ ሰው በእግዚአብሔር ዘንድ የተረገመ ነውና ፣ በዚያች ቀን ቅበሩት እንጂ ሬሳው በዕንጨት ላይ ተሰቅሎ አይደር ፣ ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር ርስት አድርጎ የሰጣችሁም ምድርን አታርክሷት ። ገላ፣ ፫ ፲፫ ።

## ምዕራፍ ፳፪ ።

፩ ወለእመ ርኢከ ላሕመ ቢጽከ አው በግዖ ኀበ ተገድፈ በፍኖት ኢትትዐወር ፣ አግብእ ሎቱ ለካልእከ ወአወፍዮ ።

የባልንጀራህን በሬ ወይም በጐዳና የጠፋ በጉን ታብይ ቸል አትበል ፣ መልሰህ ለባልንጀራህ ስጠው ።

፪ ወለእመኒ ኢኮነ ቅሩበ ኀቤከ ካልእከ ወለእመኒ ዘኢታአምሮ ታስተጋብኦ ወታአቱ ቤተከ ወታነብር ኀቤከ እስከ አመ የኀሥሦ ካልእከ ወታገብእ ሎቱ ።

ባልንጀራህ በአቅራቢያህ ባይኖርና የማታውቀው ባይሆንም ሰብስበህ ወደ ቤትህ አግባለት ፣ ባልንጀራህ እስኪፈልገው ድረስ ከቤትህ አግብተህ ካንተ ዘንድ አቈይተህ መልስለት ። ዘፀ፣ ፳፫ ፬ ፣ ፲፪ ፫ ።

፫ ከመኒ አድጎ አው ላሕሙ ከመዝ ትገብር ወከመኒ ልብሱ ከማሁ ትገብር በእንተ ኵሉ ዘገደፈ ካልእከ ወዘተገድፈ እምኀቤሁ ወረከብካሁ ኢትክል ተዐውሮቶ ።

አህያውም ቢሆን በሬውም ቢሆን እንዲህ አድርግ ፣ ልብሱም ቢሆን ባልንጀራህ ስለጣለው ገንዘብ ሁሉ እንዲህ አድርግ ፣ ከሱ ዘንድ የጠፋውንም ሁሉ ብታገኝ ቸል አትበል ።

፬ ወለእመ ርኢከ አድገ ቢጽከ አው ላሕሞ እንዘ ውዱቅ ውስተ ፍኖት ፣ ኢትትዐወሮሙ ታንሥእ ወታስተላዕል ምስሌሁ ።

የባልንጀራህን አህያ ወይም በሬውን በጐዳና ወድቆ ብታይ ቸል አትበላቸው አንሥተህ አብረህ አሟሟነው ።

፭ ወኢትትረሰይ ብእሲት በትርሲተ ብእሲ ፣ ወኢይልበስ ብእሲ ልብሰ ብእሲት እስመ ርኩስ ውእቱ በኀበ እግዚአብሔር አምላክከ ፣ ኵሉ ዘይገብሮ ለዝንቱ ።

ሴት የወንዱን ልብስ አትልበስ ፣ ወንዱም የሴቲቱን ልብስ አይልበስ ፣ ይህን የሚያደርግ ሰው በፈጣሪህ በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠላ ነውና ።

፮ ወለእመ ረከብከ እጉለ ዖፍ ቅድመ ገጽከ በውስተ ፍኖት ፣ ወእመኒ በውስተ ኵሉ ዕፀው ፣ አው በውስተ ኵሉ ምድር ፣ ወእመኒ አፍኀርተ ዘኢይሠርር ወእመኒ እንቆቅሖ ኢትንሣእ እመ ምስለ እጉሊሃ ።

በጐዳና በዛፍም ሁሉ ላይ በምድሩም ሁሉ የወፍ ጫጩት ብታገኝ ፣ የማይበር ጫጩትም ቢሆን እንቍላልም ቢሆን በፊትህ ብታገኝ እናቲቱን ከጫጩቶቿ ጋር አትውሰድ ።

፯ ዳእሙ ታሠርሖ ወታግዕዛ ለእም ወአፍኅርቲሃ ትነሥእ ለከ ከመ ትኩን ሠናይት ላዕሌከ ወይብዛኅ መዋዕሊከ ።

ላንተ በጎ ነገር ትደረግልህ ዘንድ ዘመንህም ይበዛልህ ዘንድ ጫጩቶቹን ውሰድ እንጂ እናቲቱን ነፃ አውጥተህ ስደዳት ።

፰ ወለእመ ነደቀ ቤተ ሐዲሰ ትገብር ተድባበ ለናሕስከ ወኢትገብር ቀትለ በውስተ ቤትከ ከመ ኢይደቅ እመበ ዘይወድቅ እምኔሁ ።

አዲስ ቤት በሠራህ ጊዜ ማንም ከርሱ ወድቆ ደሙን በቤትህ ላይ እንዳታመጣ ለሰገነትህ መከታ አድርግለት ።

፱ ወኢትትክል እምዘሩ ኅብር ዐፀደ ወይንከ ከመ ኢትቅስም ፍሬሁ ወዘርአከኒ ዘትዘርእ ምስለ ፍሬ ወይንከ ።

ፍሬውን አንድነት እንዳትለቅም የዘራኸውን አዝመራህንም ከወይን ፍሬ ጋር እንዳትሰበስብ በወይንህ ቦታ ላይ ሁለት ዓይነት ዘር (የተክሉን ቅመም ሁሉ) አትትከል።

፲ ወኢትሕርስ በአድግ ወበላሕም ኅቡረ ወኢትልበስ ልብሰ ዘተአንመ በፀምር ወበእጌ ።

በሬውንና አህያውን አንድነት ጠምደህ አትረስ፣ በተልባ እግርና በነጭ ሐር የተሠራውንም ልብስ አትልበስ።

፲፩ ወትገብር ለከ ዘፈረ ፍቱለ ላዕለ አርባዕቱ መዓዝነ አልባሲከ ዘትለብስ ።

በምትለብሰው በልብስህ በአራቱ ማዕዘን ላይ ላንተ የተፈተለ ዘርፍ አድርግ። ዘኍ፡ ፲፭ ፴፰ ።

፲፪ ወለእመ ጸልአ ብእሲ ለብእሲቱ ዘአውሰባ እምድኅረ ነበረ ምስሌሃ ወአምጽአ ላቲ ነገረ ምክንያት፣ ወአውፅአ ላቲ ስመ እኩየ፣ ወይቤ ነሣእክዋ ለዛቲ ብእሲት፣ ወሶበ ቦእኩ ኀቤሃ ኢረከብኩ ድንግልናሃ፣ ይነሥኡ አቡሃ ወእማ ልብሰ ድንግልናሃ ለወለቶሙ ወይስዱ ኀበ ሊቃናት ኀበ አንቀጽ ።

ማናቸውም ሰው ያገባት ሚስቱን ከእርሷ ጋር ከኖረ በኋላ ቢጠላትና የምክንያትን ነገር ቢያመጣበት፣ ይህችን ሴት አግብቻት ነበር፣ በደረስኩባትም ጊዜ ድንግልናዋን አላገኘሁም በማለት ክፉ ስም ቢያወጣበት፣ እናትና አባቷ የልጃቸው የድንግልናዋን ልብስ ይዘው በአደባባይ ወዳሉ ወደ አለቆች ይውሰዱ ።

፲፫ ወይበሎሙ አቡሃ ለይእቲ ወለት ለሊቃናት፣ ለዛቲ ወለትየ ወሀብክዎ ለዝንቱ ብእሲ ትኩኖ ብእሲተ፣ ወሶበ ጸልአ ይእዜ አምጽአ ላቲ ነገረ ምክንያት ወይቤ ኢረከብኩ ድንግልናሃ ለወለትከ ።

የዚያች ብላቴና አባትም አለቆቹን እኔ ለዚህ ሰው ሚስት ትሆነው ዘንድ ይህችን ልጄ ሰጥቸው ነበር፣ አሁን ቢጠላት የምክንያት ነገር አወራበት፣ የልጅህን ድንግልናዋን አላገኘሁም አለኝ ።

፲፬ ወናሁ ዝንቱ ውእቱ ልብሰ ድንግልናሃ ለወለትየ ወይሰፍሕዎ ለውእቱ ልብስ ቅድመ ሊቃናት ዘይእቲ ሀገር ።

የልጄ የድንግልናዋ ልብስ እነሆ ይኸው ይበላቸው፣ ያንንም ልብስ በዚያች አገር አለቆች ፊት ዘርግተው ይዩት።

፲፭ ወይእኅዝዎ ለውእቱ ብእሲ ሊቃናተ ይእቲ ሀገር ወይጌሥፅዎ ወይነሥእዎ ምእተ ሰቅለ ወይሁብዎ ለአቡሃ ለይእቲ ወለት ።

ያንንም ሰው የዚያች አገር አለቆች ይዘው ይገሥፁት (ይግረፉት) መቶ ወቄትንም ተቀብለው ለዚያች ልጅ አባት ይስጡት ።

፲፮ እስመ አውፅአ ስመ እኩየ ላዕለ ድንግለ እስራኤል ወትኩኖ ሎቱ ብእሲተ፣ ወኢይከውኖ ኅዲጎታ መጠነ ሕያው ውእቱ ።

በእስራኤል ድንግል ላይ ክፉ ስም አውጥቷልና ለሱም በግድ ሚስት ትሁነው በሕይወትም እስካለ ድረስ እርሷን መፍታት አይገባውም ።

፲፯ ወለእመሰ እሙነ ኮነ ዝንቱ ነገር ወኢተረክበ ድንግልናሃ ለይእቲ ወለት፣ ያውፅእዋ ኀበ ኆኅተ ቤተ አቡሃ ወይውግርዋ በአእባን ሰብአ ይእቲ ሀገር ወይቅትልዋ ።

ነገር ግን ይህ ነገር እውነት ሁኖ የዚያች ብላቴና ድንግልናዋ ባይገኝ ከአባቷ ቤት ደጃፍ አውጥተው በድንጊያ ደብድበው ይግደሏት ።

፲፰ እስመ ገብረት ዕበደ በውስተ ደቂቀ እስራኤል ወአዘመወት ቤተ አቡሃ ወአጽአለት፣ ወታሴስሉ እኩየ እምውስቴትክሙ ።

በእስራኤል ዘንድ ስንፍናን አድርጋለችና ያባቷንም ወገን አሰነውራለች አሰድባለችና እንዲህም አድርጋችሁ ክፉውን ከናንተ አርቁ (አጥፉ) ።

፲፱ ወለእመበ ዘተረክበ ብእሲ እንዘ ይሰክብ ምስለ ብእሲተ ብእሲ ይቅትልዎሙ ለክልኤሆሙ፣ ለውእቱኒ ብእሲ ዘሰከበ ምስሌሃ ወለይእቲኒ ብእሲት ወታሴስሉ እኩየ እምእስራኤል ።

ማናቸውም ሰው ከሰው ሚስት ጋር ተኝቶ ቢገኝ ያችን ሴትና ያን የደረሰበትን ሰው ሁለቱን ይግደሉዋቸው እንዲህ አድርጋችሁ ከናንተ ክፉውን አጥፉ ።

፳ ወለእመበ ወለት ድንግል እንተ ፍኅርት ይእቲ ለብእሲ ወረከባ ካልእ ብእሲ በውስተ ሀገር ወሰከበ ምስሌሃ ለክልኤሆሙ አውፅእዎሙ ኀበ አንቀጸ ለይእቲ ሀገር ወይውግርዎሙ በአእባን ።

ለሰው የታጨች ድንግል ልጅ ብትኖር፣ ሌላም ሰው በአገር አግኝቶ ቢደርስበት ሁለቱን ወደ አደባባይ አውጥተው በድንጊያ መትተው ይግደሏቸው ። ማቴ፡ ፩ ፲፰ ።

፳፩ ወይቅትልዎሙ ለወለትኒ እስመ ኢጸርኀት በውስተ ሀገር ወለውእቱኒ ብእሲ እስመ አኅሠረ ለብእሲተ ካልኡ ወአሰስሉ እኩየ እምውስቴትክሙ ።

እሷ ወደ አገር አልጮኸችምና፣ እሱም የባልንጀራውን ሚስት አስነውሯልና እሱንም እሷንም ሁለቱን ይግደሏቸው፣ እንዲህ እያደረጋችሁ ክፉ ክፉውን ከውስጣችሁ አጥፉ ። ዘዳ፡ ፳፩ ፲፪፡ ፳፪ ፳፩ ።

፳፭ ወለእመሰ በገዳም ረከባ ብእሲ ለወለት እንተ ፍኅርት ይእቲ ወተኀየላ ወሰከበ ምስሌሃ ቀትልዎ ለዝክቱ ዘሰከበ ምስሌሃ ለባሕቲቱ ።

ነገር ግን ሰው የታጨችውን በምድረ በዳ አግኝቶ ተበ ራትቶ ቢደርስባት ያን የደረሰባትን ሰው ብቻውን ግደሉት።

፳፮ ወለወለትሰ አልብ ዘትረስይዋ እስመ አልባቲ ጌጋይ በዘ ትመውት ይእቲ ወለት ከመ ሰበ ይትነሣእ ብእሲ ላዕለ ካልኡ ወይቀትሎ ከማሁ ውእቱ ዝንቱ ነገር ።

ያችም ልጅ በምትሞት ገንዘብ የምትሞትበት ኃጢ አት የላትምና ያችን ልጅ ግን የምታደርጓት የለም ፡ ይህ ነገር ሰው በጠላትነት ተነስቶ ባልንጀራውን እንዲገድለው እንደዚያ ነው ።

፳፯ እስመ በገዳም ረከባ ወጸርኀት ይእቲ ወለት እንተ ፍኅርት ይእቲ ወአልበ ዘይረድኣ ።

ያችም የታጨች ልጅ በምድረ በዳ አግኝቷት ጮኻ የሚረዳት አላገኘችምና እንደዚያ ነው ። ዘዳ፡ ፳፭ ፲፱ ።

፳፰ ወለእመቦ ዘረከበ ወለተ ድልግለ እንተ ኢኮነት ፍኅ ርተ ወተኀየላ ወሰከበ ምስሌሃ ወረከብዎ ይሁብ ለአቡሃ ውእቱ ብእሲ ዘሰከበ ምስሌሃ ለይእቲ ወለት ኀምሳ ዲድ ርክመ ብሩር ወትከውኖ ሎቱ ብእሲቶ ወኢይክውኖ ይኅ ድጋ መጠነ ሕያው ውእቱ እስመ አኅሠራ ።

የታጨች ያይደለች ልጃገረድን ያገኘች ሰው ቢኖር ተበረታትቶ የደረሰባትን ሰው ቢያገኙት ፡ ያችን ልጃገረድ የደረሰባት ያ ሰው ለአባቷ አምሳ ወቄት ብር ይስጠው ፡ በግድም ሚስት ትሁነው አስነውሯታልና በሕይወት ሳለ አሷን መፍታት አይገባውም ። ዘፀ፡ ፳፪ ፲፯ ።

፳፱ ወኢይንሣእ ብእሲ ብእሲተ አቡሁ ወኢይክሥት ኅፍ ረተ አቡሁ ።

ሰው ከአንጀራ እናቱ አይድረስ ፡ ያባቱንም ኃፍረት አይግለጥ ። ዘሌ፡ ፲፰ ፰ ፡ ፳ ፲፩ ፡ ፋት ፫ ፱ ።

## ምዕራፍ ፳፫ ።

፩ ወኢይባእ ዘቡቱ ነውር ወዘምቱር ውስተ ቤተ እግዚ አብሔር ከመ ኢያዘሙ ቤተ እግዚአብሔር ።

ቤተ እግዚአብሔርን እንዳያስድፍ ነውር ነቀፋ ያለ በትና አካሉ የተቈረጠ ሰው ወደ ቤተ እግዚአብሔር አይግባ ።

፪ ወኢይባእ አሞናዊ ወሞአባዊ ውስተ ቤተ እግዚአብ ሔር እስከ ሣልስ ወራብዕ ትውልድ ወእስከ ዐሥር ኢይ ባእ ቤተ እግዚአብሔር ወእስከ ለዓለም ።

የሞዓብና የአሞን ትውልድ እስከ አራትና እስከ ሦስት እስከ ዓሥርም ትውልድ ድረስ ወደ ቤተ እግዚአብሔር አይግባ ። ዘኍ፡ ፳፪ ፮ ፡ ነህ ፲፫ ፩ ።

፫ እስመ ኢተቀበሉክሙ በእክል ወበማይ ውስተ ፍኖት ሶበ ወፃእክሙ እምግብጽ ፡ ወእስመ ተዓሰብዎ ለበለዓም ወልደ ቤዖር ከመ ይርግምክሙ ።

ከግብጽ በወጣችሁ ጊዜ በጕዳና በእኽል በውኃ አል ተቀበሉዋችሁምና ፡ ይረግማችሁም ዘንድ የቤዖር ልጅ በለዓምን ገዝተውታልና ።

፬ ወኢፈቀደ እግዚአብሔር ከመ ይስምዖ ለበለዓም ወሜጣ እግዚአብሔር ለመርገሙ ውስተ በረከት ፡ እስመ አፍቀረከ እግዚአብሔር አምላክከ ።

ነገር ግን እግዚአብሔር የበለዓም ቃሉን ይሰማው ዘንድ አልወደደም ፡ ፈጣሪህ እግዚአብሔር ወዶሃልና ርግማኑን ወደ ምርቃት መለሰት ። ዘኍ፡ ፳፫ ፲፱ ።

፭ ወኢትትናገርሙ ሰላመ በዘይደልዎሙ በኵሉ መዋዕ ሊከ ለዓለም ።

በዘመንህም ሁሉ ለዘለዓለሙ በሚገባቸው ገንዘብ የጭ ቅርን ነገር አትናገራቸው (ሰላም አትበላቸው) ።

፮ ወኢታስቆርሮ ለኤዶማዊ እስመ እኁከ ውእቱ ፡ ወኢ ታስቆርሮ ለግብጻዊ እስመ ፈላሴ ኮንከ በውስተ ምድሮሙ ።

የዔሳውን ልጅ (ኢትጥላው) አትጸየፈው ወንድምህ ነውና የግብጽንም ሰው አትጸየፈው በአገራቸው ስደተኛ ሁነህ ነበርና ። ዘፍ፡ ፳፭ ፳፱ ፡ ዘዳ፡ ፲ ፲፱ ።

፯ ወደቂቅ ለእመ ተወልዱ ሎሙ በሣልስ ትውልድ ይ ባኡ ቤተ እግዚአብሔር ።

ልጆች ቢወለዱላቸው ግን በሦስተኛው ትውልድ ወደ ቤተ እግዚአብሔር ይግቡ ።

፰ ወለእመ ወፃእከ ትፃባእ ምስለ ፀርከ ተዓቀብ እምኵሉ ቃል እኩይ ።

ጠላቶችህን ልትወጋ ብትወጣ ፡ ከክፉ ነገር ሁሉ ተጠበቅ ።

፱ ወለእመቦ እምውስቴትክሙ ብእሲ ዘኢኮነ ንጹሐ እምነ ስዕበቱ ዘሌሊት ይፃእ አፍአ እምትዕይንት ወኢይ ባእ ውስተ ትዕይንት ።

በሌሊት ከሚሠራ ኃጢአት ንጹሕ ያልሆነ ሰው ቢኖር ከከተማው ወደ ውጭ ይውጣ ፡ ወደ ከተማ አይግባ ።

፲ ወፍና ሠርክ ተሐፂቦ ሥጋሁ በማይ ዐረበ ፀሐይ ይባእ ውስተ ትዕይንት ።

ፀሐይ ከገባ በኋላ ሲመሽ ሰውነቱን በውኃ ታጥቦ ወደ ከተማ ይግባ ። ዘሌ፡ ፲፭ ፭ ፡ ዘዳ፡ ፲፯ ፱ ።

፲፩ ወአሐደ መካነ ረሲ ለከ አፍአ እምትዕይንት ኅበ ትወ ፅእ ህየ ።

የምትወጣበትን ቦታ ከከተማ በውጭ አንድ ቦታ አድርግ ። ዘኍ፡ ፪ ፲፯ ።

፲፪ ወዕፀ ንሣእ ለከ ውስተ ቅናትከ ፡ ወሰበ ነበርከ ቀሠፍኮ ትከሬ ወትነሥእ ወትደፍን ኀፍረተከ ።

በመታጠቂያህም ዕንጨትን (መኳቻን) ያዝ ፡ አዳሪም በተቀመጥክ ጊዜ ቈፍረህ ተቀመጥ ፡ መሬትንም ወስደህ ኃፍረትክን ሠውር ፡ (በአፈር ድፈነው) ።

፲፫ እስመ እግዚአብሔር አምላክከ ያንሶሱ ውስተ ትዕይን
ትከ ከመ ያድኅንከ ወያግብኦሙ ለፀርከ ውስተ እዴከ በቅ
ድመ ገጽከ ወትኩን ቅድስተ ትዕይንትከ ከመ ኢያስተርኢ
ውስቴትከ ዘከነ ኀፍረት ወይትመየጥ እምኔከ ወየኀድገከ።
፲፬ ወኢታግብኦ ለገብር ኀበ እግዚኡ እምኃረ ተሠይጠ
ኀቤከ ይንበር ምስሌከ ኀበ አደሞ ወኢትማቅቆ ።

፲፭ ወኢትኩን ዘማ እምአዋልደ እስራኤል ፡ ወኢይኩን
ዘማዊ እምደቂቀ እስራኤል ።
፲፮ ወኢታብእ ዐስበ ዘማ ወኢሤጠ ከልብ ውስተ ቤተ እግዚአብሔር አም
ላክከ በበይነ ኵሉ ብፅዐት ።

፲፯ እስመ ርኩሳን እሙንቱ በኀበ እግዚአብሔር አምላ
ክከ ክልኤሆሙ ።
፲፰ ወኢትትረደይ እምቢጽከ ኢ ርዴ ወርቅ ፡ ወኢ ርዴ
እክል ፡ ወኢርዴ ኵሉ ዘከነ ትክዙ ለቢጽከ ለእመ ተለቅ
ሐከ ቢጽከ ።
፲፱ ወእምነኪር ትትረደይ ፡ ወእምቢጽከሰ ኢትትረደይ
ከመ ይባርከ እግዚአብሔር አምላክከ በኵሉ ግብርከ ላዕለ
ምድር እንተ ትበውእ ውስቴታ ከመ ትትዋረሳ ።
፳ ወለእመ በፃእከ ብፅዐተ ለእግዚአብሔር ኢታጕንዲ
ገቢሮቶ እስመ ተኃሥሦ ይትኀሠሠከ እግዚአብሔር አምላ
ክከ ወይከውን ኃጢአተ ላዕሌከ ።
፳፩ ወለእመሰ ኢፈቀድከ ትብፃዕ አልብከ ኃጢአት ፡ ዳእ
ሙ እምከመ ወፅአ እምከናፍሪከ ተዓቀብ ወግበር በከመ
በፃዕከ ተሀብ ለእግዚአብሔር ዘከመ ነበብከ በአፉከ ከማሁ
ግበር ።
፳፪ ወለእመ ቦእከ ውስተ ገራህተ ካልእከ መሐው ሰዊተ
በእዴከ ፡ ወማዕፀደ ኢታብእ ውስተ ገራህተ ካልእከ ።

፳፫ ወለእመ ቦእከ ውስተ ዐፀደ ወይኑ ለካልእከ ብላዕ እስ
ካለ እስከ ትጸግብ ነፍስከ ወውስተ ሙዳይ ብሕቱ ኢትደይ ፤

ምዕራፍ ፳፬ ።

፩ ወለእመቦ ዘነሥአ ብእሲተ ወነበረ ምስሌሃ ፡ ወእምዝ
ለእመ ኢረከበት ሞገሰ በኀቤሁ እስመ ረከበ ዘከነ ኀፍረተ
ላዕሌሃ ይጽሐፍ ላቲ መጽሐፈ ኀዳጋቲሃ ወይመይጥዋ ው
ስተ እዴሃ ወያውፅአ እምነ ቤቱ ።
፪ ወሖረት ወአውሰበት ካልአ ብእሴ ወእምዝ ጸልአ
ውእቱኒ ብእሲ ደኃራዊ ወጸሐፈ ላቲ መጽሐፈ ኀዳጋቲሃ
ወመጠዋ ውስተ እዴሃ ወአውፅአ እምቤቱ ፡ ወለእመኒ
ሞተ ውእቱ ብእሲ ደኃራዊ ዘነሥአ ሎቱ ትኩኖ ብእሲተ ።
፫ ኢይክውኖ ለዝኩቱ ብእሲ ቀዳማዊ ዘአውፅአ ከመ ይግ
ባእ ላዕሌሃ ወይንሥኣ ሎቱ ትኩኖ ብእሲተ እምድኅረ ረኰ
ሰት እስመ ርኩስ ውእቱ ዝንቱ ነገር በኀበ እግዚአብሔር
አምላክከ ።
፬ ወኢታርኵሱ ምድረ ዘይሁበክሙ እግዚአብሔር
አምላክክሙ ርስተ ።

ፈጣሪህ እግዚአብሔር ያድንህ ዘንድ ጠላቶችህንም
በፊትህ በእጅህ ይጥልልህ ዘንድ በከተማህ ይመላለስልና
የተደረገው ኀፍረትህ እንዳይታይበህ ከተማህ የጸዳች
ትሁን ፤ እንዲህ ግን ካልሆነ በረድኤት ይለይኻል ።
በንተ ዘንድ ከተገዛ በኋላ ባርያን ወደ ጌታው አትመ
ልሰው በመረጠው ዘንድ ከአንተ ጋራ ይኑር ምክራም አታ
ድናበት ። ፩ ሳሙ ፡ ፴ ፲፭ ።
ከእስራኤል ልጆች አንዲቱ ሴሰኛ አትሁን ፡ ከእስራ
ኤልም ልጆች አንዱ ሴሰኛ አይሁን ።
ከእስራኤልም ግብር የሚያገባ (የሚገብር) አይኑር ፡
ሁለቱ ሁሉ በፈጣሪህ በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠሉ ናቸ
ውና ስለ ተሳልከው ስለት ሁሉ የውሻና የሴሰኛ ዋጋ ወደ
ፈጣሪህ ወደ እግዚአብሔር ቤት አታግባ ።
ሁለቱም በፈጣሪህ በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠሉ
ናቸው ።
ባልንጀራህ ቢበድርህ ከባልንጀራህ የእኽልና የወርቅ
ማለጽ የሆነ አራጣውን ሁሉ አትከፈል (አትቀበል) ።

ከሌላው (ከአሕዛብ) ተቀበል ፡ ልትወርሳት በምትገባ
በት አገር በሥራህ ሁሉ ፈጣሪህ እግዚአብሔር ያከብርህ
(ይባርክህ) ዘንድ ከባልንጀራህ አራጣ ግን አትቀበል ።
ለእግዚአብሔር ስለት ብትሳል ስለትህን ፈጥነህ ስጥ ፡
ፈጣሪህ እግዚአብሔር ፈጽሞ ይመራመርኻልና በንተም
ኃጢአት ይሆንብኻልና ። ዘኍ ፴ ፪ ፡ መክ ፭ ፬ ።
ልትሳል ካልወደድህ ግን ኃጢአት የለብህም ፡ ነገር
ግን ከአንደበትህ ከወጣ ተጠበቅ ፡ ለፈጣሪህ ለእግዚአብ
ሔር ትሰጥ ዘንድ ተስለህ በአንደበትህ እንደተናገርከ
እንደዚያው አድርግ ።
ወደ ባልንጀራህ እርሻ ብትገባ በእጅህ እሸትህ እሸ
ትን ብላ ፡ ነገር ግን ከባልንጀራህ እርሻ ገብተህ በማጭድ
አትጨድ ።
ወደ ባልንጀራህ ወይን ቦታም ብትገባ ሆድህ እስኪት
ጠግብ ድረስ እሸቱን ብላ ፡ በአገልግል ግን አትጨምር ።

ምዕራፍ ፳፬ ።

ሚስት አግብቶ ከሷ ጋር የኖረ ሰው ቢኖር ፡ ከዚህ
በኋላ በሱ ዘንድ መወደድን ባታገኝ ፡ በሷ ኀፍረት የሆነ
ነገር አግኝቷልና የፍችዋን ደብዳቤ ጽፎ በእጅዋ ሰጥቶ
ያስወጣት ። ዘዳ ፡ ፳፫ ፲፪ ፡ ማቴ ፡ ፲፱ ፯ ።
ሂዳም ሌላ ሰው ብታገባ ከዚያም በኋላ ያገባት ሰው
ቢጠላት የመፈቻዋን ደብዳቤ ጽፎ በእጅዋ ሰጥቶ አስ
ወጥቶ ቢሰዳት ፡ ሚስት ትሆነው ዘንድ በኋላ ያገባት
ሰው ቢሞት ።
ቀድሞ ለፈታት ለዚያ ሰው ወደርሷ ይመለስ ዘንድ
ይህ በእግዚአብሔር ፊት የሚያስጸይፍ ነውና ከጐሰቈለች
በኋላ ሚስት ልትሆነው ያገባትም ዘንድ አይገባውም ።

ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር ርስት አድርጎ የሚሰጣ
ችሁ ምድርንም አታርክሱ ፡ ኤር ፫ ፩ ።

፭ ወለእመበ ዘነሥአ ብእሲት ግብተ ኢይፃእ ፀብአ ወኢ ፡ፈልብ ምንተኒ ዘያቀትውዎ ድኅኑ ውእቱ ቤቱ አሐተ ዓመተ ከመ ይትፌሣሕ ምስለ ብእሲቱ እንተ አውሰበ ።

ድንገት ሚስት ያገባ ሰው ቢኖር ወደ ሰልፍ አይውጣ የዘመቻ ፈረ ብለው ምንምን አያገብሩት ፤ ከገባት ሚስቱ ጋር ደስ ይለው ዘንድ ቤቱ አንድ ዓመት ከዘመቻ ፈረ ይዳን ። ዘዳ፡ ፳ ፯ ፣ ምሳ፡ ፭ ፲፰ ።

፮ ወኢትእኅዝ ማሕረፀ ወኢመድሐ ማሕረፅ እስመ መብዕለ ነፍስ ውእቱ ወኢየአኀዝዎ ።

ወፍጮንና መጅን መያዣ አድርገህ አትያዝ ፣ ሰውነት መመገቢያ ነውና አይያዙት ። ዘጸ፡ ፳፪ ፲፱ ።

፯ ወለእመበ ዘተረክበ ብእሲ ዘሰረቀ ነፍሰ እምአኀዊሁ እምደቂቀ እስራኤል ወተፀገሎ ወሤጦ ፣ ለይቅትልዎ ለውእቱ ሰራቂ ወታሴስሎ እኩየ እምስቴትክሙ ።

ከወንድሞቹ ከእስራኤል ልጆች ሰውን የሰረቀ ቀምቶም የሸጠው ሰው ቢኖር ያን የሰረቀው ሰው ይግደሉት እንዲህ እያደረጋችሁ ከውስጣችሁ ክፉ ክፉውን አርቁ ።

፰ ወዑቅ ርእሰከ በእንተ ትእምርተ ለምጽ ተዓቀብ ጥቀ ከመ ትግበር ኵሎ ሕገ ዘይቤሉከ ካህናት ወሌዋውያን በከመ አዘዝኩከ ተዓቀብ ዘትገብር ።

ስለ ለምጽ ምልክት ለራስህ ዕወቅ ፣ ሌዋውያንና ካህናት ያዘዙህን ሕጉን ሁሉ ትጠብቅ ዘንድ ፈጽመህ ተጠበቅ እንዳዘዝኩህ የምታደርገውን ጠብቅ ። ዘሌ፡ ፲፫ ፲፫ ።

፱ ወተዘከር ኵሎ ዘገብረ እግዚአብሔር አምላክከ ላዕለ ማርያ በፍኖት አመ ወፃእክሙ እምግብጽ ።

ከግብጽ በወጣችሁ ጊዜ ፈጣሪህ እግዚአብሔር በጐዳና በማርያ ያደረገውን ሁሉ አስብ ። ዘኍ፡ ፲፪ ፲ ።

፲ ወለእመበ ዘይፈድየከ ክልእከ ዕዳ ዘከነ ኢትባእ ውስተ ቤቱ ከመ ተእኅዝ አኀዘከ ዳዕሙ አፍአ ትቀውም ።

በልንጀራህ የሚከፍለህ ዕዳ የሆነ ገንዘብ እንዳለ በውጭ ቁም እንጂ መያዣህን ትይዝ ዘንድ ወደ ቤቱ አትግባ ።

፲፩ ወብእሴ ዕዳከ ዝክቱ ዘይፈድየከ ለሊሁ ያወፅእ አኅዘከ አፍአ ኀቤከ ።

ዕዳህን የሚከፍልህ ያ ሰው እሱ መያዣህን ከንተ ዘንድ ወደ ውጭ ያውጣልህ ።

፲፪ ወለእመ ብእሲ ነዳይ ውእቱ ፣ ኢታቢት አኅዞ ኀቤከ ።

ያ ሰው ድኻ ቢሆን ግን ፣ መያዣውን ከንተ ዘንድ አታሳድር ።

፲፫ ታገብእ ሎቱ አኅዞ ዘእንበለ ይዕርብ ፀሐይ ወይበይት በልብሱ ወትትባረክ ወይከውነከ ምጽዋተ በቅድመ እግዚአብሔር አምላክከ ።

ፀሐይ ሳይገባ መያዣውን መልስለት ፣ ልብሱን ለብሶ ይደር አንተም ትመረቃለህ ፣ በፈጣሪህ በእግዚአብሔርም ፊት ምጽዋት ይሆንልኻል ። ዘፀ፡ ፳፪ ፳፮ ።

፲፬ ወኢትፀምዎ ዐስበ ለዐሳብ ለነዳይ ዘኅጡእ ውእቱ እምአኀዊከ አው እምግዩራን ዘውስተ ሀገርከ ።

ከወንድሞችህ ወይም በአገርህ ካሉ ስደተኞች ገንዘብ ያጣ ድኻ ምንደኛ ፣ ደመወዙን አትከዳው ።

፲፭ እንተ ጸብሐት ትሁብ ዐስቦ ወኢታዕርብ ፀሐየ ላዕሌሁ እስመ ነዳይ ውእቱ ወውእቱ ተስፋሁ ወኢይግዐር ላዕሌከ ኀበ እግዚአብሔር ወኢይኩንከ ኀጢአተ ።

ድኻ ነውና አለኝታውም እሱ ነውና ወደ እግዚአብሔር እንዳይጮህብህ ኃጢአትም እንዳይሆንብህ ፀሐይ ሳይገባ በየቀኑ ደመወዙን ስጠው ። ዘሌ፡ ፲፱ ፲፫ ።

፲፮ ወኢይመውቱ ወላድያን በበይነ ውሉዶሙ ወኢይመውቱ ውሉድ በበይነ ወላድያኒሆሙ አላ አሐዱ አሐዱ በጌጋዩ ይመውት ።

አንዱም አንዱም በበደለው በደል ይሞታል እንጂ ፣ ወላጆች በልጆቻቸው ልጆችም በወላጆቻቸው በደል አይሞቱም ። ፬ ነገ፡ ፲፬ ፮ ፣ ሕዝ፡ ፲፰ ፳ ።

፲፯ ወኢትሚጥ ፍትሐ ግዩር ወዘእጓለ ማውታ ወዘዕቤር ።

እናት አባቱ የሞቱበትንና ፣ የስደተኞችን ፣ የባልቴትንም ፍርድ አትለውጥ ። ዘዳ፡ ፲ ፲፰ ፣ ኢሳ፡ ፩ ፳፫ ።

፲፰ ወተዘከር ከመ ገብር አንተ በምድረ ግብጽ ወቤዘወከ እግዚአብሔር አምላክከ እምህየ ወበበይነ ዝንቱ እኤዝዘከ እነ ትግበር ዘንተ ነገረ ።

በግብጽ አገር አንተ ተገዥ ባርያ እንደነበርህ ፈጣሪህ እግዚአብሔርም ከዚያ እንዳዳነህ አስብ ፣ ስለዚህ ይህንን ታደርግ ዘንድ አዝኻለሁ ። ዘዳ፡ ፳፬ ፳፪ ፣ ፰ ፲፩ ።

፲፱ ወለእመ ዐፀድከ እክለ ገራህትከ ወረሳዕከ አሐተ ክልስስተ ውስተ ገራህትከ ኢትግባእ ከመ ትንሣእ ፣ ለግዩር ወለእጓለ ማውታ ወለዕቤር ይኩን ከመ ይባርከ እግዚአብሔር አምላክከ በኵሉ ተግባረ እደዊከ ።

የእርሻህን አዝመራ ብታጭድ እንዲቱን ነዶ በእርሻህ ብትዘነጋ ታነሣት ዘንድ አትመለስ ፣ ፈጣሪህ እግዚአብሔር በእጅህ ሥራ ሁሉ ያከብርህ ዘንድ እናት አባቱ ለሞቱበት ልጅና ፣ ለስደተኛ ፣ ለባልቴትም ይሁን ። ዘሌ፡ ፲፱ ፱ ።

፳ ወለእመኒ ቀሠምከ ዐፀደ ወይንከ ኢትድግም ተመይጠ ድኅሬከ ከመ ታስተናጽሕ ቀሢመ ለግዩር ፣ ወለእጓለ ማውታ ፣ ወለዕቤር ይኩን ።

የወይንህን በቃ በቀሰምከ (በለቀምክ) ጊዜ ፣ አጥርተህ ትለቅም ዘንድ ዳግመኛ ወደ ኋላህ አትመለስ ፣ እናት አባቱ ለሞቱበት ልጅና ፣ ለስደተኛ ፣ ለባልቴትም ይሁን ።

፳፩ ወለእመኒ ቀሠምከ ዘይትከ ኢትድግም ተመይጦ ድኅሬከ ከመ ታስተናጽሕ ቀሢመ ፣ ለግዩር ፣ ወለእጓለ ማውታ ወለዕቤር ይኩን ።

እናት አባቱ ለሞቱበት ልጅና ለስደተኛ ለባልቴትም ይሁን እንጂ ዘይትህን በለቀምክ ጊዜ አጥርተህ ትለቅም ዘንድ ዳግመኛ ወደ ኋላህ አትመለስ ። ዘሌ፡ ፲፱ ፲ ።

፳፪ ወተዘከር ከመ ግዩር አንተ በምድረ ግብጽ ወቤዘወከ እግዚአብሔር አምላክከ እምህየ ።

አንተ በግብጽ ምድር ስደተኛ እንደ ነበርክ ፈጣሪህ እግዚአብሔርም ከዚያ እንዳዳነህ (እንዳወጣህ) አስብ ።

፳፫ ወበይነ ዝንቱ እኤዝዘከ እነ ትግበር ዘንተ ነገረ ።

ስለዚህም ይህንን ነገር ታደርግ ዘንድ እኔ አዝኻለሁ ።

| ምዕራፍ ፳፭ ። | | ምዕራፍ ፳፭ ። |
|---|---|---|
| ወለእመ ኮነ ተስናን በማእከለ ሰብእ ወመጽኡ ውስተ ዐውድ ወተሰነኑ ወአርትዑ ለዘይረትዕ ወአዕልዉ ለዘ ይጌውዕ ። | ፩ | በሰዎች መከከል ጠብ ቢሆን ፣ ሰዎችም ወደ ሸንጎ መጥተው ቢከራከሩ እውነቱን እውነት ፣ ሐሰቱን ሐሰት ብላችሁ ፍረዱ ። ዘዳ፡ ፲፱ ፲፯ ፣ ምሳ፡ ፲፯ ፲፭ ። |
| ወለእመ ኮነ ስተትቀሥፎ ያንብርዎ ቅድመ ዐውድ ለገቡ ዘይጌዉዕ ወይቅሥፍዎ በቅድሜሆሙ በአምጣነ አበሳሁ ። | ፪ | በደሉም ለመገረፍ ቢሆን ያን የሚገረፈውን ሰው በሸንጎ አስቀምጠው የበደለውን ያህል በፊታቸው ይግረፉት። |
| አርባዓ ይቅሥፍዎ በኍልቈ ወኢያብዝኁ እምኔሁ ፣ ወለእመ አብዝኁ ቀሢፎቶ እምዝንቱ አስተኀፈርከ አኀዊከ በቅድሜከ ። | ፫ | በቍጥር አርባ ይግረፉት ፣ ከአርባ አትርፈው (አብዝ ተው) አይግረፉት ፣ ከርባ አትርፈው ቢገርፉት ግን ወንድ ምህን በፊትህ አሳፈርከ (ነውረኛ አደረግህ) ። |
| ወኢትፍፅሞ አፉሁ ለላሕም ሶበ ታከይድ እክለ ። | ፬ | እኽልን በምታበራይበት ጊዜ የበሬውን አፉን አት ሰረው ። ፩ ቆሮ፡ ፱ ፱ ፣ ፩ ጢሞ፡ ፩ ፲፰ ። |
| ወለእመበ አኀው እለ ይነብሩ ኅቡረ ብእሲ ምስለ እ ኁሁ ወሞተ አሐዱ እምኔሆሙ ወአልቦ ውሉድ ኢታውስብ ብእሲቱ ነኪረ ብእሴ እኁሁ ለምታ ለያውስቦ ወው እቱ ለይበአ ኀቤሃ ወሉቱ ትኩኖ ብእሲቶ ወይንበር ምስሌሃ ። | ፭ | ወንድም ከወንድሙ ጋር አንድነት የሚኖሩ ወንድማ ማቾች ቢኖሩ ከነሳቸውም አንዱ ቢሞት ልጅ ባይኖረው የባሏ ወንድም ያግባት እንጂ ሚስቱ ሌላ ሰው አታግባ ፣ እሱ ይድረስባት ለሱ ሚስት ትሁነው ከሷም ጋር ይኑር ። ሉቃ፡ ፳ ፳፰ ። |
| ወሕፃን ዘተወልደ ይኩን ለዘሞተ ፣ ወይሰመይ በስሙ ወኢይደምሰስ ስሙ እምእስራኤል ። | ፮ | የተወለደውም ልጅ ለሞተው ሰው ይሁን ከእስራኤል ስሙ እንዳይጠፋም በስሙ ይጠራ ። ዘፍ፡ ፴፰ ፱ ። |
| ወለእመ ኢፈቀደ ውእቱ ብእሲ ያውስባ ለብእሲተ እ ኁሁ ፣ ወተዐርግ ይእቲ ብእሲት ኀበ ሊቃናት ውኀበ አን ቀጽ ወትብል ኢይፈቅድ እኁሁ ለምትየ ያቅም ስመ እኁ ሁ ውስተ እስራኤል ። | ፯ | ያ ሰው የወንድሙን ሚስት ሊያገባት ባይወድ ግን ያች ሴት በአደባባይ ወዳሉ ሽማግሎች ወጥታ የባሌ ወን ድም በእስራኤል ዘንድ የወንድሙን ስም ያስጠራ ዘንድ አልወደደም ትበል ። ሩት ፩ ፲፭ ፣ ፬ ፪ ። |
| ይጸውዕዎ ሊቃናተ ሀገር ወይበልዎ ኢትፈቅዶኑ ታቅ ም ዘርአ ለእኁከ ውስተ እስራኤል ወይበል ቀዊሞ ኢይ ፈቅድ አውስቦ ። | ፰ | የአገር ሽማግሎችም ጠርተው በእስራኤል መከከል ለወንድምህ ልጅ ልትተክ አትወድምን፤ ይበሉት ፣ እሱም ቁሞ ላገባት አልወድም ይበል ። ሩት ፬ ፮ ። |
| ወትቅረብ ይእቲ ብእሲት ኀቤሁ ቅድመ ሊቃናተ ይ እቲ ሀገር ወትፍታሕ ሣእኖ ዘእሐቲ እግሩ ወትትፋእ ውስ ተ ገጹ ወትበል ከመዝ ይግበርዎ ሰብእ ዘኢይፈቅድ ይሕንጽ ቤተ እኁሁ ። | ፱ | ያችም ሴት በዚያች አገር ሽማግሎች ፊት ወደርሱ ቀርባ ያንዲት እግሩ ጫማ ፈትታ ምራቋን እንትፍ ትበል በት ፣ የወንድሙን ቤት ይሠራ ዘንድ የማይወደውን ሰው እንዲህ ያድርጉት ትበል ። ዘኍ፡ ፲፪ ፲፬ ፣ ሩት ፬ ፯ ። |
| ወይሰመይ ስሙ በውስተ እስራኤል ቤተ ፍቱሐ አሣእን ። | ፲ | ስሙም በእስራኤል ዘንድ ጫማው የወለቀ ሰው ወገን ይባል ። ምሳ፡ ፯ ፴፫ ፣ ፩ ጢሞ፡ ፫ ፯ ። |
| ወለእመ ተባአሱ ክልኤቱ እደው ኅቡረ ብእሲ ምስለ ክልኡ ወመጽአት ብእሲቱ ለአሐዱ እምኔሆሙ ከመ ታኀ ድኅ ለምታ እምእደ ዘበጢሁ ወአልዐለት እዴሃ ወአኀዘቶ ብክልኤሆን አስከቲሁ ለይምትሩ እዴሃ ወኢትምሐክ ዐይንከ ። | ፲፩ | ሁለት ሰዎች አንዱ ካንዱ ጋራ አንድነት ቢጣሉ በሷን ከሚመታው ሰው እጅ ታስጥለው ዘንድ ከነሱ ያንዱ ሰው ሚስት መጥታ እጅዋን ዘርግታ ሁለት ብልቶቹን ብትይ ዘው እጅዋን ይቍረጧት ፣ ዓይንህም አትራራላት ። ዘዳ፡ ፲፱ ፲፫ ። |
| ወኢታንብር ለከ መዳልወ ንኡሰ ወዐቢየ ወኢትግበር ለከ በውስተ ቤትከ መስፈርተ ንኡሰ ወመስፈርተ ዐቢየ ። | ፲፪ | ላንተ ታላቅ ሚዛንና ታናሽ ሚዛን ታላቅ ቁናና ታናሽ ቁና በቤትህ አታኑር ። ምሳ፡ ፲፯ ፲፩ ፣ ሚክ፡ ፮ ፲፩ ። |
| መዳልውከኒ ርቱዐ ወጽዱቀ ይኩንከ ከመ ታብዝኅ መዋዕለ በምድር ዘይሁበከ እግዚአብሔር አምላክከ ርስተ ። | ፲፫ | ፈጣሪህ እግዚአብሔር ርስት አድርጎ በሚሰጥህ ምድ ር ዕድሜህ ይረዝም ዘንድ ፣ ሚዛንህ የቀናና እውነተኛ ይሁን ። ምሳ፡ ፲፩ ፩ ። |
| እስመ ርኩስ ውእቱ በኀበ እግዚአብሔር አምላክከ ኵሉ ዘይገብሮ ለዝንቱ ወኵሉ ዘይገብር ዐመፃ ። | ፲፬ | ይህን የሚያደርግ ሰው ሁሉ በደልንም የሚያደርግ ሁሉ በፈጣሪህ በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠላ ነውና ። |
| ወተዘከር ኵሎ ዘገብረ ላዕሌከ አማሌቅ በፍኖት አመ ወፃእከ እምድረ ግብጽ ። | ፲፭ | ከግብጽ አገር በወጣህ ጊዜ አማሌቅ በጐዳና ያደረገ ብህን ሁሉ አስብ ። ዘፀ፡ ፲፯ ፰ ፣ ዘዳ፡ ፳፬ ፱ ። |
| ዘከመ ተቃወመከ በፍኖት ወአምተረከ ጋዕዘከ እለ ይደክሙ በድኅሬከ ። | ፲፮ | በጐዳናም እንደ ተቃወመህ ካንተ በኋላ ደክመው የነ በሩትን ጓዞችህንም ነጥቆ እንዳስቀረ አስብ ። |

፲፰ ወአንተሰ ርኁብከ ወደከምከ ወኢፈራህኮ ለእግዚአብሔር አምላክከ ።

አንተም ደክሞህ ርበህ ሳለ ፈጣሪህ እግዚአብሔርን አልፈራኸውም ። ኢያ፡ ፲ ፲፱ ፡ ፪ ሳሙ፡ ፲፮ ፪ ።

፲፱ ወአመ ያዐርፈከ እግዚአብሔር አምላክከ እምኵሉ ፀርከ ዘዐውድከ ውስተ ምድር ዘይሁበከ እግዚአብሔር አምላክከ ትትዋረሳ ርስተ ትደመስሶ ለአማሌቅ እምታሕተ ሰማይ ወኢትረስዖ ።

ርስት አድርገህ ትወርሷት ዘንድ ፈጣሪህ እግዚአብሔር በሚሰጥህ ምድር በዙርያህ ካሉ ጠላቶችህ ሁሉ ፈጣሪህ እግዚአብሔር ባሳረፈህ ጊዜ አማሌቅን ከሰማይ በታች አጥፋው ፡ አትዘንጋው ። ዘፀ፡ ፲፯ ፲፱ ።

## ምዕራፍ ፳፮ ።

፩ ወለአመ በአከ ውስተ ምድር ዘይሁበከ እግዚአብሔር አምላክከ ትትዋረሳ ርስተ ወነበርከ ውስቴታ ትነሥእ እምፍሬ ምድር ዘወሀበከ እግዚአብሔር አምላክከ ።

ርስት አድርገህ ትወርሳት ዘንድ ፈጣሪህ እግዚአብሔር ወደ ሚሰጥህ ምድር ብትገባ በውስጧም ብትኖር ፡ ፈጣሪህ እግዚአብሔር ከሰጠህ ምድርህ የተገኘውን ፍሬ ውሰድ ። ምሳ፡ ፫ ፱ ፡ ሮሜ ፰ ፳፫ ።

፪ ወትወዲ ውስተ ቀርጠሉን ወተሐውር ውስተ መካን ዘኀረየ እግዚአብሔር አምላክከ ከመ ይሰመይ ስሙ በህየ ።

በአገልግልም ይዘህ በዚያ ስሙ ይጠራበት ዘንድ ፈጣሪህ እግዚአብሔር ወደ መረጠው ቦታ ሂድ ።

፫ ወትበውእ ኀበ ካህን ዘሀለወ በውእቱ መዋዕል ወትብሎ አየድዕ ዮም ቅድመ እግዚአብሔር አምላኪየ እስመ በጻሕኩ ውስተ ምድር ዘመሐለ እግዚአብሔር ለአበዊነ ከመ የሀበነ ።

በዚያ ወራት ወዳለውም ካህን ገብተህ እሷን ይሰጠን ዘንድ እግዚአብሔር ላባቶቻችን ወደ ማለላቸው ምድር ደረሽለሁና አሁን በፈጣሪዬ በእግዚአብሔር ፊት እናገራለሁ በለው ።

፬ ወይነሥእ ካህን ለውእቱ ሙዳየ ቀርጠሉን እምውስተ እደዊከ ወያነብሮ ቅድመ ምሥዋዐ ለእግዚአብሔር አምላክከ ።

ካህኑም ያንን አገልግል ከእጅህ ተቀብሎ በፈጣሪህ በእግዚአብሔር መሠውያ ፊት ያኑረው ። ሆሴዕ ፲፪ ፲፪ ።

፭ ወትብል ቅድመ እግዚአብሔር አምላክከ አበውየ ወፅኡ እምድረ ሶርያ ወወረዱ ውስተ ግብጽ ወነበሩ ህየ እንዘ ውኁዳን እሙንቱ በኍላቈሆሙ ወኮኑ በህየ ሕዝበ ዐቢየ ወመልኡ ወዐብዩ ብዙኀ ።

አባቶቼ በእግዚአብሔር ትእዛዝ ከሶርያ ምድር መጥተው ወደ ግብጽ ወረዱ ፡ እነሱም በቍጥራቸው ጥቂት ሁነው ሳሉ በግብጽ ኖሩ ፡ በዚያም ታላቅ ወገን ሆኑ ፡ በዓለም መሉ ፡ እጅግም በዙ ። ዘፍ፡ ፵፫ ፪ ።

፮ ወሣቀዩነ ግብጽ ወአሕመሙነ ወአገበሩነ ዕፁበ ግብረ ።

ግብጻውያንም መከራ አጸኑብን አስጨነቁን የሚያስጨንቅም ሥራ አሠሩን ። ዘፀ፡ ፲፩ ፲፬ ።

፯ ወጸራሕነ ኀበ እግዚአብሔር አምላከ አበዊነ ወሰምዐ እግዚአብሔር ቃለነ ወርእየ ሕማመነ ወሥራሐነ ወሥቃየነ ፤

እኛም ወደ አባቶቻችን ፈጣሪ ወደ እግዚአብሔር ጮኽን ፡ እግዚአብሔርም ድካማችንንና መከራችንን አይቶ ልመናችንን ሰማን ። ዘፀ፡ ፪ ፳፫ - ፳፭ ።

፰ ወአውፅአነ ለሊሁ እምድረ ግብጽ በእድ ጽንዕት ወበመዝራዕት ልዑል በዐቢይ ግርማ ወበዓቢይ ተአምር ወመድምም ።

እሱ በጸናች ሥልጣንና በተዘረጋች ክንድ በታላቅ መፈራት በታላቅና በድንቅ በድንቅ ተአምራት ከግብጽ አገር አወጣን ። ዘፀ፡ ፲፪ ፴፯ ፡ ዘዳ፡ ፬ ፴፬ ።

፱ ወአብአነ ውስተ ዝንቱ መካን ወወሀበናሃ ለዛቲ ምድር እንተ ትውኅዝ ሐሊበ ወመዓረ ።

ማርና ወተት የምታፈሰውን ይህችንም ምድር ሰጥቶ ወደዚህ ቦታ አገባን ። ዘፀ፡ ፫ ፰ ፡ ዘዳ፡ ፳፯ ፲፭ ።

፲ ወይእዜኒ ናሁ አምጻእኩ ቀዳሚ እክለ ምድርየ ዘወሀበኒ እግዚአብሔር ምድረ እንተ ትውኅዝ ሐሊበ ወመዓረ ወትሰግድ ቅድመ እግዚአብሔር አምላክከ ።

አሁንም እግዚአብሔር ከሰጠኝ ማርና ወተት ከምታፈሰው ምድር የምድሬን እኽል መጀመሪያ እነሆ አመጣሁ በፈጣሪህ በእግዚአብሔር ፊት ስገድ ።

፲፩ ወትትፌሣሕ በኵሉ በረከት ዘወሀበከ እግዚአብሔር አምላክከ አንተ ወቤትከ ወሌዋዊኒ ወግዩርኒ ዘኀቤከ ።

ፈጣሪህ እግዚአብሔር በሰጠህ በረከት ሁሉ አንተን ደስ ይበልህ ፡ ወገንህንም ካህንም በንተ ዘንድ ያለ ስደተኛውንም ደስ ይበለው ። ዘዳ፡ ፲፪ ፯ ።

፲፪ ወእምከመ ፈጸምከ ዐሥሮተ ኵሉ ዐሥራት ዘእክለ ኵሉ ምድርከ በሣልስ ዓም ፡ ወእምዝ ዘአመ ዳግም ትዔሥር ክልኤተ ዓሥራተ ወትሁብ ለሌዋዊ ወለግዩርኒ ወለእጓለ ማውታ ወለዕቤር ይብልዕዎ በሀገርከ ወይጽገቡ ።

በሦስተኛው ዓመት ከመሬትህ ከተገኘው እኽል አሥራት አውጥተህ በጨረስክ ጊዜ ከዚህ በኋላ ሁለተኛ አሥራት አውጥተህ ለካህኑ ፡ ለስደተኛው ፡ ለባልቴትና ፡ እናት አባቱ ለሞቱበትም ልጅ ስጠው ፡ በአገርህም በልተው ይጥገቡ ። ዘሌ፡ ፳፯ ፴ ፡ ዘዳ፡ ፲፬ ፳፱ ።

፲፫ ወትብል በቅድመ እግዚአብሔር አምላክከ አንጻሕኩ ዘእቄድስ ለከ እምነ ቤትየ ወወሀብክዎ ለሌዋዊ ወለግዩር

በፈጣሪህ በእግዚአብሔር ፊት ከገንዘቤ ለይቼ ለስደተኛና ለካህን ለባልቴትና እናት አባቱ ለሞቱበት ልጅ አን

ወሰማዕኩ ቃለ እግዚአብሔር አምላኪየ ወገበርኩ በከመ ኵሉ ትእዛዝከ ዘአዘዝከኒ ኢተዐደውኩ ትእዛዘከ ወኢረሳዕኩ ።

፲፭ ወበሕማምየኒ ኢበላዕኩ እምኔሁ ፡ ወኢምዕኩ መሥዋዕተ ኃጢአት እምኔሁ ለርኩሰ ወኢወደይኩ ውስተ በድን እምኔሁ ወሰማዕኩ ቃለ እግዚአብሔር አምላኪየ ወገበርኩ ኵሎ ዘአዘዝከኒ ።

፲፮ ወነጽር እምቤተ መቅደስከ እምሰማይ ወባርክ ሕዝበከ እስራኤለ ወምድረ እንተ ወሀብከነ ዘከመ መሐልከ ለአበዊነ ከመ ተሀበነ ምድረ እንተ ትውሕዝ ሐሊበ ወመዓረ ።

፲፯ ወበዛቲ ዕለት እግዚአብሔር አምላክከ አዘዘከ ከመ ትግበር ኵሎ ዘንተ ኵነኔሁ ወትዕቀብ ፍትሐ ወትግበር በኵሉ ልብከ ወበኵሉ ነፍስከ ወትሕሩ በፍናዊሁ ወትዕቀብ ፍትሐ ወኵነኔሁ ወትስማዕ ቃሎ ።

፲፰ እስመ እግዚአብሔር ኀረየከ ዮም ከመ ትኩኖ ሕዝበ ለርእሱ በከመ ይቤለከ ከመ ትዕቀብ ኵሎ ትእዛዞ ወትኩን መልዕልተ ኵሉ አሕዛብ ።

፲፱ ወነበረ ለከ ስመ ዐቢየ ወምክሐ ወክብረ ከመ ትኩን ሕዝበ ቅዱሰ ለእግዚአብሔር አምላክከ በከመ ይቤለከ ።

ምዕራፍ ፳፯ ።

፩ ወአዘዞሙ ሙሴ ለአእሩግ እስራኤል ወይቤሎሙ ዑቁ ከመ ትግበሩ ኵሎ ዘንተ ትእዛዘ ዘአነ እኤዝዘክሙ ዮም ።

፪ ወአመ ተዐድውዎ ለዮርዳኖስ ውስተ ምድር ዘይሁበክሙ እግዚአብሔር አምላክክሙ ታቀውሙ ለክሙ አእባነ ዐበይተ ወትመርግዎን መሬተ ፀዐዳ ።

፫ ወትጽሕፉ ውስተ ውእቶን እእባን ኵሎ ነገረ ለዝንቱ ሕግ ሶበ ዐደውክሙ ዮርዳኖስ ሶበ ቦእክሙ ውስተ ይእቲ ምድር ዘይሁበክሙ እግዚአብሔር አምላክሙ ለአበዊክሙ በከመ መሐለ ሎሙ ከመ የሀብክሙ ምድረ እንተ ትውሕዝ ሐሊበ ወመዓረ በከመ ይቤለክሙ እግዚአብሔር አምላክሙ ለአበዊክሙ ።

፬ ወሶበ ዐደውክሙ ዮርዳኖስ ታቀውምዎን ውስተ ደብረ ጌባል ለውእቶን እእባን እለ አነ እኤዝዘክሙ ዮም በእንቲአሆን ወትመርግዎን መሬተ ፀዓዳ ።

፭ ወትነድቅ በህየ ምሥዋዐ ለእግዚአብሔር አምላክከ በአእባን ዘኢገሠሥዎን ሐፂን እለ ኢከና ውቁራተ ወበቶን ትነድቅ ምሥዋዐ ለእግዚአብሔር አምላክከ ።

፮ ወትሠውዕ ላዕሌሆን መሥዋዕተ መድኃኒት ፡ ብላዕ ወጽገብ በህየ ወተፈሣሕ በቅድመ እግዚአብሔር አምላክከ ።

፯ ወጸሐፍ ውስተ ውእቶን እእባን ፡ ዘንተ ኵሎ ሕገ ጥዩቀ ጥቀ ።

፰ ወይቤሎሙ ሙሴ ለካህናት ወለሌዋውያን ወለኵሉ ሕዝበ እስራኤል አርምም ወስማዕ እስራኤል በዛቲ ዕለት ኮንከ ሕዝበ ለእግዚአብሔር አምላክከ ፡ ወስማዕ ቃሎ ወግ

ጽፎ ሰጠሁት ፡ እንዳዘዝከኝ ትእዛዝም ሁሉ ትእዛዝህን አላፈረስኩም አልዘነጋሁም ።

ከሱም የአዝን እንጀራ አልበላሁም ፡ ከሱም ኃጢአት የሚሆን መሥዋዕት አልሠዋሁም ፡ ከሱም የቀብሬ እንጀራ አልበላሁም ፡ የፈጣሪዬን የእግዚአብሔርን ቃል ሰማሁ ፡ ያዘዝከኝንም ሁሉ ሰማሁ ። ዘሌ፡ ፯ ፳ ፡ ፳፪ ፲፱ ።

በሰማይ ሁነህ ማደሪያህ ቤተ መቅደስን ተመልከት ፡ ወገኖችህ እስራኤልንም አክብር ፡ ተድላ ደስታ የሚገኝ በት ምድርን ትሰጠን ዘንድ ለአባቶቻችን እንደ ማልክላ ቸው የሰጠኸንም ምድር አክብር ። ዘኁ፡ ፮ ፲፫ ።

ይህን ሁሉ ፍርዱን ታደርግ ዘንድ ትእዛዙንም ትጠ ብቅ ዘንድ በፍጹም ልቡናህ ፡ በፍጹም ሰውነትህ ትሠራው ዘንድ በሕጉም ጸንተህ ትኖር ዘንድ ፍርዱንና ሥርዓቱን ትጠብቅ ዘንድ ቃሉንም ትሰማ ዘንድ ፈጣሪህ እግዚአብ ሔር በዚች ቀን አዘዘህ ። ዘዳ፡ ፳፮ ፲፰ ።

ትእዛዙን ሁሉ ትጠብቅ ዘንድ ከአሕዛብም ሁሉ በላይ ትሆን ዘንድ እንደ ነገረህ የራሱ ወገን ትሆነው ዘንድ እግዚአብሔር ዛሬ መርጦሃልና ። ዘፀ፡ ፲፱ ፭ ።

እንደ ነገረህ ለፈጣሪህ ለእግዚአብሔር የተለየህ ወገን ትሆነው ዘንድ ታላቅ ስም አጠጣልህ ፡ እንድትመከና እን ድትከብርም አደረገህ ። ዘዳ፡ ፳፰ ፩ ፡ ፴፪ ፰ ።

ምዕራፍ ፳፯ ።

ሙሴ የእስራኤልን ሽማግሎች እንዲህ ብሎ አዘዛ ቸው ፡ እኔ አሁን የማዝዛችሁን ይህን ሁሉ ትእዛዝ ታደርጉ ዘንድ ዕወቁ ።

ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር ወደ ሚሰጣችሁ አገር ለመ ሄድ ዮርዳኖስን በተሻገራችሁ ጊዜ ለናንተ ታላላቅ ደንጊ ያዎችን አቁማችሁ በኖራ ቀቧቸው ። ኢያ፡ ፬ ፩ ።

ማርና ወተት የምታፈሰውን አገር ይሰጣችሁ ዘንድ የአባቶቻችሁ ፈጣሪ እግዚአብሔር እሰጣችኋለሁ ብሎ እን ደማለላቸው ዮርዳኖስን ተሻግራችሁ የአባቶቻችሁ ፈጣሪ እግዚአብሔር ወደ ሚሰጣችሁ ወደዚያች አገር በገባችሁ ጊዜ የዚህን ሕግ ነገር ሁሉ በነዚያ ደንጊያዎች ላይ ጻፉ ። ኢያ፡ ፰ ፴፪ ።

ዮርዳኖስን በተሻገራችሁ ጊዜ እኔ አሁን ስለ እነሳቸው የማዝዛችሁን እነዚያን ደንጊያዎች ጌባል በሚባል ተራራ ላይ አቁማችሁ በረንቅ (በኖራ) ቀቧቸው (ለቅልቋቸው) ።

ብረት በልነካቸው ባልለዘቡ ድንጋዮች ለፈጣሪህ ለእ ግዚአብሔር በዚያ መሠውያን ሥራ ፡ በነሳቸው ለፈጣሪህ እግዚአብሔር መሠውያን አዘጋጅ ። ዘፀ፡ ፳ ፳፭ ።

በነሳቸው ላይ ድኅነት የሚገኝበት መሥዋዕትን ሠዋ በዚያም በልተህ ጠግበህ በፈጣሪህ በእግዚአብሔር ፊት ደስ ይበልህ ። ኢያ፡ ፰ ፴፩ ።

ፈጽሞ የታወቀ (የተገለጠ) አድርገህ ይህን ሕግ ሁሉ በነዚያ ድንጋዮች ላይ ጻፍ ። ዘዳ፡ ፳፯ ፲፰ ።

ሙሴም ከህናትን ሌዋውያንንና የእስራኤልን ወገኖች ሁሉ እስራኤል ሆይ ፡ ዝም ብለህ ስማ በዚች ቀን ለፈጣ ሪህ ለእግዚአብሔር ወገን ሆንሃል ፡ ቃሉንም ስምተህ እሴ

በር ኵሉ ትእዛዞ ወኵነኔሁ ዘአነ እኤዝዘከ ዮም ።
፲፩ ወአዘዞሙ ሙሴ ለሕዝብ በይእቲ ዕለት ወይቤሎሙ
እሉ እሙንቱ እለ ይቀውሙ ወይባርክዎ ለሕዝብ በደ
ብረ ገሪዛን ዓዲወክሙ ዮርዳኖስ ፡ ስምዖን ወሌዊ ፡ ወይ
ሁዳ ፡ ወይሳኮር ፡ ወዮሴፍ ፡ ወብንያም ።
፲፫ ወእሉ እሙንቱ እለ ይቀውሙ ለረጊም በደብረ ጌባል
ሮቤል ፡ ወጋድ ፡ ወአሴር ፡ ወዛብሎን ፡ ወዳን ፡ ወንፍታሌም ።
፲፬ ወያወሥኡ ሌዋውያን ወይብልዎሙ ለኵሉ
እስራኤል በዐቢይ ቃል ።
፲፭ ርጉም ለይኩን ብእሲ ዘይገብር ግልፎ ወስብኮ ዘርኩስ
በኀበ እግዚአብሔር ግብረ ኬንያ ፡ ወዘይሠይም ወየኀብእ
ወያወሥኡ ፡ ኵሉ ሕዝብ ወይብሉ አሜን ወአሜን ።

፲፮ ርጉም ለይኩን ዘያስተሐቂ አቡሁ ወእሞ ፡ ወይብሉ
ኵሉ ሕዝብ አሜን ወአሜን ።
፲፯ ርጉም ለይኩን ዘይሰርቅ ደወለ ቢጹ ፡ ወይብሉ ኵሉ
ሕዝብ አሜን ወአሜን ።

፲፰ ርጉም ለይኩን ዘያስሕቶ ፍኖተ ለዕውር ፡ ወይብሉ
ሕዝብ አሜን ወአሜን ።
፲፱ ርጉም ለይኩን ዘይጌምዕ ፍትሐ ግዩር ወዘእጓለ ማው
ታ ወዘዐቤር ፡ ወይብሉ ኵሉ ሕዝብ አሜን ወአሜን ።

፳ ርጉም ለይኩን ዘይሰክብ ምስለ ብእሲተ አቡሁ እስመ
ከሠተ ኀፍረተ አቡሁ ፡ ወይብሉ ኵሉ ሕዝብ አሜን
ወአሜን ።
፳፩ ርጉም ለይኩን ዘይሰክብ ምስ ኵሉ እንስሳ ፡ ወይብሉ
ኵሉ ሕዝብ አሜን ወአሜን ።
፳፪ ርጉም ለይኩን ዘይሰክብ ምስለ እኅቱ እመኒ እንተ እም
አቡሁ ፡ ወእመኒ እንተ እምእሙ ፡ ወይብሉ ኵሉ ሕዝብ
አሜን ወአሜን ።
፳፫ ርጉም ለይኩን ዘይሰክብ ምስለ እመ ብእሲቱ ፡ ወይ
ብሉ ኵሉ ሕዝብ አሜን ወአሜን ።
፳፬ ርጉም ለይኩን ዘይዘብጦ ካልኦ በነገረ ጕሕሉት ፡ ወይ
ብሉ ኵሉ ሕዝብ አሜን ወአሜን ።
፳፭ ርጉም ለይኩን ዘይነሥእ ሕልያነ ከመ ይቅትል ነፍሰ
ወደመ ንጹሐ ፡ ወይብሉ ኵሉ ሕዝብ አሜን ወአሜን ።

፳፮ ርጉም ለይኩን ኵሉ ብእሲ ዘኢይቀውም ይግበር ቃለ
ዘውስተ ዝንቱ ሕግ ፡ ወይብሉ ኵሉ ሕዝብ አሜን ወአሜን ።

ምዕራፍ ፳፰ ።

፩ ወሶእመ ሰሚዐ ሰማዕከ ቃለ እግዚአብሔር አምላክከ
ወዐቀብከ ከመ ትግበር ኵሎ ትእዛዞ ዘአነ እኤዝዘከ ዮም
ይሬስየከ እግዚአብሔር አምላክከ መልዕልተ ኵሉ አሕዛበ
ምድር ።
፪ ወይበጽሐከ ዝንቱ ኵሉ በረከት ወይረክበከ ለእመ
ሰማዕከ ቃለ እግዚአብሔር አምላክከ ።

ዛሬ የማዝህን ትእዛዙንና ፍርዱን ሁሉ አድርግ አላቸው ።
ሙሴ በዚያች ቀን ሕዝቡን እንዲህ ብሎ አዘዛቸው ፤ ዮርዳኖስን በተሻገራችሁ ጊዜ ገሪዛን በሚባል ተራራ ላይ ቆመው ሕዝቡን የሚመርቁት እሊህ ናቸው ፤ ስምዖን ፡ ሌዊ ፡ ይሁዳ ፡ ይሳኮር ፡ ዮሴፍና ብንያም ናቸው ።
ለመርገምም በጌባል ተራራ የሚቆሙ እሊህ ናቸው ፤ ሮቤል ፡ ጋድ ፡ ዛብሎን ፡ አሴር ፡ ንፍታሌምና ዳን ናቸው ።
እነዚያ ሌዋውያንም ለእስራኤል ሁሉ በታላቅ ቃል እንዲህ ብለው ይመልሱላቸዋል ።
በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠላ (ርኩስ የሆነ) የተቀረጸ ጣኦትን የሚያደርግ ሰው ሠራሽ ጣኦትንም ሠውሮ የሚያኖር ሰው የተረገመ ይሁን ይበሉዋቸው ፡ ሕዝቡም ሁሉ መልሰው (አሜን) ይሁን ይሁን ይበሉ ። ዘፀ ፳ ፬ ።
እናት አባቱን የሚያቃልል ሰው የተረገመ ይሁን ፤ ይበሉዋቸው ሕዝቡም ሁሉ መልሰው ይሁን ይሁን ይበሉ ።
የባልንጀራውን ድንበር የሚሰርቅ (የሚያፈርስ) ሰው የተረገመ ይሁን ይበሏቸው ፡ ሕዝቡም ሁሉ መልሰው ይሁን ይሁን ይበሉ ።
ዕውሩን ጐዳና የሚያስተው የተረገመ ይሁን ይበሏቸው ፤ ሕዝቡም ሁሉ መልሰው ይሁን ይሁን ይበሉ ።
እናት አባቱ በሞቱበት ልጅ ፡ በመጻተኛና ፡ በበልቴትም ፍርድ የሚያደላ ሰው የተረገመ ይሁን ይበሏቸው ፤ ሕዝቡም ሁሉ መልሰው ይሁን ይሁን ይበሉ ።
ያባቱን ኀፍረት ገልጧልና ከእንጀራ እናቱ የደረሰ ሰው የተረገመ ይሁን ይበሏቸው ፡ ሕዝቡም ሁሉ መልሰው ይሁን ይሁን ይበሉ ። ዘሌ ፲፰ ፰ ፣ ዘዳ ፳፪ ፴ ።
በእንስሳም የሚደርስ ሁሉ የተረገመ ይሁን ይበሉዋቸው ፡ ሕዝቡም ሁሉ ይሁን ይሁን ይበሉ ።
ከአባቱ የተወለደች ወይም ከናቱ ከተወለደች ከእኅቱ የደረሰ ሰው የተረገመ ይሁን ይበሏቸው ፤ ሕዝቡም ሁሉ ይሁን ይሁን ይበሉ ። ዘሌ ፲፰ ፱ ፣ ፳ ፲፯ ።
በሚስቱ እናት በማቱ የሚደርስ ሰው የተረገመ ይሁን ይበሏቸው ፡ ሕዝቡም ሁሉ ይሁን ይሁን ይበሉ ።
በሥውር ባልንጀራውን የሚመታ ሰው የተረገመ ይሁን ይበሏቸው ፡ ሕዝቡም ሁሉ ይሁን ይሁን ይበሉ ።
ነፍስን ለመግደል ንጹሕ ደምንም ለማፍሰስ ማማለጃ (ጉቦ) የሚቀበል ሰው የተረገመ ይሁን ይበሏቸው ፡ ሕዝቡም ሁሉ ይሁን ይሁን ይበሉ ። ዘፀ ፳፫ ፰ ።
በዚህ ሕግ ያለውን ቃል ያደርግ ዘንድ የማይጸና ሰው የተረገመ ይሁን ይበሏቸው ፡ ሕዝቡም ሁሉ ይሁን ይሁን ይበሉ ። ዘዳ ፳፰ ፲፭ ፣ ኤር ፲፩ ፫ ። ገላ ፫ ፲ ።

ምዕራፍ ፳፰ ።

የፈጣሪህ የእግዚአብሔርን ቃል መስማትን ብትሰማ ፡ እኔም አሁን የማዝህን ትእዛዙን ሁሉ ታደርግ ዘንድ ሕጉን ብትጠብቅ ፈጣሪህ እግዚአብሔር በምድር ካሉ ከአሕዛብ ሁሉ በላይ ያደርግሃል ። ዘፀ ፲፭ ፳፮ ፣ ዘሌ ፳፮ ፫ ።
የፈጣሪህ የእግዚአብሔርን ቃል ከሰማህ (ይህ ሁሉ ምርቃት ይደርስሃል) ይደረግልሃል ። ዘዳ ፳፰ ፲፭ ።

| | | |
|---|---|---|
| ቡሩክ ትከውን በሐቅል ፡ ወቡሩክ ትከውን በሀገር ። | ፫ | በከተማም በበረኻም የተባረክህ የተመረቅህ ትሆናለህ ። |
| ቡሩክ ይከውን ፍሬ ከርሥከ ፡ ወቡሩክ ይከውን እክለ ምድርከ ወቡሩክ ይከውን መራዕየ አባግዒከ ወአልሕምቲከ ። | ፬ | የሆድህም ፍሬ (ልጅህ) የተመረቀ ይሆናል ከምድርህ የተገኘ አዝመራህም የተባረከ ይሆናል የበጎችህም የላሞችህም መንጋ የተባረከ ይሆናል ። ዘዳ፡ ፲፩ ፲፫ ፡ ፯ ፫ ። |
| ቡሩክ ይከውን መዛግብቲከ ወትራፋቲከ ። | ፭ | ድልብህና ግንዛብህም የተባረከ ይሆናል ። |
| ቡሩክ ትከውን በበአትከ ፡ ወቡሩክ ትከውን በፀአትከ ። | ፮ | በመግባትህና በመውጣትህም የተመረቅህ ትሆናለህ ። |
| ወያገብኦሙ እግዚአብሔር አምላክከ ውስተ እዴከ ለፀርከ ከመ ይትቀጥቀጡ በታሕተ እገሪከ ፡ በአሐቲ ፍኖት ይወፅኡ ይትቀበሉከ ፡ ወበሰብዑ ፍኖተ ይነትዑ እምቅድመ ገጽከ ። | ፯ | ፈጣሪህ እግዚአብሔርም ከእግርህ በታች ይወድቁ ዘንድ ጠላቶችህን በእጅህ ይጥልልኻል ፡ ይቀበሉህም ዘንድ በአንድ መንገድ ይመጡብኻል ፡ በሰባትም ጎዳና ከፊትህ ይሸሻሉ ። |
| ወይፌኑ እግዚአብሔር በረከቶ ውስተ አብያቲከ ወውስተ ኵሉ ዘወደይከ እዴከ በውስተ ምድር ዘወሀበከ እግዚአብሔር አምላክከ ። | ፰ | እግዚአብሔርም በቤትህ በረከቱን ይልክልኻል ፡ ፈጣሪህ እግዚአብሔር በሰጠህ ምድር በእጅህ በያዝከው ገንዘብህ ሁሉ በረከቱን ያሳድራል ። ዘሌ፡ ፳፭ ፳፩ ። |
| ወያቀውመከ እግዚአብሔር ሎቱ ሕዝበ ቅዱሰ በከመ መሐለ እግዚአብሔር ለአበዊከ ፡ ለእመ ሰማዕከ ቃለ እግዚአብሔር አምላክከ ወሖርከ በፍናዊሁ ። | ፱ | ፈጣሪህ የእግዚአብሔርን ቃል ከሰማህ ፡ በሕጉም ጸንተህ ከኖርህ እግዚአብሔር ለአባቶችህ እንደማለ ለሱ የተለየህ ወገን አድርጎ ያቆምኻል ። ዘፀ፡ ፲፱ ፮ ። |
| ወይሬእዩ ኵሉ አሕዛበ ምድር ከመ ተሰምየ ላዕሌከ ስሙ ለእግዚአብሔር አምላክከ ወይፈርሁከ ። | ፲ | በዚህ ዓለም ያሉ አሕዛብም ሁሉ የፈጣሪህ የእግዚአብሔር ስም በአንተ እንደ ተጠራ አይተው ይፈሩሃል ። |
| ወያስተበዝኀከ እግዚአብሔር አምላክከ ውስተ ሠናይት በውሉደ ከርሥከ ወበእክለ ምድርከ ። | ፲፩ | ፈጣሪህ እግዚአብሔርም ከአብራክህ በተከፈሉ ልጆችህ ከምድርህም በተገኘው አዝመራ በበጎ ረድኤት የብዙ ብዙ ያደርግኻል ። ምሳ፡ ፲ ፳፪ ። |
| ወያስተዋልዶን ለእንስሳከ በውስተ ምድር ዘመሐለ እግዚአብሔር አምላክከ ለአበዊከ ከመ የሀብከ በከመ መዋዕለ ሰማይ ዲበ ምድር ። | ፲፪ | ጠፈር በአድማስ ጸንቶ እንዲኖር ለአባቶችህ እንደ ማለላቸው ፈጣሪህ እግዚአብሔር በዚህ ዓለም አጽንቶ ያኖርህ ዘንድ ከብቶችህም እንዲዋለዱ ያደርጋቸዋል ። |
| ወይፈትሕ ለከ እግዚአብሔር መዝገበ ቡሩከ ፡ ሰማየ ከመ የሀብ ዝናመ በመዋዕሊሁ ለምድርከ ፡ ከመ ይባርክ ለከ ኵሎ ተግባረ እደዊከ ወትሌቅሕ አንተ ለብዙኃን አሕዛብ ወአንተሰ ኢትትሌቃሕ ፡ ወትኬንኖሙ አንተ ለብዙኃን አሕዛብ ፡ ወለከሰ ኢይኬንኑከ ። | ፲፫ | ምድርህ በምታበቅልበት ወራት ሰማይ ዝናም ለዘር ይሰጥህ ዘንድ ፡ የእጅህንም ሥራ ሁሉ ይባርክልህ ዘንድ እግዚአብሔር መልካሙን መዝገብ ሰማዩን ይከፍትልኻል ፡ አንተ ለብዙ አሕዛብ ታበድራለህ ፡ አንተ ግን አትበደርም አንተ ብዙ አሕዛብን ትገዛቸዋለህ ፡ አንተን ግን አይገዙህም ። ፬ ነገ፡ ፳፪ ፬ ፡ ምሳ፡ ፬ ፳፯ ። |
| ወይሠይመከ እግዚአብሔር ውስተ ርእስ ወአኮ ውስተ ዘነብ ፡ ወትከውን መልዕልተ ወኢትከውን መትሕተ ፡ ለእመ ሰማዕከ ቃለ እግዚአብሔር አምላክከ ወትእዛዘ ኵሉ ዘአነ እኤዝዘከ ዮም ከመ ትዕቀብ ወትግበር ። | ፲፬ | ዛሬ እኔ የማዝህን የፈጣሪህ የእግዚአብሔርን ቃል ብትሰማ ትእዛዙንም ብትጠብቅና ብትፈጽም ፡ እግዚአብሔር ራስ ያደርግኻል እንጂ ፡ ጅራት (ገዥ ያደርግኻል እንጂ ተገዥ) አያደርግህም ። ኢያ፡ ፩ ፯ ። |
| ወኢትትገሐሥ እምኵሉ ቃል ዘአነ እኤዝዘከ ዮም ኢየማነ ወኢፀጋመ ፡ ከመ ትሑር ድኅረ አማልክተ በዕድ ታምልኮሙ ። | ፲፭ | ታመልካቸው ዘንድ የአሕዛብን ጣኦታት በትከተልና እኔ ዛሬ ከዘዝኩህም ቃል ወደ ቀኝ ወደ ግራ በትል ፡ ከሁሉ በላይ ትሆናለህ እንጂ ከሁሉ በታች አትሆንም ። |
| ወለእመሰ ኢሰማዕከ ቃለ እግዚአብሔር አምላክከ ከመ ትዕቀብ ኵሎ ትእዛዞ ዘአነ እኤዝዘከ ዮም ይመጽእ ላዕሌከ ኵሉ ዝንቱ መርገም ወይረክበከ ። | ፲፮ | እኔ አሁን የማዝህን ትእዛዙን ሁሉ ትጠብቅ ዘንድ የፈጣሪህ የእግዚአብሔርን ቃል ብትሰማ ግን ይህ ሁሉ ርግማን ይደርስብኻል ፡ መከራም ያገኝኻል ። |
| ወትከውን ርጉመ አንተ በሐቅል ወበሀገር ። | ፲፯ | አንተ በከተማም በበረኻም የተረገምክ ትሆናለህ ። |
| ወይከውን ርጉመ መዛግብቲከ ወትራፋቲከ ። | ፲፰ | ድልብህም ግንዛብህም የተረገመ ይሆናል (ይጠፋል) ። |
| ወርጉመ ይከውን ፍሬ ከርሥከ ወእክለ ምድርከ ወመራዕየ አልሕምቲከ ወአባግዒከ ። | ፲፱ | ከአብራክህ የተከፈለ ልጅህም የተረገመ ይሆናል ፡ ከምድርህ የተገኘ አዝመራም ይጠፋል ፡ የበጎችህና የላሞችህም መንጋ ርጉም ይሆናል (ይጠፋል) ። |
| ወርጉም አንተ በበአትከ ፡ ወበፀአትከ ። | ፳ | አንተም በመግባትህም በመውጣትህም የተረገምክ ትሆናለህ ። ኢሳ፡ ፴ ፲፯ ፡ ፶፩ ፳ ። |
| ወይፌኑ እግዚአብሔር ላዕሌከ ንዴተ ወረኀበ ወብድብደ ወይጠፍእ ኵሉ ዘወደይከ እዴከ ውስቴቱ ወይሜር | ፳፩ | እግዚአብሔርም በንተ ረኃብን ፡ ችጋርን ፡ ቸነፈርን ያመጣብኻል በእጅህ የያዝከውም ሁሉ ይጠፋል ፡ እስን |

| | | |
|---|---|---|
| ወከ እስከ ይደመስስከ ፍጡነ በበይነ እከየ ምግባሪከ እስመ ኀደገኒ ። | | ትተኸኛልና ስለ ሥራህ ክፋት ፈጥኖ እስኪያጠፋህ ድረስ ሞትን ያጠፋኻል ። ዘዳ፡ ፯ ፳፫ ፡ ሚክ፡ ፪ ፱ ። |
| ወያተሉ እግዚአብሔር ሞተ ላዕሌከ እስከ ያጠፍአከ ፍጡነ እምድር እንተ ውስቴታ ትበውእ ህየ ከመ ትት ዋረሳ ። | ፳፩ | ትወርሳት ዘንድ አንተ ከምትገባበት ምድር ፈጥኖ እስኪያጠፋህ ድረስ እግዚአብሔር ሞትን ያመጣብኻል ። ዘሌዋ፡ ፳፯ ፲፯ ። |
| ወይቀሥፈከ እግዚአብሔር በጸዊ ሲሕ ፡ ወበፈጸንት ፡ ወበአስሬር ፡ ወበፍርሃት ፡ ወበድንጋጼ ፡ ወበዐባር ፡ ወበኀጢእ ፡ ወይሰድዱከ እስከ ያጠፍኡከ ። | ፳፪ | እግዚአብሔርም (በደዌ ሲሕ) በሆድ ደዌና በንዳድ ፡ (አስሬር) በቍርማት በፍርሃት ፡ በድንጋጼ ፡ በድርቅና እኽልን በማጣት ያጠፋኻል እስኪያጠፋህም ድረስ ከገር አውጥተው ይሰዱኻል ። ዘሌ፡ ፳፯ ፲፮ ፡ ፩ ነገ፡ ፰ ፴፯ ። |
| ወትከውን ሰማይ በመልዕልተ ርእስከ ብርተ ፡ ወምድርኒ በታሕቴከ ሐፂነ ። | ፳፫ | ከራስህ በላይ ያለች ሰማይ ናስ ትሆንብሃለች በበታችህ ያለች ምድርም ብረት ትሆንብሃለች ። ዘሌ፡ ፳፯ ፲፱። |
| ወይሬስዮ እግዚአብሔር ለዝናመ ምድርከ ቆብረ ፡ ወመሬት ይወርድ እምሰማይ ላዕሌከ እስከ ይቀጠቅጠከ ወእስከ ያጠፍአከ ። | ፳፬ | እግዚአብሔርም በምድርህ ላይ የሚዘንመውን ዝናም ጽጋግ ያደርገዋል ፡ ፈጽሞ እስኪያጠፋህም ድረስ አፈር (ዋግ) ከሰማይ ይወርድብኻል ። |
| ወይገብረከ እግዚአብሔር ከመ ትትቀተል በቅድመ ፀርከ በአሐቲ ፍኖት ትወፅእ ኀቤሆሙ ፡ ወበሰቡዑ ፍናው ትነትዕ እምቅድመ ገጾሙ ወትከውን ዝርወ ውስተ ኵሉ መንግሥታተ ምድር ። | ፳፭ | እግዚአብሔር በጠላትህ ፊት እንድትሞት ያደርግኻል በአንዲት ጐዳና ወደነሳቸው ወጥተህ ከፊታቸው በሰባት ጐዳና ትሸሻለህ በአሕዛብ መንግሥታትም ሁሉ ትበተናለህ ። ኤር፡ ፲፭ ፬ ፡ ሕዝ፡ ፳፫ ፵፮ ። |
| ወይከውኑ አብድንቲከ መብልዐ ለአዕዋፈ ሰማይ ወኢ ትረክብ ዘይቀብረከ ። | ፳፮ | የሚቀብርህ አጥተህ ሬሳዎችህ ለሰማይ ወፎች ምግብ ይሆናሉ ። ፩ ሳሙ፡ ፲፯ ፵፬ ፡ መዝ፡ ፸፱ ፪ ። |
| ወይቀሥፈከ እግዚአብሔር በመቅሠፍተ ግብጽ በዐበቅ አኩይ ውስተ ነፍስትከ ወበሀከክ ዘአልቦ ፈውስ ። | ፳፯ | እግዚአብሔር የግብጽ ሰዎችን ባጠፋበት መቅሠፍት በክፉ ችፌ ድኅንነት በሌለበት እከክ ሰውነትህን ያጠፋኻል ። |
| ወይቀሥፈከ እግዚአብሔር በድቀት ወበዓዊር ወበድንጋጼ ልብ ። | ፳፰ | እግዚአብሔር በመውደቅ ፡ በዕውርነት (በድንብርብር) በልቡናም ድንጋጤ ያጠፋሃል ። ዘዳ፡ ፳፰ ፴፬ ። |
| ወትገብእ ወታመረስስ መዐልተ ከመ ያመረስስ ዕዉር በውስተ ጽልመት ወኢትረክብ ፍኖተ ወትትገፋዕ ወትት በረበር በኵሉ መዋዕሊከ ወኢትረክብ ዘይረድአከ ። | ፳፱ | ዕውር በጨለማ እንዲርመሰመስ ተመልሰህ በቀን ትርመሰመሳለህ መንገድም አታገኝም ፡ በዘመንህም ሁሉ የተገፋህ የተዘረፍህም ትሆናለህ የሚረዳህንም አታገኝም ። |
| ወታወስብ ብእሲተ ወየሀይደክያ ካልእ ብእሲ ፡ ወትነድቅ ቤተ ወኢትነብር ውስቴቱ ፡ ወትተክል ወይነ ወኢ ትቀሥሞ ። | ፴ | ሚስት ታገባለህ ሌላም ሰው ይቀማኻል ፡ ቤትም ትሠራለህ አትኖርበትም ፡ ወይንን ትተክላለህ ፡ ነገር ግን ፍሬውን አትለቅምም ። ዘዳ፡ ፳፰ ፯ - ፺ ፡ ፳ ፮ ። |
| ወይጠብሑ ላሕመከ ወኢትበልዕ እምኔሁ ፡ ወየሀይዱ አድግከ ወኢያገብኡ ለከ ፡ ወይገብኡ አባግዒከ ለአግብርት ወለፀርከ ወኢትረክብ ዘይረድአከ ። | ፴፩ | በሬህን ያርዱታል ነገር ግን ከሥጋው አትበላም ፡ አህያህን ይቀሙኻል አይመልሱልህም ፡ በጎችህን ለጠላቶችህና ለባሮችህ አሳልፈው ይሰጣሉ የሚረዳህም አታገኝም ። |
| ወይገብኡ ደቂቅከ ወአዋልዲከ ለካልእ ሕዝብ ወትሬኢ በአዕይንቲከ እንዘ ይኩረዕዎሙ ወአልቦ ዘትክል ገቢረ ። | ፴፪ | ወንዶች ልጆችህና ሴቶች ልጆችህ ተማርከው ወደ አሕዛብ ይሄዳሉ ፡ ራስ ራሳቸውን ሲቀጠቅጧቸው በዓይኖችህ ታያለህ ፡ ነገር ግን ምንም የምታደርገው ነገር የለም ። |
| ወይበልዕ ሕዝብ ነኪር ዘኢተአምር እክለ ምድርከ ወጻማከ ፡ ወትከውን ጽዑረ ወሥቁየ በኵሉ መዋዕል ። | ፴፫ | ከምድርህም የተገኘውን አዝመራህን የደከምክበትን ገንዘብህን የማታውቀው ሕዝብ ይበላብኻል ፡ አንተም በዘመንህ ሁሉ የተጨነቅህና የተገፋህ ትሆናለህ ። |
| ወትከውን ምሑዐ በምርአየ አዕይንቲከ ወኢትሬኢ ። | ፴፬ | ዓይኖችህ በሚያዩት ሁሉ ትሸሻለህ ፡ አታይም (ምሑዐ ዕብድ ትሆናለህ) ። |
| ወይቀሥፈከ እግዚአብሔር በደዌ አኩይ ውስተ ብረኪከ ወውብተ አቍያጺከ ወውስተ አዕማደ እገሪከ በዘኢ ትክል ሐይወ እምሰኰና እግርከ እስከ ርእስከ ። | ፴፭ | ከጫማህ ጀምሮ እስከ ራስህ ድረስ መዳን በማትችል ገንዘብ እግዚአብሔር ጕልበትህን ጭንህን በትህን በሚያሳብጥ በክፉ ደዌ ይመታኻል ። ዘዳ፡ ፳፰ ፳፯ ። |
| ወይወስደከ እግዚአብሔር ኪያከኒ ወመላእክቲከኒ ዘሜምከ ለከ ውስተ ሕዝብ ዓቢይ ዘኢተአምር አንተ ወኢ አበዊከ ፡ ወታመልክ በህየ ባዕዳነ አማልክተ ዕፀወ ወአእበነ ። | ፴፮ | እግዚአብሔር በብዙ ሕዝብ ላይ ከሾመልህ አለቆችህ ጋር አንተ ወደማታውቀው አባቶችህም ወደማያውቁት አገር አስማርከ ይወስድኻል ፡ በዚያም ሌሎች የዕንጨትና የድንጋይ አማልክትን ታመልካለህ ። |

፴፰ ወትከውን በህየ ድንጉፀ፡ ወትከውን አምሳለ ወነገረ
ለኵሉ አሕዛብ ዘኀቤሆሙ ይወስደከ እግዚአብሔር ።

፴፱ ወታወፅእ ብዙኀ ዘርአ ውስተ ገራህትከ ወታበውእ
ውኁደ እስመ አንበጣ በልዖ ።
፵ ወትተክል ዐፀደ ወይን ወትትጌበሮ ወኢትሰቲ እም
ወይኑ ወኢትትፌሣሕ በቱ እስመ ዕፄ አኩይ በልዖ ።
፵፩ ወታጠሪ ዕፀወ ዘይት ውስተ ኵሉ ደወልከ ወኢትት
ቀባዕ ቅብአ እምኔሁ እስመ ተነግፈ ፍሬሁ ።
፵፪ ወትወልድ ደቂቀ ወአዋልደ ወኢያተርፍዎሙ ለከ
እስመ ይነሥእዎሙ ወይፄውውዎሙ ።
፵፫ ወለኵሉ እክለ ምድርከ ወለኵሉ ተክለ ዕፀዊከ አና
ኵዕ ያጠፍኦ ።
፵፬ ወፈላሲ ዘሀለወ ኀቤከ የዐርግ መልዕልቴከ ወአንተሰ
ትከውን መትሕተ ።
፵፭ ወውእቱ ይሌቅሐከ ወአንተ ኢትሌቅሖ፡ ውእቱ
ይከውነከ ርእሰ፡ ወአንተ ትከውኖ ዘነበ ።

፵፮ ወይመጽእ ላዕሌከ ዝንቱ ኵሉ መርገም ወይዴግነከ
ወይረክበከ እስከ ያጠፍአከ ወይደመስሰከ፡ እስመ ኢሰማ
ዕከ ቃለ እግዚአብሔር አምላክከ ከመ ትዕቀብ ትእዛዞ
ወኵነኔሁ ወኵሎ ዘአዘዘከ ።
፵፯ ወይውን ትእምርተ ላዕሌከ ወመድምም ላዕለ ዘርእከ
እስከ ለዓለም እስመ ኢያምለክሁ ለእግዚአብሔር አምላክከ
በትፍሥሕት ወበሠናይ ልብ ።
፵፰ ወበዝ ኵሉ ትትቀነይ ለጸላእትከ ዘይፌኑ እግዚአብ
ሔር ላዕሌከ በረኃብ፡ ወበጽምእ፡ ወበዕርቃን ወበኀጢአ
ኵሉ፡ ወይወዲ ለከ ጋጋ ዘሐፂን ውስተ ክሳድከ እስከ
ያጠፍአከ ።
፵፱ ወያመጽእ እግዚአብሔር ላዕሌከ ሕዝበ እምርሑቅ
እምአጽናፈ ምድር ከመ ርዶተ ንስር ሕዝብ ዘኢትሰምዕ
ነገሮሙ ።
፶ ሕዝብ ግሩመ ገጽ ዘኢያከብር ገጸ ልሂቅ፡ ወኢይምህር
ንኡሰ ።
፶፩ ወያጠፍእ እጕለ መራዕይከ ወእክለ ምድርከ እስከ
ኢያተርፍ ለከ እክለ፡ ወኢ ወይነ፡ ወኢ ቅብአ፡ ወኢ መ
ራዕየ አልሕምቲከ ወአባግዒከ እስከ ያጠፍአከ ።
፶፪ ወይደመስሰከ እምውስተ ኵሉ አህጉሪከ እስከ ያወድቅ
አረፋቲከ ዐበይተ፡ ወእጽዋኒከ ዘዐቶን ትትአመን ዘውስተ
ኵሉ በሐውርቲከ ወይሣቅየከ በውስተ ኵሉ አህጉሪከ ዘወ
ሀበከ እግዚአብሔር አምላክከ ።
፶፫ ወትገብእ ትብላዕ ውሉደ ከርሥከ ሥጋ ደቂቅከ ወአ
ዋልዲከ ዘወሀበከ እግዚአብሔር አምላክከ በምንዳቤከ
ወበሥቃይከ ዘሣቀየከ ጸላኢከ በውስተ አህጉሪከ ።
፶፬ ዘርህጺ ወለምለሚ ወትደንዖ ዐይኑ ለእኁሁ ወለ
ብእሲቱ እንተ ውስተ ኅፅኑ ወለዘተርፉ ውሉድ ዘአትረፉ
ሎሙ ።

በዚያም የደነገጥህ ትሆናለህ፡ እግዚአብሔር አስማርኮ በሚወስድህ በዚያም ለአሕዛብ መተረቻ መዘበቻ ትሆናለህ ። ፩ ነገ፡ ፱ ፰፡ ኤር፡ ፳፬ ፱፡ ሕዝ፡ ፲፬ ፰ ።

በእርሻህ ብዙ ዘር ዘርተህ ጥቂት ታገባለህ፡ አንበጣ በልቶታልና ። ሚክ፡ ፮ ፲፭፡ ሐጌ፡ ፩ ፮ ።

ወይን ተክለህ ትኰተኵተዋለህ ነገር ግን ከወይኑ አትጠጣም፡ በሱም ደስ አይልህም ክፉ ትል በልቶታልና ።

በአውራጃህ ሁሉ የዘይት ወይራን ትተክላለህ፡ ነገር ግን ፍሬው ረግፏልና ከሱ ዘይቱን አትቀባም ።

ወንዶች ልጆችንና ሴቶች ልጆችን ትወልዳለህ፡ ነገር ግን ማርከው ይወስዱዋቸዋል፡ አያስቀሩልህም ።

ከምድርህ የተገኘ አዝመራህን አታክልትህንም ሁሉ ኩብኩባ ያጠፋዋል ።

በንተ ዘንድ ያለ ስደተኛ ከንተ በላይ ይሆናል፡ አንተም ከሱ በታች ትሆናለህ ። ዘዳ፡ ፳፰ ፲፫ ።

እሱ ያበድርሃል፡ አንተ ግን አታበድረውም፡ እሱ ራስ ይሆንሃል፡ አንተ ግን ጅራት ትሆነዋለህ፡ (እሱ ገዥ ይሆንሃል፡ አንተ ተገዥ ትሆነዋለህ) ። ዘዳ፡ ፳፰ ፲፪ ።

ይህ ሁሉ ርግማን ይደርስብሃል፡ ትእዛዙንና ፍርዱን ያዘዘህንም ሁሉ ትጠብቅ ዘንድ የፈጣሪህ የእግዚአብሔርን ቃል አልሰማህምና ፈጽሞ እስኪያጠፋህ ድረስ ይህ ሁሉ መከራ ተከትሎ ያገኝሃል ።

ፈጣሪህ እግዚአብሔርን በተድላ በደስታ፡ በበጎ ልቡና ሁነህ አላመለክኸውምና በንተ ተአምራት ይደረግብሃል በልጆችህም ለዘለዓለሙ ድንቅ ተአምራት ይደረግባቸዋል ።

በዚህም ሁሉ ላይ እግዚአብሔር በሚሰድቡህ ጠላቶችህ ትገዛለህ በውኃ ጥምና፡ በረኃብ፡ ከልብስ በመራቆትና ሁሉንም በማጣት ትገዛለህ፡ እስኪያጠፋህም ድረስ በአንገትህ ላይ የብረት ቀንበር (ጽኑ አገዛዝ) ያገባብሃል ።

እግዚአብሔር ከአገር ዳርቻ ከሩቅ አገር ቋንቋቸውን የማትሰማው አሕዛብን እንደ አሞራ አወራረድ ፈጥኖ ያመጣብሃል ።

ፊቱ የሚያስፈራ የሽማግሌን ፊት የማያከብር፡ ለሕፃንም የማይራራ አሕዛብን ያመጣብሃል ።

ወይንህን ዘይትህን የላሞችህንና የበጎችህን መንጋ ሳያስቀር እስኪያጠፋህ ድረስ ደርሶ ከምድርህ የተገኘውን አዝመራህ ያጠፋብሃል ። ዘዳ፡ ፳፰ ፴፫ ።

በአገርህ ያሉ የምትታመንባቸው አምባዎችህንና የጸኑ ቅጽሮችህን እስኪያፈርሳቸው ድረስ ደርሶ ከአገሮችህ ሁሉ ያጠፋሃል፡ ፈጣሪህ እግዚአብሔር በሰጠህ አገሮችህ ሁሉ መከራ ያጸናብሃል ። ፪ ነገ፡ ፳፭ ፬ ።

በአገርህ ሳለህ ጠላትህ በመጣብህ መከራ ሁሉ ፈጣሪህ እግዚአብሔር የሰጠህን ከባሕርይህ የተወለዱ የሴቶች ልጆችህንና የወንዶች ልጆችህን ሥጋ ትበላለህ ።

በአንተ ዘንድ ተደላድሎና ተቀማጥሎ ሁሉ ጊዜ ይኖር የነበረ ሰው ዓይኑ ወንድሙንና አቅፋው የምትተኛ ሚስቱን አሕዛብ ያስቀሩዋቸው፡ የቀሩ ልጆቹንም ትነፍጋቸዋለህ ። ዘዳ፡ ፲፭ ፱፡ ፲፫ ፮ ።

፶፭ ወይሁብሞሙ ለለአሐዱ እምኔሆሙ ሥጋ ውሉዶሙ ይሴሰዩ ፡ እስመ ኢያተረፉ ሎሙ ወኢምንተኒ በሥቃይ ወበምንዳቤ ዘሣቀዩከ ጸላእትከ በኵሉ አህጉሪከ ።

በአገሮችህ ሁሉ ሳለህ ጠላቶችህ በጸኑብህ መከራ ፡ ምንም ምን አላስቀሩላቸውምና ይመገቡ ዘንድ ከነሳቸው ላንዱም ላንዱም የልጆቻቸውን ሥጋ ይሰጡዋቸዋል ።

፶፮ ወእንተ ርህጽትኒ ይእቲ እምኔክሙ ፡ ወእንተኒ ድክምት ይእቲ ትሜህሮን ለእገሪሃ ሐዊረ ውስተ ምድር እስመ ርኅጽት ይእቲ ወድክምት ወትደነዕም ዐይና ለምታ ዘዲበ ኀፅና ወለወልዳ ወለወለታ ።

ድልድል ቅምጥል ነበረችና ደካማም ናትና ፡ ለእግሮቿ መንገድ ታስተምራቸዋለች ፡ ዓይኗም በጠገቧ የሚተኛ ባሏን ይነፍገዋል ፡ ሴት ልጅዋንና ወንድ ልጅዋንም ይነፍጋቸዋል ። ዘዳ፡ ፳፰ ፶፬ ፡ ኢሳ፡ ፵፯ ፩ ።

፶፯ ወለሥጋሃ ዘእምውስተ አባላ ውእቱ ወሕፃና ዘወለደት ትበልዕ ጽሚተ ስበ ኀጥአት ኵሎ በምንዳቤ ወበሥቃይ ዘይሣቅየከ ጸላኢከ በውስተ አህጉሪከ ።

ከወገኗ የተወለደ ዘመዷንም ዓይኗ ይነፍገዋል ፡ በአገርህ ሳለህ ጠላትህ በጸናብህ መከራ ተይዛ ሁሉን ባጣች ጊዜ በእራስ ቤቷ የወለደችው ልጅዋን በሥውር ትበላዋለች ። ዘፍ፡ ፴፱ ፲ ።

፶፰ ወለእመ ኢሰማዕከ ከመ ትግበር ኵሎ ዘንተ ነገሮ ለዝንቱ ሕግ ዘጽሑፍ ውስተ ዝንቱ መጽሐፍ ከመ ትፍራህ ስመ ክቡረ ወስቡሐ ዘእግዚአብሔር አምላክከ ።

በዚህ መጽሐፍ የተጻፈ የዚህን ሕግ ነገር ሁሉ ታደርግ ዘንድ ይህን የከበረና የተመሰገነ የፈጣሪህ የእግዚአብሔርን ስም ትፈራ ዘንድ ባትሰማ ። ዘፀ፡ ፮ ፫ ።

፶፱ ወይገብር እግዚአብሔር ነኪረ መቅሠፍተከ ፡ ወመቅሠፍተ ዘርእከ ፡ ወመቅሠፍተ ዐቢየ ወመድምመ ፡ ወደዌ እኩየ ወሕማመ ።

እግዚአብሔር ያንተንና የልጆችህን መቅሠፍት ልዩ ያደርግብኻል ፡ ታላቅ መቅሠፍትን ክፉ ደዌንና ጽኑ መከራን ያመጣብኻል ። መዝ፡ ፲፯ ፯ ፡ ፻፩ ፳፩ ።

፷ ወይገብእ ላዕሌከ ኵሉ ደዌሆሙ ለግብጽ እኩይ ዝክቱ ዘኢፈራህከ እምኔሁ ወኢፈራህከ እምቅድመ ገጹ ወያተሉ ዲቤከ ።

ከመገለጹ የተነሣ ያልፈራኸው ያ ጽኑ የግብጻውያን መከራ ሁሉ ወዳንተ ይመለሳል ። ዘዳ፡ ፯ ፲፭ ።

፷፩ ወኵሎ ደዌ ወኵሎ መቅሠፍተ ዘኢኮነ ጽሑፈ ውስተ ዝንቱ መጽሐፈ ሕግ ያመጽእ እግዚአብሔር ላዕሌከ እስከ ያጠፍአከ ወእስከ ትደመሰሱ ።

ሕግ በተጻፈበት በዚህ መጽሐፍ ያልተጻፈ ደዌ ሁሉ መቅሠፍቱም ሁሉ ወዳንተ ይመልሳል ፡ እስኪያጠፋህም ድረስ ደርሶ እናንተ ፈጽማችሁ እስክትደመሰሱ ድረስ መከራውን ሁሉ ያመጣባችኋል ።

፷፪ ወትተርፉ ኅዳጣነ በኍልቍ እምድኅረ ኮነ ከመ ከዋክብተ ሰማይ ብዝኅከ እስመ ኢሰማዕከ ቃለ እግዚአብሔር አምላክከ ።

የፈጣሪህ የእግዚአብሔርን ቃል አልሰማህምና ብዛትህ እንደ ሰማይ ከዋክብት ከሆነ በኋላ በቍጥር ጥቂት ትቀራላችሁ ። ዘዳ፡ ፳፮ ፭ ፡ ፲ ፳፪ ።

፷፫ ወበከመ ተፈሥሐ እግዚአብሔር ላዕሌከ ከመ ይግበር ሠናያተ ለከ ወአብዝኀከ ከማሁ ይትፌሣሕ እግዚአብሔር ዲቤከ ከመ ይሥሩከ ወትጠፍእ እምድር እንተ ውስቴታ ትበውእ ህየ ከመ ትትዋረሳ ።

በን ነገር ሊያደርግልህ እግዚአብሔር በንተ ደስ እንዳለው እንዳበዛህም ያጠፋህም ዘንድ እግዚአብሔር በንተ ጥፋት ደስ ይለዋል ፡ ትወርሳት ዘንድ በዚያ በምትገባበት ምድር ትጠፋለህ ። ኢሳ፡ ፷ ፭ ፡ ኤር፡ ፴፪ ፵፩ ።

፷፬ ወይዘርወከ እግዚአብሔር አምላክከ ውስተ አሕዛብ እምአጽናፈ ምድር እስከ አጽናፈ ምድር ፡ ወትትቀነይ በህየ ለበዕዳን አማልክት ፡ ለዕፀው ወለአእባን ዘኢተአምር አንተ ወኢ አበዊከ ።

ፈጣሪህ እግዚአብሔር ከምድር ዳርቻ ጀምሮ እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ በአሕዛብ አገር ይበትንኻል ፡ በዚያም አንተ ለማታውቃቸው አባቶችህም ለማያውቋቸው ለልዩ ልዩ ጣኦታት ለደንጊያዎችና ለዕንጨቶች ትገዛለህ ።

፷፭ ወበህየኒ በውስተ ውእቱ አሕዛብ ኢያዐርፈከ ወኢያበውሐከ ትቁም በእግርከ ፡ ወይሁበከ በህየ እግዚአብሔር ልበ ኅዙነ ወአዕይንተ ጥፉአተ ወነፍሰ ሙስንተ ።

በዚያም በአሕዛብ አገር ከመከራ አያሳርፍህም በእግርህም ትቆም ዘንድ አያሳናብትህም ፡ በዚያም እግዚአብሔር ልቡናህን ያሳዝነዋል ፡ ዓይንህን ያፈዘዋል ሰውነትህንም ያደክመዋል ። ዘሌ፡ ፳፮ ፴፮ ፡ አሞ፡ ፱ ፬ ።

፷፮ ወትከውን ሕይወትከ ስቅልተ ቅድመ አዕይንቲከ ወትደነግፅ ለሊከ መዐልተ ወሌሊተ ወኢትትአመን ለሕይወትከ ።

ድኅነትህ ከዓይንህ የራቀች (የተሰቀለች) ትሆናለች ፡ አንተም ቀንም ሌትም ትደነግጣለህ ፡ ሕይወትህንም አታምናትም ።

፷፯ ለአመ ጸብሐ ትብል እፎ እንጋ ይመሲ ፡ ወለእመ መስየ ትብል እፎ እንጋ ይጸብሕ እምፍርሃተ ልብ ዘትደነግፅ ወእምዘያስተርእየከ ውስተ አዕይንቲከ ወዘትሬኢ ።

ሲነጋ እንጃ እንዴት ይመሻል ትላለህ ፡ ሲመሽም ስለ ልብህ ፍርሃት በዓይንህም ከሚታይህ አንተም ከምታየው የተነሣ ሲመሽ እንጃ ፡ እንዴት ይነጋል ትላለህ ።

፷፰ ወያገብአከ እግዚአብሔር ውስተ ግብጽ በአሕማር ወእንተ ምድርኒ በእግር ዝንቱ ዘእቤለከ ኢትደግሙ እንከ ርእዮታ ዓዲ ።

እግዚአብሔርም በባሕር በመርከብ በየብስም በእግር ወደ ግብጽ ይመልስኻል ፡ ዳግመኛ አታያትም ያልኩህ ይህ ነው ። ኤር፡ ፵፫ ፯ ፡ ሆሴዕ ፰ ፲፫ ።

| | | |
|---|---|---|
| ወትከውኑ በህየ አግብርተ ወአእማተ ለፀርክሙ ወአልቦ ዘይምሕረክሙ ። | ፷፰ | በዚያም ለጠላቶቻችሁ ሴቶች ባሮችና ወንዶች ባሮች ትሆናላችሁ ይቅር የሚላችሁም የለም ። |
| ምዕራፍ ፳፱ ። | | ምዕራፍ ፳፱ ። |
| ወዝንቱ ውእቱ ነገረ ኪዳን ዘአዘዘ እግዚአብሔር ለሙሴ ከመ ይትከየዶሙ ለደቂቀ እስራኤል በምድረ ሞአብ ዘእንበለ ዝክቱ ኪዳን ዘተከየዶሙ በኮሬብ ። | ፩ | በኮሬብ ከተማማላቸው ከዚህ ቃል ኪዳን ነገር በቀር የእስራኤልን ልጆች በሞአብ አውራጃ ይማማላቸው ዘንድ እግዚአብሔር ለሙሴ ያዘዘው የቃል ኪዳን ነገር ይህ ነው ። |
| ወጸውዖሙ ሙሴ ለኵሉ ደቂቀ እስራኤል ወይቤሎሙ ለሊክሙ ርኢክሙ ኵሎ ዘገብረ ለክሙ እግዚአብሔር በምድረ ግብጽ ላዕለ ፈርዖን ወላዕለ መንግብቱ ወላዕለ ኵሉ ዓበይቱ ወላዕለ ኵሉ ምድሩ ። | ፪ | ሙሴም የእስራኤልን ልጆች ሁሉ ጠርቶ ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር በፈርዖንና በሹማምንቱ በመኳንንቱም በአገሩም ሁሉ በግብጽ አገር ያደረገላችሁን ሁሉ እናንተ አይታችኋል አላቸው ። ዘፀ፡ ፲፱ ፬፡ ዘዳ፡ ፳ ፫ ። |
| መቅሠፍተ ዓቢየ ዘርእያ አዕይንቲክሙ ወዝክተ ተአምረ፡ ወመድምመ ዐቢየ፡ ወእደ ጽንዕተ፡ ወመዝራዕተ ልዑለ ። | ፫ | ዓይኖቻችሁ ያዩትን መቅሠፍትን ያንንም የተደነቀና ገናና ተአምራት የጸናች እጅንና የተዘረጋች ክንድን አይታችኋል ። |
| ወወሀበክሙ እግዚአብሔር አምላክክሙ ልበ ከመ ታእምሩ፡ ወዐይነ ከመ ትርአዩ፡ ወዕዝነ ከመ ትስምዑ፡ እስከ ዛቲ ዕለት ። | ፬ | ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔርም ታውቁ ዘንድ ልብን፡ ታዩ ዘንድ ዓይንን ትሰሙ ዘንድ ጆሮን እስከዚች ቀን ድ ስ ሰጣችሁ ። ኢሳ፡ ፮ ፱፡ ዮሐ፡ ፲፪ ፵፫ ። |
| ወወሰደክሙ አርብዐ ዐመተ ውስተ ገዳም፡ ወአልባሲክሙኒ ኢበልየ ወአሣእኒክሙኒ ኢበልየ እምእገሪክሙ ። | ፭ | እግዚአብሔር በምድረ በዳ አርባ ዘመን አዘራችሁ፡ ልብሳችሁ አላለቀም፡ በእግራችሁ ያለ ጫማችሁም አላረጀም ። ዘዳ፡ ፩ ፫፡ ፰ ፬ ። |
| እንዘ እክለ ኢትበልዑ፡ ወወይነ ወሜሰ ኢትሰትዩ እስከ በጻሕክሙ ውስተ ዝንቱ መካን ከመ ታእምሩ ከመ ውእቱ እግዚአብሔር አምላክክሙ ። | ፮ | እሱ እግዚአብሔር ፈጣሪያችሁ እንደሆነ ታውቁ ዘንድ እኽል ሳትበሉ፡ ወይንንና ጠጅን ሳትጠጡ፡ እስከዚህ ቦታ ድረስ ደረሳችሁ ። ዘፀ፡ ፲፮ ፬፡ ዘዳ፡ ፰ ፫ ። |
| ወወፅአ ሴዎን ንጉሠ አሞሬዎን ወዖግ ንጉሠ ባሳን፡ ወተቀበሉክሙ ይትቃተሉክሙ ወቀተልናሆሙ ወነሣእነ ምድሮሙ ። | ፯ | የባሳን ንጉሥ ዖግና የሐሴቦን ንጉሥ ሴዎን ወጥተው ይዋጓችሁ ዘንድ ተቀበሏችሁ፡ ወጋናቸው አገራቸውንም ወሰድን ። ዘዳ፡ ፪ ፴፪፡ ፫ ፩ ። |
| ወወሀብክዎሙ ይእተ ምድረ ለሮቤል ወለጋድ ወለመንፈቀ ነገደ ምናሴ ። | ፰ | ያችንም አገር ለሮቤልና ለጋድ ለምናሴ ነገድ እኩሌታም ሰጠኋቸው ። ዘዳ፡ ፫ ፲፫፡ ዘኍ፡ ፴፪ ፴፫ ። |
| ወዕቀቡ ከመ ትግበሩ ኵሎ ነገረ ዝንቱ ኪዳን ከመ ታእምሩ ኵሎ ዘትገብሩ ። | ፱ | የምታደርጉትን ሁሉ ታውቁ ዘንድ የዚህን የቃል ኪዳን ነገርም ታደርጉ ዘንድ ሕጉን፡ ጠብቁ ። |
| ወናሁ ቆምክሙ አንትሙ ኵልክሙ ቅድመ እግዚአብሔር አምላክክሙ፡ ወበበይተ ነገድክሙ፡ ወሊቃውንቲክሙ፡ ወመኳንንቲክሙ ወጸሐፍቲክሙ፡ ወኵሉ ተባዕተ እስራኤል ። | ፲ | እናንተም ሁላችሁ በፈጣሪያችሁ በእግዚአብሔር ፊት እነሆ ቆማችኋል፡ የነገዶቻችሁ ሹማምንት፡ አለቆቻችሁ መኳንንቶቻችሁና ጸሐፊዎቻችሁ፡ የእስራኤልም ወንዶች ሁሉ ። |
| ወአንስትያክሙ፤ ወውሉድክሙ ወግዩር ዘሀለወ ማእከለ ትዕይንቲክሙ እምሐጣቤ ዕፅክሙ እስከ ሐዋሬ ማይክሙ ። | ፲፩ | ሚስቶቻችሁ ልጆቻችሁ በከተማችሁ ያለ ስደተኛ፡ ዕንጨት ለቃሚያችሁና፡ ውኃ ቀጂያችሁ ሁሉ ። |
| ከመ ትስምዑ ኪዳኖ ለእግዚአብሔር አምላክክሙ ወመርገሞኒ ለእግዚአብሔር አምላክክሙ ዘተከየደ ምስሌክሙ ዮም ። | ፲፪ | አሁን ከናንተ ጋር የተማማለው የእግዚአብሔር መርገሙንና የፈጣሪያችሁ የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳኑን ትሰሙ ዘንድ ። |
| ከመ ይረሲከ ሕዝበ ሎቱ፡ ወውእቱኒ ከመ ይኩንከ አምላከ፡ በከመ መሐለ ለአበዊከ ለአብርሃም ወለይስሐቅ ወለያዕቆብ ። | ፲፫ | ለአባቶቻችሁ ለአብርሃም፡ ለይስሐቅና ለያዕቆብ እንደ ማለላቸው እርሱ ላንተ የፍቅር አባት ትሆነው ዘንድ አንተም ለሱ ወገን ትሆነው ዘንድ እነሆ በፊቱ ቆማችኋል ። |
| ወአኮ ለክሙ ለባሕቲትክሙ ዘአቀውም አነ ዘንተ ኪዳነ ወዘንተ መርገመ ። | ፲፬ | እኔም ይህን ቃል ኪዳንና ይህን ርግማን በናንተ ላይ ብቻ የማጸናው አይደለም ። ዘፍ፡ ፲፯ ፯፡ ዘፀ፡ ፯ ፯ ። |
| አላ ለእለሂ ሀለዉ ዝየ ዮም ምስሌክሙ ቅድመ እግዚአብሔር አምላክክሙ፡ ወለእለሂ ኢሀለዉ ዝየ ምስሌክሙ ዮም ። | ፲፭ | አሁን በዚህ ከናንተ ጋራ በፈጣሪያችሁ በእግዚአብሔር ፊት ለሌሉና አሁን በዚህ ከናንተ ጋራ ላሉም ነው እንጂ ። ግብ፡ ሐዋ፡ ፪ ፴፱ ። |

| | | |
|---|---|---|
| እስመ ለሊክሙ ተአምሩ ዘከመ ነበርነ ውስተ ግብጽ ፡ ወዘከመ ኀለፍነ እንተ ማእከሎሙ ለእልክቱ አሕዛብ ወተዐደውናሆሙ ። | ፲፮ | በግብጽ እንደ ኖርን በነዚህም አሕዛብ መካከል አልፈናቸው እንደ ሄድን እናንተ ታውቃላችሁና ። |
| ወርኢክሙ ርኵሶሙ ወአማልክቲሆሙ ዕፀ ፡ ወእብነ ፡ ወብሩረ ፡ ወወርቀ ወብርተ ፡ ዘገብሩ ለሊሆሙ ። | ፲፯ | እነሱ የሠሩዋቸው ደንጊያንና ዕንጨትን ፥ ወርቅንና ብርን ናስንም የሚሆኑ ጣኦቶቻቸውንና ኃጢአታቸውን አይታችኋል ። ዘሌ፡ ፳፮ ፴ ፡ ፩ ነገ፡ ፳፱ ፳፰ ። |
| ኢይኩን እምኔክሙ ኢ ብእሲ ወኢ ብእሲት ፡ ወኢ ሕዝብ ፡ ወኢ ነገድ ፡ ወኢ መኑሂ ዘይኀድግ ልቦ እምእግዚአብሔር አምላክክሙ ፡ ወየሐውር ያምልኮሙ ለእልክቱ አማልክተ አሕዛብ ወኢይኩን እምኔክሙ ሥርው እኪት እንተ ታበቍል ወታፈሪ ሐምዘ ወምረተ ። | ፲፰ | ወንድም ቢሆን ሴትም ብትሆን ወገንም ቢሆን ፥ ነገድም ቢሆን ፡ ማንም ማን ልቡናውን ከፈጣሪያችሁ ከእግዚአብሔር አርቆ እነዚያን የአሕዛብ ጣኦቶች የሚያመልካቸው ከናንተ አይገኝ ፥ ከናንተም ሐሞትንና እሬትን የሚያበቅል ክፉ ሥር (ልቡና) አይኑርባችሁ ። |
| ወሰሚዐክሙ ቃለ ዝንቱ መርገም ዘይቤ በልቡ ይሠረ ኢ.ት እስመ በዕበየ ልብየ ገበርኩ ወሖርኩ ከመ ኢያዐሪ መዊተ መአብስ ምስለ ዘኢአበሰ ። | ፲፱ | የዚህን የርግማን ነገር ከሰማችሁ በኋላ ሂጄ በልቡናዬ ስንፍና አድርጌዋለሁና በልቡ እግዚአብሔር ይቅር ይለኛል የሚል ሰው ቢኖር አውቆ የበደለ ሰው ሳያውቅ ከበደለ ሰው ጋራ በፍዳ እንዳይተካከል ይወቅ ። |
| ኢይፈቅድ እግዚአብሔር ከመ ይሣሀሎ አላ በጊዜሃ መዐቱ ለእግዚአብሔር ፡ ወቅንኡ ያውዕዮ ለውእቱ ብእሲ ፡ ወይተልዎ ዝንቱ ኵሉ መርገም ዘዝንቱ ኪዳን ዘጽሑፍ ውስተ ዝንቱ መጽሐፈ ሕግ ወይሰዐር እግዚአብሔር ስሞ እምታሕተ ሰማይ ። | ፳ | የእግዚአብሔር ቍጣውና ለአምላክነቱ የቀናው ቅናት ፈጥኖ ያጠፋዋል እንጂ በዚህም በዳግም ሕግ የተጻፈ የዚህ የቃል ኪዳን ርግማን ይከተለዋል እንጂ እግዚአብሔርም ከሰማይ በታች ስሙን ያጠፋል እንጂ ይቅር ይለው ዘንድ አይወድም ። መዝ፡ ፸፱ ፩ ፡ ፸፰ ፭ ። |
| ወያግብኦ እግዚአብሔር ውስተ እኪት ወይፈልጦ እምኵሉ ደቂቀ እስራኤል በኵሉ ዝንቱ መርገም ዘዝንቱ ኪዳን ዘጽሑፍ ውስተ ዝንቱ መጽሐፈ ሕግ ። | ፳፩ | በዳግም ሕግ በተጻፈ በዚህ በመሐላው መርገም ሁሉ ከእስራኤል ልጆች ሁሉ ለይቶ ፥ እግዚአብሔር በመከራ ይጥለዋል ። ዘዳ፡ ፴ ፲ ። |
| ወይብሉ ድኅረ ትውልደ ደቂቅክሙ እለ ይትነሥኡ እምድኅሬክሙ ወነኪርኒ ዘይመጽእ እምርኁቅ ብሔር ወይሬእዩ መቅሠፍታ ለይእቲ ምድር ወደዌሃ ዘፈነወ እግዚአብሔር ላዕሌሃ ። | ፳፪ | ከናንተ በኋላ የሚነሱ ልጆቻችሁና ከሩቅ አገር የሚመጣ ባዕድም እግዚአብሔር ያመጣበት የዚያችን አገር መከራዋ መቅሠፍቷን ያያሉ ። ዘዳ፡ ፳፱ ፳፬ ። |
| ተይ ፡ ወጼው ፡ ያነድድ ውስተ ኵለንታሃ ፡ ወኢትዘራእ ፡ ወኢታበቍል ወኢይወፅእ ውስቴታ ኵሉ ሐመልማል በከመ ተገፍትዓ ሰዶም ፡ ወገሞራ ፡ ወአዳማ ፡ ወሴብዮን ፡ እለ ገፍትዖን እግዚአብሔር በመዐቱ ። | ፳፫ | በሁለንትናዋ ድኝ ፡ ጨው (እሳት) ሲነድ ዘር ሳይዘራባት ቡቃያን ሳታበቅል እግዚአብሔር ተቈጥቶ ያጠፋቸው ገሞራና ሰዶም ሴባዮና አዳማ እንደጠፉ በቢም ልምላሜ ሳታወጣና ሳታስገኝ አይተው ። መሳ፡ ፬ ፵፭ ። |
| ወይብሉ ኵሉ አሕዛብ ለምንት ከመዝ ገብረ እግዚአብሔር ለዛቲ ምድር ፡ ወምንት ውእቱ መንሱቱ ለዝንቱ መዐት ዐቢይ ። | ፳፬ | አሕዛብ ሁሉ እግዚአብሔር ይህችን አገር ለምን እንዲህ አደረጋት ፥ የዚህስ የጽኑ መዓት ጥፋት ምንድር ነው ፤ ይላሉ ። ዘዳ፡ ፳፱ ፳፬ ። |
| ወይብሉ እስመ ኀደጉ ኪዳኖ ለእግዚአብሔር አምላከ አበዊሆሙ ዘተከየደ ምስለ አበዊሆሙ አመ አውፅኦሙ እምድረ ግብጽ ። | ፳፭ | መላሾችም ከግብጽ አገር በወጣቸው ጊዜ ከአባቶቻቸው ጋር የተማማለውን ያባቶቻቸውን ፈጣሪ የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን አፍርሰዋልና ። |
| ወሖሩ ወአምለኩ በዕዳነ አማልክተ ወሰገዱ ሎሙ ለዘኢየአምሩ ወለዘኢይበቍዕዎሙ ። | ፳፮ | ሂደውም ልዩ የሆኑ ጣኦታትን አምልከዋልና ለማያውቋቸውና ለማይጠቅሟቸውም ሰግደውላቸዋልና ። |
| ወተምዐ መዐተ እግዚአብሔር ላዕለ ዛቲ ምድር ወአምጽአ ላዕሌሃ ኵሎ መርገመ ዘጽሑፍ ውስተ ዝንቱ መጽሐፈ ሕግ ። | ፳፯ | እግዚአብሔር በዚህች አገር ላይ ፈርዶ (ተቈጥቶ) በዚህ በዳግም ሕግ የተጻፈውን ርግማን ሁሉ አመጣበት ። መዝ፡ ፲፩ ፯ ። |
| ወአሰሰሮሙ እግዚአብሔር እምገጸ ምድሮሙ በመዐት ወበመንሱት ወበመቅሠፍት ዐቢይ ከመ ይእዜ ዘንቡእ ለእግዚአብሔር አምላክነ ። | ፳፰ | እግዚአብሔር ከአገራቸው በጥፋት በጽኑ መቅሠፍት በቍጣ አጠፋቸው ፤ ዛሬ እኛ እንደምንቀበለው ያለ መቅሠፍት ለፈጣሪያችን ለእግዚአብሔር የተሠወረ መቅሠፍት አለው ። |
| ወዘኢያስተርኢ ለነ ወለውሉድነ ለዓለም ከመ ንግበር ኵሎ ዘይብል ዝንቱ ሕግ ። | ፳፱ | የሚታየው (የተገለጸው) መቅሠፍት ግን ይህ ዳግም ሕግ የሚያዘውን ሁሉ እናደርግ ዘንድ ፥ ለኛና ለዘለዓለምም ለልጆቻችን ነው ፥ ብለው ይመልሱላቸዋል ። |

## ምዕራፍ ፴ ።

፩ ወኢመ መጽአ ላዕሌከ ኵሉ ዝንቱ ነገር በረከቲሂ ወመርገሙሂ ዘአቀምኩ ቅድሜከ ተዘከሮ በልብከ በውስተ ኵሉ አሕዛብ ኀበ ዘረወከ እግዚአብሔር ህየ ።

፪ ወተመየጥ ኀበ እግዚአብሔር አምላክከ ወስማዕ ቃሎ ኵሎ ዘአነ እኤዝዘከ ዮም በኵሉ ልብከ ወበኵሉ ነፍስከ ።

፫ ወየኀድግ ለከ እግዚአብሔር ኵሎ ኀጣውኢከ ወይምሃለከ ወከዕበ ያስተጋብአከ እግዚአብሔር እምኵሉ አሕዛብ እለ ውስቴቶሙ ዘረወከ ህየ ።

፬ ወለእመኒ ውስተ አጽናፈ ሰማይ ዘረወከ ያስተጋብአከ እምህየ እግዚአብሔር አምላክከ ።

፭ ወይወስደከ ውስተ ይእቲ ምድር እንተ ተዋረሱ አበዊከ ወትወርሳ ወይገብር ሠናይተ ላዕሌከ ወያበዝኀከ ወይፌድፈደከ እምአበዊከ ።

፮ ወያሌብሎ እግዚአብሔር ለዝክቱ ልብከ ወልበሙ ለዘርእከ ከመ ታፍቅሮ በኵሉ ልብከ ፡ ወበኵሉ ነፍስከ ከመ ትሕየው አንተ ወዘርእከ ።

፯ ወያገብእ እግዚአብሔር አምላክከ ለዝንቱ መርገም ላዕለ ፀርከ ወላዕለ እለ ይጸልኡከ ፡ ወላዕለ እለ ይሰድዱከ ።

፰ ወአንተሰ ተመየጥ ወስማዕ ቃለ እግዚአብሔር አምላክከ ወግበር ኵሎ ትእዛዞ ዘአነ እኤዝዘከ ዮም ።

፱ ወብዙኀ ያጸንዐከ እግዚአብሔር አምላክከ በኵሉ ተግባረ እደዊከ ወበውሉደ ከርሥከ ወበዘርአ ምድርከ ፡ ወበአስተዋልዶ እንስሳከ ፡ እስመ ይትመየጥ እግዚአብሔር አምላክከ ከመ ይትፌሣሕ ላዕሌከ በሠናይ በከመ ተፈሥሐ ላዕሌከ በአኰቴ ወበከመ ተፈሥሐ ላዕለ አበዊከ ።

፲ ለእመ ሰማዕከ ቃለ እግዚአብሔር አምላክከ ከመ ትዕቀብ ወከመ ትግበር ኵሎ ትእዛዞ ወኵሎ ኵነኔሁ ወፍትሐ ዘጽሑፍ ውስተ ዝንቱ መጽሐፈ ሕግ ወለእመ ገባእከ ኀበ እግዚአብሔር አምላክከ በኵሉ ልብከ ወበኵሉ ነፍስከ ።

፲፩ እስመ ዛቲ ትእዛዝ ዘአነ እኤዝዘከ ዮም ኢኮነት ክብደ ወኢኮነት ርኅቅተ እምኔከ ።

፲፪ ወኢኮነት ውስተ ሰማይ ከመ ኢትበል መኑ የዐርግ ውስተ ሰማይ ወያመጽአ ለነ ወንስምዓ ወንግበራ ።

፲፫ ወኢኮነት ማዕዶተ ባሕር ወእመ ትብል መኑ እምዐደወ ለነ ማዕዶተ ባሕር ወያመጽአ ለነ ወያሰምዓነሃ ወንግበራ ።

፲፬ እስመ ናሁ ቅርብት ይእቲ ለከ ጥቀ ቃል ውስተ አፉከ ወውስተ ልብከ ወውስተ እደዊከ ከመ ትግበራ ።

፲፭ ወናሁ ሜምኩ ቅድመ ገጽከ ዮም ሕይወተ ፡ ወሞተ ፡ ሠናይተ ፡ ወእኪተ ።

፲፮ ወሕይወትሰ ለእመ ሰማዕከ ቃለ እግዚአብሔር አምላክከ ወዐቀብከ ትእዛዞ ኵሎ ዘአነ እኤዝዘከ ዮም ፡ ከመ

## ምዕራፍ ፴ ።

ይህ ሁሉ ነገር በመጣብህ ጊዜ በፊትህ ያኖርሁት ርግማኑና ምርቃቱ በደረሰብህ ጊዜ እግዚአብሔር በሚበትንህ በዚያ በአሕዛብ አገር ሁሉ በልብህ አስበው ።

እኔ አሁን የማዝህን ቃሉን ሰምተህ በፍጹም ልቡናህ፡ በፍጹም ልቡናህ ወደ ፈጣሪህ ወደ እግዚአብሔር ተመለስ ። ኢሳ ፶፭ ፯ ፡ ኤር ፡ ፫ ፴ ።

እግዚአብሔርም ይቅር ብሎ ኃጢአትህን ያስተሠርይልሃል ፡ ዳግመኛም እግዘአብሔር በነሳቸው ዘንድ ከበተነህ ከዚያ ከአሕዛብ ሁሉ ይሰበስብሃል ።

በሰማይ ዳርቻም ቢበትንህ ፈጣሪህ እግዚአብሔር ከዚያ ይሰበስብሃል ። ዘዳ፡ ፳፰ ፷፬ ፡ ነህ፡ ፩ ፱ ።

አባቶችህ ወደ ወረሱዋት ወደዚያችም አገር ይመልስሃል ፡ ትወርሳትም ዘንድ ፡ በጎ ነገርንም ያደርግልሃል ከአባቶችህ ይልቅ ፈጽሞ እንድትበዛ ያደርግሃል ።

እግዚአብሔርም ይህን አላዋቂ ልብህንና የልጆችህንም ልብ አንተም ልጆችህም በሕይወት እንድትኖሩ በፍጹም ልቡናህ ፡ በፍጹም ሰውነትህ እንድትወዱው ያደርግሃል ።

ፈጣሪህ እግዚአብሔር ይህን ርግማኑን ወደ ተጻራሪዎችህና ከገር አስወጥተው ወደ ሚሰዱህ ጠላቶችህ ይመልሰዋል ።

አንተ ግን ተመልሰህ የፈጣሪህ የእግዚአብሔርን ቃል ስማ ፡ እኔ አሁን የማዝህንም ትእዛዙን ሁሉ አድርግ ።

ፈጣሪህ እግዚአብሔርም በእጅህ ሥራ ሁሉ ከብሕርይህ በተከፈለው ልጅህና ከምድርህ በሚገኘው እንስሳ ከብቶችህንም በማዋለድ (በማራባት) እጅግ ያጸናሃል ፡ በንተም ጥፋት በአባቶችህም ጥፋት ደስ እንዳለው በንተም ድኅነት ደስ ይለው ዘንድ በረድኤት ወዳንተ ይመለሳልና ።

በዚህ በዳግም ሕግ የተጻፉት ትእዛዙን ቅጣቱንና ፍርዱን ሁሉ ትጠብቅና ትሠራውም ዘንድ የፈጣሪህ የእግዚአብሔርን ቃል ብትሰማ በፍጹም ልቡናህና በፍጹም ሰውነትህም ወደ ፈጣሪህ ወደ እግዚአብሔር ብትመለስ ወዳንተ ይመለሳልና ። ዘዳ ፳፩ ፲፩ ፡ ፳፰ ፷፫ ።

እኔ አሁን የማዝህ ይህች ትእዛዝ የከበደች የጸናች አይደለችም ከንተም የራቀች አይደለችም ።

ሰምተን እንሠራት ዘንድ ወደ ሰማይ ወጥቶ ማን ያመጣልናል እንዳትል በሰማይም አይደለችም ።

ሰምተን እናደርጋት ዘንድ ወንዙን ተሻግሮ አምጥቶ ማን ባሰማን ነበር ብትልም ከባሕር ማዶ አይደለችም ። ምሳ፡ ፴ ፬ ፡ ዮሐ፡ ፫ ፲፫ ፡ ሮሜ ፲ ፮ ።

በፍህ ልታስተምራት ፡ በልብህ ልትጠብቃት ፡ በእጅህም ልትሠራት ፡ እነሆ ይህች ቃል ላንተ እጅግ ቅርብ ናት ።

ሞትንና ሕይወትን ፡ ክፉንና በጎንም ፡ እነሆ በፊትህ አኖርኩልህ ። ዘዳ፡ ፴ ፲፬ ፡ ሮሜ ፲፮ ፯ ።

ሕይወት ፈጣሪህ እግዚአብሔርን ትወደው ዘንድ እኔ አሁን የማዝህን ትእዛዙን ሁሉ ትጠብቅ ዘንድ በሕጉም

ታፍቅር ለእግዚአብሔር አምላክከ ወትሑር በኵሉ ፍና
ዊሁ ፡ ወትዕቀብ ኵነኔሁ ወፍትሖ ወትትበዛኅ ወተሐዩ ወይ
ባርከከ እግዚአብሔር አምላክከ በኵሉ ምድር እንተ ውስ
ቴታ ትበውእ ህየ ከመ ትትዋረሳ ።

፲፯ ወለእመሰ ተመይጠ ልብከ ወአበይከ ሰሚዐ ወስሕትከ
ወሰገድከ ለባዕዳን አማልክት ወተቀነይከሙ ፡ ናሁ አይዳዕ
ኩከ ዮም ከመ ጠፊአ ትጠፍእ።
፲፰ ወኢይነውኅ መዋዕሊከ ውስተ ምድር እንተ ውስቴታ
ዓዲወ ተኀዱ ዮርዳኖስ ህየ ከመ ትትዋረሳ ።
፲፱ ወናሁ አሰምዕ ለከ ዮም ሰማየ ወምድረ ከመ ሜምኩ
ቅድሜከ ሕይወተ ወሞተ ፡ በረከተ ወመርገመ ፡ ወኅረያ
ለከ ለሕይወት ከመ ትሕየው አንተ ወዘርእከ ።

፳ ወአፍቅሮ/ ለእግዚአብሔር አምላክከ ወሰማዐ ቃሎ
ወአጽንዖ ኪያሁ እስመ ውእቱ ሕይወትከ በዘበቱ ይነውኅ
መዋዕሊከ ከመ ትንበር ውስተ ምድር ዘመሐለ እግዚአብ
ሔር ለአበዊከ ለአብርሃም ወለይስሐቅ ወለያዕቆብ ከመ
የሀበሙ ።

ምዕራፍ ፴፩ ።

፩ ወፈጸመ ሙሴ ተናግሮቶሙ ለኵሉ ደቂቀ እስራኤል
ዘንተ ኵሎ ነገረ ።
፪ ወይቤሎሙ ምእት ወዕሥራ ዓመት ሊተ ዮም ፡ ወእ
ክል እንከ በዊአ ወወፂአ፡ ወበሕቱ ይቤለኒ እግዚአብሔር
ኢተዐድዎ ለዝንቱ ዮርዳኖስ ።
፫ ወውእቱ እግዚአብሔር ዘየሐውር ቅድሜከ ያጠፍ
ኦሙ እምቅድመ ገጽከ ለኵሉ አሕዛብ፡ ወኢያሱኒ የሐ
ውር ቅድመ ገጽከ በከመ ይቤ እግዚአብሔር ።
፬ ከማሁ ይገብሮሙ በከመ ገብሮሙ ለሴዎን ወለዓግ
ክልኤቱ ነገሥተ፡ አሞሬዎን እለ ይነብሩ ውስተ ማዕዶተ
ዮርዳኖስ ወለምድሮሙ በከመ ሠረዎሙ ።

፭ ወአግብኦሙ እግዚአብሔር ለክሙ ወግበርዎሙ በከ
መ አዘዝኩክሙ ።
፮ ትበዕ ወጽናዕ ወኢትፍራህ ወኢትደንግፅ ወኢትፅብስ
በቅድመ ገጾሙ እስመ እግዚአብሔር አምላክከ ውእቱ
የሐውር ምስሌከ ወኢየኀድገከ ወኢያሰትተከ ።
፯ ወጸውዖ ሙሴ ለኢያሱ ወይቤሎ በቅድመ ኵሉ እስ
ራኤል ትበዕ ወጽናዕ እስመ አንተ ትበውእ ቅድሜሁ ለዝ
ንቱ ሕዝብ ውስተ ምድር ዘመሐለ እግዚአብሔር ለአበዊ
ክሙ ከመ የሀበሙ ወአንተ ታወርሶሙ ።
፰ ወእግዚአብሔር የሐውር ምስሌከ ወኢየኀድገከ ወኢ
ያሰትተከ ወኢትፍፍራህ ወኢትደንግፅ ።
፱ ወጸሐፎ ሙሴ ለዝንቱ ነገረ ሕግ ውስተ መጽሐፍ ወወ
ሀቦሙ ለካህናት እለ ይፀውሩ ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር
ለደቂቀ ሌዊ ወለሊቃውንቲሆሙ ለደቂቀ እስራኤል ።

ጸንተህ ትኖር ዘንድ ፍርዱንና ሥርዓቱን ትጠብቅ ዘንድ
የፈጣሪህ የእግዚአብሔርን ቃል ብትሰማ ነው፡ ይህን ሁሉ
ብታደርግ ትበዛለህ በሕይወትም ትኖራለህ፡ ትወርሳት
ዘንድ በምትገባበትም አገር ሁሉ በዚያ እግዚአብሔር
ያከብርኻል ፡ (ይባርክኻል) ። ዘዳ፡ ፮ ፭ ፡ ፬ ፲፱ ።
ልቡናህ ወደ ኀጢአት ቢመለስ መስማትንም እምቢ
ብትል ከሕጉም ወጥተህ ብትስት ልዩ ለሆኑ አማልክትም
ብትሰግድ ግን ፡ ፈጽመህ እንድትጠፋ እኔ አሁን ነገርኩህ።
ትወርሳትም ዘንድ ወደዚያ ዮርዳኖስን በምትሻገርበት
ምድርም ዘመንህ (ዕድሜህ) አይበዛም ። ዘዳ፡ ፳፮ ፫ ።
ሞትንና ሕይወትን፡ ርግማንና ምርቃትን፡ በፊትህ እን
ዳኖርኩልህ እነሆ እኔ አሁን ሰማይንና ምድርን አስማብኻ
ለሁ ፡ አንተ ከልጆችህ ጋር በሕይወት ትኖር ዘንድ ሕይ
ወትን ምረጣት ። ዘዳ፡ ፴፬ ፵ ።
ፈጣሪህ እግዚአብሔርን ውደደው ፡ ቃሉንም ስማ ፡
ይሰጣቸው ዘንድ ለአባቶችህ ለአብርሃም ፡ ለይስሐቅና
ለያዕቆብ እግዚአብሔር በማለላቸው ምድር ጸንተህ እንድ
ትኖር ፡ ዘመንህ በሚበዛ ገንዘብ እሱ ሕይወትህ ነውና
እሱን አጽናው ። ዘዳ፡ ፲ ፳ ፡ መዝ፡ ፳፮ ፩ ።

ምዕራፍ ፴፩ ።

ሙሴ ይህን ሁሉ ነገር ለእስራኤል ልጆች ሁሉ ተና
ግሮ ጨረሰ ።
አሁን እኔ መቶ ሃያ ዘመን ሁኖኛል ፡ መውጣትና መግ
ባት አችላለሁ ፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ይህን ዮርዳኖስ
አትሻገረውም አለኝ አላቸው ። ዘኍ፡ ፳፯ ፲፯ ።
ፊታውራሪ ሁኖ በፊትህ የሚሄድ እግዚአብሔር አሕ
ዛብን ሁሉ ከፊትህ ያጠፋቸዋል ፡ በፊትህ የሚሄድ ኢያ
ሱም እግዚአብሔር እንዳለ ያጠፋቸዋል ።
በዮርዳኖስ ማዶ የሚኖሩ ሁለቱን የአሞሬዎን ነገሥ
ታት ዓግንና ሴዎንን እንዳጠፋቸው እንዲሁ ያጠፋቸዋል ፡
አገራቸውንም እንዳጠፋባቸው አገራቸውንም ያጠፋ
ባቸዋል ። ዘኍ፡ ፳፩ ፳፫ ፡ ዘዳ፡ ፫ ፳፩ ።
እግዚአብሔር በእጃችሁ ጥሉላችኋል እንዳዘዝኳች
ሁም አድርጓቸው አላቸው ። ዘዳ፡ ፯ ፪ ።
ጨክን በርታ ፡ አትፍራ ፡ አትደንግጥ እሱ እግዚአብ
ሔር በረድኤት ከንተ ጋራ ይኖራልና ፡ አይለይህምና አያ
ቃልልህምና በፊታቸው አትድከም ።
ሙሴም ኢያሱን ጠርቶ ይሰጣቸው ዘንድ እግዚአብ
ሔር ላባቶቻችሁ ወደ ማለላቸው አገር አንተ በዚህ ወገን
ፊት ትገባለህና ታወርሳቸውም አለህና ፡ በእስራኤል ፊት
ጨክን በርታ አለው ። ዘዳ፡ ፱ ፫ ።
እግዚአብሔርም ከንተ ጋራ በረድኤት ይኖራልና አይ
ለይህም አይንቅህምና አትፍራ አትደንግጥ አለው ።
ሙሴም ይህን የሕግን ነገር በመጽሐፍ ጽፎ የሕጉ
ማደሪያ ታቦትን ለሚሸከሙ ለሌዊ ልጆች ለካህናት ለእስ
ራኤል ልጆች አለቆችም ሰጣቸው ። ዘዳ፡ ፲፯ ፲፰ ።

፲ ወአዘዞሙ ሙሴ በይእቲ ዕለት ወይቤ እምድኅረ ሰብዐቱ ዓመት በዓመተ ኅድገት አመ በዓለ መጸለት ።

ሙሴም በዚያች ቀን ከሰባት ዓመት በኋላ ዳስ ጥለው በዓል በሚያደርጉበት ጊዜ በዓመተ ኅድገት ዘመን እንዲህ ብሎ አዘዛቸው ። ዘሌ፡ ፳፫ ፴፬ ፡ ዘዳ፡ ፲፭ ፩ ።

፲፩ አመ የሐውር ኵሉ እስራኤል ከመ ያስተርኢ ቅድመ እግዚአብሔር አምላክከ ውስተ መካን ዘኀረየ እግዚአብሔር አንብብዎ ለዝንቱ ሕግ ቅድመ እግዚአብሔር ።

እግዚአብሔር በመረጠው ቦታ በፈጣሪህ በእግዚአብሔር ፊት ሊታይ እስራኤል ሁሉ በሄደ ጊዜ ፡ ይህን ሕግ በእግዚአብሔር ፊት አንብቡት ።

፲፪ አስተጋቢአክሙ ሕዝበ ከመ ይስምዑ እደዊሆሙ ወአንስቲያሆሙ ወደቂቆሙ ፡ ወግዩራን እለ ውስተ ሀገርክሙ ከመ ይስምዑ ወያእምሩ ፈሪሆቶ ለእግዚአብሔር አምላክሙ ወሰሚዖሙ ከመ ይግበሩ ኵሎ ሕጎ ለዝንቱ ቃል ።

ሴቶችና ወንዶች በአገራችሁም ያሉ በደተኞች ልጆቻችሁም ሁሉ ይሰሙ ዘንድ የፈጣሪያቸው የእግዚአብሔርን አምልኮቱን ያውቁ ዘንድ ሰምተውም የዚህን ቃል ሥርዓት ሁሉ ይሠሩ ዘንድ ሕዝቡን ሰብስባችሁ አንብቡት አላቸው ። ዘዳ፡ ፬ ፲ ።

፲፫ ወደቂቆሙኒ እለ ኢየአምሩ ይስምዑ ወይትመሀሩ ፈሪሆቶ ለእግዚአብሔር አምላክሙ በኵሉ መዋዕሊሆሙ ዘየሐይዉ እሙንቱ ዲበ ምድር እንተ ውስቴታ ተዐድዉ ዮርዳኖስ አንትሙ ከመ ትትዋረስዋ በህየ ።

የሚያውቁ ልጆቻቸውም በዚያ ትወርሷት ዘንድ ዮርዳኖስን በምትሻገሩባት ምድር እነሳቸው በሚኖሩበት ዘመን ሁሉ የፈጣሪያችሁ የእግዚአብሔርን አምልኮቱን ሰምተው ይማሩ ዘንድ አንብቡት ብሎ አዘዛቸው ።

፲፬ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ናሁ ቀርበ መዋዕለ ሞትከ ጸውዖ ለኢያሱ ወቁሙ ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ወአዝዞ ፡ ወሖሩ ሙሴ ወኢያሱ ውስተ ደብተራ ዘመርጡል ፡ ወቆሙ ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ።

እግዚአብሔርም ሙሴን እነሆ የምትሞትበት ወራት ቀረበ ፡ ኢያሱን ጠርተኸው ልዩ በሆነች ድንኳን ደጃፍ ቁሙኝ አለው ፡ ሙሴና ኢያሱም ልዩ ወደ ሆነች ድንኳን ሄደው በደብተራ ኦሪት ደጃፍ ቆሙ ።

፲፭ ወወረደ እግዚአብሔር በዐምደ ደመና ወቆመ ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ፡ ወቆመ ዐምደ ደመናሂ ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ።

እግዚአብሔር በዓምደ ደመና ወርዶ በደብተራ ኦሪት ደጃፍ ተገለጠ ፡ ዓምደ ደመናውም በደብተራ ኦሪት ደጃፍ ተተከለ ። ዘፀ፡ ፴፫ ፱ ።

፲፮ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ናሁ ትነውም አንተ ምስለ አበዊከ ወይትነሣእ ዝንቱ ሕዝብ ወይዜምው ድኅረ አማልክተ ባዕድ ዘውስተ ምድር እንተ ውስቴታ ይበውኡ ወየኀድጉኒ ወይትሔወሩ ኪዳንየ ዘተካየድኩዎሙ ።

እግዚአብሔርም ሙሴን እነሆ አንተ እንደ አባቶችህ ትሞታለህ ፡ ይህም ወገን ተነሥቶ እኔን ትተው በሚገቡበት አገር ያሉ የአሕዛብን ጣኦታት ያመልካሉ ፡ የተማማልኳቸው መሐላንም ቸል ይላሉ አለው ።

፲፯ ወእትመዓዕ መዐተ በላዕሌሆሙ በይእቲ ዕለት ወእኅድጎሙ ወእሜይጥ ገጽየ እምኔሆሙ ወይከውኑ መብልዐ ለፀሮሙ ወትረክቦሙ ብዙኃት እኪት ወሥቃይ ፡ ወይብሉ በይእቲ ዕለት ፡ እስመ ኀደገነ እግዚአብሔር አምላክነ ወኢ ሀለወ ምስሌነ ረከበተነ ዛቲ እኪት ።

በዚያችም ቀን ቁጣን ተቈጥቼ እለያቸዋለሁ ገጸ-ረድኤቴንም ከነሱ እመልሳለሁ ፡ ለጠላቶቻቸውም ምግብ ይሆናሉ ፈጽሞ ብዙ መከራ ታገኛቸዋለች ፡ በዚያችም ቀን ፈጣሪያችን እግዚአብሔር ተለይቶናልና በረድኤትም ከኛ ጋር የለምና ይህች መከራ አገኘችን ይላሉ ።

፲፰ ወአንሰ መይጠ እመይጥ ገጽየ እምኔሆሙ በይእቲ ዕለት በእንተ ኵሉ ኃጣውኢሆሙ ዘገብሩ ወገብኡ ኀበ አማልክተ ባዕድ ።

እኔም ስለ ሠሩት ኃጢአታቸው ሁሉ የአሕዛብ ጣኦታትንም ስላመለኩ በዚያች ቀን ገጸ-ረድኤቴን ከነሳቸው እመልሳለሁ ። ዘዳ፡ ፴፩ ፲፯ ።

፲፱ ወይእዜኒ ጸሐፍ ነገራ ለዛቲ ማኅሌት ወመሀርዎሙ ኪያሃ ለደቂቀ እስራኤል ወይደይዋ ውስተ አፉሆሙ ከመ ትኩነኒ ዛቲ ማኅሌት ስምዐ ላዕለ ደቂቀ እስራኤል ።

አሁንም የዚያችን ምስጋና ነገር ጽፈህ እሷን ለእስራኤል ልጆች አስተምራቸው ፡ ይህችም ምስጋና (መዝሙር) በእስራኤል ልጆች ላይ ምስክር ትሆነኝ ዘንድ በቃላቸው ያስተምርዋት ።

፳ እስመ አበውኦሙ ውስተ ምድር ቡርክት ዘመሐልኩ ለአበዊሆሙ ምድር እንተ ትውኅዝ ሐሊበ ወመዓረ ፡ ወበሊዖሙ ወጸጊቦሙ የዐብዱ ወይገብኡ ኀበ አማልክተ ባዕድ ወያመልክዎሙ ወያምዕዑኒ ወየኀድጉ ኪዳንየ ።

ተድላ ደስታ ወደምታስገኝ ለአባቶቻቸው ወደ ማልኩላቸው ምድር አገባቸዋለሁና በልተው ከጠገቡም በኋላ ይስታሉና ወደ አሕዛብ አማልክትም ተመልሰው ያመልኳቸዋልና ቃል ኪዳኔንም አፍርሰው ያሳዝኑኛልና ።

፳፩ ወትቀውም ላዕሌሆሙ ዛቲ ማኅሌት ስምዐ ቅድመ ገጾሙ እስመ ኢትትረሳዕ እምውስተ አፉሆሙ ወእምውስተ አፈ ውሉዶሙ እስመ አነ አአምር እከዮሙ ኵሎ ዘይገብሩ በዝየ እንበለ አብኦሙ ውስተ ይእቲ ምድር ቡርክት ዘመሐልኩ ለአበዊሆሙ ።

ከነሳቸው አንደበትና ከልጆቻቸው አንደበት የምትዘነጋ ስለ ሆነ ፡ ለአባቶቻቸው ወደ ማልኩላቸው ወደዚያች ወደ ከበረች አገር ሳላገባቸው እኔ በዚህ የሚሠሩት ኃጢአታቸውን ሁሉ አውቃለሁና ይህች ምስጋና (መዝሙር) በፊታቸው ምስክር ሁና ትነሣባቸዋለች አለው ።

፳፪ ወጸሐፋ ሙሴ ለዛቲ ማኅሌት በይእቲ ዕለት ወመሀሮሙ ኪያሃ ለደቂቀ እስራኤል ።

ሙሴም ያችን ምስጋና በዚያች ቀን ጽፎ ለእስራኤል ልጆች እሷን አስተማራቸው ።

፳፭ ወአዘዘ ሙሴ ለሌዋውያን ወይቤሎሙ ጽናዕ ወትበዕ እስመ አንተ ታበውኦሙ ለደቂቀ እስራኤል ውስተ ምድር ዘመሐለ እግዚአብሔር ለአበዊሆሙ ወውእቱ ይሄሉ ምስሌከ ፡፡

፳፮ ወሶበ አኅለቀ ሙሴ ጽሒፎታ ለዛቲ ነገረ ሕግ ውስተ መጽሐፍ እስከ ፈጸማ አዘዘሙ ለሌዋውያን እለ ይፀውሩ ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር ፡፡

፳፯ ወይቤሎሙ ንሥኡ ዘተ መጽሐፈ ወአንብርዋ ውስተ ከርሣ ለታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር አምላክክሙ ወይንበር ህየ ስምዐ ለከ ፡፡

፳፰ እስመ አነ አአምር ውሂከተከ ወክሳደከ ጽኑዐ ወእንዘ አነ ሀሎኩ ዓዲየ ሕያው ዮም አምዓዕክምዎ ለእግዚአብሔር ፣ እፎኬ ፈድፋደ እም ድኅረ ሞትኩ ፡፡

፳፱ አስተጋብኡ ኀቤየ ዐበይተ ነገድክሙ ወሊቃናቲክሙ ወመኳንንቲክሙ ወጸሐፍቲክሙ ከመ እንግሮሙ ይስምዑ ዘንተ ኵሉ ነገረ ወአሰምዕ ላዕሌሆሙ ሰማየ ወምድረ ፡፡

፴ እስመ አነ አአምር ከመ እምድኅረ ሞትኩ አብሶ ትኤብሱ ወተኀድግዋ ለፍኖት እንተ አዘዝኩክሙ ወትመጽእ ላዕሌክሙ እኪት በደኃሪ መዋዕል እስመ ትገብሩ እኪተ ቅድመ እግዚአብሔር አምላክክሙ ከመ ታምዕዕዎ በግብረ እደዊክሙ ፡፡

፴፩ ወነገሮሙ ሙሴ ወአስምዖሙ ለኵሉ ማኅበረ እስራኤል ነገሩ ለዛቲ ማኅሌት ፍጹመ ፡፡

## ምዕራፍ ፴፪ ፡፡

፩ ወይቤ አጽምእ ሰማይ ወእንግርከ ፣ ወትስማዕ ምድር ቃለ አፉየ ፡፡

፪ ወተወከፍዎ ከመ ነጠብጣብ ለነገርየ ወይረድ ከመ ጠል ነቢብየ ፣ ወከመ ዝናም ውስተ ገዳም ፣ ወከመ ጊሜ ውስተ ሣዕር ፡፡

፫ እስመ ስመ እግዚአብሔር ጸዋዕኩ ፣ ሀቡ ዕበየ ለአምላክነ ፡፡

፬ እግዚአብሔር ጻድቅ በምግባሩ ፣ ወርቱዕ ኵሉ ፍናዊሁ ፣ እግዚአብሔር ጻድቅ ወአልቦ ዐመፃ ፣ ጻድቅ ወኄር እግዚአብሔር ፡፡

፭ አበሱ ወአከ ሉቱ ትውልድ ርኩሳን ትውልድ ዕሉት ወግፍትዕት ከመዝኑ ተዐሥይዎ ለእግዚአብሔር ፡፡

፮ ዝ ሕዝብ ዐብድ ወአኮ ጠቢብ ፣ አኮኑ ውእቱ አቡከ ዘፈጠረከ ፣ ፈጠረከሂ ወገብረከ ፡፡

፯ ተዘከሩ መዋዕለ ትካት ፣ ወለብዉ ዓመተ ትውልደ ትውልድ ፣ ተሰአሎ ለአቡከ ወይነግረከ ወለአእሩጊከ ወይዜንዉከ ፡፡

፰ አመ ከፈሎሙ ልዑል ለአሕዛብ ወዘከመ ዘርኦሙ ለደቂቀ አዳም ፣ ወአቀመ አድባሪሆሙ ለአሕዛብ ወበበኍል

፳፭ ሙሴም ሌዋውያን የእስራኤል ልጆች እግዚአብሔር ላባቶቻቸው ወደ ማለላቸው ታገባቸዋለህና እሱም በረድኤት ከንተ ጋራ ይኖራልና ጨክን በርታ ፣ ብሎ አዘዘው ፡፡

፳፮ ሙሴ እስኪ ጨርሳት ድረስ ደርሶ ይህችን የሕግን ነገር በመጽሐፍ ጽፎ በጨረሰ ጊዜ የእግዚአብሔር የሕጉ ማደሪያ ታቦትን የሚሸከሙ ሌዋውያንን ፡፡

፳፯ ይህችን መጽሐፍ ወስዳችሁ በፈጣሪያችሁ በእግዚአብሔር በሕጉ ማደሪያ ታቦት ውስጥ አኑሯት ፣ ላንተ ምስክር ይሆንህ ዘንድ በዚያ ይኑር ብሎ አዘዛቸው ፡፡

፳፰ ቅሠፈኝ ፣ ቅሠፈኝ ብለህ ማነሣሣትህን ክሳደ ልቡናህም ጽኑ እንደሆነ አውቃለሁና እኔ ገና በሕይወት ሳለሁ እግዚአብሔርን ያሳዘናችሁት ከሞትኩስ በኋላ እንዴት ፈጽማችሁ ታሳዝኑት ይሆን ! ፡ ዘፀ፡ ፴፪ ፱ ፡፡

፳፱ ይህን ሁሉ ነገር ይሰሙ ዘንድ እንድነግራቸው አለቆቻችሁና በወገኖቻችሁ ላይ የተሾሙ መኳንንቶቻችሁን ጸሐፊዎቻችሁን ዳኞቻችሁን ወደኔ ሰብስቡ ፣ ሰማይንና ምድርን አሰማባቸዋለሁ ፡ ዘዳ፡ ፲፯ ፲፰ ፣ ፴ ፲፱ ፡

፴ ከሞትኩ በኋላ ፈጽማችሁ እንድትበድሉ ያዘዝኋችሁንም ሕግ እንድታፈርሷት እኔ አውቃለሁና በእጃችሁም ሥራ ታሳዝኑት ዘንድ በፈጣሪያችሁ በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአት ትሠራላችሁና ኋላ በፍጻሜ ዘመን መከራ ትመጣባችኋለች ፡ ዘፍ፡ ፵፱ ፩ ፣ ዘዳ፡ ፴፪ ፳ ፣ ፪ ፴ ፡

፴፩ ሙሴም ለእስራኤል ወገኖች ሁሉ እውነት የሆነ የዚህች የምስጋና ነገር አሰምቶ ነገራቸው ፡

## ምዕራፍ ፴፪ ፡፡

፩ ሰማይ ስማኝ ልንገርህ ፣ ምድርም ከአፌ የወጣውን ቃል ትስማ ፡

፪ ምድር ዝናምን እንድትቀበለው እናንተም ነገሬን ተቀበሏዋት ፣ ጠል ከሰማይ ወርዶ ከምድር እንዲስማማ ነገሬም ከልቡናችሁ ገብቶ ይስማማ ፣ ዝናም በምድረ በዳ ወርዶ እንዲስማማ ፣ ካፊያም ከመስክ ወርዶ እንዲስማማ ነገሬም ከልቡናችሁ ይስማማ አለ ፡፡ ኢሳ፡ ፶፭ ፲ ፡

፫ የእግዚአብሔርን ስም ጠርቻለሁና ለፈጣሪያችን ምስጋና አቅርቡ ፡ መዝ፡ ፸፪ ፯ ፡፡

፬ እግዚአብሔር በሥራው ሁሉ እውነተኛ ነው ፣ ሥራውም ሁሉ የቀና ነው ፣ እግዚአብሔር እውነተኛ ነው ፣ ሐሰትም የለበትም እግዚአብሔር እውነተኛና ቸርም ነው ፡፡

፭ አደፈኞች ልጆች በደሉ ፣ ነገር ግን እሱን የጐዱ አይደለም ፣ ወንጀለኞች ገልበጥባጣም ልጆች ናቸው ፣ ለእግዚአብሔር እንዲህ ያለ ወረታ ትመልሱለታላችሁን ፤ ፡

፮ ይህ ወገን ሰነፍ ነው ፣ ዕውቀትም የሌለው አላዋቂ ነው ፣ የፈጠረህ አምላክህ እግዚአብሔር አይደለምን ፤ ፡

፯ የድሮውን (የኖኅን) ዘመን አስቡ ፣ ለልጅ ልጅ ጸንቶ የሚኖር ዘመንንም አስተውሉ ፣ አባትክን ጠይቀው ይነግርኻል ፣ ሽማግሎችንም ጠይቃቸው ይነግሩኻል ፡

፰ እግዚአብሔር አሕዛብን በቦታ እንደ ለያቸው የአዳምንም ልጆች እንደ በተናቸው እግዚአብሔርን በሚያገለ

ቆሙ ለመላእክተ እግዚአብሔር ።

፱ ወኮነ ያዕቆብ መክፈልተ ሕዝቡ ለእግዚአብሔር ፡ ወእስራኤልኒ ሐብለ ርስቱ ።

፲ ወአቀበሙ በውስተ በድው በውስተ ፋልል ፡ በሐሩር ወዘጽምእ ፡ ሐፀሮሙ መገቦሙ ወመርሐሙ ወአቀበሙ ከመ ብንተ ዐይን ።

፲፩ ወከመ ንስር ዘይከድን ወያስተጋብእ እጕሊሁ ታሕተ ክነፊሁ ፡ ወከመ የሐቅፍ እጕሊሁ በገበዋቲሁ ፡ ወሐዘሎሙ በክነፊሁ ወፆሮሙ በእንግድዓሁ ።

፲፪ እግዚአብሔር ባሕቲቱ መርሖሙ ወአልቦ ምስሌሆሙ አምላክ ነኪር ።

፲፫ ወአዕረጎሙ ዲበ ኃይለ ምድር ወሴሰዮሙ እክለ ገራውህ ወሐፀፆሙ በመዓር እምኰኵሕ በቅብዕ እምእብን ጽንዕት ።

፲፬ በቅብዐ ላሕም ወበሐሊበ በግዕ ምስለ መዋዕለ ጠሊ ወላሕም እጐለ አልሕምት ወአበግዕ ምስለ ቄቅሐ ሥርናይ ወደመ አስካል ሰትዩ ወይነ ።

፲፭ በልዐ ያዕቆብ ወጸግበ ፡ ክረየ ጽጋብ ለምንዙኑ ፡ ሰብሐ ወገዝፈ ወርኅበ ፡ ወኀደጎ ለእግዚአብሔር ፈጣሪሁ ወርኅቀ እምእግዚአብሔር ሕይወቱ ።

፲፮ ወወሀኩኒ በዝ ነኪር ፡ ወአምረሩኒ በርኵሶሙ ።

፲፯ ሦዑ ለአጋንንት ወአኮ ለእግዚአብሔር ፡ ለአማልክት እለ ኢየአምርዎሙ አማልክተ ግብት እለ ይትገበሩ ወኢይበቍዑ ወእለ ኢየአምሩ አበዊሆሙ ።

፲፰ ኀደጉ ለእግዚአብሔር ፡ ዘወለደከ ወረሳዕከ ለእግዚአብሔር ዘሐፀነከ ።

፲፱ ወርእየ እግዚአብሔር ወቀንአ ወተምዐ መዐተ ላዕለ ደቂቆሙ ወአዋልዲሆሙ ።

፳ ወይቤ እመይጥ ገጽየ እምኔሆሙ ወእሬእዮሙ ዘይከውኑ በደኃሪቶሙ ፡ እስመ ውሉድ ዓላውያን እሙንቱ ውሉድ እለ አልቦሙ ሃይማኖት ።

፳፩ እሙንቱሰ አቅንኡኒ በዘኢኮነ አምላክ ፡ ወአምዕዑኒ በአማልክቲሆሙ ፡ ወአነ አቀንኦሙ በዘኢኮነ ሕዝብ ፡ ወአምዕዖሙ በሕዝብ ዘኢይሌብዉ ።

፳፪ እስመ እሳት ትነድድ እመዐትየ ወታውዒ እስከሲኦል ታሕተ ወትበልዓ ለምድር ወለኵሉ ፍሬሃ ወታነድድ መሠረታተ አድባር ።

፳፫ ወአስተጋብአሙ ለእኪት ፡ ወአኀልቅ አሕጻየ በላዕሌሆሙ ፡ ወየኀልቁ በረኀብ ፡ ወይከውኑ መብልዐ ለአዕዋፈ ሰማይ ።

፳፬ ወይደክም ጽንዖሙ ፡ ወእፌኑ ላዕሌሆሙ ስነነ አራዊተ ምድር ምስለ ሐምዝ ከመ ይጕየዩ እምድር ።

ግሉ በመላእክት ቍጥር የአሕዛብን አውራጃዎች እንደ ወሰናቸው ይነግሩኻል ።

ያዕቆብም ለእግዚአብሔር ዕድልነት ያለው ወገን ሆነ እስራኤልም ርስትነት ያለው ወገን ሆነ ።

(ፋልል) ወዝ በሌላበት ምድረ በዳ ጠበቃቸው ውኃ ጥምና ድርቅ በጠናበት ጠበቃቸው መና ከደመና አውርዶ እየመገበ በደመና መራቸው እንደ ዓይን ብሌንም ጠበቃቸው ።

አሞራ ገላግሌቱን በክንፉ እንደሚሠውር በክንፈ ረድኤቱ ሠወራቸው ፡ በጕኑም ገላግሌቱን እንዲያቀፍ በገበ ረድኤቱ አቅፎ አወጣቸው ። ዘፀ ፲፱ ፬ ።

እግዚአብሔር ብቻውን መራቸው ከነሱቸው ጋር ሌላ አምላክ አልነበረም ።

ከምድር ወደሚገኘው አዝመራ አውጥቶ የእርሻዎች እኽልን መገባቸው ፡ ከማን በተገኘ ማር ከጭንጫማው ድንጋይም በተገኘ ቅቤ መገባቸው ። ኢሳ፡ ፶፰ ፲፬ ።

ከላሙና ከፍየሉ ወረሞ ጋር በበግ ወተትና በላሙ ቅቤ አሳደጋቸው ልጠ ጕርዶ ከወጣለት ሥንዴ ጋራ የበጎችንና የላሞችን ጊደር ወተት መገባቸው ፡ የዘለላውንም ደም ወይን አድርገው ጠጡ ። መዝ፡ ፹፩ ፲፮ ።

ያዕቆብም በልቶ ጠግቦ የተወደደ (ያዕቆብን) ጥጋብ አቀናጣው ፡ ወፈረ ደነደነ ሰባ ፡ ፈጣሪው እግዚአብሔርን ተወው ፡ አነዋወሩም ከእግዚአብሔር ራቀ ።

በዚህ በጣኦቱ ቅሠፈኝ ቅሠፈኝ ብለው አነማውኝ በር ኵሰታቸውም አስቈጡኝ (አሳዘኑኝ) ።

ለእግዚአብሔር ያይደለ ለአጋንንት መሥዋዕት ሠዉ ለማያውቋቸው አማልክት ተሠርተው ለማይረቡ ለማይ ጠቅሙ አባቶቻቸው ለማያውቋቸው ድንገት ለተገኙ ጣኦታት ሠዉ ። መዝ፡ ፻፮ ፴፯ ።

የፈጠረህ እግዚአብሔርን ተውከው ተከበክበ ያሳደ ገህ እግዚአብሔርንም ዘነጋኸው ። ኢሳ፡ ፲፯ ፲ ።

እግዚአብሔርም ይህን አይቶ ለአምላክነቱ ቀና በሴት ልጆቻቸውና በወንዶች ልጆቻቸውም ተቈጣ ።

ገጸ ረድኤቴን ከነሱቸው እመልሳለሁ ፡ ሃይማኖት የሌላቸው ወንጀለኞች ልጆች ናቸውና ፡ ኋላ በፍጻሜ ዘመን ምን እንዲሆኑ አያቸዋለሁ አለ ። ዘዳ፡ ፴፩ ፲፯ ።

እነሱቸውስ አምላክ ባይደለ ጣኦት አስቀኑኝ በአማልክቶቻቸውም አሳዘኑኝ እኔም ባልሆነ ወገን አስቀናቸዋለሁ ያጠፉናል ብለው ልብ በማያደርጓቸው ወገኖች አሳዝናቸዋለሁ ። መዝ፡ ፸፰ ፶፰፡ ሆሴ፡ ፩ ፱ ።

ከቁጣዬ የተነሣ (እሳት) ድርቅ ትሆናለችና ሥር መሠረት ትነቅላለች ፡ ከፍሬዋም ሁሉ ጋር ምድርን ታጠፋ ታለች የተራራዎችንም መሠረት ታደርቃለች ።

ለመከራ እሰበስባቸዋለሁ ፡ በጦርም እጠፋቸዋለሁ ፡ በረኃብ አልቀው በሰማይ ለሚበሩ ወፎች ምግብ ይሆናሉ ።

ኃይላቸው ይደክማል ከዚህ ዓለም ይጠፉ ዘንድ ከመርዝ ጋራ የምድር አባቦች ጥርሶችን እሰድባቸዋለሁ ።

| | | |
|---|---|---|
| በአፍአ ያጸምቶሙ መጥባሕት ለውሉዶሙ ወበውስተ አብያቲሆሙ ድንጋጼ ለወራዙቶሙ ምስለ ደናግሊሆሙ ፡ ለሕፃናቲሆሙ ምስለ አእሩጊሆሙ ። | ፳፭ | ልጆቻቸውን በዘመቻ ጦር ያጠፋቸዋል ፡ ጐልማሶቻቸውን ከቆነጃጅቶቻቸው ጋር ሽማግሌዎቻቸውን ከልጆቻቸው ጋራ በቤቶቻቸው ድንጋጼ ያጠፋቸዋል ። |
| ወእቤ ከመ እዝርዎሙ ፡ ወእስዐር እምድር ዝክሮሙ ፡ ወእምእጓለ እመሕያው ። | ፳፮ | አጠፋቸው ዘንድ ላጥፋቸው አልኩ ፡ ከሰው ለይቼ ከዚህ ዓለም ስም አጠራራቸውን አጠፋ ዘንድ ላጥፋቸው አልኩ ። ሕዝ፡ ፳ ፲፫ ። |
| በመዐት ፀረ ኮኑኒ ከመ ኢይትዐበዩ ፀር ፡ ወኢይበሉ እዴነ ጸንዐት አኮ እግዚአብሔር ዘገብሮ ለዝ ኵሉ ። | ፳፯ | ጣላትን በማምለክ ጠላቶች ሆኑኝ ፡ አሕዛብ እንዳይታበዩና ሥልጣናችንም በእስራኤል ላይ ጸናች እንዳይሉ ይህን ሁሉ ያደረገ እግዚአብሔር አይደለምን፤ ለምን ይታበያሉ ። ዘኍ፡ ፲፱ ፲፮ ፡ ኤር፡ ፲፱ ፩ ። |
| እስመ ሕዝብ ሕጉላነ ምክር እሙንቱ ፡ አልቦሙ ምልሕ ወኢሃይማኖት ። | ፳፰ | ምክር ያጡ ወገኖች ናቸው ፡ ምግባርም ሃይማኖትም የሌላቸው ወገኖች ናቸውና ። |
| ወኢሐለይዎ ከመ ያእምርዎ ለዝንቱ ወኢየአምርዎ በመዋዕል ዘይመጽእ ። | ፳፱ | ይህንም ሊያውቁት አላሰቡትም በሚመጣውም ዘመን የሚሆነውን አላወቁም ነበር ። |
| እፎ ያነትዮሙ እሐዱ ለዐሠርቱ ምእት ፡ ወክልኤቱ ይሰድድዎሙ ለእልፍ ፡ እስመ እግዚአብሔር ፈደዮሙ ወአምላክነሂ አግብኦሙ ። | ፴ | ቢያውቁማ ኖሮ እግዚአብሔር ፍዳውን አምጥቶባቸዋልና ፈጣሪያችንም በአሕዛብ እጅ ጥሏቸዋልና ፡ አንዱ ሰው እንዴት ሺሑን ያሳድዳቸው ነበር! ሁለቱስ እንዴት ዓሥሩን ሺሕ ያሸሹዋቸው ነበር! ። ፩ ሳሙ፡ ፱ ፱ ፡ ፩ ፰ ። |
| እስመ ኢኮነ አምላክነ ከመ አማልክቲሆሙ ፡ ፀርነሰ ዓብዳን ። | ፴፩ | ፈጣሪያችን እንደ አማልክቶቻቸው አይደለም እኮ! ጠላቶቻችን ግን ሰነፎች ናቸው ። |
| እስመ ከመ ዐፀደ ወይነ ሰዶም ዐፀደ ወይኖሙ ፡ ወሐረጎሙኒ እምነ ገሞራ ወአስካሉሙኒ አስካለ ሐሞት ፡ ወቀምሖሙኒ መሪር ። | ፴፪ | የሕጋቸው ማደሪያ የሆነ ልባቸው እንደ ሰዶም ሕግ ማደሪያ ነውና ፡ ወገናቸውም ከገሞራ ወገን ነውና ፡ ሕጋቸውም የሚያጠፋ ሕግ ነውና ዘለላውም መራራ ነውና ፡ ሰነፎች ናቸው ። |
| ሕምዘ አርዌ ምድር ወይኖሙ ሕምዘ አፍዖት ዘይቀትል ። | ፴፫ | ሕጋቸው የምድር እባብ መርዝ ነው ፡ የሚገድልም የፍኝት መርዝ ነው ። ኢያ፡ ፳፬ ፲፫ ፡ መዝ፡ ፶፰ ፬ ። |
| አኮኑ ዝንቱ ትእዛዝ ዘእምኀቤየ ውእቱ ወተኀትሙ ውስተ መዛግብትየ ። | ፴፬ | ይህ ትእዛዝ በኔ ዘንድ ተጠብቆ የለምን፤ አሕዛብስ በመዝገቤ የታተሙ አይደሉምን፤ ። ኢዮ፡ ፲፬ ፲፮ ። |
| በዕለተ ኵነኔየ እትቤቀሎሙ ወበጊዜ ይድኀፅ እግሮሙ እስመ ቀርበ ዕለተ ኀርትምናሆሙ ፡ እስመ በጽሐት ወድልውት ይእቲ ለክሙ ። | ፴፭ | የሚጐሰቁሉበት ቀን ቀርቧልና የሚጠፉበትም ቀን ደርሷልና እግራቸው የሚሰናከሉበትም ጊዜ ይህች ለነሱ የተዘጋጀች ናትና ፍርድ በሚደረግበት ቀን እበቀላቸዋለሁ። |
| እስመ ይፈትሕ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ፡ ወይትናበብ በእንተ አግብርቲሁ ፡ እስመ ርእዮሙ ከመ ተመስዉ ወኀልቁ ወተዘንጕጉ በኀበ ሀለዉ ። | ፴፮ | እግዚአብሔር ለወገኖቹ ለእስራኤል ይፈርዳልና ፡ ስለ ባሮቹም በአሕዛብ ይናገርባቸዋልና እበቀላቸዋለሁ አለ ፡ እሊህ እስራኤል እንደ ሰም ቀልጠው እንደጠፉ በያሉበትም እንደተሸሚጡ አይቷቸዋልና ። |
| ወሰበ ሠርሑ ይቤ እግዚአብሔር አይቴ እሙንቱ አማልክቲክሙ እለ ትትዌከሉ ቦሙ ። | ፴፯ | በመከራው ተይዘው በደከሙም ጊዜ ፡ እግዚአብሔር የምታምኑባቸው አማልክቶቻችሁ ወዴት ናቸው፤ ። |
| ወእለ ትበልዑ መሳብሕተ መሥዋዕቶሙ ፡ ወትሰትዩ ወይነ ሞጻሕቶሙ ፡ ይትነሥኡኬ ወይርድኡክሙ ወይኩኑክሙ መድኀኔክሙ ። | ፴፰ | የመሥዋዕታቸውን ስብ የምትበሉላቸው ወይናቸውን ፍልቅ አድርጋችሁ የምትጠጡላቸው ጣኦቶቻችሁ ወዴት ናቸው፤ ተነሥተው ይርዷችሁ የሚያድኗችሁ ይሁኗ አለ ። |
| አእምሩ አእምሩ ከመ አነ ውእቱ እግዚአብሔር ወአልቦ ባዕድ አምላክ ዘእንበሌየ ፡ አነ እቀትል ወአሐዩ ፡ እቀሥፍሂ ወእሣሃል ፡ ወአልቦ ዘያመስጥ እምእዴየ ። | ፴፱ | እንዲህንስ ትታችሁ ፈጣሪያችሁ እኔ እንደሆንኩ ያለ እኔም ሌላ ፈጣሪ እንደሌለ ዕወቁ! ዕወቁ! እኔ እገድላለሁ ፡ አድንማለሁ በመከራው እገርፋለሁ ፡ ይቅርም እላለሁ ፡ ከእጄ የሚያመልጥም የለም ። መዝ፡ ፶፱ ፳፮ ። |
| እስመ አሌዕል ውስተ ሰማይ እዴየ ፡ እምሕል በየማንየ ወእብል ሕያው አነ ለዓለም ። | ፵ | እጄን ወደ ሰማይ ዘርግቼ ለዘለዓለም ሕያው ነኝ ብዬ በሥልጣኔ እምላለሁ ። ዘኍ፡ ፲፬ ፴ ። |
| ወአበልሖ ከመ መብረቅ ለመጥባሕትየ ፡ ወትቀውም እዴየ በኵነኔየ ወእትፈደዮሙ በቀለ ለፀርየ ወእትቤቀሎሙ ለጸላእትየ ። | ፵፩ | ሥልጣኔን እንደ መብረቅ አፋጥናታለሁ ፡ ሥልጣኔም በፍርዴ ትጸናለች ጠላቶቼን ተበቅዬ አጠፋቸዋለሁ ፡ ጠላቶቼን እበቀላቸዋለሁ ። መዝ፡ ፯ ፲፪ ፡ ሕዝ፡ ፳፩ ፱ ። |

፵፪ ወአሰክሮን በደሞሙ ለአሕጻየ ወትበልዕ ሥጋሆሙ መጥባሕትየ እምደመ ቅቱላን ወፂዉዋን እርእስተ መላእክተ ፀር ።

፵፫ ይትፌሥሑ ኵሎን ሰማያት ኅቡረ ወይሰግዱ ሎቱ ኵሎሙ መላእክተ እግዚአብሔር ወይትፌሥሑ አሕዛብ ምስለ ሕዝቢሁሙ ፡ ወይብሉ ኵሎሙ ውሉደ እግዚአብሔር ጽኑዕ ውእቱ ።

፵፬ እስመ ይትቤቀል ደመ ደቂቁ ይትቤቀል ወይትፈደዮሙ በቀለ ለፀሩ ፡ ወይትቤቀሎሙ ለጸላእቱ ፡ ወያነጽሕ እግዚአብሔር ምድረ ለሕዝቡ ።

፵፭ ወጸሐፉ ሙሴ ለዛቲ ማኅሌት በይእቲ ዕለት ወመሀሮሙ ለደቂቀ እስራኤል ፡ ወቦአ ሙሴ ወነገሮሙ ለሕዝብ ወአስምዖሙ ውእቱ ወኢያሱ ወልደ ነዌ ።

፵፮ ወሶበ አኅለቀ ሙሴ ነጊሮቶሙ ለኵሉ እስራኤል ይቤሎሙ ዕቀብዎ በልብክሙ ለዝንቱ ኵሉ ነገር ዘአስማዕኩክሙ ዮም ፡ ዘትኤዝዙ ደቂቅክሙ ዮም ከመ ይዕቀቡ ወይግበሩ ኵሉ ነገሮ ለዝንቱ ሕግ ።

፵፯ እስመ ኢኮነ ከንቶ ዝንቱ ነገር ለክሙ ፡ እስመ ውእቱ ሕይወትክሙ ወበበይነ ዝ ነገር ይነውኅ መዋዕሊክሙ ውስተ ምድር እንተ ላቲ ተዐድዉ ዮርዳኖስ ከመ ትትዋረስዋ በሀየ ።

፵፰ ወነበቦ እግዚአብሔር ለሙሴ በይእቲ ዕለት ወይቤሎ ዕርግ ውስተ ደብረ አባሪም ዘውስተ ደብረ ናባር ዘምድረ ሞዓብ ዘመንገለ ገጸ ኢያሪኮ ፡ ወረአያ ለምድረ ከነዓን ዘእሁቦሙ ለደቂቀ እስራኤል ይምልክዋ ።

፵፱ ወሙት በውስተ ደብር ዘውስቴቱ ተዓርግ ህየ ፡ ወተወሰክ ኀበ ሕዝብከ ከመ ሞተ አሮን እኁከ በውስተ ደብረ ሆር ወአተወ ኀበ ሕዝቡ ።

፶ እስመ ክሕድክሙ ቃልየ በቅድመ ደቂቀ እስራኤል በኀበ ማየ ቅስት ዘቃዴስ በገዳም ዘፂን ፡ እስመ ኢቀደስክሙኒ በቅድመ ደቂቀ እስራኤል ።

፶፩ ወረአያ ለይእቲ ምድር ቅድሜከ ወሀየሰ ኢትበውእ ።

## ምዕራፍ ፴፫ ።

፩ ወከመዝ ይእቲ በረከት ዘባረኮሙ ለደቂቀ እስራኤል ሙሴ ብእሴ እግዚአብሔር ዘእንበለ ይሙት ።

፪ ወይቤ እግዚአብሔር እምነ ሲና መጽአ ወመጽአ ወአስተርአየነ በሴይር ፡ ወአፅረፈ በደብረ ፋራን ምስለ አእላፈ ቃዴስ እለ እምየማኑ መላእክቲሁ ወእለ ምስሌሁ ።

፫ ወምሕኮሙ ለሕዝቡ ወለኵሎሙ እለ ተቀደሱ በእዴሁ ፡ ወእሉሂ እሊአከ እሙንቱ ።

፬ ወረከቡ ሕገ በቃለ ዚአሁ ዘአዘዘነ ፡ ወርስተ ለሕዝበ ያዕቆብ ።

፭ ወይከውን መልአከ እምፍቁር ፡ ተጋቢኦሙ መላእክተ አሕዛብ ምስለ ነገደ እስራኤል ።

፮ አንሥኦ ለሮቤል ኢይሙትኒ ወይኩን ብዙኀ ኍላቌሁ ።

ፍላጻዎቼን በደማቸው አሰክራቸዋለሁ ፡ ሥልጣኔም ሰውነታቸውን ታጠፋለች ፡ ከተወጉትና ከተማረኩትም ደም ፍላጻዎቼን አሰክራለሁ ፡ ሾተሌም የጠላቶች አለቆች ቸብቸቦን ትቈርጣለች ። ኤር፡ ፵፯ ፲ ፡ መሳ፡ ፩ ፪ ።

ሰማያት ሁሉ (ልዑላኑ) አንድነት ደስ ይላቸዋል ፡ የእግዚአብሔር መላእክት (አለቆች) ሁሉ ይሰግዱለታል ፡ ወገኖች ከወገኖቻቸው ጋራ ደስ ይላቸዋል የእግዚአብሔርም ልጆች (እስራኤል) ሁሉ ጽኑ ነው ይላሉ ።

በልጆቹ ደም ተበቅሎ በጠላቶቹ ፍዳን ያመጣባቸዋል ጥንተ ጠላቶቹንም ይበቀላቸዋልና ፡ እግዚአብሔር ከነዓንን ለወገኖቹ (ለእስራኤል) የምትገባ አድርጎ ያወርሳቸዋል ።

ሙሴ በዚያች ቀን ይህችን (ማኅሌት) ምስጋና ጽፎ ለእስራኤል ልጆች አስተማራቸው ፡ ሙሴም ገብቶ እሱ አሰምቶ ለሕዝቡ ነገራቸው የነዌ ልጅ ኢያሱም አሰማቸው ።

ሙሴም ለእስራኤል ልጆች ነገሮ ከጨረሰ በኋላ ፡ ሕጉን ጠብቀው የዚችን የሕግ ነገር ሁሉ ያደርጉ ዘንድ ፡ ለልጆቻችሁ የምታዙት እኔ አሁን ያሰማኋችሁና ይህን ሁሉ ነገር በልባችሁ (ጠብቁት) አስተውሉት ።

እሱ ሕይወታችሁ ስለሆነ ይህ ነገር ለናንተ ከንቱ አይደለምና ፡ ስለዚህ ነገር ትወርሷት ዘንድ ዮርዳኖስን በምትሻገሩላት አገር ዘመናችሁ በዚያ ይበዛል ።
ምሳ፡ ፫ ፪ ። ሮሜ ፲ ፭ ።

እግዚአብሔርም በዚያች ቀን ሙሴን እንዲህ ሲል ተናገረው ፡ በኢያሪኮ አንጻር በሞዓብ አውራጃ በናቦር ተራራ ወዳለ ወደ አባሪም ተራራ ወጥተህ ይገዟት ዘንድ ለእስራኤል ልጆች የምሰጣቸው ከነዓንን እያት ።

ወንድምህ አሮን ሖር በሚባል ተራራ ሙቶ ወደ ወገኖቹ እንደተጨመረ አንተም ወደ ምትወጣበት ተራራ ወደ ወገኖችህ ተጨመር ። ዘኍ፡ ፳ ፳፭ ።

ጺን የሚባል ዕንጨት ባለበት በቃዴስ ምድረ በዳ ጠብ ክርክር በተደረገበት ውኃ ቃሌን ስለ ካዳችሁ በእስራኤል ልጆች ፊት አላመሰገናችሁኝምና ።

በፊትህ ያለች ያችንም ምድር እያት ፡ ወደዚያ ግን አትገባም ብሎ ለሙሴ ነገረው ። ዘዳ፡ ፫ ፳፪ ።

## ምዕራፍ ፴፫ ።

የእግዚአብሔር ሰው ሙሴ ሳይሞት የእስራኤልን ልጆች የመረቃቸው ምርቃት እንዲህ ናት ። ዘፍ፡ ፵፱ ፳፰።

እግዚአብሔር ከደብረ ሲና ወጥቶ መጥቶ በሴይር ተገለጠልኝ ፡ ከሱም ጋር ያሉ መላእክት በቀኙ ያሉ እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር በፋራን ተራራ (በረድኤት) ዐረፈ አለ።

በቃሉ ለተለዩ (ሌዋውያን) ሁሉና ለወገኖቹም (እስራኤል) ራራላቸው ፡ እነዚህም (ሌዋውያን) ወገኖችህ ናቸው።

ባዘዘን ቃሉም ሕጉን አገኙ (ጠበቁ) ለያዕቆብም ወገኖች ሕጉ ርስት ሁኖ ተሰጣቸው ። ዮሐ፡ ፯ ፲፱ ።

ከወዳጅ (ከያዕቆብ) ዳዊት ይወለዳል ፡ የአሕዛብም አለቆች ከእስራኤል ወገኖች ጋራ አንድ ሁነው ይገዙለታል ።

በነፍስ እንዳይሞትብኝ ሮቤልን (በጸሎት) እፈልገዋለሁ ቍጥሩም ብዙ ይሁን ። ዘፍ፡ ፵፱ ፬ ።

፯ ወለዝንቱኒ ይሁዳ ስምዖ እግዚኦ ቃሎ ለይሁዳ፡ ወይግባእ ውስተ ሕዝቡ፡ ወእደዊሁ ይኰንናሁ፡ ወኩኖ ረዳኤ እምፀሩ ።

ይህንን ይሁዳን ነገር አድርጎ ተናገረው አቤቱ! የይሁዳ ጸሎቱን ስማ፡ ወደ ወገኖቹም ይመለስ፡ ሥልጣኖቹም ይግዙ፡ ከጠላቶቹም ረዳት ሁነው ።

፰ ወለሌዊኒ ይቤሎ አግብእ ለሌዊ ቃሎ ወጽድቆ ለብእሲ ጻድቅ ዘአመክርዎ በመከራ፡ ወጸአልዎ በኀበ ማየ ቅስት ።

ሌዊንም ነገር አድርጎ ተናገረው፡ በመከራ ለፈተኑት ጠብ ክርክር በተደረገበትም ውኃ ለሰደቡት ።

፱ ዘይቤሎሙ ለአቡሁ ወለእሙ ኢርኢኩክሙ ወበአኀዊሁኒ ኢያእመረ ወበደቂቁኒ ኢለበወ ወዐቀበ ቃለከ፡ ወተማኀፀነ ኪዳነከ ።

እናት አባቱን አላየኋችሁም ላላቸው በወንድሞቹ (በእስራኤል) የሚደረገውን (ፍቅር) ላላወቀ በልጆቹም የሚደረገውን ላላስተዋለ ቃልህን ለጠበቀ በቃል ኪዳንህም የተማጠነ ። ዘፀ፡ ፴፰ ፴፡ ፲፯ ፯፡ መዝ፡ ፻፯ ፲፯ ።

፲ ከመ ይንግሩ ኵነኔከ ለያዕቆብ ወሕገከ ለእስራኤል ወከመ ይደዩ ዕጣነ በማዕጠንትከ ወበኵሉ ጊዜ ውስተ ምሥዋዒከ ።

አምልኮትህን ለያዕቆብ ሕግህንም ለእስራኤል ያስተምሩ ዘንድ በጥናህም ዕጣንን ይጨምሩ ዘንድ፡ በመሠውያህም በየጊዜው መሥዋዕትን ይሠዉ ዘንድ፡ እውነተኛ ለሆነ ሰው ለሌዊ የትሩፋቱን ዋጋ ስጠው ።

፲፩ ወባርክ እግዚኦ ኀይሎ፡ ወተወከፍ ግብረ እደዊሁ፡ ወአውርድ ክበደ ላዕለ እለ ይትቃወምዎ ፀሩ፡ ወኢታንሥኦሙ ለእለ ይፃረርዎ ።

አቤቱ! ሠራዊቱን አብዛ በቃሉ የጸለየውንም ጸሎት ተቀበል፡ በሚከራከሩት ጠላቶቹም መከራ አምጣባቸው የሚጣሉት ጠላቶቹንም በረድኤት አታድናቸው ።

፲፪ ወለብንያምኒ ይቤሎ፡ ፍቁረ እግዚአብሔር የኀድር ተአሚኖ፡ ወእግዚአብሔር ይጼልሎ በኵሉ መዋዕሊሁ፡ ወየዐርፍ ማእከለ መታክፊሁ ።

ብንያምንም ነገር አድርጎ ተናገረው፡ የእግዚአብሔር ወዳጅ ብንያም ከመከራው ተዘልሎ ይኖራል፡ እግዚአብሔርም በዘመኑ ሁሉ ከመከራው ይሠውረዋል፡ በወንድሞቹም መከከል ይኖራል ።

፲፫ ወለዮሴፍኒ ይቤሎ እምበረከተ እግዚአብሔር ምድሩ ወእምዝናመ ሰማይ ወጠል ወእምነቅዐ ቀላይ ዘእምታሕቱ ።

ዮሴፍንም ነገር አድርጎ ተናገረው፡ ምድሩ ከእግዚአብሔር በተገኘ በረከት ጠልንና የሰማይ ዝናምን አግኝታ ከምድር የወጣ የመስኖ ውኃን ጠጥታ እኽልን ታበቅላለች ።

፲፬ ወለለሰዐቱ እክሉ፡ ወእምሥርቀተ ፀሐይ ወእምነ ጕላቊሆሙ ለአውራኅ ።

ፀሐይ እየወጣ፡ ወራት በበቱ ቍጥር እኽሉ በየሰዓቱ ነው ። ዘፍ፡ ፵፱ ፳፭ ።

፲፭ ወይቀድም እምአርእስተ አድባር፡ ወእምውስተ አርእስተ አውግር ዘአኤናዎን ።

(አኤናዎን) ዘለዓለም ጸንተው ከሚኖሩ ከረብታዎችና ከተራሮች ራስ ቀርቦ ይታያል ። ዕንባ፡ ፫ ፯ ።

፲፮ ምድር እንተ ዘልፈ ጽግብት ወሥናይት ለዘአስተርአየ በውስተ ዕፀ ጳጦስ ለይምጻእ ዲበ ርእሱ ለዮሴፍ ወበርእሱ ይክበር በውስተ አኀዊሁ ከመ በኵረ ላሕም ስኑ ።

ምድሩ ሁል ጊዜ ዝናሙን ጠሉን የጠገበች ያማረች (የተወደደች) ናት፡ ጳጦስ በሚባል ዕንጨት የታየ የእግዚአብሔር ረድኤት በዮሴፍ (ይምጣ) ይደር፡ በወንድሞቹም መካከል በሥልጣኑ ይክበር፡ መወደዱም ከላም መጀመሪያ እንደተወለደ ወይፈን ነው ። ዮሐ፡ ፮ ፴ ።

፲፯ ወእምአቅርንት ዘአሐዱ ቀርኑ አቅርንቲሁ፡ ወይወግአሙ ለአሕዛብ በሙ ኅቡረ እስከ አጽናፈ ምድር ዝንቱ አእላፍ ዘኤፍሬም፡ ወዝንቱ አእላፍ ዘምናሴ ።

ቀንዱ አንድ እንደሆነ ርኤም በቀንዱ እንዲከብር በሥልጣኑ ይከብራል፡ በምድር ዳርቻ ያሉ አሕዛብን በሥልጣኑ አንድነት ያጠፋቸዋል፡ ይህ የኤፍሬም ወገን ነው ይባላል፡ ይህም የምናሴ ወገን ነው ይባላል ።

፲፰ ወለዛብሎንሂ ይቤሎ፡ ተፈሣሕ ዛብሎን በፀአትከ፡ ወይሳኮር በማኅደርከ፡ እለ ያጠፍእዎሙ ለአሕዛብ ።

ዛብሎንንም ነገር አድርጎ ተናገረው፡ ዛብሎን ወደ ዘመቻ በመውጣትህ ደስ ይበልህ ይሳኮርም ከዘመቻ በመግባትህ ደስ ይበልህ እነዚህ አሕዛብን የሚያጠፉዋቸው ናቸው ።

፲፱ ወጸውዑ በህየ ወሦዑ መሥዋዕተ ጽድቅ እስመ ብዕለ ባሕር የሐፅነከ ወየሐንፀከ፡ ወንዋዮሙ ለእለ ይነብሩ ውስተ ጰራልያ ።

እውነተኛ መሥዋዕትን ሠውተው በዚያ (በደብረ ታቦር) አመሰገኑ (የባሕር ሃብት) የአሕዛብን ገንዘብ ትመገባለህና ቤትህንም ያንጽልሃልና በደሴት የሚኖሩ የአሕዛብ ገንዘብ ያንተ ገንዘብ ነው ። ኢሳ፡ ፪ ፫፡ መዝ፡ ፬ ፭ ።

፳ ወለጋድሂ ይቤሎ፡ ርኁብ በረከቱ ለጋድ ከመ አንበሳ የኀድር ቀጥቂጦ መዝራዕተ መላእክት ።

ጋድንም ነገር አድርጎ ተናገረው፡ የጋድ ገንዘቡ ብዙ ነው የጠላቶቹን ክንድ አድቅቆ እንደ አንበሳ ተዘልሎ ይኖራል ። ዘፍ፡ ፵፱ ፬፡ ዘዳ፡ ፳፫ ፳፪ ።

፳፩ ወርእየ ቀድሚሁ ከመ በህየ ተከፈልዋ ለምድር መላእክት እንዘ ጉቡአን መሳፍንት ኅቡረ ምስለ መልአከ አሕ

ከእስራኤል ወገኖችና ከእስራኤል አለቃ (ከኢያሱ ጋር) ሹማምንት አንድነት ተሰብስበው አለቀች በዚያ እን

ዘብ፡ ወምስለ ሕዝበ እስራኤል እግዚአብሔር ገብረ ጽድቀ ወኮነኒሁ ምስለ እስራኤል ።
፳፪ ወለዳንሂ ይቤሎ፡ ዳን እጓለ አንበሳ፡ ወይሠርር እምነ ባሳን ።
፳፫ ወለንፍታሌምኒ ይቤሎ፡ ንፍታሌም ጽጉብ እምሠና ያት ወይጸጊብ እምበረከት እግዚአብሔር ፡ ወይትዋረስ ባሕረ ወሊበ ።
፳፬ ወለአሴርሂ ይቤሎ፡ ቡሩክ ውእቱ እምውሉደ አሴር፡ ወይከውን ኅሩየ ለአኀዊሁ ወየሐጽብ በቅብዕ እገሪሁ ።
፳፭ ዘሐጺን ወዘብርት አሣእኒሁ፡ ወይከውን በከመ መዋዕ ሊከ ኀይልከ ።
፳፮ አልቦ ከመ አምላኩ ለፍቁር ዘይነብር ውስተ ሰማይ ውእቱ ረዳኢከ ወዕበየ ሥኑ ለሰማይ ።
፳፯ ወይከድንከ እግዚአብሔር ፍጽመ በኀይለ መዝራዕት እኤናዎን ወይወፅእ እምቅድመ ገጽከ ፀርከ፡ በከመ ይቤ ከመ ያጥፍአሙ ።
፳፰ ወያነብሮ ለእስራኤል ተአሚኖ ባሕቲቶ ውስተ ምድረ ያዕቆብ፡ ውስተ ምድረ ሥርናይ፡ ወወይን፡ ወሰማይኒ ለከ ምስለ ደመና ወጠል ።
፳፱ ወብፁዕ አንተ እስራኤል መኑ ከማከ ሕዝብ ዘእግዚአ ብሔር ያድኅኖ ወያፀንዐከ ወይረድአከ ወበመጥባሕትከ እልገትከ ሕሰው ፀርከ ወአንተ ትጼዐን ላዕለ ክሳዳቲሆሙ ።

ደተከፈሏት በፊቱ አየ፡ እግዚአብሔር ፍርዱንና ቸርነቱን ከእስራኤል ጋር አደረገ ። ዘኍ፡ ፴፪ ፩፡ ፳፩ ፲፰ ።
ዳንንም ነገር አድርጎ ተናገረው፡ ዳን የአንበሳ ግልገል (ደቦል) ነው፡ ከባሳን ዘሎ ይወጣል፡ (ይዘምታል) ።
ንፍታሌንም ነገር አድርጎ ተናገረው፡ ንፍታሌም ከበጎቹ (ተድላ ደስታ) የጠገበ ነው፡ የእግዚአብሔርን በረከት ይጠግባል (ያገኛል) ባሕሩንና ደቡቡን (፬ቱን መዓዝን) ይገዛል ። ዘፍ፡ ፵፱ ፳፩፡ ሕዝ፡ ፳ ፵፯ ።
አሴርን ነገር አድርጎ ተናገረው፡ አሴር ከእስራኤል ይልቅ የተመረቀ ነው፡ ለወንድሞቹም የተመረጠ ይሆናል እግሮቹን በዘይት ይታጠባል ። ዘፍ፡ ፵፱ ፳ ።
ጫማዎቹ የናስና የብረት ናቸው፡ ኃይልህም እንደ ዘመንህ ነው ።
በሰማይ እንደ ሚኖር እንደ እስራኤል ፈጣሪ ያለ የለም፡ ረዳትህም እሱ ነው፡ ዝናም ለዘር ጠል ለመከር የሚ ሰጥም እሱ ነው ። ዘፀ፡ ፲፰ ፲፩፡ ዘዳ፡ ፴፪ ፲፰ ።
እግዚአብሔር ፈታውራሪ ሁኖ በዘለዓለማዊ ክንዱ ኃይል ከመከራው ይሠውርኻል፡ እግዚአብሔር ያጠፋቸው ዘንድ አጠፋቸዋለሁ ብሎ እንደ ተናገረ ጠላትህ ከፊትህ ይወጣል (ይጠፋል) ።
እስራኤልንም ወይንና ሥንዴ ባለበት በያዕቆብ አገር ብቻውን ተዘልሎ እንዲኖር ያደርገዋል፡ ሰማይም ከጠልና ከደመና ጋር ላንተ ዝናም ይሰጣል ።
እስራኤል ሆይ፤ አንተ ንዑድ ክቡር ነህ እግዚአብ ሔር የሚያድነው እንዳንተ ያለ ማን ነው፤ ይረዳኻል ያጸና ኻል፡ በሾተልህ ገድለህ ሰልበህ ኑር፡ ጠላትህ አንተን አጠፋለሁ ማለቱ ሐሰት ነው፡ አንተ ግን የጠላቶችህ አን ገታቸውን ረግጠህ ትገዛቸዋለህ ። ፪ ሳሙ፡ ፯ ፳፫ ።

ምዕራፍ ፴፬ ።

፩ ወዐርገ ሙሴ እምአባሬም ዘሞዓብ ውስተ ደብረ ናበር ውስተ ርእሰ ፋስጋ ዘሀለወ ቅድመ ኢያሪኮ፡ ወአርአዮ እግዚአብሔር ኵሎ ምድረ ገለአድ፡ ወኵሎ ምድረ ንፍ ታሌም ወኵሎ ምድረ ምናሴ፡ ወኵሎ ምድረ ይሁዳ እስከ ደኃሪት ባሕር ።
፪ ወገዳመ ወአድያሚሃ ለኢያሪኮ ሀገረ ፊንቆን እስከ ሴይር ።
፫ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ዛቲ ይእቲ ምድር ዘመሐልኩ ለአብርሃም ወለይስሐቅ ወለያዕቆብ ወእቤሎሙ ለዘርእክሙ እሁባ ወናሁ አርአይኩከሃ ለከ በአዕይንቲከ፡ ወባሕቱ ህየ ኢትበውእ ።
፬ ወሞተ ሙሴ ቍልዔሁ ለእግዚአብሔር በምድረ ሞዓብ በቃለ እግዚአብሔር ።
፭ ወቀበርዎ ውስተ ምድረ ናበው ቅሩበ ቤተ ፌጎር ወአልቦ ዘየአምር መኑሂ መቃብሮ እስከ ዛቲ ዕለት ።
፮ ምእት ወዕሥራ ዓመቲሁ ሎቱ ለሙሴ አመ ሞተ፡ ወኢተሐምጋ አዕይንቲሁ ወኢማሰና ።

ምዕራፍ ፴፬ ።

ሙሴ የሞዓብ ክፍል ከምትሆን ከአባሪም በኢያሪኮ አንጻር ወዳለ ወደ ፋስጋ ራስ ናበር ወደ ሚባለው ተራራ ወጣ፡ እግዚአብሔርም የገለዓድንና የንፍታሌምን ምድር ሁሉ የምናሴንና የይሁዳን ምድር ሁሉ እስከ ባሕር መጨረሻ ድረስ አሳየው ። ዘዳ፡ ፲፩ ፳፬ ።
የፊንቆን አገር የምትሆን የኢያሪኮንም አውራጃ እስከ ሴይር ድረስ አሳየው ። ፪ ሳሙ፡ ፲፰ ፳፫ ።
እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው፤ ለልጆቻችሁ እሰጣታለሁ ብሎ ለአብርሃም ለይስሐቅና ለያዕቆብ የማል ኩላቸው ምድር ይህች ናት፡ እነሆ ላንተ በዓይኖችህ አሳየ ሁህ፡ ነገር ግን ወደዚያ አትገባም ። ዘፍ፡ ፲፪ ፯ ።
የእግዚአብሔር ባለሟሉ ሙሴም እንደ እግዚአብሔር ቃል በሞዓብ ምድር ሞተ ።
በፌጎር (ጣኦት) ቤት አቅራቢያ በምትሆን በሞዓብ ምድር ቀበሩት፡ ነገር ግን እስከዚች ቀን ድረስ ማንም ማን መቃብሩን የሚያውቅ የለም ። ይሁ፡ ፩ ፱ ።
ሙሴም በሞተ ጊዜ ዕድሜው መቶ ሃያ ዘመን ሁኖት ነበር፡ ዓይኖቹም አልደፈረሱም አልፈዘዙም ነበር ።

| | | |
|---|---|---|
| ወበከይዎ ደቂቀ እስራኤል ለሙሴ በአራበት ዘሞዓብ በኀበ ዮርዳኖስ ዘመንገለ ኢያሪኮ ሠላሳ መዋዕለ፥ ወተፈጸመ መዋዕለ ላሁ ለሙሴ ዘበከይዎ ። | ፰ | የእስራኤል ልጆች ለሙሴ የኢያሪኮ አንጻር በምትሆን በዮርዳኖስ ማዶ ባለች የሞዓብ ክፍል በምትሆን በአራበት ሠላሳ ቀን አለቀሱለት፥ ለሙሴ ያለቀሱለትም ወራት አለቀ። |
| ወኢያሱ ወልደ ነዌ ተመልአ መንፈሰ ጥበብ እስመ ወደየ እዴሁ ሙሴ ላዕሌሁ ወተአዘዙ ሎቱ ኵሉ ደቂቀ እስራኤል፥ ወገብሩ ኵሎ ዘከመ አዘዘ እግዚአብሔር ለሙሴ ። | ፱ | ሙሴ በአንብሮተ እጅ ሹሞታልና የነዌ ልጅ ኢያሱም ጥበብ የሚገልጽ መንፈስ ቅዱስን ተመላ፥ የእስራኤልም ልጆች ሁሉ ታዘዙለት፥ እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው ሁሉን አደረጉ። ዘኍ፥ ፳፯ ፲፰፥ ኢሳ፥ ፲፩ ፪። |
| ወኢተንሥአ እንከ ነቢይ ውስተ እስራኤል ዘከመ ሙሴ ዘተናገሮ እግዚአብሔር ገጸ በገጽ ። | ፲ | እግዚአብሔር ፊት ለፊት እንደ ተናገረው እንደ ሙሴ ያለ ነቢይ ከዚያ ወዲህ በእስራኤል ዘንድ አልተነሣም ። |
| ወበኵሉ ተአምር፥ ወመድምም ዘፈነዎ እግዚአብሔር ከመ ይግበሮ በምድረ ግብጽ ላዕለ ፈርዖን ወላዕለ መገብቱ ወላዕለ ምድሩ ። | ፲፩ | በግብጽ ምድር በመኳንንቱና በፈርዖን በአገሩም ላይ ያደርገው ዘንድ እግዚአብሔር በላከው ተአምራት ሁሉ ቃል ለቃል እንደተናገረው ። |
| ዐበይተ መድምመ፥ ወእደ ጽንዕተ፤ ወመዝራዕተ ልዑለ ኵሎ ዘገብረ ሙሴ በቅድመ ኵሉ እስራኤል ። | ፲፪ | ሙሴ በእስራኤል ፊት ታላላቅ ተአምራት በጸናች (ዘጠኝ መቅሠፍት) በተዘረጋች ክንድ (ዓሥረኛ ሞተ በኵር፥ ዓሥራ አንደኛ ሥጥመተ ባሕርን) አደረገ። |

ተፈጸመ ኦሪት ዘዳግም፥
ወስብሐት ለእግዚአብሔር ጸጋዌ ጸጋ ፍጹም፥
አሜን።

ፍጹም ጸጋን ለሰጠ ለእግዚአብሔር፥
ክብር ምስጋና ይግባውና፥ ሙሴ ዳግመኛ
የተናገረው ነገር ደረሰ ተፈጸመ።